ያልታተሙ የሰበር ውሳኔዎች

ቅፅ - 2

በዳንኤል ፍቃዱ (ጠበቃና የህግ አማካሪ) ተሰብስቦ በአንድ ተቀናበረ



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ.200968

ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡.....አቶ ሙሉጌታ ኃ/ማርያም- ቀርበዋል

ተጠሪ፡.....አቶ ነጋሽ ያደቴ- ተወካይ አባይነህ ነጋሽ ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የእርሻ መሬት የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.251106 ጥቅምት 26 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ከሳሽ በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ክልል ዉስጥ ግብር እየገበርኩበት ያለዉን ሁለት ቀርጥ (አዋሳኝ በመጥቀስ) የእርሻ መሬት ይዞታዬን የካቲት ወር 1989 ዓ.ም ባደረግነዉ ዉል ለጊዜያዊ ችግሬ መዋያ ብር 7000 (ሰባት ሺህ) ከተከሳሽ ተቀብዬ መሬቱን ለተከሳሽ የሰጠሁ፣ ገንዘቡን ስመልስለት ደግሞ መሬቱን ሊመልስልኝ የተስማመን ሲሆን፣ ተከሳሽ ገንዘቡን ተቀብሎኝ መሬቱን እንዲያስረክበኝ ፈቃደኛ ስላልሆነ፣ ተከሳሽ ገንዘቡን ተቀብሎኝ የእርሻ መሬቱን እንዲያስረክበኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ ክርክር ከሳሽ በዚህ መሬት መብትና ጥቅም የለዉም፤ ተከሳሽ ይህን መሬት በዉል አልተቀብኩም፤ መሬቱን በዉል ተቀብለአል የሚባል ከሆነ ዉሉ ተደርጓል ከተባለ ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ ከ21 ዓመታት በላይ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር በመመርር ባሳለፈዉ ዉሳኔ ከሳሽ የግብር ደረሳኝ ያቀረበ በመሆኑ በመሬቱ ላይ መብትና ጥቅም አለዉ፤ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ተከሳሽ መሬቱን ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ መያዙን ገልጸዉ የተከራከሩ በመሆኑ ይህ ጊዜ ሲሰላ ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠዉ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ዉሳኔ አንጻር በ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ ሊታገድ ይገባል በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበለትን ይግባኝ በትዕዛዝ በመሰረዝ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔና ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ጥር 7 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች ግብር የሚገብርበትን አከራከሪዉን የእርሻ መሬት ይዞታዬን ከተጠሪ ገንዘብ ወስጀ የሰጠሁት በመሆኑ አመልካች ከተጠሪ የወሰድኩትን ገንዘብ ስመልስለት ይዞታዉን ሊመልስልኝ ተስማመን ስለሆነ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም፤ አመልካች መሬቱን ለተጠሪ የሰጠሁት በወለድ አግድ ዉል መልስ በመሆኑ የባለይዞታዉ መብት በይርጋ ሊቋረጥ የማይችል እና አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ የመፋለም ክርክር ስለሆነ ጉዳዩ በይርጋ ዉድቅ ሊሆን አይገባም ተብሎ የሥር ፍ/ቤት ብይን ተሽሮ ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክር ገብተን እንዲንከራከር እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት በ249/2013 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ምንም ዓይነት የመያዣ ዉል አልፈጸምኩም፤ የመያዣ ዉል አለ ቢባል እንኳን ክስ የቀረበዉ ከ21 ዓመት በላይ የሆነዉ ስለሆነ ክሱ በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነዉ መባሉ የሚነቀፍበት አግባብ የለም፤ አመልካች ያቀረበዉ ክስ ዉልን የሚመለከት እንጂ የመፋለም አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ ማግኘት ያለበት ፡በዚህ ጉዳይ ተገቢ የሆነ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመያዝ ዉሳኔ የተሰጠ መሆን አለመሆኑን? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰዉ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረግነዉ ዉል ለክርክር መነሻ የሆነዉን ይዞታ ለተጠሪ የሰጡት ከተጠሪ ገንዘብ ተቀብዬ ሲሆን ገንዘቡን ስመልስለት ተጠሪ ደግሞ መሬቱን ሊመልስኝ ተስማምተን ስለሆነ አሁን ገንዘቡን ወስዶ መሬቱን እንዲያስረክበኝ የሚል ነዉ፡፡ ስለሆነም አመልካች አከራከሪዉን መሬት ለተጠሪ ሰጠሁት የሚለዉ በዉል ምክንያት መሆኑን ነዉ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር ከአመልካች ጋር ምንም ዓይነት ዉል አላደረግኩኝም፤ ዉሉ አለ ቢባል እንኳን ከ21 ዓመት በላይ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት

ተከራክሯል፡፡ ስለሆነም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በይርጋ መቃወሚያ ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት ተገቢዉን ጭብጥ በመለየት በመያዝ በማጣራት አግባብነት ካለዉ ሕግ አንጻር መርምሮ መወሰንን ይጠይቃል፡፡

እንደሚታወቀዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 (1) መሰረት ማስረጃ ተቀብሎ ከመመርመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ አስቀድሞ ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያ ደረጃ ለቀረበለትና ማናቸዉም ተከራካሪ ወገን ላቀረበዉ መቃወሚያ ዉሳኔ መስጠት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ እንዲሁም ፍ/ቤቱም በቀረበዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ተቀብሎ ሌላዉ ተከራካሪ ወገን በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበዉን ክርክር ከሰማ በኋላ ዉሳኔ ለመስጠት ተገቢ መስሎ የሚገምተዉ ማስረጃ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ይሰጣል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.245 (1) ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ከዚህ የህግ ደንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለዉ በቀረበዉ የመጀመሪያ መቃወሚያ ላይ አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝ ፍ/ቤት ማስረጃ በመስማት በመጣራት ዉሳኔ መስጠት እንደሚገባዉ ያስገነዝባል፡፡

በዚህ መሰረት አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር አከራካሪዉን መሬት ለተጠሪ በዉል ሰጥቻለሁኝ ያለዉ ሲሆን፣ ተጠሪ በበኩሉ ደግሞ ከአመልካች ጋር ምንም ዓይነት ዉል አላደረግንም፣ ዉል አለ ቢባል እንኳን በይርጋ የሚታገድ ነዉ በማለት ክዳዉ ተከራክሯል፡፡ አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገነዉ ዉል መሬቱን ሰጥቻለሁ ያለዉን፣ በተጠሪ በኩል የተካደ ስለሆነ፣ በግራ ቀኙ መካከል አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ተጣርቶ ነጥሮ መዉጣት ያለበት ጭብጥ አመልካች ለክርክር መነሻ የሆነዉን መሬት በዉል ለተጠሪ ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም? አመልካች መሬቱን በዉል ለተጠሪ ሰጥቷል የሚባል ከሆነ የአመልካች ክስ በይርጋ የሚታገድ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ግራ ቀኙን ካከራከረዉ ከዉል አንጻር ጭብጥ መስርቶ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በማጣራት በሕጉ አግባብ ተገቢ ነዉ ያሉትን ዉሳኔ ማሳለፍ ይገባቸዉ ነበር፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር አስመልክቶ ከዉል አንጻር ሳይመርምሩ ክሱን ዉድቅ ማድረጋቸዉ የህግ ድጋፍ የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የግራ ቀኙን ክርክር መሰረት በማድረግ ከዉል አንጻር ጭብጥ በመመስረት አጣርቶ አለመወሰናቸዉ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.97708 በ15/4/2012 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.251106 በ26/2/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ሐተታዉ በተመለከተዉ አግባብ አመልካች ለክርክር መነሻ የሆነዉን የመሬት ይዞታ በክሱ በተጠቀሰዉ አግባብ በዉል ለተጠሪ ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም? አመልካች መሬቱን በዉል ለተጠሪ ሰጥቷል የሚባል ከሆነ የአመልካች ክስ በይርጋ የሚታገድ ነዉ

ወይስ አይደለም? የሚለዉን ከግራ ቀኙ የሚቀርብ ማስረጃ ካለ በመመርመር፣ አግባብነት ባለዉ ማስረጃም በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ብይን እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 (1) መሰረት ተመልሶለታል፡፡

3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. ይህ ዉሳኔ ታህሳስ 4 ቀን 2014 ዓ.ም ተነቧል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ማ/አ **የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት**

የሰ.መ.ቁ.200968

ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ.ም

ስሜ በተራ ቁጥር 3ኛ ላይ የምገኘው ዳኛ የልዩነት ሀሳቤን እንደምከተለው አስቀምጫለሁ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ባቀረበው ክስ ለአሁን ተጠሪ የእርሻ መሬት ይዞታዬን ገንዘብ ተቀብዬው መሬቱን እንዲጠቀምበት ያስረከብኩትና ገንዘቡን ስመልስለት መሬቱን እንዲመልስልኝ (ወለድ አግድ) ተስማምተን በ1989 ዓ/ም የእርሻ መሬቴን የሰጠሁት ሲሆን አሁን ገንዘቡን ወስዶ መሬቴን እንዲመልስልኝ ብጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆኑ መሬቴን እንዲለቅልኝ ሲል የጠየቀ ሲሆን የአሁን ተጠሪም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክሱ በይርጋ ውድቅ እንዲሆንለት ጠይቆ በፍሬ ነገሩ ላይም መልስ ሰጥቷል፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 69302 ላይ በሰጠው ውሳኔ አንድ የእርሻ መሬት ባለይዞታ በመሬት የመጠቀም መብት ለማስከበር በ10 ዓመት ውስጥ ክስ ካላቀረበ ክሱ ይርጋ ቀሪ እንደሚሆን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በሰጠው መሰረት የአሁን አመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው ሲል ክሱን ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የቀረበውን ዳኝነትና የእርሻ መሬት ይዞታን በተመለከተ ከህገ መንግስቱ ጀምሮ ያሉትን ህጎች እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም አንዲሁም የኢፌዴሪ ፌደሬሽን ም/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ካለመገንዘብ የደረሱበት ድምዳሜ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይሄውም ማንኛውም በእርሻ መሬት ላይ የሚደረጉ ውሎችን እንደማንኛውም የግል ንብረት ላይ የሚደረጉ ውሎች በፍ/ብ/ህግ የውል ድንጋጌዎች ሲዳኙ ይታያል፡፡ በፍ/ብ/ህጋችን ላይ ስለመሬት የተደነገጉት ድንጋጌዎች መሬትን በግል ንብረትነት እይታ መነሻነት ተወስዶ የተቀመጡ ድንጋጌዎች ሲሆኑ የፍ/ብ/ህግ 1173፣ 1178፣ 1179 እና ሌሎቹም ድንጋጌዎች ይህንኑ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ይሁንና ከደርግ መንግስት ጀምሮ በመሬት ላይ ያለው የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ የተለወጠና መሬት የህዝብና የመንግስት ሆኖ ባለይዞታው ከመሬት ባለቤትነት ያነሰ መብት ያለው መሆኑ ማንኛውም ሰው ግንዛቤ የለውም ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ የኢፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 40(3) የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ ነው፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው ሲል ደንግጎ ይገኛል፡፡ ይህ ሆኖ ባለበት የእርሻ መሬት ላይ የሚደረጉ ክርክሮችን በተመለከተ ህገ መንግስቱን መሰረት በማድረግ የወጡ ህጎች እያሉ የኢፌዴሪ ፌደሬሽን ም/ቤት ውሳኔዎች እያሉ በፍ/ብ/ህጉ ድንጋጌዎች እይታ መዳኘት ተገቢነት የሌለውና የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ይሆናል፡፡ የኢፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 40(4)

የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡፡ አፈጻጸሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል ሲል ደንግጎ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የእርሻ መሬት የሚተላለፈው ባለይዞታ ለቤተሰቡ አባላት በውርስና በስጦታ ልያስተላልፍ የሚችል ሲሆን ከባለይዞታው የቤተሰብ አባለት ውጪ የሚደረጉ የእርሻ መሬት ማስተላለፍ ጉዳይ የእርሻ መሬት ባለይዞታውን ከይዞታው የሚያፈናቅለው በመሆኑ ህገ መንግስቱን የሚጻረር ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት በተለያዩ የእርሻ መሬት ክርክሮች ላይ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣ የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔና ሌሎቹንም መመልከት ይቻላል፡፡ እነዚህ ውሳኔዎች የእርሻ መሬት በተመለከተ በሚነሱ ክርክሮች የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ጨምሮ የሚሰጡት ውሳኔዎች ከህገ መንግስቱ ጋር የሚጻረሩ በመሆኑ ህገ መንግስቱን በመተርጎም የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት የሰጣቸው ውሳኔዎች ናቸው፡፡ ከእርሻ መሬት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች ይርጋን በተመለከተ የእርሻ መሬት ይዞታ በህገ ወጥ መንገድ ተላልፎ የተገኘ እንደሆነ ክሱ በይርጋ የማይታገድ መሆኑን የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣ የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 5ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና ሌሎችም ውሳኔዎች በቂና አስገዳጅ ማሳያዎች ናቸው፡፡ መሬት በህጋዊ መንገድ የተላለፈ ስለመሆን አለመሆኑና በህገ ወጥ መንገድ የተላለፈ ስለመሆኑ የኢፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 40(4) ባስቀመጠው ድንጋጌ መሰረት የየክልሎቹ የገጠር መሬትን ለማስተዳደር የወጡት አዋጆች በግልጽ ደንግገው የሚገኙ ሲሆን የእርሻ መሬት በህጋዊ መንገድ የሚገኘው ከመንግስት በምሬት ስገኝ፣ ከመሬት ባለይዞታው በውርስ ወይም በስጦታ ለቤተሰቡ ሲተላለፍ ሲሆን ከዚህ ውጪ የሚደረጉ የእርሻ መሬት ማስተላለፍ ሁሉ ህገ ወጥ የሚሆኑ ናቸው፡፡ የቤተሰብ አባል ማለት ምን እንደሆነ እነዚሁ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጆች ደንግገው ይገኛሉ፡፡ በዚህ ጉዳይ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 179827 ላይ በሰጠው ውሳኔ እንድ ሰው የገጠር መሬት በህጋዊ መንገድ የያዘ ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ ጊዜ ድረስ መሬቱን የያዘው በህገ ወጥ መንገድ መሆኑ ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያን በስነ ስረዓት መቃወሚያነት ሊያነሳ የማይችል ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ የፌደራል እና የየክልሎቹን የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጆችንም ማየት ይቻላል፡፡ ሌላው የኢፌዴሪ ፌደሬሽን ም/ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን፣ 1ኛ ዓመት፣ 2ኛ መደበኛ ስብሰባ መጋቢት 3 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔም ይርጋን በተመለከተ ተጠሪ ከአመልካች ላይ ለ50 ዓመት የእርሻ መሬት ተከራይቻለሁ በማለት ያቀረበው ክርክር የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ድንጋጌን የሚቃረን ከአዋጁ ውጪ የባለይዞታነት ማረጋገጫ ደብተር አውጥቼበታለሁ በማለቱ ብቻ ባለይዞታው ይዞታውን እንዲያጣ እና ከይዞታው እንዲፈናቀል የሚያደርገው በመሆኑና የኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(4) የሚቃረን ስለሆነ ተፈጻሚነት የለውም ሲል ውሳኔ ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ/ቁጥር 79394 ላይ በሰጠው ውሳኔ በህግ እንዲደረግ ያልተፈቀደ ወይም የህግ ክልከላ ባለበት ጉዳይ ላይ የተደረገ ውል ህገ ወጥ ውል በመሆኑ ከመነሻውም ውጤት የሌለውና ፈራሽ መሆኑን፣ የውሉ መሰረታዊ ዓላማ በህግ ያልተፈቀደና የተከለከለ ሆኖ ሲገኝ ዳኞች ህገ ወጥ የሆነው ውል በቀረበላቸው ማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ውጤትና ተፈጻሚነት የለውም በማለት ለመወሰን የሚችሉና ህገ ወጥ የሆነውን ውል ውድቅ ለማድረግ በህጉ የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት በዚህ ጉዳይ 1. ክሱ የአሁን አመልካች በወለድ አግድ ውል የእርሻ መሬቴን ለተጠሪ ሰጥቼዋለሁ ሲል ያቀረበውን ዳኝነት ወለድ አግድ ህገ ወጥ የሆነ በእርሻ መሬት ላይ የተደረገ ውል መሆኑ በማያሻማ ሁኔታ እየታወቀ ክሱን በይርጋ ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ 2. የኢፌዴሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 40(3 እና 4) መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የህዝብና የመንግስት ሀብት መሆኑንና ባለይዞታው ከይዞታው ያለመነቀል መብት ያላቸው ስለመሆኑ ተደንግጎ እያለ በህገ ወጥ መንገድ የሚተላለፉ የእርሻ መሬቶች ሁሉ

በይርጋ የማይታገዱ ስለመሆኑ የፌደሬሽን ም/ቤት እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ሰጥተውበት እያለ ይህ ሁሉ ታልፎ የአሁን አመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ ይህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው እላለሁ፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካችን ክስ በይርጋ ውድቅ መደረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ የአሁን ተጠሪ ክስ የቀረበበትን የመሬት ይዞታ ከአሁን አመልካች አልተቀበልኩትም የሚል ክርክር ያለው በመሆኑ በፍሬ ጉዳዩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን መመለስ ሲገባ ህገ ወጥ በሆነ የወለድ አገድ ውል ላይ በመመስረት ክሱ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆን አለመሆኑ ተጣርቶ እንዲወሰን ተብሎ መመለሱ ህጉን ያልተከተለና ካለአግባብ ተከራካሪ ወገኖችን ላልተፈለገ ወጪና የጊዜ ብክነት የሚዳርግ በመሆኑ ተገቢ አይደለም እላለሁ፡፡

ማ/አ

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

ሰ/መ/ቁ፡-200948

ቀን፡-30/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ መ/ር ሲራጅ መሀመድ

ተጠሪ፡ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል::

ፍርድ

ጉዳዩ ከውል ውጭ ኃላፊነትን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነዉ፡፡የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን የአሁኑን አመልካች ጨምሮ ሌሎች 4 ሰዎች ላይ ባቀረበው ክስ ንብረትነቱ ከተከሳሾች የአንዳቸው ወይም የሁሉም የሆነ የሠ/ቁ.1-06754 አ.አ የሆነ ተሽከርካሪ በ25/04/2006ዓ.ም በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 4 አለም ባንክ አከባቢ ተጠሪ የመድን ሽፋን የሰጠውን የሰ/ቁ.4-01850አ..ት የሆነውን ተሽከርካሪ በመግጨት ጉዳት አድርሷል፡፡ተጠሪ ከደንበኛው ጋር ባለው ውል ስምምነት ለደረሰው ጉዳት ብር 19,250.00 ለደንበኛው ከፍሏል፣ስለሆነም ተከሳሾች ግንዘቡን እንዲተኩ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡አመልካች በበኩሉ አደጋ አድራሹን ተሽከርካሪ በ2005 ዓ.ም ለአቶ ጉግሳ ይልማ በመሸጥ መኪናውን ያስረከብኩት ስለሆነ ደረሰ ስለተባለው ጉዳትም የማውቀው ነገር የለም፣በእኔ

ላይ የቀረበው ክስ አለአግባብ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ሌሎች ተከሳሾች መልስ አላቀረቡም ቀርበውም አልተከራከሩም ተብሎ የታለፈ መሆኑን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክርና ማስረጃ መርምሮ የባለቤት ስም ዝውውር ባልተከናወነበት ጊዜ ሁሉ በባለቤትነት የሚታወቀው ሰው ንብረቱ በስሙ በመገኘቱ ብቻ ኃላፊ የሚሆን ስለመሆኑ ሰበር ችሎቱ መ/ቁ.24643 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል፡፡የቀረበው ማስረጃ ጉዳት ያደረሰው መኪና ለመሸጥ በሂደት ላይ ያለና አመልካች ለአቶ ጉግሳ ይልማ ለተባለው ሰው በማስተላለፍ ሂደት ላይ ያለ መሆኑን እንጂ ስመ ሀብቱ ሙሉ በሙሉ ወደ ገዥ መተላለፉን አያስረዳም፣ስለዚህ ለደረሰው ጉዳት አመልካችን ጨምሮ የስር ተከሳሾች ኃላፊ ናቸዉ በማለት የተጠየቀውን ብር 19,250.00 በአንድነትና በነጣላ ለተጠሪ እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኝ ክርክር መርምሮ መኪናው ጉዳት ባደረሰበት ጊዜ አመልካችን ጨምሮ በስር ተከሳሾች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ በመሆኑ በፍ/ሀ/ቁ 2081 መሰረት ባለሞተር ተሽከርካሪው ባለቤት የጉዳት ካሳ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ አጽንቷል፡፡ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ፤ አደጋው የደረሰው በ25/04/2006 ዓ.ም ሲሆን ክሱ የቀረበዉ ታህሳስ 22/2011 ዓ.ም ሲሆን ክሱ የቀረበው ጉዳቱ ከደረሰ ከ5 ዓመት ከ2 ወር በኋላ በመሆኑ ክሱ በይርጋ መታገድ ሲገባ መታለፉ የህግ ስህተት ነው፡፡ጉዳት አደረሰ የተባለው ተሽከርካሪ ለአቶ ጉግሳ ይልማ በቀን 21/04/2006 ዓ.ም በተፈፀመ የሽያጭ ውል ያስተላለፍኩ መሆኑን እና የተሸከርካሪዉ ባለቤት አቶ ጉግሳ ይልማ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ቀርቦ እያለ የሥር ፍ/ቤት ሽያጩ በሚመለከት አካል አልተመዘገበም፣አልፀደቀም በማለት ውድቅ ማድረጉ አግባብ አይደለም፣የሽያጭ ውሉ ባልተካደበት የጉዳት ካሳ እንዲከፍል መወሰኑ የህግ ስህተት ነዉ፤ተሽከርካሪውን የገዛዉ ሰዉ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ጠይቄ የስር ፍ/ቤት አለመቀበሉ አግባብ አይደለም፣ስለዚህ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀበት በመሆኑ እንዲሻር በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች መኪናውን መቼ እንደሸጠ መኪናውን የያዘው ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ የስር ፍ/ቤት አጣርተው የይርጋን ጉዳይ ባለየበት ይህንን አልፎ ስመ ሀብቱ ሙሉ በሙሉ አልዞረም በማለት አመልካችን ተጠያቂ ያደረገበት

አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ ባቀረበው መልስ ጉዳት ያደረሰው መኪና በአደጋው ቀን ስመ ሀብቱ በአመልካች ስም እንደነበር ከመንገድ ትራንፖርት ባለስልጣን ለስር ፍርድ ቤት የቀረበው ማስረጃ ያረጋግጣል፣ ምዝገባው ያስፈለገው ዋናው ዓላማ አንዱ እንዲህ ዓይነት ኃላፊነት በቀላሉ ለመለየት ሲሆን በውል ተሸጠ የሚለው ከአደጋ ቀን በኋላ መሆኑን ደጋፊ ሰነዶች ያረጋግጣሉ፣ስለዚህ ስመ ሀብቱ ሳይተላለፍ በአመልካች ስም ተመዝግቦ ስላለ በሰበር መ/ቁ.24643 ከተሰጠው ውሳኔ አንፃር አመልካች በፍ/ህ/ቁ 2081(1) መሰረት ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት ተብሎ መወሰኑ ስህተት የለበትም፡፡ይርጋን በተመለከተ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2143(2) መሰረት ጥፋቱ የመነጨው ከወንጀል ድርጊት ጋር በተያያዘ ሲሆን ሾፈሩ በንብረት ላይ ላደረሰው ጥፋት በደንብ መተላለፍ ወንጀል የተቀጣ በመሆኑ ይርጋው 2 ዓመት ሳይሆን 5 ዓመት ይሆናል፡፡ተጠሪ ክስ ያቀረበው ከ5 ዓመት በፊት መሆኑ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጦ የአመልካች መቃወሚያ በብይን ውድቅ በመደረጉ የተፈፀመ ስህተት የለም፡፡አመልካች የመንደር ውል ምክንያት በማድረግ ገዢ ጣልቃ እንዲገባ መጠየቁ አግባብ ስላልሆነ መታለፉ ትክክል ነው፡፡ስለዚህ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ በተጠሪ ደንበኛ ተሸከርካሪ ላይ ጉዳት አደርሷል የተባለዉ የሰሌዳ ቁጥር የሠ/ቁ.1-06754 የሆነዉ ተሸርካሪ ጉዳት በደረሰበት ጊዜ በአመልካች ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ከሚመለከተዉ አካል አጣርቶ ያረጋገጠዉ ፍሬነገር ጉዳይ ነዉ፡፡ባለሞተር ተሸከርካሪ ግዙፍነት ያለዉ ልዩ ተንቀሳቃሽ ንብረት በመሆኑ ባለቤትነት የሚረጋገጠዉ በምዝገባ ስርዓት ስለመሆኑ ከአዋጅ ቁጥር 681/20002 አንቀጽ 4 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡መብቱን የማስተላለፍ ዉልም ይህንኑ ስርዓት ተከትሎ መፈጸም ያለበት ስለመሆኑ ከአዋጁ አንቀጽ 6/3/ እና ከፍ/ብ ህግ አንቀጽ 1186/2/ ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡የምዝገባ ስርዓት አስፈላጊነቱ በአንድ በኩል ባለሞተር ተሸከርካሪ ካለዉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አኳያ ለባለንብረቱ ጥበቃ ለማድረግ ሲሆን በሌላም በኩል የሶስተኛ ወገን መብትና ጥቅም ከማስከበር

አንጻር ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እንደሆነ ይታመናል፡፡የተሸከርካሪ መለያ፣መመርመሪያና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 ዓላማ እና ይዘትም ይህንኑ የሚያስገነዘብ ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የአመልካች መከራከሪያ ነጥብ በሁለት ተከፍሎ ሊታይ የሚችል ነዉ፡፡አንደኛዉ ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባል የሚል ሲሆን ሌላኛዉ ተሸከርካሪዉ ጉዳት ባደረሰ ጊዜ ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ ተልለፏል በሚል ምክንያት በሃለፊነት ሊጠየቅ አይገባም የሚለዉ ነዉ፡፡በእኛም በኩል በቅድሚያ መታየት የሚገበዉ የይርጋ መቃወሚያ የታለፈበት ምክንያት ተገቢ መሆን አለመሆኑ ላይ ነዉ፡፡

በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 244 እና 245 እንደተደነገገዉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ወደ ስረ ነገር ክርክር ከመግባቱ በፊት እልባት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ ክሱ በሁለት ዓመት ይርጋ ጊዜ ይታገዳል በማለት አመልካች ያቀረበዉን መቃወሚያ አስመልክቶ ሥር ፍርድ ቤት በብይን ዉድቅ ማድረጉን የስር መዝገብ አስቀርበን ተመልክተናል፡፡ከመዝገቡ እንደሚታዉ ፍርድ ቤቱ በ30/08/2011ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ብይን ይዘት ሲታይ አደጋዉ የደረሰዉ በ25/04/2006ዓ.ም መሆኑን እና ክሱ የቀረበዉ በ22/04/2011ዓ.ም ሆኖ በዚህ መካከል ያለዉ ጊዜ 2ዓመት ያለፈዉ ቢሆንም ይርጋዉ ጊዜ መታሰብ ያለበት በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2143/1/ ላይ የተመለከተዉ ሁለት ዓመት ጊዜ ሳይሆን በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ሁለት መሰረት በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 572 እና 217/1/ሠ አግባብ መሆኑን በማመላከት ክሱ እስከ አምስት ሊቀርብ እንደሚችል እና የአምስት ዓመት ጊዜዉ ያላለፈበት መሆኑን በማረጋገጥ የአመልካችን ይርጋ ክርክር ዉድቅ ማድረጉን ያጣያል፡፡

በእኛም በኩል ከክርክሩ እንደተገነዘብነዉ ጉዳት አድራሹ ተሸከርካሪ አሽከርካሪ በቸልተኝነት የተጠሪ ደንበኛ ተሸከርካሪ በመግጨት በንብረት ላይ ጉዳት በማድረሱ የትራፊክ በደንብ መተላለፍ የተቀጣ መሆኑ አላከራከረም፡፡ለፍትሓብሔር ክስ የይርጋዉ ጊዜ የሚታሰበዉ በፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 2143/1/ የተመለከተዉ የሁለት ዓመት ጊዜ ገደብ ሳይሆን በፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 2143/2/ መሰረት ድርጊቱ በወንጀል የሚያሥጠይቅ መሆኑን ተክተሎ በወንጀል ሕጉ የተመለከተዉ ይርጋ ጊዜ ተፈጻሚነት እንዲኖረዉ መደረጉ አግባብነት ያለዉ ነዉ፡፡በተመሳሳይ ጉዳይ ይህ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ/58920 ላይ የሰጠዉ ዉሳኔም ይህንኑ የምያስገነዘብ ነዉ፡፡ነገር ግን የወንጀል ይርጋ እንደወንጀሉ ክብደት የሚለያይ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለዉ የትኛዉ ነዉ የሚለዉ ከድርጊቱ አንጻር መታየት አለበት፡፡ከዚህ አኳያ ጉዳቱ የደረሰዉ ተሸከርካሪ ከተሸከርካሪ ግጭት በመሆኑ ተፈጻሚነት ያለዉን የይርጋ ጊዜ

ለመለየት የሚቻለዉ በድርጊቱ ጥፋተኛ የሆነዉ ሰዉ የሚቀጣዉ በትራፊክ ደንብ መተላለፍ ብቻ ነዉ ወይስ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 572 ወይም ሌላ ከፍ ያለቅጣት በሚደነግገዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ ነዉ የሚለዉ ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡

በዚህ ረገድ ይህ በሰር ችሎት በመ/ቁ/194880 ላይ የወንጀል ህግ ቁጥር 572 ተፈጻሚነት ወሰን አስመልክቶ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ከዉሳኔዉ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 572 አነጋገር መሰረት አንድ አሽከርካሪ ወይም እግረኛ በቸልተኛነት የትራፊክ ደንብ በመጣስ በፈጸመዉ ድርጊት ሌላዉ አሽከርካሪ ወይም እግረኛ የሌላዉን ሰዉ ሕይወት፣አካል፣ጤና ወይም ንብረት ለአደጋ ሲያጋልጥ (ሲጎዳ) የመጀመሪያዉ አሽከርካሪ ወይም እግረኛ የትራፊክ ደንብን በመጣስ ሌላዉን ሰዉ ለአደጋ በማጋለጡ የሚጠየቅበት ድንጋጌ እንጂ በተያዘዉ ጉዳይ የተከሰተዉን አንደኛዉ አሽከርካሪ የትራፊክ ደንብ በቸልተኛነት በመጣሱ ምክንያት በሁለት ተሽከርካሪዎች መካከል ግጭት በመፈጠሩ በሁለተኛዉ ተሽከርካሪ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ጉዳት አድራሹን አሽከርካሪ በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ የተደነገገ ድንጋጌ አይደለም፡፡

በወንጀል ሕጋችን በአንቀጽ 677(1/ለ እና 2) ስር በተደነገገዉ መሰረት ማንም ሰዉ በመንግስት ወይም በሕዝብ ንብረት ላይ በቸልተኛነት በድንጋጌዎቹ በተገለጸዉ አነጋገር ጉዳት በማድረሱ ሊጠየቅ ከሚችል በስተቀር በንብረት መብቶች ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች ስድስተኛ መጽሐፍ ርእስ አንድ ስር በተደነገጉ ድንጋጌዎች መሰረት በመንግስት ወይም በሕዝብ ወይም በግለሰብ ንብረት ላይ በቸልተኛነት ጉዳት ማድረስ እንደ መደበኛ ወንጀል ተቆጥሮ የሚያስጠይቅ አይደለም፡፡ እንዲሁም ምንም እንኳን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2 መሰረት በቸልተኛነት የትራፊክ ደንብ በመጣስ በሰዉ አካል ላይ ጉዳት ማድረስ በወንጀል የሚያስጠይቅ ቢሆንም ከላይ እንደተመለከተዉ በተለይም አንድ አሽከርካሪ በቸልተኛነት የትራፊክ ደንብ በመጣስ በሚያሽከረክረዉ ተሽከርካሪ ራሱ ሌላ ተሽከርካሪ ወይም ንብረት በመግጨት በሌላ ተሽከርካሪ ወይም በሌላ ንብረት ላይ ጉዳት ቢያደርስ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን በወንጀል ሕጉ አልተደነገገም፡፡ይህም የሆነበት ምክንያት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 662 ስር በተደነገገዉ መርህ ላይ እንደተመለከተዉ በሌላ ሰዉ ንብረትና የኢኮኖሚ መብት ወይም በገንዘብ ሊተመኑ በሚችሉ መብቶች ላይ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት ከፍተኛነት ደረጃ ታይቶ በሕጉ ስድስተኛ መጽሐፍ ስር እንደወንጀል ድርጊት ተቆጥሮ በግልጽ አስቀጪነታቸዉ ካልተደነገገ በስተቀር እንደአነስተኛ ድርጊት ተቆጥሮ አጥፊዎች በደንብ መተላለፍ እንዲቀጡ ማድረግ የሕግ አዉጭዉ ፍላጎት በመሆኑ ነዉ፡፡ከዚህም በመነሳት ተጠሪ በደንበኛዉ እግር በመተካት ከጉዳት አድራሹ ካሳ ለመጠየቅ መሰረት ያደረገዉ ድርጊት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 572 የሚገዛ ባለመሆኑ ከዚህ አንጻር ታይቶ የይርጋ ጊዜዉ 5ዓመት ነዉ ተብሎ መወሰኑ ስህተት ነዉ፡፡

ይልቁንም የጉዳት አድራሹ ድርጊት የትራፊክ ደንብ መተላለፍ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 856 ስር የሚያስቀጣ በመሆኑ የይርጋ ጊዜም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 773 ስር የተደነገገዉ የአንድ ዓመት ጊዜ ነዉ፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ በወንጀል ህጉ የተመለከተዉ የይርጋ ጊዜ በፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 2143/1/ስር ከተመለከተዉ ጊዜ ያነሰ በመሆኑ እና ክሱ የቀረበዉ የፍትሓብሔር ሃላፊነትን የሚመለከት እንደመሆኑ ተፈጻሚነት ያለዉ በፍ/ብ/ህጉ አንቀጽ 2143/1/ የተመለከተዉ የሁለት ዓመት ጊዜ ገደብ ነዉ ብለናል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ ክሱን ያቀረበዉ በ22/04/2011ዓ.ም ሲሆን ጉዳቱ ከደረሰበት 25/04/2006ዓ.ም ጀምሮ ወይም ለደንበኛዉ መኪና ማስጠገኛ ወጪ ከከፈለበት ከ21/12/2006ዓ.ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ያለዉ ጊዜ ሲታሰብ ሁለት ዓመት ጊዜ አልፎበታል፡፡ይህም በመሆኑ ክሱ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2143/1/ የተደነገገዉ ሁለት ዓመት ጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የቀረበ መሆኑን ስለሚያሣይ ክሱ በይርጋ መታገድ ሲገባዉ ታልፎ በፍሬነገሩ ላይ ዉሳኔ መሰጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/በዚህ ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ/271073 ላይ በቀን 30/08/2011ዓ.ም የሰተዉ ብይን እና በቀን በ11/02/2012ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መ/ቁ/247111 ላይ በ28/03/2013ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/በዚህ ጉዳይ የተጠሪ ክስ በይርጋ ታግዷል ብለናል፡፡

3ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

የስር ፍርድ ቤት መ/ቁ/271073 በመጣበት ሁኔታ ይመለስ፡፡

<u>መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡</u>

ሂ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-200929

ቀን፤-30/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ሕዳሴ ቴሌኮም አ/ማ

ተጠሪ ፡- 1. አቶ ገዛኸኝ ለማ

2. አቶ ሕዝቂያስ ታፈሰ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ከሳሽ፣ ተጠሪዎች ተከሳሾች ሆነው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ያቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች የሽያጭ ሠራተኛ ሆነው ሲሰሩ በውስጥ አዲት በሚደረግበት ጊዜ ብር 204,250.00 በጉድለት ስለተገኘ ገንዘቡን እንዲከፍሉ፤ 2ኛ ተጠሪም የ1ኛ ተጠሪ ዋስና ተያዥ በመሆናቸው እስከ 100,000.00 በአንድነትና ነጠላ ኃላፊነት እንዲከፍሉ የሚል ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ የሠጡት መልስ ገቢና ወጪውን ያልለየ፣ ከመቼ እስከመቼ የተደረገ አዲት ስለመሆኑ ግልጽ አይደለም፡፡ በውጭ አዲተር አዲት ይደረግልኝ ብለዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ጉድለት የለም፣ ዋስ የሆንኩት 1ኛ ተጠሪ የመስመር ሠራተኛ እያለ ነው፤ ልጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58351 ግራቀኙን አከራክሮና በተፈቀደለት የሂሳብ ባለሙያ ድጋሜ ኦዲቱ እንዲሰራ በማድረግ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ 1ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉና 2ኛ ተጠሪ እስከ ብር 100,000.00 ድረስ በአንድነት እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ይግባኝ ተቀብሎ በድጋሜ ኦዲቱ እንዲሰራ ካዘዘ በኋላ 1ኛ ተጠሪ ብር 204,250.00 ገንዘብ ማጉደላቸውን የቀረበው ማስረጃ ያሳያል፡፡ ነገር ግን ይህንኑ ገንዘብ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት GSM Mobile Prepaid Card certificate ገቢ ስለመሆኑ ማስረጃ ያቀረቡ ቢሆንም በትክክል ገንዘቡ ገቢ ስለመሆኑ የሚረጋገጠው ቅጽ 7 (ውስጣዊ ደረሰኝ) ያላቀረቡ መሆኑን በመግለጽ ኦዲት የሰራው ተቋም ገልጿል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ገንዘቡ ገቢ ስለመሆኑ ቅጽ 7 ደረሰኝ ከአመልካች ተቋም ማግኘታቸውን በመግለጽ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲያያዝላቸው የጠየቁ ሲሆን አመልካች አዲስ ማስረጃ ሊያያዝ አይገባም፤ ይያያዝ ቢባል እንኳን የሽያጭ ገንዘቡ ወደባንክ ገቢ ከሆነው ስሊፕ ጋር ያልቀረበ በመሆኑ ፍርድ ቤቱን ለማሳሳት የቀረበ ነው ሲል አስተያየቱን አቅርቧል፡፡ የቀረበው ማስረጃ የአመልካች ማሕተም ያረፈበት፣ የአመልካች ሠነድ አለመሆኑ ያልተካደ በመሆኑና ማስረጃው ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የሚያግዝ በመሆኑ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 345 መሠረት ፍርድ ቤቱ ተቀብሎ በማያያዝ በጉድለት ተገኘ የተባለው ብር 204,250.00 ለአመልካች በቅጽ 7 (የውስጥ ደረሰኝ) ገቢ የተደረገ ስለመሆኑ ስለተረጋገጠ 1ኛ ተጠሪ ያጎደሉት ገንዘብ የለም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የገንዘብ ጉድለቱ በኦዲት ምርመራ ተረጋግጧል፡፡ ከሥነ-ሥዓት ውጭ አዲስ ማስረጃ መቀበሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ማስረጃው የገቢ ሠነድ ማስረጃ አይደለም፡፡ የውስጥ ደረሰኝ አይደለም፤ ቢሆን እንኳን ከባንክ ስሊፕ ጋር ያልቀረበ ስለሆነ ውጤት ሊኖረው አይችልም የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ማስረጃው የተያያዘበት አግባብነትና ማስረጃው ገንዘብ ገቢ ማድረጋቸውን የሚያሳይ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርብ በማዘዙ ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ የቅጽ 7 ሰነድ ከሥራ ተሰናብቼ ስለነበር ማግኘት ባለመቻሌ ያልቀረበ ሲሆን በኋላ ግን 1ኛ ተጠሪ የአመልካች ኃላፊን አስፈቅዶ ሠነዶችን ፈትሾ ያገኘው ነው፡፡ ሠነዱ የገቢ ደረሰኝ ሲሆን የገቢ ደረሰኝ አለመሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ያልተካደ ነው፡፡ ማስረጃው ተመዝኖ የተሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል ብለዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ይግበኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የክርክር አመራር ተገቢ መሆን አለመሆኑን እና የማስረጃ ምዘና መርህን መሠረት አድርጎ መወሰን አለመወሰኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ያቀረበው ክስ 1ኛ ተጠሪ የአመልካች የሽያጭ ሠራተኛ ሆነው ሲሰሩ በውስጥ ኦዲት በሚደረግበት ጊዜ ብር 204,250.00 በጉድለት ስለተገኘ ገንዘቡን እንዲከፍሉ፤ 2ኛ ተጠሪም የ1ኛ ተጠሪ ዋስና ተያዥ በመሆናቸው እስከ 100,000.00 በአንድነትና ነጠላ ኃላፊነት እንዲከፍሉ የሚል ሲሆን

ተጠሪዎች በበኩላቸው ገንዘቡ አልጎደለም፤ የኦዲት አሰራሩ ተገቢነት የለውም፣ ድጋሜ ኦዲት ይደረግልን ለክሱ ልንጠየቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል። ፍርድ ቤት የቀረበለትን የፍትሐ ብሔር ክርክር ጉዳዩን ለማስረዳት በሕግ ተቀባይነት ባለውና ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ማስረጃ በማረጋገጥ ማን የተሻለ እንዳስረዳ የመወሰን ኃላፊነት አለበት። ክርክርን ለማስረዳት ማስረጃ የሚቀርብበት ሥርዓት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 223 መሠረት የሰው ማስረጃ ዝርዝር እና በፅጁ የሚገኝ የፅሁፍ ማስረጃን የሚቀርብበት ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 145 መሰረት ደግሞ በተከራካሪ ፅጅ የሌሉ ወይም ለማቅረብ ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቁ ማስረጃዎች በፍርድ ቤት እገዛ የሚቀርቡበት ነው። የሠነድ ማስረጃ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 137 መሠረት ክሱ እስከሚሰማበት ጊዜ ድረስ ማቅረብ የሚቻል ሲሆን በእነዚህ ሂደቶች ማስረጃው ያልቀረበው ተከራካሪው ባለማወቁ ወይም አዲስ የተገኘ ማስረጃ ከሆነ ደግሞ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 256 አግባብ ማስረጃው እንዲቀርብ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል። በዚህ አግባብ ማስረጃ እንዲቀርብ የሚጠየቀው ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ሊሆን ይገባል። ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በይግባኝ ደረጃ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 327(3) እና 345 መሠረት በልዩ ሁኔታ ማስረጃ የሚስተናገድበት ሥርዓትም ተዘርግቷል።

ተጠሪ ክሱን ለማስረዳት የኦዲት ውጤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤት የማስረጃውን ትክክለኛነት ማጣራት ከፈለገ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 264 በተሠጠው ስልጣንና ኃላፊነት ድጋሜ ኦዲት እንዲሰራ በማዘዝ ክርክሩን መወሰን ይችላል። በዚህም አግባብ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የኦዲት ሥራው በድጋሜ እንዲከናወን አዟል። የቀረበው የኦዲት ውጤት 1ኛ ተጠሪ የገንዘብ ጉድለት ያለባቸው መሆኑን ያሳያል። ነገር ግን ይህንኑ ገንዘብ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት GSM Mobile Prepaid Card certificate ገቢ ስለመሆኑ ማስረጃ ያቀረቡ ቢሆንም በትክክል ገንዘቡ ገቢ ስለመሆኑ የሚረጋገጠው ቅጽ 7 (ውስጣዊ ደረሰኝ) ያላቀረቡ መሆኑን ኦዲት የሰራው ተቋም መግለጹ ተከትሎ 1ኛ ተጠሪ ገንዘቡ ገቢ ስለመሆኑ ቅጽ 7 ደረሰኝ ከአመልካች ተቋም ማግኘታቸውን በመጥቀስ በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲያያዝላቸው የጠየቁ ሲሆን ፍርድ ቤቱ አመልካች ክርክር እንዲያቀርብበት ካደረገ በኋላ የቀረበው ማስረጃ የአመልካች ማሕተም ያረፈበት፣ የአመልካች ሠነድ አለመሆኑ ያልተካደ በመሆኑና ማስረጃው ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የሚያግዝ በመሆኑ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 345 መሠረት ተቀብሎ በማያያዝ በጉድለት ተገኘ የተባለው ብር 204,250.00 ለአመልካች በቅጽ 7 (የውስጥ ደረሰኝ) ገቢ የተደረገ ስለመሆኑ ስለተረጋገጠ 1ኛ ተጠሪ ያጎደሉት ገንዘብ የለም ሲል ድምዳሜ ላይ ደርሷል። የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 345(1)(ለ) እና 327(3) ላይ ይግባኝ ሰሚ ፍር ቤት ትክክለኛ ፍትሕ ለመስጠት የሚረዳ ተጨማሪ ማስረጃ ማያያዝ የሚችል ስለመሆኑ የተመለከተ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤትም በዚህ ድንጋጌ ማዕቀፍ ማስረጃውን በመቀበሉ የፈጸመው የሥነ-ሥርዓት ሕግ ጥሰት የለም ብለናል።

ለቀረበው ክስ የግራቀኙን ማስረጃ ፍርድ ቤቱ ከተቀበለ በኋላ በፍትሐ ብሔር ክርክር የምንከተለው የማስረዳት ደረጃ ከሁለቱ ወገን የተሻለ ያስረዳው ማን ነው (preponderance of evidence) የሚለውን በመመርመር እና የማስረጃ ተገቢነት፣ የማስረጃው ተቀባይነትን ደንቦችን መከተል እና ለማስረጃው የሚሰጠውን ክብደት (weight of evidence) በመለየት የመወሰን ኃላፊነት ማስረጃ ለመስማትና ለመመዘን ኃላፊነት ያለባቸው ፍርድ ቤቶች ዋና ተግባር ነው። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 80(3) በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃ መዝኖ 1ኛ ተጠሪ ገንዘብ ስለማጉደላቸው አልተረጋገጠም በሚል የደረሰበት የፍሬ ነገር ድምዳሜና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ የማስረጃ ምዘና መርሕ ስህተት ያልተገኘበት ስለሆነ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 193074 ጥቅምት 16 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14397 ጥቅምት 14 ቀን 2012 የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 200919

ጥቅምት 01 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡ አቶ በቀለ ድሪብሳ- ጠበቃ ዘነበ ጥላሁን ጋር ቀረቡ

ተጠሪ ፡ አቶ የምክር በሪሁን- ጠበቃ ግሩም አየለ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን የአፈጻጸም ክርክሩ በተጀመረበት የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች የፍርድ ባለእዳ ተጠሪ ደግሞ የፍርድ ባለመብት በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩን አመጣጥ ስንመለከት ተጠሪ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15170 አመልካችን ጨምሮ በ5 ሰዎች ላይ በቀድሞ ወረዳ 17 ቀበሌ 21 የሚገኝ የቤት ቁጥር 552 እንዲያስረክቡኝ እና ስመሀብት እንዲያዛውሩልኝ ይወሰንልኝ የሚል ክስ አቅርበው መስከረም 26 ቀን 1999 ዓ.ም. አመልካችን ጨምሮ 4 ተከሳሾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ተወስኗል፡፡ ተጠሪም ይህንን ውሳኔ መሰረት በማድረግ በአፈጻጸም መዝገብ ቁጥር 109064 የአፈጻጸም አቤቱታ አቅርበው ቤቱን ከተረከቡ በኋላ አመልካች እና 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ ደስታ ከፈኔ ተጠሪ ቤቱን እንዲረከቡ በተሰጠው ውሳኔ ላይ የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ውሳኔውን አሽረዋል፡፡ የውሳኔውን መሻር ተከትሎ አመልካች እና ባለቤታቸው ተጠሪ በአፈጻጸም

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የተረከቡትን ቤት መልሰው እንዲያስረክቧቸው አቤቱታ አቅርበው ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች እና ለባለቤታቸው ወ/ሮ ደስታ ከፈኔ አስረክበው አፈጻጸሙ በመጠናቀቁ የአፈጻጸም መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ አጠቃላይ ይዞታዬ 391 ካ.ሜ. የነበረ ሲሆን ከዚህ ላይ ለአመልካች እና ባለቤታቸው ቤቱን ከ200 ካ.ሜ. ይዞታ ጋር ሳስረክብ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ይቀረኛል፡፡ ስለዚህ በቀሪው 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማት ማኔጅመንት የይዞታ ምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ እንዲሰጠኝ ይታዘዝልኝ በማለት በተዘጋው የአፈጻጸም መዝገብ ላይ አቤቱታ አቅርበው ፍርድ ቤቱም በተጠሪ አቤቱታ መሰረት የምስክር ወረቀት

ተዘጋጅቶ ለተጠሪ እንዲሰጥ አዟል፡፡ አመልካች በዚህ ትእዛዝ ላይ የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ቅሬታው በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 337 መሰረት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካች በ06/05/2013 ዓ.ም. የተጻፈ የሰበር ቅሬታ ያቀረቡት በስር ፍርድ ቤት በተሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ ተፈጽሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ለማሳረም ሲሆን የቅሬታው ይዘት በ191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ ለተጠሪ ካርታ እንዲሰጥ ፍርድ አልተሰጠም፡፡ የአፈጻጸም ትእዛዙ ሲሰጥም አመልካች አስተያየት እንድሰጥ አልተደረገም፡፡ ይዞታው ለ15 ዓመት ግብር የገበርኩበት ስለሆነ ለተጠሪ ካርታ ተሰርቶ ይሰጥ መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎትም የአመልካችን የሰበር ቅሬታ መርምሮ የተሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ ፍርዱን የተከተለ ነው አይደለም? የሚለውን ለማጣራት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪም በ01/07/2013 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት መልስ የአፈጻጸም ትእዛዙ የተሰጠው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15170 መስከረም 26 ቀን 1999 ዓ.ም. በተሰጠ ፍርድ መሰረት ነው፡፡ በዚህ ውሳኔ ቤት እንድረከብ የተወሰነ ቢሆንም አመልካች እና ወ/ሮ ደስታ ከፈኔ በውሳኔው ላይ የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25551 ቤት እንድረከብ የተሰጠውን ውሳኔ ክፍል በመሻሩ ከአመልካች እና ከባለቤታቸው በአፈጻጸም የተረከብኩትን ቤት ከ200 ካ.ሜ. ቦታ ጋር መልሼ አስረክቤአለሁ፡፡ አመልካች በውሳኔው መሰረት ሳይረከቡ የቀረ ነገር የለም፡፡ በተጨማሪም የይዞታ የምስክር ወረቀት ተሰርቶ እንዲሰጠኝ የታዘዘው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02371፣ 04076፣ 04952፣ 34520 እንዲሁም በፌደራል ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 09161 እና 38575 የተሰጡ ውሳኔዎች ታይተው በመሆኑ በተሰጠው የአፈጻጸም ትእዛዝ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም በ16/07/2013 ዓ.ም. የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር ቅሬታቸውን አጠናክረዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንጻር ለቅሬታ መነሻ ከሆነው ትእዛዝ እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ለቅሬታ መነሻ የሆነው የአፈጻጸም ትእዛዝ ለተጠሪ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ሰርቶ ይስጥ የሚል ነው፡፡ አመልካች ይህንን ትእዛዝ የሚቃወሙት ተጠሪ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰራላቸው የተሰጠ ውሳኔ የለም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በመዝገብ ቁጥር 15170 እና በሌሎች መዝገቦች ላይ በተሰጠ ውሳኔ መሰረት የአፈጻጸም ትእዛዙ የተሰጠ መሆኑን በመግለጽ ትእዛዙ ተገቢ መሆኑን ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያሻው ለተጠሪ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ተሰርቶ እንዲሰጣቸው የተሰጠ ፍርድ አለ ወይስ የለም? የሚለው ይሆናል፡፡

በፍርድ አፈጻጸም ጊዜ ፍርድ ቤቶች ሊያስፈጽሙ የሚገባው በተሰጠው ፍርድ መሰረት መሆን እንዳለበት የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 378 እና ተከታይ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ ከተዘረጋው ስርአት ውጪ የአፈጻጸም ችሎት የፍርዱን ይዘት በሚቀይር መልኩ ወይም ፍርድ ያልተሰጠበትን ነገር ማስፈፀም አይችልም፡፡ የፍርድ አፈጻጸም ስርአት አንድ ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በራሱ አማካኝነት በህጉ የተዘረጋውን የአፈጻጸም ስርአት በመከተል ወደውጤት የሚቀይርበት በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አፈጻጸሙ ፍርዱን የተከተለ መሆኑን የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ 191 ካ.ሜ. ይዞታን በተመለከተ ፍርድ ተሰጥቶበታል የሚሉት አንድም በመዝገብ ቁጥር 15170 በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመስከረም 26 ቀን 1999 ዓ.ም. የተሰጠውን ፍርድ በመጥቀስ ሲሆን እኛም የዚህን ፍርድ ይዘት ተመልክተናል፡፡ የፍርዱ ይዘት ተጠሪ አመልካችን ጨምሮ በአራት ሰዎች እና በአዲስ አበባ መስተዳድር የስራ ከተማ ልማት ቢሮ ላይ በቀድሞ ወረዳ 17 ቀበሌ 21 በካርታ ቁጥር 17910 የተመዘገበውን የቤት ቁጥር 552 የሆነውን ቤት ለመረከብ እና ስመ ሀብት እንዲዛወርላቸው ክስ አቅርበው አራቱ ተከሳሾች የተጠቀሰውን ቤት ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የተወሰነ መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች እና 2ኛ ተከሳሽ የነበሩት የአመልካች ባለቤት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25551 የይግባኝ ቅሬታ አቅርበው ተጠሪ ቤት እንዲረከቡ የተሰጠው ውሳኔ መሻሩን የፍርዱ ግልባጭ የሚያመለክት ሲሆን በተጠሪም የታመነ ጉዳይ ነው፡፡ ይህም ማለት ተጠሪ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 15170 በግልጽ ቤት ይረከቡ በሚል የተፈረደላቸው ፍርድ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25551 በሰጠው ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ በመዝገብ ቁጥር 15170 በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በተሰጠ ውሳኔ መሰረት ለተጠሪ ሊፈጸምላቸው የሚችል ነገር የለም ማለት ነው፡፡ የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ትእዛዙን ሲሰጥ በምክንያትነት የጠቀሰው የተጠሪ አጠቃላይ ይዞታ 391 ካ.ሜ. ሲሆን ከዚህ ይዞታ ላይ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 349 መሰረት

200 ካ.ሜ. ቦታ ተቀንሶ አመልካች እና ባለቤታቸው ሲረከቡ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ለተጠሪ ይቀራል በሚል ነው። ነገር ግን ተጠሪ ክስ ያቀረቡበት የመዝገብ ቁጥር 15170 ላይ ተጠሪ ቤት እንዲረከቡ የተሰጠው ውሳኔ በተሻረበት ሁኔታ ለተጠሪ ምን ያክል ይዞታ እንደሚቀር እና በሚቀረው ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰራ በአፈጻጸም ችሎት ሊታዘዝ የሚችልበት የህግ አግባብ የለም። ይህ ማለት ግን ተጠሪ ከፍርድ ቤት የአፈጻጸም ትእዛዝ ውጪ ለሚመለከተው የመንግስት አካል የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው መጠየቅ አይችሉም ማለት አይደለም። ስለዚህ ተጠሪ ይዞታው ላይ በሚመለከተው የመንግስት አካል የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲሰጣቸው ከሚጠይቁ እና ይህ አካል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካላቸው በተገቢው የህግ አግባብ አለኝ የሚሉትን መብት ክስ በማቅረብ ከሚያስከብሩ በስተቀር ተጠሪ በጠቀሱት በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 15170 ላይ የተሰጠው ውሳኔ የተሻረ በመሆኑ ለተጠሪ የይዞታ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በማድረግ የሚፈጸም ፍርድ የለም።

ሌላው ተጠሪ ከአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እስከ ፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 02371፣ 04076፣ 04952፣ 34520 እንዲሁም በፌደራል ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 09161 እና

38575 የተሰጡ ውሳኔዎች ታይተው ነው የአፈጻጸም ትእዛዝ የተሰጠው በማለት የሚያነሱትን ክርክር ስንመለከት በነዚህ በውሳኔዎች ላይም ቢሆን አመልካች የቤት ቁጥር 552 ን በተመለከተ ሁከት ይወገድልኝ ክስ አቅርበው ውድቅ የተደረገበት እንጂ ተጠሪ የሚገባቸው ይዞታ ምንያክል እንደሆነ ተረጋግጦ ፍርድ ያረፈበት አይደለም።

ሲጠቃለል የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለተጠሪ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ተሰርቶ እንዲሰጥ በማለት የአፈጻጸም ትእዛዝ የሰጠው ተጠሪ መብት አግኝቻለሁ የሚሉበት ቤት እንዲረከቡ የተሰጠው ውሳኔ በተሻረበት እና ተጠሪ 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ መብት ያላቸው መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ ፍርድ በሌለበት በመሆኑ በፍ/ስ/ስ/ህ/ህጉ የተዘረጋውን የአፈጻጸም ስርአት የሚቃረን እና ከአፈጻጸም ችሎት ስልጣን ውጪ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው። ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ስህተት ሳያርም መቅረቱ መሰረታዊ ህግ ስህተት በመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል።

<u>ውሳኔ</u>

1ኛ. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር109006 በ10/03/2012 ዓ.ም. እና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 247114 በ22/04/2013 ዓ.ም. የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል።

2ኛ. ተጠሪ ቤት እንዲረከቡ የተሰጠው ውሳኔ በተሻረበት እና 191 ካ.ሜ. ይዞታ ላይ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ተሰርቶ እንዲሰጣቸው የተሰጠ ፍርድ በሌለበት የአፈጻጸም ትእዛዝ መሰጠቱ ተገቢ አይደለም ብለናል።

3ኛ. ይህ ውሳኔ ተጠሪ ለሚመለከተው የመንግስት አካል የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ጥያቄ እንዳያቀርቡ የሚያግድ አይደለም።

4ኛ. በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገ ክርክር ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል። ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፈርማ አለበት

ማ/አ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-200871

ቀን፡-27/01/2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ
ፀሐይ መንክር
ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ አባይነህ አለባቸው ፡- ጠበቃ የሸበር መልኬ ቀርበዋል

ተጠሪ፡- አቶ መሉጌታ አዳነ -ተወካይ ላንቺስል አዳነ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ጎንደር ዞን ከፍኛ ፍርድ ቤት በተጀመረው ቤትና ይዞታን ለማስለቀቅ የቀረበውን ክርክር ተጠሪ ከሳሽ አመልካች 1ኛ ተከሣሽ በዚህ ክርክር ያልተጠሩት እማሆይ ታከለች ረታ 2ኛ ተከሣሽ እነ ወ/ሮ ነገሱ አለባቸው 4 ሰዎች ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የከተማ ቤትና ይዞታን በሚመለከት የቀረበ የመፋለም ክርክር የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ ሰኔ 12ቀን2006ዓ/ም በተፃፈ ክሳቸው በወረታ ከተማ ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 042 የሆነውንና አዋሣኙ የተጠቀሰውን ቤት የተጠሪ እናትና አባት ቤት ቢሆንም ወላጆቹ ከሞቱ በኋላ ለአመልካቹ በአደራ ተሰጥቶት እየተጠቀመበት መሆኑን እንዲያስረክበው ቢጠይቀውም ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረችዋ እማሆይ ታከለች ረታ መሬት ነው በሚል ምክንያት ለመልቀቅ ፈቃደኛ አለመሆኑን በመዘርዘር ቤቱን እንዲለቅለት እንዲወሰንለት ጠይቋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካች ቀርቦ ቤቱ የተጠሪ እናትና አባት ሐብት ስላልሆነ ክስ ማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የለውም ሲል የመጀመሪያ መቃወሚያና ተጠሪው ማስረጃ አለማቅረቡን የተጠሪ አባት የደም ችግር ስለነበረበት ለደህንነቱ ሲባል ከሚኖርበት ቤት የተሻለ መሆኑ ታምኖበትና ከእናታቸው ከእማሆይ ታከለች ረታ ጋር ተማክረው እንዲኖርበት በመደረጉ እንጅ የቤቱ ባለሃብት አለመሆኑን፣ የመብራትና ውሃ ደረሰኝ የቤት ባለሃብትነትን የማያረጋግጥ መሆኑን በመዘርዘር ቤቱ የአመልካች አባትና የእማሆይ ታከለች ረታ ሃብት ነው ሲል ተከራክሯል፡፡ የእማሆይ ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው የታለፈ ቢሆንም በኋላ መሞታቸው ስለተረጋጠ ተተኪዎች ቀርበው መልስ ሰጥተዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ ደረጃ ላይ እያለ ጣልቃ ገቦች ቀርበው ቤቱ የሁለተኛ ተከሣሽና የባለቤታቸው (የጣልቃ ገቦች አያት) መሆኑን እነርሱ ተሣታፊ ሣይሆኑ በወንድ አያታቸውን ድርሻ ላይ የሚደረገው ክርክር መብታቸውን እንደሚጎዳ በመዘርዘር መብታቸው እንዲከበርላቸው በመጠየቅ አመልካች ካቀረበው ክርክር ጋር ተመሣሣይነት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጣልቃ ገቦች የሚያቀርቡት አቤቱታ በይርጋ የታገደ ነው በክርክሩ ጣልቃ ለመግባት የሚያስችል መብትና ጥቅም የላቸውም እንዲሁም ክርክራቸው አመልካች ከሚያቀርበው ክርክር ጋር ተመሣሣይ በመሆኑ ውድቅ እንዲደረግለት ተከራክሯል፡፡ እማሆይ ታከለች ረታ በመሞታቸው አመልካችና ጣልቃ ገብ በክርክሩ ተተኪ ሆነው መልስ መስጠት እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው ተፈቅዶላቸው መልስ ሰጥተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክሩን ውድቅ ካደረገ በኋላ ግራ ቀኙ ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር እንዲሁም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተለያዩ የከተማው የመንግስት አካላት አጣርተው መግለጫ እንዲያቀርቡለት ትዕዛዝ ሰጥቶ የቀረበለትን መግለጫ አከራካሪው ቤትና ይዞታ የተጠሪ አባትና እናት ሃብት ነው ወይስ የአመልካች አባት የአቶ አለባቸው አድገህና የእማሆይ ታከለች ረታ የሚለውን ጭብጥ ይዞ መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት የአመልካች አባት ከ1953 ዓ/ም አከራካሪውን ይዞታ ገዝተው ቤት ለመስራት በ1963ዓ/ም ፈቀድ ጠይቀው የነበረ ቢሆንም በ1976ዓ/ም በማዘጋጃ ቤቱ በተደረገ ምሪት ይዞታውን የተጠሪው አባት የተመራው መሆኑ፣ የአመልካች አባት ከ1976ዓ/ም ጀምሮ ግብር ከፍለውበት የማያውቁ መሆኑን፣ ለአጎራባች ባለይዞታዎች በተሰጣቸው ካርታ ላይ የተጠሪ አባት መመዝገቡ መረጋገጡን የአመልካች አባት ከሞቱ በኋላ ሀሰተኛ የፍርድ ቤት ውሣኔ ተዘጋጅቶ ቤቱ በአመልካች እናት በሚች እማሆይ ታከለች ረታ ስም መመዝገቡንና የተጠሪ አባት ማሕደር ከማዘጋጃ ቤት እንዲጠፋ መደረጉን እንዲሁም የአመልካች ባለቤት ወረታ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የምትሰራ ስለመሆኑ ተረጋግጧል በሚል አመልካች ይዞታውን ለቆ ለተጠሪ እንዲያስረክብ ወስኗል፡፡ ይህ ውሣኔ በየደረጃው በሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ስለፀና አመልካች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ተብሎ እንዲታረምለት ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች ታሕሣስ 14ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው ለክርክሩ መንስዔ የሆነው ይዞታ በአመልካች አባት የተገዛና ቤት የሰራበት ስለመሆኑ ሚች ከሞቱም በኋላ በእናታቸው ስም የተመዘገበ ስለመሆኑ

በማስረጃ ተረጋግጦ ግለ በአጎራባች ይዞታ ላይና ውሃና መብራት ደረሰኝ ላይ የተጠሪ አባት መመዝገቡ የተመዘገበበት ሁኔታ ግምት ውስጥ ሳይገባ እንደ ባለሃብት መቆጠሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተበሎ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በስር ፍርድ ቤት አመልካች አከራካሪውን ቤት ለተጠሪ እንዲያስረክብ የተወሰነበት አግባብነት ከማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር ተጣርቶ እንዲወሰን ታዞ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፅኑፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ሚያዚያ 6ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ መልሱ ማስረጃ የመመዘን ስልጣኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አለመሆኑንና በጥቅሉ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የማስረጃ ምዘና ስህተት የተፈፀመበት አይደለም የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር መልስ መልስ አቅርቦ ክርክሩ ተጠናቋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የስር ፍርድ ቤት በሰጠውና በየደረጃው በሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች በፀናው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ ማስረጃ ምዘና ስህተት መኖር አለመኖሩ ላይ መልስ ለመስጠት የግራቀኙን ክርክር ለጉዳዩ አግባብት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘበብ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረው ተጠሪ ባቀረበው ክስ በወረታ ከተማ የሚገኘውና ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ከአባቱ በውርስ የተላፈለት ቢሆንም ተጠሪው የሁለተኛ ተከሳሽ እማሆይ ታከለች ረታ ነው በሚል የያዘበት መሆኑን በመዘርዘር እንዲለቅለት ጠይቋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ተጠሪ አባቱን ተክቶ የውርስ ድርሻውን ከሚካፈል በስተቀር ቤቱ የተጠሪ አባት ሳይሆን የተጠሪ አያት የአመልካች አባትና የእማሆይ ታከለች ረታ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡ ጣልቃ ገቦችም ቀርበው ከአመልካች ጋር ተመሣሣይነት ያለው ክርክር አቅርበዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት አከራካሪው ቤትና ይዞታ ባለሃብት ማን ነው የሚለውን ጭብጥ ይዞ በግራቀኙንና ራሱ በሰጠው ትዕዛዝ ተጣርቶ የቀረበለትን ማስረጃ መዝኗል፡፡ በዚህም መሰረት የቀረቡት የግራ ቀኙ ምስክሮች በጥቅሉ እንደሚያቀርቡት ክርክር ያስረዱ ቢሆንም የወረታ ከተማ ማዘጋጃ ቤት አጣርቶ ባቀረበው ከመልስ በተጨማሪ ገለልተኛ የሆነው የዞኑ ስራና ከተማ ልማት መምሪያ ስጉዳዩ አጣርቶ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቶ ከአጎራባች ይዞታዎች ሰነድ እና የአካባቢውን ሕዝብ ጠይቆ ባቀረበው መልስ ይዞታውን የአመልካች አባት የተጠሪ አያት በ1953ዓ/ም ገዝተው በ1963ዓ/ም ቤት ለመገንባት ፈቃድ የጠየቁበት ቢሆንም በ1976ዓ/ም ይዞታው ወደ ሽንሻኖ ገብቶ ለተጠሪ አባት ተመርቶ ቤት የተሰራበትና ወደ ባህር ዳር እስከሚሔድ ድረስም የተጠሪ አባት በቤቱ ውስጥ ይኖር እንደነበር ማረጋገጡን በሌላ በኩል የአመልካች አባት ከሞቱ በኋላ ሐሰተኛ የፍርድ ቤት ሰነድ(ውሣኔ) ተዘጋጅቶ ግልፅ ባልሆነ መንገድ ይዞታው ወደ አመልካች እናት የተዛወረ መሆኑን በአንፃሩ የተጠሪ አባት ሰነድ ከማዘጋጃ ቤቱ እንዲጠፋ የተደረገ ስለመሆኑ

ስለተረጋጠ አመልካች ይዞታውን እንዲለቅ ተወስኗል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በድጋሚ አጣርቶና ተጨማሪ ማስረጃ አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት መደምደሚያና የሰጡት ፍርድ ተገቢነት በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር አንፃር ሲመዘን መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆዎችን መሰረት ያላደረግ ነው የሚያስብል ምክንያት ስላላገኘን ተከታዩን ውሣኔ ወስነናል፡፡

ውሣኔ

1) የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 97966 ጥቅምት 17ቀን 2013ዓ/ም በጉዳዩ ላይ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ሲል የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2) ይህ ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዝግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ዒ/መ የማይነበብ የአምስት

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ቤቶች ልማት ጽ/ቤት-ዐ/ህግ

ይታያል ደምሴ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡ 1ኛ. አሳሳሸኝ ሃብተ ማርያም ጠበቃ አቶ በላይ ኃ/ስላሴ

2ኛ. መላከ ምህረት ተክለወልድ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍርድ

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው ለክርክር ምክንያት የሆኑት ቤቶች ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ በመንግስት እጅ የቆዩ ለመሆኑ ተረጋግጦ ባለበት ለተጠሪዎች እንዲመለሱ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነበትን አግባብነት በዚሁ ችሎት በመ/ቁ/119591 ላይ ከተሰጠው ውሳኔ አኳያ መርምሮ ለመወሰን ነው፡፡

የክርክሩ ሥረ ነገር አመጣጥ እንዲህ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪዎች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች እና በሌሎች አራት ግለሰቦች ላይ ባቀረቡት ክስ በካርታ ቁጥር 16/30549 ተመዝግበው የሚታወቁት የቤት ቁጥር 677፣ 678፣ 679 እና 680 የሆኑት ከአውራሻቸው ግራዝማች ሀብተማርያም ካብትይመር በውርስ የተላፈላቸው ሲሆኑ ቤቶቹን የአሁን አመልካች ይዞ እያከራየ በመሆኑ ለቆ እንዲያስረክባቸው በተለያየ ጊዜ ሲጠይቁ

ቆይተው ከእነዚህ ቤቶች ውስጥ የቤት ቁር 678 እና 679 ያስረከባቸው ቢሆንም ቀሪዎቹን የቤት ቁጥ 677 እና 680 በስር ፍርድ ቤት ከ2ኛ እስከ 5ኛ ለተጠቀሱት ግለሰቦች እያከራየ ያለ መሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገዶ ተከራዮቹን አስወጥቶ እንዲያስረክባቸው ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት አመልካች ቀርቦ የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ እና አማራጫ የስረ ነገር ክርክር አቅርቧል፡፡ የመቃወሚያው ይዘትም ክስ የቀረበባቸው ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 47/67 ከተጠሪዎች አውራሽ እጅ በትርፍነት ተወርሰው መንግስት እጅ የገቡ በመሆኑ በቤቶቹ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም የላቸውም፤ ቤቶቹ በአዋጅ አልተወረሱም የሚባል ከሆኑም ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣኑ የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ክርክሩን ለመስማት የስረ ነገር ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡ በአማራጭ የስረ ነገር ክርክር ደግሞ ቤቶቹ በመንግስት ተወርሰው ከ40 ዓመት በላይ መንግስት እያከራየ ይዞ የቆየ በመሆኑ ሊመለሱ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በመቃወሚያው ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይኸው ጉዳይ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ክርክር ተደርጎበት በሰ/መ/ቁ/119591 ላይ ግንቦት 21/2009 ዓ.ም በዋለው ችሎት "መጣራት አለባቸው" የተባሉት ነጥቦች ተለይተው ፍሬ ነገሮቹ በተገቢው ማስረጃ ከተጣሩ በኋላ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑ ላይ እንዲወስን ተመልሶለታል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በድጋሚ ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የዘጋ ቢሆንም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይኑን በመሻር በክሱ ስረ ነገር ክርክር ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን መልሶለታል፡፡

በዚህ መልኩ ጉዳዩ የተመለሰለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን በመስማት እንዲሁም ለጉዳዩ አወሳሰን ይረዳኛል ያለውን ማጣራት ካደረገ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ለክርክር ምክንያት የሆኑት ቤቶች ከሌሎች ቤቶች ጋር በ1968 ዓ.ም በመንግስት ተወረሰው የነበረ ቢሆንም በ1972 ዓ.ም የህብረተሰባዊ ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር የግራዝማች ሀ/ማርያም ወራሾች ለሆኑት በአሁን ተጠሪዎች ስም ክስ የቀረበባቸውን ቤቶች ጨምሮ በካርታ ቁጥር 16/30549 የተመዘገበ የባለሃብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠ መሆኑን፤ የአሁን አመልካች እነዚህን ቤቶች ለአሁን ተጠሪዎች እንዲያስረክብ በ1984 ዓ.ም ውስጥ ከተለያዩ የመንግስት አስተዳደር አካላት በደብዳቤ ሲጠየቅ የነበረ እና በቤቶቹ ላይም የቤትና የቦታ ግብር በተጠሪዎች ስም ሲከፈል የነበረ ስለመሆኑ ማረጋገጡን ጠቅሶ ለተጠሪዎች የተሰጠው ካርታ ባልተሻረበት አመልካች ቤቱን አልለቅም የሚልበት ምክንያት የለም በማለት ቤቶቹን ለቆ ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ ወስኗል፡፡ አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ዘግቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ጥር 04/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ከላይ

በዚህ ፍርድ መግቢያ ላይ የተጠቀሰውን ነጥብ ለማጣራት ሲባል ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ነጥብ አኳያ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ በዚሁ ችሎት ቀደም ሲል በመ/ቁ/119591 ላይ ከተሰጠው ውሳኔ አንፃር ይመርምር የሚል ነው፡፡ የተጠቀሰው የሰበር መዝገብ ቁጥር ግራ ቀኙ በክስ መቃወሚያው ጉዳይ ላይ ክርክር አድርገው ውሳኔ የተሰጠበት ነው፡፡ የውሳኔው ይዘትም በአሁን አመልካች በኩል የፍርድ ቤቱን ዳኝነት ስልጣን አስምልክቶ ያቀረበው መቃወሚያ በማስረጃ ተጣርቶ ፍርድ ቤቱ ስልጣን ያለው መሆኑን ያለመሆኑ ላይ እንዲወስን የሚል ነው፡፡ በዚሁ አግባብ ፍርድ ቤቱ አጣርቶ የዳኝነት ስልጣን የለኝም ያለ ቢሆንም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተሽሮ በፍሬ ነገር ላይ ክርክር ተሰምቶ እንዲወሰን ተደርጓል፡፡

በክሱ ስረ ነገር ክርክር ሂደት በማስረጃ የተረጋገጠው ደግሞ ክስ የቀረበባቸው ቤቶች ቀደም ሲል ለአሁን ተጠሪዎች ከተመለሱት ቤቶች ጋር ተወርሰው የነበረ ቢሆንም በ1972 ዓም በቤቶቹ ላይ ሥልጣን ባለው አካል በተጠሪዎች ስም የባለሀብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠ መሆኑን፤ ከዚህ በኋላም ቢሆን አመልካች ቤቱቹን ለተጠሪዎች እንዲያስረክብ ከተለያዩ የመንግስት አስተዳደር አካላት በፅሁፍ ሲጠየቅ የነበረ መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ ፍሬ ነገሮች የሚያሳዩት ተጠሪዎች ክስ በቀረበባቸው ቤቶች ላይ አግባብ ባለው አስተዳደር አካል በተሰጠ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተረጋገጠ መብት ያላቸው መሆኑን እና ክሱም በፍርድ ኃይል ይህንኑ መብት ለማስከበር የቀረበ የባለሃብትነት ክርክር መሆኑን ነው፡፡

እንግዲህ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍል የባለሃብትነት ምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የዚሁ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብት እንደሆነ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1195(1) ይደነግጋል፡፡ በእርግጥ በዚህ መልኩ የተሰጠ ምስክር ወረቀት በራሱ ፍፁም ሳይሆን ሊስተባበል የሚችል ማስረጃ ነው፡፡ ሊስተባበል የሚችለውም የባለሀብትነት ምስክር ወረቀቱ የተሰጠው ከደንብ ውጭ በሆነ አሰራር ወይም ማስረጃውን ለመስጠት ሥልጣን በሌለው አስተዳደር ክፍል መሆኑን፤ ወይም ማስረጃው የተሰጠው በማይረጋ ፅሁፍ መሰረት ወይም ለከሳሽ መቃወሚያ ሊሆን በማይችል ፅሁፍ መሰረት መሆኑን፤ ወይም ማስረጃው የተሰጠበት ንብረት የተገኘው የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠ በኋላ ስለመሆኑ በማስረዳት እንደሆነ ከፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1196 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የዚህ ድንጋጌ አጠቃላይ መንፈስ የሚያስገነዝበው በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1195(1) የባለሃብትነት ማስረጃን በመያዝ ብቻ የተወሰደውን የህግ ግምት ማስተባባል የሚቻለው ማስረጃው የተገኘው ከህግ አግባብ ውጭ በሆነ ሁኔታ መሆኑን በማስረዳት እንደሆነ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ አመልካች ቤቶቹ ተወርሰው ለረጅም ጊዜ በመንግስት እጅ የቆዩ ናቸው የሚል መከራከሪያ ከማቅረቡ ውጭ ከተወረሱ በኋላ በቤቶቹ ላይ በአሁን ተጠሪዎች ስም የተሰጠው የባለሃብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከህግ አግባብ ውጭ በሆነ ሁኔታ የተሰጠ መሆኑን

በማስረዳት ያስተባበለው ነገር የለም፡፡ ይህ ባልተረጋገጠብት የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ የቀረበውን ክስ ሞብጥ እና በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/257712 ላይ ታህሳስ 13/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ እግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

ሰ/መ/ቁ፡-200816

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ
ፀሐይ መንክር
ኑረዲን ከድር
መላኩ ካሣዬ
እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ልማት ፋና የደን ማሕበር

ተጠሪ፡- የአቶ አበበ ወልደየስ ሚስትና ወራሾች

1) ወ/ሮ ብዙዬ ደጀኔ
2) ወ/ሮ አረጋሽ አበበ
3) ወ/ሮ ፀሐይ አበበ
4) አቶ ተመስገን አበበ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጠሪዎች አባት የተከሉትን ባሕር ዛፍ ከሕግ ውጪ ቆርጦ ወስዶል የተባለውን አመልካች የባህር ዛፉን ግምት ለማስከፈል የቀረበ የንብረት ክርክርን የሚመለከት ሆኖ አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጀመረው ክርክር የአሁን ተጠሪዎች ከሣሽ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡

ተጠሪዎች ሰኔ 6ቀን 2008ዓ/ም በተፃፈ ክሳቸው በደሴ ከተማ ቧንቧ ውሐ ክፍለ ከተማ ሚች አባታቸው በሊዝ የመሬት ስሪት ስርዓት ይዘው ለከተማ ግብርና ከሚጠቀሙበት 1035 ካሬ ሜትር ስፋት ካለው ይዞታቸው አዋሣኝ የሆነው መሬት ላይ ወደ ደሴ ከተማ የሚገባውን ናዳ ለመከላከል በአካባቢው ማሕበረሰብ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተሣትፎ ባሕር ዛፍ እንዲተከልበት ከደሴ ከተማ አስተዳደር ከተወሰነ በኋላ ማህበረሰቡ ለመትክል ፈቃደኛ ባመለመሆኑ የተጠሪዎች አውራሽ እንዲተክሉበት ተፈቅዶላቸው ብቻቸውን ተክለው ያሣደጉትንና በማህበራዊ ፍርድ ቤትም የተረጋጠላቸውን ባሕር ዛፍ አመልካች ምንም መብት ሣይኖረው 500 አውራጅ፣ 800 ማገር 350 ቋሚ 3000 ጠርዝ በአጠቃለይ ግምቱ 94,000.00 የሚያወጣውን ባሕር ዛፍ ሰኔ 1ቀን 2001ዓ/ም ቆርጦ የተጠቀመበት መሆኑን በመዘርዘር ግምቱን ከልዩ ልዩ ወጪ ጋር እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል።

አመልካች መሬቱ የመንግስት በመሆኑ ተጠሪዎች ክስ የማቅረብ መብት የሌላቸው መሆኑን፤ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት ከውል ውጪ በመሆኑ ክስ የማቅረቢያ ጊዜው ማለፍንና ግምቱም የተጋነነ መሆኑን፣ ጉዳዩ አስተዳደራዊ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ክሱን በቀጥታ የማዬት ስልጣን የሌለው መሆኑን በመዘርዘር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና አመልካች ማሕበር በመሆኑ ከከተማ አስተዳሩ 34,000 ካሬ ሜትር መሬት ለከተማ ግብርናና ለደን ልማት ተሰጥቶት ከ1994ዓ/ም ጀምሮ ባሕር ዛፍ አልምቶ እየተጠቀመ የሚገኝ እንጅ የተጠሪን ባሕር ዛፍ ቆርጦ አለመውሰዱን በከተማው እና በተጠሪ ይዞታ ላይ ይደርስ የነበረውን ናዳ እየተከላከለ ያለው ባሕር ዛፍ አመልካች የተከለው መሆኑን ለተጠሪም ባሕር ዛፍ እንዲተክሉ ፈቃድ ያልተሰጣቸው መሆኑን በመዘርዘር የተጠሪ ክስ ውድቅ እንዲሆንለት ተከራክሯል።

የስር ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን ውድቅ ካደረገ በኋላ የተጠሪዎች አውራሽ በመንግሰት ቦታ ላይ ባሕር ዛፍ እንዲያለሙ ተፈቅዶላቸው አልምተው ነበር ወይስ አልነበረም? አልምተው ነበር ከተባለስ አመልካች ቆጥሮ ወስዷል ወይስ አልወሰደም? የሚሉትን ነጥቦች በጭብጥነት ይዞ የግራቀኙ ያቀረቧቸውን ማስረጃዎች እና ጉዳዩ የሚመለከተው የክፍለ ከተማው የመንግስት አካል ስለጉዳዩ አጣርቶ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ የቀረበለትን ማስረጃ መርምሮ የተጠሪዎች አውራሽ ባህር ዛፍ ተክየበታለሁ የሚሉት መሬት የመንግስት መሆኑንና እንዲተክሉበት ፈቃድ የተሰጣቸው ስለመሆኑ አላረጋጡም ሲል ክሱን ውድቅ አድርጓል።

በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኙት ተጠሪ የይግባኝ አቤቱታቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱም ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ባህር ዛፍ የተጠሪዎች አውራሽ መትከላቸው በተረጋጠበት ባሕር ዛፉን እንዲተክሉ ፈቃድ አልተሰጣቸውም በሚል ያቀረቡት ክስ ውድቅ የመደረጉን ተገቢነት በጭብጥነት ይዞ የግራ ቀኙን ክርክርና ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ የቀረበለትን ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የከተማው ምክር ቤት ለተጠሪዎች አባት ፈቅዶላቸው ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ባሕር ዛፍ መትከላቸውን አመልካችም የራሱን ባሕር ዛፍ ሲቆርጥ የተጠሪዎች አባት የተከሉትን ባሕር ዛፍ ደርቦ መቁረጡ አረጋግጫለሁ በሚል የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሮ በባለሙያ የተገመተውን 27,977.60 ብር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል። ይህ ውሣኔም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ተብሎ ፀንቷል።

ይህ ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚለው አመልካች ጥር 4ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ፣ የተጠሪዎች አውራሽ

ከሚመለከተው የመንግስት አካል ተፈቅዶላቸው ባህር ዛፍ መትከላቸውና ባሕር ዛፉን አመልካች የቆረጠባቸው ስለመሆኑ ሣይረጋገጥ የባህር ዛፍ ግምትና ወጪና ኪሣራ እንዲከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው ተበሎ እንዲታረም ጠይቋል።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ከመሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ አንፃር እንዲመረመር ተጠሪዎችም የመልስ ክርክር እንዲያቀርቡ በታዘዙት መሰረት የመልስ ክርክራቸውን አቅርበዋል።ተጠሪዎች በበኩላቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወሰነው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር ውሣኔው እንዲፀናላቸው ተከራክረዋል። አመልካችም የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር መልስ መልስ አቅርበው የግራ ቀኙ ክርክር ተጠናቋል።

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል። እንደተመረመረው ለክርክሩ መነሻ የሆነው የተጠሪዎች አውራሽ ጉዳዩ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ባገኙት ፈቃድ መሰረት በመንግስት ይዞታ ላይ ተክለው ተንከባክበው ያሣደጉትን ባሕር ዛፍ አዋሣኝ የሆነው ተጠሪ የራሱን ባሕር ዛፍ ሲቆርጥ የእነሱን ጨምሮ የቆረጠባቸው መሆኑን በመዘርዘር ግምቱን እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል። አመልካች ተጠሪ በመንግስት ፈቃድ ባሕር ዛፍ አለመትከላቸውን እሱም ቆርጦ አለመውሰዱን በመዘርዘር ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል።

የተካደ ፍሬ ነገርን በማስረጃ የማጣራት የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው የሰር ፍርድ ቤቶች በመንግስት ይዞታ ላይ ባሕር ዛፍ እንዲተክል የፈቀደለት የክፍለ ከተማው ሕዝብ ለመትከል ፈቃደኛ ሣይሆን ሲቀር የተጠሪዎች አውራሽ እንዲተክሉበት የተፈቀደላቸውና ተክለው ሲንከባከቡ የነበረ ስለመሆኑ፣ ካደገ በኋላም ለመቁረጥ እንዲፈቀድላቸው ጉዳዩ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ጥያቄ አቅርበው ለረዜው ለመቁረጥ ያልደረሰ መሆኑን የተገለፀላቸው ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ በማቅረብ ተረጋግጧል። አመልካችም የተጠሪዎች አባት የተከሉትን ባሕር ዛፍ ጨምሮ በመቁረጥ የወሰደ ስለመሆኑ በምስክሮች ተረጋግጧል። አመልካችም ከተሰጠው ይዞታ በላይ መያዙ በቦታው ከአመልካች በፊት የተጠሪዎች አባት ባህር ዛፍ ተክለው ሲንከባከቡ እንደነበር ተረጋግጧል። ይህን ማስረጃ የመዘነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባህር ዛፉን በባለሙያ እንዲገመት ተደርጎ የባህር ዛፉን ግምትና ወጪና ኪሣራ እንዲከፍል ወስኗል።

እንዲሚታወቀው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3) እንደሚደነግገው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበት ዋና ዓላማ የመጨረሻ ውሣኔ በተሰጣባቸው ጉዳዮች የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተትን ማረም መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። በዚህ መሰረት በያዝነው ጉዳይ እንዲጣራ የተፈለገው የማስረጃ ምዘና መርህን ሚመለከት ጉዳይ በመሆኑ በሰር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ የቀረቡት ማስረጃዎች ካረጋገጡት ፍሬ ነገር አንፃር በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተገኘ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

ውሣኔ

1) የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 0104428 በሆነው ጥቅምት 24ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-30550 ታሕሳስ 9ቀን 2013ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል።

2) ይህ የሰበር ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የቤራሣቸውን ይቻሉ።

ትዕዛዝ

1. ይህ ችሎት የካቲት 5ቀን 2013ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል። መዝገቡ እልባት ያገኘ በመሆኑ ተዘግቷል፣

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-200687

ቀን፡-30/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ አይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ኃ/የተ/የግ/ማህበር- ጠበቃ ንጉሴ እሰየው ቀረቡ

ተጠሪ፡ አቶ ኢብራሒም አይዶግዱ- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የስራ ዉል መቋረጥ የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው ኦሮሚያ ክልል በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ሰበታ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ከመዝገብ እንደሚታዉ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ የምግብ ባለሙያ ሁኜ በቀን 28/04/2000 ዓ.ም በወር 2500 ዶላር ደመወዝ ተቀጥሬ እየሰራሁ እያለ በቀን 22/08/2011 ዓ.ም ያለጥፋት ከህግ ውጪ ውልህን ጨርሰሀል በማለት ከስራዬ አሰናብቶኛል፣ስለዚህ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ ተብሎ የአገልግሎት ክፍያ፣የካሳ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ፣ ክፍያ የዘገየበት እና ለአውሮፕላን ቲኬት በአጠቃላይ 41,264.33 ዶላር ወይም በኢትዮጵያ ብር 1,190,477.44 ከ10% የጠበቃ አበል ጋር እንዲከፈልኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡አመልካች በበኩሉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገው

የስራ ስምምነት ለተወሰነ ጊዜ ለአንድ አመት የሚቆይ ሆኖ ውሉ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ሊቋረጥ እንደሚችል ተስማምተናል፣ተጠሪ ተቀጥሮ ሲሰራበት የቆየው የስራ መደብ ላይ የኢትዮጵያ ዜጋ በብቃት ሊሰሩ የሚችሉት ነው።ለአንድ የውጪ ዜጋ ደግሞ ፈቃድ የሚሰጠው የሀገር ውስጥ ሰራተኞች ግንዛቤ እና ልምድ እስከሚያገኙ ብቻ ነው።ስለዚህ የሀገር ውስጥ ዜጎች መስራት እየቻሉ የውጭ ዜጋ መስራት የለበትም።ውላችን ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ሲሆን የውጭ ዜጋ ሆኖ ተጠሪ ላልተወሰነ ጊዜ መስራቱ ከህግ ውጪ በመሆኑ ውሉ የተቋረጠው በህግ አግባብ በመሆኑ የተጠየቀው ክፍያ ሊከፈለው አይገባም በማለት ተከራክረዋል።

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች እና ተጠሪ የተፈራረሙት የስራ ውል ከ23/04/2010 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ዓመት ጸንቶ የሚቆይ መሆኑን የሚያሳይ ቢሆንም በአዋጅ ቁ/377/96 አንቀጽ 10 ስር ከተገለጹት ምክንያቶች ውስጥ በየትኛው ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የተገለጸ ነገር የለም።ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ስለተባለ ብቻ የህጉን መስፈርት አሟልቷል የሚያስብል አይደለም፣ተጠሪ ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ስራ ሲሰራ እንደቆየ የሚያሳይ ማስረጃ አመልካች አላቀረበም።ተጠሪ ተቀጥሮ ሲሰራበት የቆየው ስራ ደግሞ በባህሪው በቀጣይነት የሚሰራ ስራ በመሆኑ እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.43160 ላይ በሰጠው ዉሳኔ በአንቀጽ 10 ስር ተዘርዝረው ካሉት ስራዎች ውጭ ከሆነ ይህ ውል የተወሰነ ጊዜ ነው ቢባል እንኳን የተወሰነ ጊዜ ዉል ሊሆን አይችልም በማለት አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል።የውጭ ሀገር ዜጋ ስለሆነ ውሉ የተወሰነ ጊዜ ነው የሚል ህግ የለም፣ስለዚህ የስራ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ ነው፣አመልካች የውሉ ጊዜ ስለተጠናቀቀ በማለት ውሉን ማቋረጡ የህግ መሰረት የለውም፣ስንብቱ ከህግ ውጭ ነው በማለት የተጠየቁ ክፍያዎች ለተጠሪ እንዲከፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል።

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ ጉዳዩ አያስቀርብም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል።አመልካች ለኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኝ ክርክር ሰምቶ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለውም በማለት አጽንቷል።ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ።

አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፤ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ ከውጭ ሀገር ዜጋ ጋር የተደረገ የቅጥር ውል የሚል ሲሆን ይህንን የሚያረጋግጥ በስር ፍ/ቤት ሰነዱ ቀርቦ እያለ እና በቅጥር ውሉ አንቀጽ 11(ሐ) መሰረት ከተዋዋይ ወገኖች መካከል አንዱ ወገን ውሉን በማንኛውም ጊዜ መቋረጥ እንደሚቻል ተመልክቷል፣በኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 474/2012 አንቀጽ 19(1) መሰረት የውጭ ሀገር ዜጎችን የሚቀጥር ባለሀብት ለኢትዮጵያዊያን አስፈላጊውን የስራ ላይ ስልጠና እንዲሰጥ እና እውቀት እንዲተላለፍ በማድረግ የውጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች በኢትዮጵያዊያን እንዲተኩ የማድረግ ግዴታ ያለበት ሲሆን በዚሁ መሰረት አመልካች የተጠሪ የስራ ውል በውላቸው መሰረት እንዲቋረጥ ማድረጉ ህጋዊ ስንብት ነው።ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ለ11 ዓመት የሰራው በጊዜያዊነት የስራ ቅጥር ውሉ እየታደሰ እና የስራ ፍቃዱም እንዲታደስ በማድረግ ነው።ተጠሪ በቋሚነት መቀጠሩን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረበም።ስለዚህ ለዜጎች ቅድሚያ የሥራ ዕድል ለመስጠት ሲባል በህጋዊ መንገድ የተቋረጠ

ዉል ላይ ብር 1,190,477.44 እንዲከፈል የተወሰነው መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻር በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ቅጥሩ ለተወሰነ ጊዜ መሆኑን የቅጥር ውሉ ላይ ከመመልከቱ አንፃር የስር ፍ/ቤት ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የስራ ውል ነው በሚል መነሻ ስንብቱ ህገወጥ ነው ማለቱን አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ ባቀረበው መልስ በውላችን መሰረት አመልካች በቅድሚያ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሳይሰጥ እንዲሁም የውሉ ቀን ሳይጠናቀቅ ውሉን ማቋረጡ ስንብቱን ህገ ወጥ ያደርጋል፡፡ በተጠሪ ድርጅት ላልተወሰነ ጊዜ ተቀጥሬ ለ11 ዓመታት ሲሰራ መቆየቴ በስር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡አንድ ሰራተኛ ለተወሰነ ወይስ ላልተወሰነ ጊዜ ነው የተቀጠረው ለማለት የሚቻለው ሰራተኛው የተቀጠረበት ስራ ባህሪይ እንጂ በውሉ ላይ ለጊዚያዊ ስራ ተቀጥሪዋል ስለተባለ ብቻ እንደማይሆን ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ.43160 ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፣ አመልካች ስራው እንዳልተጠናቀቀ እና በተጠሪ ስራ ቦታ ሌላ ሰው መቅጠሩ ተጠሪ ላልተወሰነ ስራ እንደተቀጠረ ያረጋግጣል፡፡ስለዚህ በድርጅቱ ለተከታታይ ለ11 ዓመት አገልግዬ ያለአገልግሎት ክፍያ፣ ያለማስጠንቀቂያ፣ የቲኬት ክፍያ እና ያለምንም ክፍያ ያሰናበተኝ ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በማለት የሰጡት ውሳኔ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እና ክርክሩን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረዉ የስራ ዉል የተቋረጠዉ በአመልካች አነሳሽነት መሆኑ አላከራከረም፡፡አመልካች አጥብቆ የምከራከረዉ ተጠሪ የዉጭ ሀገር ዜጋ በመሆኑና ዉሉም ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ስለሆነ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ ሊባል አይገባም በማለት ነዉ፡፡

በመሰረቱ የስራ ዉል እንደማናቸዉም ዉል የግራቀኙን መብትና ግዴታ በሚመለከት በአሰሪዉ እና በሰራተኛዉ ነጻ ፈቃድና ስምምነት የሚደረግ ዉል ቢሆንም በህግ የተጠበቁ ዝቅተኛ የሥራ ሁኔታዎችን የሚቀንስ ወይም የሚቃረን ሊሆን አይችልም፡፡የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር1156/2011 አንቀጽ4 ድንጋጌ ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ይህንኑ ያስገነዝባሉ፡፡የስራ ዉል አይነት በተመለከለተ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ ሊደረግ እንደሚችል የአዋጁ አንቀጽ 4/1/ ድንጋጌ ይዘት ያሣያል፡፡ከዚህም የምንገዘነበዉ የስራ ዉሉ ቆይታ በጊዜ ወይም እንደስራዉ ባህርይ በተዋዋዮች ሊወሰን የሚችል ስለመሆኑ ነዉ፡፡ይሁን እንጂ የሰራተኛዉን የስራ ዋስትና እና የመደራደር አቅም ዉስንነት ከግምት በማስገባት የስራ ዉሉን ቆይታ ጊዜ ወይም ባህርይ ለመወሰን የሚረዱ ሁኔታዎች በህግ ተደንግጎ እናገኛለን፡፡በዚህ ረገድ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ አንቀጽ 9 እና 10 ድንጋጌዎች እንደሚያሣዩን በመርህ ደረጃ የስራ ዉል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚገመት ሲሆን በተወሰኑ ሁኔታዎች እና ምክንያቶች ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ ተብሎ የሥራ ዉል ሊደረግ የሚችል

መሆኑን ነዉ፡፡ስለዚህም አሰሪዉ እና ሰራተኛዉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ በሚል መስማማት የሚችሉ ቢሆንም ጉዳዩ አከራካሪ ሆኖ ከቀረበ ዉሉ ከህጉ ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑ ሊመመርመር ይገባል፡፡በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ችሎት ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ክርክር ዉሳኔ የሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ እንዳመለካተዉ የሥራ ዉሉ ቆይታ ጊዜ አስመልክቶ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ በሚል መዋዋላቸዉ ብቻ ሳይሆን ዉሉ ከስራዉ ባህርይ ጋር ተገናዘቦ መታየት እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ሰበር መ/ቁ11924፣መ/ቁ/ 25765፣መ/ቁ.43160 እና ሌሎች መሰል መዝገቦችን ማየት ይቻላል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በግራቀኙ መካከል የተደረገዉ ዉል ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ መሆኑን እና በየጊዜዉ እየታደሰ መቆየቱንና ለመጨረሻ ጊዜም በ23/04/2010ዓ.ም ለአንድ ዓመት የተራዘመ መሆኑን ዉሉ የተቋረጠዉ በ22/08/2011ዓ.ም ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት አረጋግጧል፡፡ፍርድ ቤቱም ዉሉ ለተወሰነ ጊዜ ነዉ ቢባልም የስራዉ ባሕርይ ሲታይ የድርጅቱ ቋሚ ወይም ቀጣይነት ያለዉ ስራ ነዉ በሚል ምክንያት ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/43160 ላይ የሰጠዉን ዉሳኔ ድጋፍ በማድረግ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጠራል በማለት ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ከክርክሩ እንደሚታየዉ ተጠሪ ለ11ዓመት በቋሚነት አገልግያለዉ በሚል ምክንያት የሥራ ዉሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጠራል በማለት የሚከራከር ቢሆንም ዉሉ በየጊዜዉ እየታደሰ የቆየ መሆኑ በተጠሪም አልተካደም፡፡በእርግጥ የስራ ዉል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ስራ የተደረገ ነዉ የሚያሠኘዉ የዉሉ ይዘት ብቻ ሳይሆን በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ አንቀጽ 10 ስር የተዘረዘሩት ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች መኖራቸዉ መረጋገጥ እንዳለበት የህጉ አገላለጽ እና ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ 43160 እና ሌሎች መሰል መዝገቦች ላይ የሰጠዉ ዉሳኔ ያስገነዝባል፡፡ይሁንና የሰበር ችሎቱ ዉሳኔ በዚህ መዝገብ ከቀረበዉ ክርክር አኳያ ተፈጻሚነት አለዉ ወይ የሚለዉ ከጉዳዩ ባህርይ አንጻር መመርመር አለበት፡፡

ከመዝገቡ እንደሚታየዉ ተጠሪ የተቀጠረበት የሥራ መደብ የድርጅቱ ቋሚ ወይም ቀጣይነት ያለዉ ስራ አይደለም የሚል ክርክር የለዉም፡፡የአመልካች ዋነኛ መከራከሪያ ነጥብ ተጠሪ ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረዉ እና ዉሉ እየታደሰ የቆየዉ የዉጭ ሀገር ዜጋ በመሆኑ በቋሚነት ሊቀጠር አይችልም የሚል ነዉ፡፡ተጠሪ የዉጭ ሀገር ዜጋ መሆኑ አከራካሪ እስካልሆነ ድረስ የሥራ ዉሉን ዓይነት በመወሰን ረገድ የሚኖረዉ ዉጤት ከአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ እና ሌሎች አግባብነት ካላቸዉ ህጎች ጋር ተገናዝቦ መታየት አለበት፡፡

የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 የዉጭ አገር ሠራተኞች የሚቀጠሩበትን ሁኔታ የሚደነግግ ሲሆን በዚህም መሠረት የዉጭ አገር ዜጋ በማናቸዉም የስራ መስክ ተቀጥሮ ለመስራት የሚችለዉ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ወይም ክልል ሲሆን የክልል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ የሚሰጠዉን የስራ ፍቃድ ሲያገኝ እና የስራ ፍቃድ የሚሰጠዉም በአንድ የስራ መስክ ለማገልገል እስከ ሦስት ዓመት ሲሆን በየዓመቱ መታደስ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 174 ላይ ከተመለከተዉ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚህ ረገድ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ተመሳሳይ ይዘት ያለዉ መሆኑን ልብ ይለዋል፡፡የአዋጁን አንቀጽ 171/1/ሠ እና 176 መመልከት ይቻላል፡፡የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻልን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ (መግቢያዉን መመልከት ይቻላል) የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር

769/2004 በአንቀጽ 37(2)፣ በዚህ አዋጅ የተተካዉ የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 280/94 አንቀጽ 36(2) እንዲሁም አሁን በስራ ላይ ያለዉ የእንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 አንቀጽ 22(4) የዉጭ ዜጎችን የሚቀጥር ባለሀብት ለኢትዮጵያዉያን አስፈላጊዉ ስልጠና እንዲዘጋጅ እና እንዲሰጥ በማድረግ በተወሰነ ጊዜ ዉስጥ የዉጭ አገር ዜጋ ሠራተኞችን እንዲተኩ ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ቀደም ሲል በስራ ላይ የነበሩት ሁለቱ የእንቨስትመንት አዋጆችም ሆነ አሁን በስራ ላይ ያለዉ የእንቨስትመንት አዋጅ ዓላማዎች ናቸዉ ተብለዉ ከተዘረዘሩት ዉስጥ አንዱ ለኢትዮጵያዉያን ሰፊ እና ጥራት ያለዉ የስራ ዕድል መፍጠር እና ለአገሪቱ ዕድገት የሚያስፈልገዉን የዕዉቀት፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ማሳለጥ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 280/94 አንቀጽ 4(6)፣ በአዋጅ ቁጥር 769/2004 እና አዋጅ ቁጥር 1180/2012 አንቀጽ 5 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለዉ በአገራችን የግል እንቨስትመንትን ማስፋፋት አስፈላጊ ከሆነባቸዉ ምክንያቶች ዉስጥ አንዱ መንግስት ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በአገሪቱ ዉስጥ በማንኛዉም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራት እና ለመተዳደሪያ የመስራት መብት ለመተግበር በተለይም ሰፊ የሥራ እድል ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ መከተል እንዳለበት በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 41 /1/ እና 4) በተጣለበት ግዴታ መሠረት ለዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠር ለዜጎች የስራ ዋስትና ማረጋገጥ መሆኑን ነዉ፡፡አንድ ዓላማ ያላቸዉ የተለያዩ ህጎች በሚኖርበት ጊዜ በተለያዩ የህግ ክፍሎች በሚገኙ ድንጋጌዎች ተደጋጋፊ ሆነዉ የጋራ ዓላማ የሚያሳኩበትን የህግ ትርጉም መሻት የህግ ባለሙያዎች ሊመርጡት የሚገባ የህግ አተረጓጎም ዘይቤን መከተል በህግ አተረጓጎም ዕዉቅና ከተሰጣቸዉ መርሆዎች አንዱ ሲሆን ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁጥር 21448 ላይ በሰጠዉ የህግ ትርጉም ለዚህ መርህ ዕዉቅና ሰጥቶታል፡፡

ከዉጭ አገር ዜጎች የቅጥር ሁኔታ ጋር በተያያዘ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 174 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ዓላማዉ ምን እንደሆነ በግልጽ የሚያመላክት ድንጋጌ ባይኖርም ከላይ ከተመለከቱት የእንቨስትመንት ህጎች ድንጋጌዎች እንዲሁም በኢፌዲሪ ህገ መንግስት መሠረት መንግስት ለእራሱ ዜጎች የስራ ዕድል ለማመቻቸት ካለበት ግዴታ አንፃር ሲታይ በአዋጁ አንቀጽ 174 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ አጠቃላይ ዓላማ የግል ድርጅቶች የዉጭ አገር ዜጎችን የሚቀጥሩት ለስራ ዕድል ፈጠራ ዓላማ ሳይሆን ለድርጅቱ ስራ አስፈላጊነታቸዉ ከታመነበት ብቻ መሆኑን ነዉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ የዉጭ ሀገር ዜጋ በሀገር ዉስጥ ስራ እንዲቀጠር የሚፈለገዉ በዘርፉ በቂ ባለሙያ በሀገር ዉስጥ ሳይኖር ወይም የእዉቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ ዓላማ በመያዝ ስለመሆኑ የኢንቨስትመንት አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ የወጣዉ ደንብ የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነዉ፡፡ደንብ ቁጥር 474/2012 አንቀጽ 19/1/ይመለከታል፡፡በሌላ በኩል ከላይ እንደተገለጸዉ፣ የስራ ቅጥር ዉል ጊዜ ጋር በተያያዘ በአዋጁ አንቀጽ 9 እና 10 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ የዜጎችን የስራ ዋስትና የማረጋገጥ ዓላማ ያለዉ ነዉ፡፡የስራ ዋስትና ከስራ ዕድል ፈጠራ ጋር በተያያዘ የሚታይ በመሆኑም በዚህ መብት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን እድል ይፈጥራል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በመሆኑም የስራ ቅጥሩ በሚመለከተዉ አካል ይሁንታ የሚፈጸም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ አሠሪ ከዉጭ አገር ሠራተኛ ጋር በሚያደርገዉ ዉል ዉሉ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ በተመለከተ ተስማምተዉ የሚያስቀጡት የጊዜ ገደብ ህጋዊ ዉጤት ያለዉ በመሆኑ አሠሪዉ የዉሉ ጊዜ ሲያበቃ ዉሉን አቋርጦ ሠራተኛዉን የማሰናበት መብት ይኖረዋል፡፡በዚህ ረገድ

በተመሳሳይ ክርክር ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ/194630 ላይ (ያልታተመ) የሰጠዉ ዉሳኔም ተመሳሳይ አቋም የተወሰደበት መሆኑን ያሣያል፡፡

በመሆኑም በተያዘዉ ጉዳይ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተደረገዉ የስራ ዉል በጊዜያዊ ቅጥር ላይ የተመሠረተ ሆኖ በየጊዜዉ እየታደሰ ተጠሪ ለአስራ አንድ ዓመታት በአመልካች ዘንድ ሲሰራ የቆየ መሆኑ ያላከራከረ ሲሆን፣ አመልካች ዉሉ ከተጠሪ ጋር እንዲቀጥል ተስማምቶ ዉሉ ታድሶ በመካከላቸዉ ግንኙነቱ እንዲቀጥል ለማድረግ የስራ ፈቃድ እንዲታደስ ያስፈልጋል፡፡ዉጪ ሀገር ዜጋ የስራ ፈቃድ የሚታደሰዉ በአሰሪዉ ጥያቄ መነሻ መሆኑን አዋጁ ያሳያል፡፡በአዋጁ አንቀጽ 174(2-4) ላይ በተመለከተዉ ድንጋጌ መሠረት የስራ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር (በክልል ሲሆን ቢሮ) የሚሰጠዉ የስራ ፍቃድ እና አድሳት ማንኛዉም የግል ድርጅት ያለሚኒስቴሩ (ቢሮዉ) ዕዉቅና እና ይሁንታ የዉጭ አገር ዜጎችን እንዳይቀጥር ለመከላከል ታስቦ የተቀረጸ ስለመሆኑ ከድንጋጌዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሆኑም አሠሪዉ ድርጅት ከዉጭ አገር ዜጋ ጋር በጊዜያዊነት ያደረገዉ የስራ ቅጥር ዉል ግንኙነት እንዲቀጥል የስራ ፈቃድ አስፈላጊ በመሆኑ ለሠራተኛዉ የስራ ፍቃድ በሚመለከተዉ አካል አለመታደሱም አመልካች የቅጥር ዉሉ እንዲያራዝም የሚያስፈልግበት ምክንያት አለመኖሩን የሚያሣይ ነዉ፡፡

በአጠቃላይ በየደረጃዉ ያሉት ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከፍ ሲል በዝርዝር ከተመለከተዉ አንፃር በማየት ስንበቱ ህጋዊ ነዉ ማለት ሲገባቸዉ በአዋጁ አንቀጽ 9 እና 10 ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ለዉጭ አገር ዜጋ ሠራተኛም ጭምር ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በመዉሰድ በግራ ቀኝ መካከል ለተወሰነ ጊዜ የተደረገን የስራ ዉል ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይገመታል በሚል ሃሳብ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉን ክርክር ዉድቅ በማድረግ ስንብቱ ህገ ወጥ ነዉ በማለት የሰጡት ዉሳኔ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸዉን ድንጋጌዎቹ ዓይነተኛ ዓላማ እና ተጠሪ የዉጭ ሀገር ዜጋ ከመሆኑ አኳያ በህጉ የተፈቀደለትን መሰረት በማድረግ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ለመስራት ግራቀኙ ያደረጉት ስምምነት ተገዥ ሊሆኑ ይገባል የሚለዉን የዉል አጠቃላይ መርህ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስንበቱ ህጋዊ ነዉ ከተባለ ለተጠሪ የሚከፈል ክፍያ አለ ወይ የሚለዉንም መርመርናል፡፡በዚህ ረገድ ከስር መዝገብ እንደሚታዉ ተጠሪ ስንበቱ ህገ ወጥ ነዉ በሚል ምክንያት የስንብት፣ካሳ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ እና ክፍያ የዘገየበት የሚል የጠየቃቸዉ ክፍያዎች ሲሆኑ በተጨማሪም ወደ ሀገር ቤት የሚመለስበት የትኬት ክፍያ ብር 431.053(አራት መቶ ሰላሳ አንድ ከዜሮ ሃምሳ ሶስት ሳንቲም ዶላር) አመልካቹ እንድከፍል ጠይቋል፡፡የሥር ፍርድ ቤትም ይህንኑ በመቀበል ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ከላይ እንደተመለከተዉ በዚህ ሰበር ችሎት ዉሳኔ መሰረት ስንበቱ ህጋዊ ነዉ ስለተባለ ህገ ወጥ ስንብት ነዉ ተብሎ በስር ፍርድ ቤት የተወሰኑት ክፍያዎች ተገቢነት የላቸዉም፡፡ይሁንና ዉሉ ሲቋረጥ ተጠሪ ወደ ሀገሩ የሚመለስበት የትኬት ወጪ በአመልካች እንደሚሸፈን የግራቀኙ ዉል አንቀጽ 9/d/ ላይ ተመላክቷል፡፡አመልካችም ይህን በሚመለከት በመካድ ያቀረበዉ ክርክር የለም፡፡ ስለዚህም የሥራ ውሉ ሲቋረጥ የመመለሻ ትኬት ወጪ በአመልካች የሚሸፈን ስለመሆኑ በስምምነቱ የተመለከተ በመሆኑ ይህንኑ በተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ መሰረት አመልካች ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

ዉሳኔ

1ኛ/የሰበታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 11361 በቀን 19/06/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት፣ የፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 39465 በቀን 29/07/2012 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.333832 በቀን 06/04/2013 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2ኛ/ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያደረገዉን የስራ ዉል ማቋረጡ በህጋዊ መንገድ በመሆኑ ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባዉ ክፍያ ወደ ሀገሩ የመመለሻ ትኬት ወጪ ብቻ ነዉ ተብሏል፡፡በዚሁ መሰረት 431.053(አራት መቶ ሰላሳ አንድ ከዜሮ ሃምሳ ሶስት ሳንቲም ዶላር)በወቅቱ የባንክ ምንዛሪ ተለዉጦ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ብለናል፡፡በዚሁ ልክ የጠበቃ አበል 10% ጨምሮ ይክፈል ብለናል፡፡የስር ፍርድ ቤትም ይህንኑ አዉቆ እንዲያስፈጽም የዉሳኔ ግልባጭ ይተላለፍለት፡፡ይጻፍ

3ኛ/የሰበር አጣሪ ችሎት በቀን 04/05/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ እግድ ተነስቷል፡፡

4ኛ/በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዜ/መ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 200564

ቀን ፡- ሕዳር 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች ፡- የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ጥበበ መኮንን - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- 1. ወ/ሮ የጆቴወርቅ ኪዳኔ

2. አቶ ሚሊዮን ቀጣው

3. አልማዝ ቀጣው

4. ወርቅነሽ ቀጣው

5. መንበረ ቀጣው

6. ሔለን ቀጣው

7. ዮዲት ቀጣው

8. ምሥራቅ ቀጣው

ይሕ መዝገብ ከሰበር መዝገብ ቁጥር 204121 ጋር ተጣምሮ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የውል አለመፈጸምና የኪሣራ አከፋፈልን የተመለከተ ክርክር ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች ከሳሽ ሲሆን ተጠሪዎች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች ግንቦት 04 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ የክስ ማመልከቻ ያቀረበው ክስ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና ከ2ኛ-8ኛ ተጠሪዎች አባት የሆኑት አቶ ቅጣው መሸሻ ከአመልካች ጋር በተደረገ የንግድ ቤት ኪራይ ውል በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 05 ቀበሌ 12 የቤት ቁጥሩ 1165 የሆነ የንግድ ቤት በወር ብር 212.50 እየከፈሉ ከ1969 ዓ/ም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2004 ዓ/ም ድረስ እየከፈሉ ሲጠቀሙበት ቆይተው የተከራዩትን ቤት ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ከአከራዩ ዕውቅና ውጪ ለሦስተኛ ወገን አከራይተው የማይገባ ጥቅም በማግኘታቸው ምክንያት አመልካች የኪራይ ተመኑን በማስተካከል በወር ብር 31,479.00 እንዲከፍሉ አድርጓል፡፡ አቶ ቅጣው ቅሬታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በዚህ መካከል አቶ ቅጣው መሸሻ ውል ሳያድሱ ሕዳር 13 ቀን 2005 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ውል ያላደስነው ባለቤቱ ሕመም ላይ ስለቆየና ሞግዚትነትና ወራሽነት እስከምናረጋገጥ ድረስ ስለሆነ ጊዜ እንዲሰጠን በማለት በጽሁፍ አመልክተዋል፤ ውዝፍ ዕዳውን በተመለከተ የአንድ ዓመት የመክፈያ ጊዜ እንዲሰጣቸው ጠይቀው ከአመልካች ጋር የውል ሥምምነት አድርገዋል፡፡ በሥምምነቱ መሠረት ዕዳውን መክፈል ጀምረው ያቋረጡ ሲሆን እስከ ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስም ሲገለገሉበት ቆይተዋል፡፡ ስለሆነም የኪራይ ገንዘብ ብር 2,311,503.59 ተጠሪዎች ከወለድ ጋር እንዲከፍሉ ሲል ዳኝነት ጠይቋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ በፍ/ሕ/ቁ. 2024(መ) መሠረት ከሁለት ዓመት በላይ የተጠራቀመ የቤት ኪራይ ክፍያዎችን አመልካች የመጠየቅ መብቱ በይርጋ የታገደ ነው፣ በንግድ ቤት ያለኝ መብትና ግዴታ በሌላ የፍርድ ቤት ክርክር የተወሰነ በመሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው፣ የንግድ ድርጅቱ የባለቤቱ የግል ሀብት ነው ስለተባለ 1ኛ ተጠሪ ክፍያው አይመለከተኝም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ በፍሬ ነገሩም የኪራይ ዋጋ ብር 31,479.00 እንዲሆን የተደረገ ሥምምነት የለም፡፡ መክፈል ካለብኝ እንኳን በብር 212.50 ሂሳብ ነው፡፡ ሟች ባለቤቱ ሳይዋዋል ነው የሞተው፤ ባለቤት ከሞተ በኋላ ሟች ትክክለኛ ኪራይ ለማስከፈል የጀመረውን ክርክር ለማስቀጠል በ10/05/2005 ዓ/ም እና በ08/08/2005 ዓ/ም ለአመልካች ጥያቄ አቅርቤያለሁ፡፡ ከአመልካች ጋር በ09/08/2005 ዓ/ም ያደረግሁት ሥምምነት ንግዱ ወደኪሣራ እንዳይገባ በማሰብ አለ የተባለው ብር 547,287.13 ዕዳ በከፊል ከፍዬ ቀሪው ደግሞ ንግዱን እያንቀሳቀስኩኝ ለመክፈል የታለመ ነው፡፡ በውሉ መሠረት ብር 200,000.00 ከከፈልኩኝ በኋላ ቀሪዎቹ ተጠሪዎች ባለመፍቀዳቸው ንግድ ቤቱ አስተዳዳሪ ተመድቦለት አስረክቤያለሁ፡፡ ከዚህ በኋላም ከንግዱ ምንም ዓይነት ጥቅም አላገኘሁም፡፡ በውሉ መሠረት የቅጣት ክፍያ 10% ሊያስከፍል የሚችለው ኪራይ የዘገየባቸውን የመጀመሪያ

ስድስት ወራት ብቻ ነው፤ በውሉ አንቀጽ 3(3) መሠረት ከስድስት ወር በላይ ክፍያ ቢዘገይ ውሉን የመሠረዝ መበት አመልካች አለው፡፡ ከስድስት ወራት በላይ ላለው ጊዜ ቅጣት ልከፍል አይገባም ብለዋል፡፡

ከ2ኛ-8ኛ ያሉት ተጠሪዎች በበኩላቸው ሚች አባታችን ከሕግ ውጭ አከራይቷል መባሉ በማስረጃ ያልተረጋገጠ ነው፤ የኪራይ ጭማሪ ተደርጓል የተባለውም የተጋነነ እና እኛን የማያስገደድ ነው፡፡ ከተገደድንም በውሉ መሠረት ብር 212.50 ወርሃዊ ሂሳብ ብቻ ነው፡፡ ሚች ከሞተ አንስቶ በንግድ ቤቱ ፈቃድ በማሳደስ ሲጠቀሙበት እና ሲሰሩበት የነበሩት 1ኛ ተጠሪ እንጂ ከ2ኛ-8ኛ ያለነው ተጠሪዎች ባለመሆናችን ለዕዳው ኃላፊነት የለብንም፡፡ ውል ሳንገባ ወራሽ በመሆናችን ብቻ ለዕዳው ልንጠየቅ አይገባም፡፡ አመልካች ጻፍኩት ያለው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤዎች ለእኛ አልደረሰም፡፡ አመልካች የንግድ ቤቱን ተረክበን በማለት በጽሁፍ አሳውቀነዋል፡፡ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ውድቅ ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ከ2ኛ - 8ኛ ያሉት ተጠሪዎች በንግድ ቤቱ ላይ ወራሽነት ቢያረጋግጡም በንግድ ቤቱ ባለመጠቀማቸው ኃላፊነት የለባቸውም፡፡ 1ኛ ተጠሪ በአዲስ ክፍያ ለመክፈል ተስማምተው መክፈልም ጀምረዋል፡፡ ስለሆነም ቀሪውን ዕዳም የመክፈል ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ከሚያዚያ 01 ቀን 2004 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ ያለውን የ57 ወራት ብር 1,780,137.93 1ኛ ተጠሪ ለአመልካች ይክፈሉ፤ የውል ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ከስድስት ወር በኋላ ውል መሠረዝ እየቻለ ያልሰረዘ በመሆኑ ከስድስት ወራት በላይ ላለው ቅጣት 1ኛ ተጠሪ ሊከፍሉ ስለማይገባ የስድስት ወር ቅጣት ብር 18,887.40 ብቻ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው፤ በአጠቃላይ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ጋር ብር 2,066,045.33 1ኛ ተጠሪ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ሆነ 1ኛ ተጠሪ በተለያዩ መዝገቦች ያቀረቡትን ይግባኝ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም የኪራይ ውሉ ያልተቋረጠው 1ኛ ተጠሪ በተለያዩ ጊዜ ውሉ እንዳይቋረጥ እና ዕዳውን ለመክፈል ጊዜ እንዲሰጣቸው በመጠየቃቸውና መክፈልም በመጀመራቸው ነው፡፡ ቅጣት ብር 264,344.97 ሊከፈል ይገባል፡፡ ከ2ኛ - 8ኛ ተጠሪዎች በንግድ ቤቱ መጠቀም አለመጠቀማቸው ሳይሆን የሚች አባታቸውን ዕዳና መብት ስለሚወርሱ ነው ክሱ የቀረበው፤ በግልጽ ውርሱ ተጣርቶ አንወርስም አላሉም፤ ወራሽ በመሆናቸው ለዕዳው ኃላፊ ናቸው ሊባል ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ከ2ኛ - 8ኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች በፍርድ ቤት ክርክር የንግድ ቤቱ ወራሽ መሆናቸው በተገለጸበት ሁኔታ ለዕዳው ኃላፊነት የለባቸውም መባሉ ሕጋዊነቱን ለመመርመር ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርብ በማዘዙ 1ኛ ተጠሪ በውሉ ኪራይ ካልተከፈለና ከስድስት ወራት በኋላ ውሉን የመሠረዝ መበት እንዳለው ተመልክቷል፤ ባለመሰረዙ ምክንያት ከስድስት ወራት በኋላ ያለውን ቅጣት ሊጠይቅ አይችልም ብለዋል፡፡ ከ2ኛ - 8ኛ ያሉት ተጠሪዎች በበኩላቸው የአባታችን ወራሽ በመሆናችን ብቻ ልንጠየቅ አይገባም፤ የኪራይ ውል አልተዋዋልንም፣ የንግድ ቤቱን እንድንረከብ ሆነ እንድንጠቀም አልተደረገም፣ ስለሆነም ለዕዳው ተጠያቂነት የለብንም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰበር መዝገብ ቁጥር 204121 አመልካች ላይ ያቀረቡት የሠበር አቤቱታ ይዘት ደግሞ በፍ/ሕ/ቁ. 2024(መ) መሠረት ከሁለት ዓመት በላይ የተጠራቀመ የቤት ኪራይ ክፍያዎችን አመልካች የመጠየቅ መብቱ በይርጋ የታገደ ነው፣ በንግድ ቤት ያለኝ መብትና ግዴታ በሌላ የፍርድ ቤት ክርክር የተወሰነ በመሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው፣ የንግድ ድርጅቱ የባለቤቱ የግል ሀብት ነው ስለተባለ ክፍያው አይመለከተኝም፤ የንግድ ቤቱን ውርስ አጣሪ እያስተዳደረው ስለመሆኑና በንግድ ቤቱ ላይ መብት እንደሌለኝ የሚያስረዱ መዝገቦችን የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃነት አስቀርቦ አለመመርሩ ስህተት ያለበት ነው። የተሻሻለ የኪራይ ውል ሆነ የኪራይ ዋጋ የለም የሚል ነው። የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የንግድ ቤት የሚች የግል ሀብት ነው ተብሎ በተወሰነበት ሁኔታ 1ኛ ተጠሪ የቤት ኪራይ እንዲከፍሉ የተወሰነበት አግባብነትን ለማጣራት አመልካች መልስ እንዲያቀርብ የታዘዘ ሲሆን አመልካች ያቀረበው መልስ ይዘት 1ኛ ተጠሪ ዕዳው መኖሩን አምነው በአዲስ የኪራይ ዋጋ ለመክፈል የውል ሥምምነት ከማድረጋቸውም ባሻገር ክፍያ የጀመሩ በመሆኑ የፍ/ሕ/ቁ. 2024(መ) መሠረት በይርጋ ሊታገድ አይችልም። በ1ኛ ተጠሪ እና ከ2ኛ-8ኛ ድረስ ባሉት ተጠሪዎች መካከል የውርስ ሀብት ክርክር ተደርጎ መወሰኑ አመልካች ካቀረበው ክስ ጋር የሚገናኝ ባለመሆኑ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ሊባል አይገባውም። 1ኛ ተጠሪ ሚች ባለቤት በመሆናቸውና በንግድ ቤቱም በጋራ ሲጠቀሙ የነበረ፣ ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላም መጠቀም የቀጠሉ ስለሆነ ዕዳው ለትዳር ጥቅም የዋለ በመሆኑ ኃላፊ መባላቸው ተገቢ ነው። የንግድ ቤቱ የግል ሀብት ነው ተብሎ የተወሰነው ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ/ም ሲሆን አመልካች እንዲከፈለው የጠየቀው ዕዳ ከሚያዚያ 01 ቀን 2004 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ ስለሆነ ክፍያውን የማይከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም። አመልካች ተቋም እንደመሆኑ መጠን የኪራይ ተመን ሲያሻሻል ከተከራይ ጋር ሥምምነት ማድረግ እንደማይጠበቅበት ሕጉ ይደነግጋል። 1ኛ ተጠሪ በገቡት የውል ግዴታ መሠረት የተወሰነ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ተጨማሪ ማስረጃ አስቀርቦ የሚመረምርበት አግባብ የለም በማለት ተከራክሯል። 1ኛ ተጠሪ የመልስ መልስ አቅርበዋል።

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘውን ጭብጥ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል።

እንደመረመርነው አመልካች ግንቦት 04 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ የክስ ማመልከቻ ያቀረበው ክስ የ1ኛ ተጠሪ ባለቤትና ከ2ኛ-8ኛ ተጠሪዎች አባት የሆኑት አቶ ቅጣው መሸሻ ከአመልካች ጋር በተደረገ የንግድ ቤት ኪራይ ውል በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 05 ቀበሌ 12 የቤት ቁጥሩ 1165 የሆነ የንግድ ቤት የተከራዩ ሲሆን ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ከአከራዩ ዕውቅና ውጪ ለሦስተኛ ወገን አከራይተው የማይገባ ጥቅም በማግኘታቸው ምክንያት አመልካች የኪራይ ተመኑን በማስተካከል በወር ብር 31,479.00 እንዲከፍሉ አድርጓል። አቶ ቅጣው ቅሬታ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም። በዚህ መካከል አቶ ቅጣው መሸሻ ውል ሳያድሱ ሕዳር 13 ቀን 2005 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ስለሆነም የሚች ባለቤት የሆኑት 1ኛ ተጠሪ በገቡት የውል ሥምምነት መሠረት እና ከ2ኛ-8ኛ ያሉት ተጠሪዎች ወራሽ በመሆናቸው ከሚያዚያ 01 ቀን 2004 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ ያለውን የኪራይ ገንዘብ ከነቅጣቱ ብር

2,311,503.59 እንዲከፍሉ የሚል ሲሆን ተጠሪዎች በፍ/ሕ/ቁ. 2024(መ) መሠረት ከሁለት ዓመት በላይ የተጠራቀመ የቤት ኪራይ ክፍያዎችን አመልካች የመጠየቅ መብቱ በይርጋ የታገደ ነው፣ 1ኛ ተጠሪ በንግድ ቤት ያለኝ መብትና ግዴታ በሌላ የፍርድ ቤት ክርክር የተወሰነ በመሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና በሥረ-ነገሩም ለኪራይ ገንዘቡ ኃላፊ አይደለንም ሲሉ ተከራክረዋል።

ተጠሪዎች የፍ/ሕ/ቁ. 2024(መ) መሠረት በማድረግ ከሁለት ዓመት በላይ የተጠራቀመ የቤት ኪራይ ክፍያዎችን አመልካች የመጠየቅ መብቱ በይርጋ የታገደ ነው በሚል ያቀረቡትን መቃወሚያ ስንመርምር ድንጋጌው መብትን አስመልክቶ ክስ የማቅረቢያ ጊዜን ቀሪ የሚያደርግ የይርጋ ጽንሰ ሃሳብ ያለው አይደለም። በክርክር ሂደት ፍሬ ነገሮችን ማረጋገጥ የሚቻልባቸው ዘዴዎች ማስረጃ፣ በፍርድ ቤት በሚሠጥ የእምነት ቃል፣ ፍርድ ቤት በራሱ ግንዛቤ ሊወስድባቸው የሚችሉ ጉዳዮች /Judicial notice/፣ የሕግ ግምት (presumption of fact) እና የመሓላ ቃል ሲሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 2024(መ) የተመለከተም ፍሬ ነገር ከማረጋገጫ ዘዴዎች ከሆኑት አንዱ መካከል ስለሕግ ግምት የተደነገገ ነው። የኪራይ ገንዘብን አስመልክቶ አልተከፈለኝም በሚል አከራይ ለሚያቀርበው ክርክር ተከሳሽ የሆነው ወገን ከፍያለሁ የሚል ክርክር የሚያቀርብ ከሆነ እና ያልተከፈለው ኪራይ ገንዘብ ሁለት ዓመት ጊዜ ያለፈው መሆኑ ሲረጋገጥ ፍርደ ቤቱ ኪራይ ገንዘቡ እንደተከፈለ ግምት የሚወስድበት ነው። ስለሆነም ጉዳዩ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሆኖ የሚቀርብ ሳይሆን በፍሬ ነገሩ ክርክር ሂደት በክሱ የተመለከቱ ጉዳዮች በፍሬ ነገር ማረጋገጫ ዘዴዎች የተረጋገጠ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነው። በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች የሚከራከሩት ኪራይ ገንዘቡን ከፍለናል የሚል ሳይሆን ገንዘቡን የመክፈል በውል ሆነ በውርስ ሕግ አንገደድም የሚል በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ኪራዩ እንደተከፈለ የሕግ ግምት የሚወስድበት አግባብ የለም።

በሀሉተኛ ደረጃ በ1ኛ ተጠሪ የቀረበው መቃወሚያ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው የሚል ነው። በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5(1) መሠረት በሕግ ሥልጣን የተሠጠው ማናቸውም ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ ፍርድ ከሠጠ በኋላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ሥረ-ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ፤ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ማቅረብ አይችሉም። በድንጋጌው መሠረት ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ አልቋል ለማለት የተዘረዘሩት አራት መስፈርቶች በአንድነት መሟላት አለባቸው። የመጀመሪያው መስፈርት ጉዳዩን የተመለከተው <u>በሕግ ሥልጣን የተሠጠው</u> (ሠረገዘ የተጨመረ) ማናቸውም ፍርድ ቤት መሆኑ ነው። በሕግ ሥልጣን የተሰጠው የሚለው ትርጉም የሚያስፈልገው መስፈርት ነው። በፍርድ ቤት የሥረ-ነገር ሥልጣን ሳይኖረው የተሠጠ ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 212 እንደተመለከተው በይግባኝ እስካልተለወጠ ድረስ የጸና በመሆኑ ጉዳዩን አስቀድሞ ፍርድ እንደተሠጠበት የሚያስቆጥር ነው። ስለሆነም በሕግ ሥልጣን የተሠጠው የሚለው የሥረ-ነገርና አካባቢያዊ ሥልጣንን የሚመለከት ሳይሆን አስቀድሞ ጉዳዩ የታዬው በሕግ ዳኝነት ለመስጠት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት ወይም ዳኝነት ነክ አካል መሆኑን ለማመላከት ነው። ይህም በፍርድ ቤት ሥልጣን ሳይኖረው ፍርድ መስጠት እንደ አስገዳጅ ውሳኔ የሚቆጠርና የሚፈጸም መሆኑን የሚያሳይ እና በኢትዮጵያ እንዳልተሰጠ የሚቆጠር ፍርድ (void judgment) እንደሌለ ያስረዳል። ዳኝነት ለመስጠት በሕግ ሥልጣን

ያልተሠጣቸው አካላት ጉዳዩ ላይ አስቀድመው በአስተዳደር ማየታቸው ሆነ ውሳኔ መስጠታቸው ጉዳዩን በፍርድ እንዳለቀ የማያስቆጥር እና ክርክር ከማድረግ የሚከለክል አይሆንም፡፡ ይህም በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 እና አንቀጽ 79(1) እንደተመለከተው የመዳኘት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች እና የዳኝነት ነክ አካል ብቻ መሆኑን የሚያሳይ እና በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 50(2) የመንግሥት አካላትን የሥልጣን ክፍፍል መርህን (principle of separation of powers) የተከተለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ሁለተኛው መስፈርት አስቀድሞ በፍርድ ቤት የተሠጠው የመጨረሻ ፍርድ መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ክርክሩን አይቶ ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ እልባት ወይም ውጤት የሠጠበት መሆን እንዳለበት የሚያስረዳ መስፈርት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ በመሰማት ላይ እያለ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ሆነ በይግባኝ ደረጃ ላይ እያለ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 69(2)፣ አንቀጽ 70(መ) እና አንቀጽ 73 በተመለከተው አግባብ መዝገቡ ከተዘጋም፤ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74(1) እንደተመለከተው በተቋረጠው ጉዳይ አዲስ ክስ ማቅረብ መከልከሉ ጉዳዩ በፍርድ አልቋል የሚለውን መርህ የሚከተል ነው፡፡ በሌላ በኩል በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231(1) የተመለከተው በክስ አቤቱታው የተገለጸው የማያስከስስ መሆን ወይም የሥረ-ነገር ሥልጣን አለመኖር ምክንያት ተደርጎ ክሱ መቋረጡ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ያልተሠጠበት ስለሆነ በፍርድ እንዳለቀ የሚያስቆጥር አይሆንም፡፡ የክስ ምክንያት ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ መኖሩን፣ የተጠየቀው ዳኝነት በፍርድ ቤት የሚዳኝ መሆን አለመሆኑን እና በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተመለከቱት ጉዳዮች ቢረጋገጡ የተጠየቀውን ዳኝነት ለከሳሽ ለመወሰን ህግ የሚፈቅድ መሆን አለመሆኑን መመርመርን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህም የክስ ምክንያት የሌለው ጉዳይ የሚለው በዋነኛነት ዳኝነቱን ለመጠየቅ ከህግ የመነጨ ግንኙነት እያለው ግን በፍርድ ቤት ሊዳኙ የማይችሉ ጉዳችን (non-justiciable matters) የጉዳዩ ባሕሪ በፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር ሊወድቁ የማይችሉ፣ አከራክሮ ሊፈጸም የሚችል ውሳኔ ሊሰጥባቸው የማይችሉ በመሆናቸውና ከሳሽ ወገን ክሱን ሲያቀርብ የጠቀሰው ወይም የገለጸው የክሱ መሰረት የሆነው ምክንያት በህግ የክስ መሰረት ሊሆን የማይችል ከሆነ የማያስከስስ ነው ተብሎ ክሱ ውደቅ የሚደረግበት ሥርዓት ነው፡፡ ጉዳዩም በሥረ-ነገሩ ታይቶ ውሳኔ ያላረፈበት በመሆኑ እንደ መጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር አይደለም፡፡ የሥረ-ነገር ሥልጣን ባለመኖር ክሱ ውድቅ መደረጉም ሥልጣን ባለው ሌላ የዳኝነት አካል ጉዳዩ ቀርቦ ሊወሰን የሚችል በመሆኑና በሥረ-ነገሩ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ ያልተሠጠበት በመሆኑ በፍርድ እንዳለቀ ጉዳይ ተቆጥሮ መቃወሚያ ሊቀርብበት የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም የመጨረሻ ፍርድ የሚለው በሥረ-ነገሩ መታየትን መሠረት ያደረገ ቅድመ ሁኔታ መኖር እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ሦስተኛው መስፈርት አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ሥረ-ነገሩና ጭብጡ አሁን ከተያዘው ጉዳይ ጋር አንድ ዓይነት መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ጉዳይ አንድ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ፍርድ ቤቱ በጭብጥነት የመረመረው ጉዳይ አሁን በተያዘው ክርክርም በጭብጥነት ተይዞ የሚመረመር ከሆነ ውጤቱ አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበት ይሆናል፡፡ ሥረ-ነገሩ ተመሳሳይ ሆኖ ነገር ግን የሚያዘው ወይም የተያዘው ጭብጥ የተለያዬ ከሆነ በተያዘው ጭብጥ ላይ የቀደመ ፍርድ ባለመኖሩ ጉዳዩ በፍርድ እንዳለቀ ሳይቆጠር ክርክሩ ቀጥሎ ፍርድ ሊያርፍበት የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ በሕጉ ላይ የተቀመጠው አራተኛው መስፈርት

የተከራካሪዎች ወይም ከተከራካሪዎች መብት ያገኙ ሦስተኛ ወገኖች ተመሳሳይ መሆን እና በእነርሱ መካከል ያለ ክርክር መሆኑ ነው። የዚህ መስፈርት መነሻ ፍርድ የአስገዳጅነት ሀይል ሆነ ውጤት የሚኖረው በተከራካሪዎች መካከል ብቻ ነው የሚል ነው። ከተከራካሪዎች ውጭ ፍርዱን በመያዝ መብት ማቋቋም ሆነ ማስፈጸም አይቻልም። ፍርድ ቤት ጉዳዩን የሚመረምረው ሆነ ፍርድ የሚሠጠው ከተከራካሪዎች መካከል የተሻለ መብት ያለው ማን ነው ከሚለው ነጥብ አኳያ ብቻ ነው። በጉዳዩ ላይ ያላቸው መብት በፍርድ ቤቱ ሳይመረመር እና የመደመጥ ሆነ የመከላከል መብታቸው ሳይከበር ተከራካሪ ያልሆኑ ወገኖች ላይ ፍርዱ አስገዳጅነት አለው ሊባል አይችልም። የተከራካሪዎች ተመሳሳይነት የሚለው ከተከራካሪዎች በሕግ ሆነ በውል መብት የተላለፈላቸውን ሦስተኛ ወገኖች የመብታቸው ምንጭ የቀድሞው ክርክር ላይ ተከራካሪ በሆኑት ወገኖች ልክ በመሆኑ በእነዚህ ወገኖች ላይም ጉዳዩ አስቀድሞ በፍርድ እንዳለቀ የሚያስቆጥር ነው።

በተያዘው ጉዳይ መቃወሚያው የቀረበው 1ኛ ተጠሪ እና ከ2ኛ - 8ኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች መካከል የንግድ ቤቱን አስመልክቶ ያደረጉት ክርክርና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 180343 ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የንግድ ቤቱ የሚች ቅጣው መሸሻ የግል ሀብት ነው ተብሎ መወሰኑን መሠረት በማድረግ ነው። በዚህ ክርክር ውርስ ማጣራት ሂደትን ተከትሎ አመልካች የኪራይ ገንዘብ የጠየቀበት የንግድ ድርጅቱ የውርስ ሃብት መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ጭብጥ ሲሆን አሁን በሰበር ችሎት ደረጃ የተያዘው ጉዳይ ደግሞ የኪራይ ገንዘብ አከፋፈልን የሚመለከት በመሆኑ የጭብጥ ልዩነት ያለው ነው። በውርስ ክርክሩ አመልካች ባለመሳተፉና ሊሳተፍም የማይችል በመሆኑ የተከራካሪዎች ተመሳሳይነትም የለም። ሥለሆነም ጉዳዩ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5(1) መሠረት በፍርድ ያለቀ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አልተቀበልነውም።

በሥረ ነገሩ አመልካች የኪራይ ገንዘብ እንዲከፈለው የጠየቀ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 05 ቀበሌ 12 የቤት ቁጥሩ 1165 የሆነ የንግድ ቤት ላይ አመልካች እና ሟች ቅጣው መሸሻ ባደረጉት የኪራይ ውል መነሻ የሚጠቀሙበት ሲሆን አመልካች የኪራይ ተመን ለማሻሻል በሕግ ባለው ሥልጣን መሠረት ከጥቅምት 30 ቀን 2004 ዓ/ም በኋላ ላለው ጊዜ በወር ብር 31,479.00 እንዲከፍሉ አድርጓል። በማሻሻያው ላይ ቅሬታ ቀርቦም ተቀባይነት ያጣ በመሆኑ የውል ማሻሻያው ተግባራዊ ይሆናል። በሕግ አግባብ የተደረገ ውል በተዋዋዮች መካከል በፍ/ሕ/ቁ. 1731(1) እንደተመለከተው እንደ ሕግ የሚቆጠር መሆኑ እና በፍ/ሕ/ቁ. 1785(2) መሠረት በውል ዓይነተኛ መጣስ ከሌለ በስተቀር መፈጸም እንዳለበት የተደነገገ መሆኑ ሲታይ በተቻለ መጠን ተዋዋዮች ባስተላለፉት መብትና ግዴታ ልክ ውሉን የመፈጸም ግዴታ አለባቸው።

ተከራይ የሆኑት አቶ ቅጣው መሸሻ ሕዳር 13 ቀን 2005 ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ በመሆናቸው ከሚያዚያ 01 ቀን 2004 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ ያለውን የኪራይ ገንዘብ ከነቅጣቱ ብር 2,311,503.59 ተጠሪዎች እንዲከፍሉ አመልካች ዳኝነት ጠይቋል። 1ኛ ተጠሪ ክፍያው አይመለከተኝም የሚሉት የውል ግዴታ አልገባሁም፣ የንግድ ቤቱ በፍርድ ቤት ክርክር የሚች የግል ሀብት ተብሏል፣ ውርስ አጣሪው ንብረቱን ተረክቦ እያስተዳደረው ነው በሚል ነው። 1ኛ ተጠሪ የሚች ቅጣው መሸሻ ባለቤት

በመሆናቸው ከባለቤታቸው ጋር የነበራቸው ጋብቻ በሞት እስኪፈርስ ድረስ በጋራ ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ አልተካደም፤ ንብረቱ የባለቤታቸው የግል ቢሆን እንኳን የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 62(1) መሠረት ገቢው የጋራ ስለሚሆን በጋራ ለሚጠቀሙበት ንግድ ሥራ ወጪውንም በጋራ የመክፈል ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡፡ ጋብቻው በሞት ከፈረሰ በኋላም በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች መካከል 1ኛ ተጠሪ በ10/05/2005 ዓ/ም እና በ08/08/2005 ዓ/ም ለአመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ሆነ ከአመልካች ጋር በ09/08/2005 ዓ/ም ብር 547,287.13 ዕዳ ለመክፈል ያደረጉት ሥምምነት እና በውሉ መሠረት ብር 200,000.00 መክፈል መጀመራቸው በንግድ ቤቱ መጠቀማቸውን መቀጠላቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ አመልካች የኪራይ ገንዘብ እስከጠየቀበት ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ 1ኛ ተጠሪ በንግድ ቤቱ ላይ ከ2ኛ-8ኛ ድረስ ካሉት ተጠሪዎች ጋር የውርስ ክርክር በማድረግ መቀጠላቸው መረጋገጡ ሆነ አመልካች ንብረቱን እንዲረከባቸው ኃላፊነትን ስለማውረድ ክስ ባላቀረበበት ሁኔታ ንብረቱን ለውርስ አጣሪ አስረክቤያለሁ በሚል ለኪራይ ገንዘቡ ኃላፊ ልሆን አይገባም የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለሆነም በሥር ፍርድ ቤቶች 1ኛ ተጠሪ ለኪራይ ገንዘብ ኃላፊ ናቸው ተብሎ መወሰኑ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ከ2ኛ-8ኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች የሚች ቅጣው ወራሾች በመሆናቸው የአባታቸውን ዕዳ እንዲከፍሉ የቀረበ ዳኝነት ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከ2ኛ - 8ኛ ያሉት ተጠሪዎች በንግድ ቤቱ ላይ ወራሽነት ቢያረጋግጡም በንግድ ቤቱ ባለመጠቀማቸው ኃላፊነት የለባቸውም ብሏል፡፡ ከ2ኛ-8ኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች የሚች አባታቸው ወራሽ ሲሆኑ አመልካች የኪራይ ገንዘብ የጠየቀበትን የንግድ ቤት ጨምሮ የውርስ ሀበት መውረሳቸውን ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 180343 የተሰጠው ውሳኔ ያስገነዝባል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 826(1) መሠረት ሚች ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ውርሱ የሚከፈት ሲሆን በንዑስ ቁጥር ሦስት እንደተመለከተው የሚች መብቶችና ግዴታዎች ወደወራሾች ይተላለፋሉ፡፡ ሚች አባታቸው የንግድ ቤት ከአመልካች በመከራየታቸው ምክንያት የሚመጣ ዕዳን ከ2ኛ-8ኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች ወራሾች በመሆናቸው ብቻ ለዕዳው ኃላፊ ናቸው፡፡ በንግድ ቤቱ መጠቀም አለመጠቀማቸው በጭብጥነት የሚመረመር አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ወራሾች መሆናቸውን አረጋግጦ እያለ በንግድ ቤት አልተጠቀሙም በሚል ለክሱ ኃላፊ አይደሉም በሚል የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

አመልካች ክፍያው ሳይፈጸም በመዘግየቱ ቅጣት እንዲከፈለው ጠይቋል፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 1790 እና 1791 እንደተመለከተው ውል ያልተፈጸመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ውል ያልፈጸመው ወገን የደረሰውን የጉዳት ኪሣራ መክፈል አለበት፡፡ የሚከፈለው ኪሣራ ተዋዋዮች በፍ/ሕ/ቁ. 1889 መሠረት አስቀድመው የወሰኑት ከሆነ በውሉ የተመለከተውን መጠን ሲሆን ተዋዋዮች አስቀድመው ኪሣራውን ካልወሰኑ በክርክር ሂደት ፍርድ ቤት ኪሣራውን በማስረጃ አጣርቶ የሚወስነው ይሆናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እስከ ስድስት ወራት ድረስ ያለውን የቅጣት ክፍያ 10% እንዲከፈል የወሰነ ሲሆን ቀሪ ቅጣት ክፍያውን ውድቅ ያደረገው በውሉ አንቀጽ 3(3) መሠረት ከስድስት ወር በላይ ክፍያ ቢዘገይ ውሉን የመሠረዝ መብት አመልካች እያለው መብቱን ሳይጠቀም ለተጠራቀመው ቅጣት ክፍያ እንዲከፈለው መጠየቅ አይችልም

በማለት ነው፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 1784 እና ከ1786-1789 መሠረት ውል በፍርድ ቤት ወይም በተናጠል በተዋዋይ ወገን ሊሠረዝ ይችላል፡፡ በውሉ የተመለከቱ ሁኔታዎች ሲሟሉ ተዋዋይ ወገን ውሉን በተናጠል የመሠረዝ መብት የሚኖረው ሲሆን ወሉን የመሰረዝ መብቱን አለመጠቀሙ እንደውል እንዲፈጸም ከመጠየቅ ወይም ውሉ ባለመፈጸሙ ምክንያት ጉዳት ሲደርስ ጉዳት ኪሣራ እንዳይጠይቅ የሚያደርግ አይደለም፡፡

አመልካች ውሉን የመሠረዝ መብት ባለመጠቀሙ የውል አፈጻጸም የቀጠለ እስከሆነ ድረስ እና ተጠሪዎች ክፍያ ሳይከፍሉ ለቆዩበት ጊዜ በውሉ የተመለከተው የጉዳት ኪሣራ/ቅጣት እንዲከፍሉ መጠየቁ ሕግን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በፍ/ሕ/ቁ. 1893 እንደተመለከተው ዳኞች መቀጫ መቀነስ የሚችሉት ውሉ በከፊል ከተፈጸመ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የኪራይ ውል ክፍያው በየወሩ የሚከፈል በመሆኑ እና ተጠሪዎች ከሚያዚያ 01 ቀን 2004 ዓ/ም እስከ ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም ድረስ ላሉት 57 ወራት ክፍያ ባለመክፈላቸው በየወሩ ለዘገየው ክፍያ በውሉ የተመለከተውን ቅጣት የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤት ቅጣት ክፍያው በከፊል ብቻ ነው ሊከፈል የሚገባው ሲል የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 194706 በጥቅምት 16 ቀን 2013 ዓ/ም እና በመዝገብ ቁጥር 195936 ታህሳስ 08 ቀን 2013 ዓ/ም እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 191209 ግንቦት 04 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. 1ኛ ተጠሪ እና ከ2ኛ - 8ኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች ብር 2,311,503.59 በጋራ ለአመልካች እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውሳኔው መሠረት እንዲያስፈጽም አዘናል፡፡ ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-200555

ቀን፡-29/02/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ መሐመድ አበራ- አልቀረቡም

ተጠሪዎች ፡-1. አቶ ታጁ ጌታዬ }

2. ሀሰን አሊ } አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት ተጠቃሚነት መብት የሚመለከት ነዉ፡፡በስር በወግድ ወረዳ ፍርድ ቤት ተዋበች አስናቀዉ ከሳሽ የአሁን አመልካች 1ኛ ተከሳሽ በዚህ መዝገብ ላይ በተከራካሪነት ያልተሰየሙት ካሳዉ መንግስቱ 2ኛ ተከሳሽ የአሁን ጣልቃ ገቦች ከሌሎች ስድስት ጣልቃ ገቦች ጋር በመሆን በጣልቃ ገብነት ተከራክረዋል፡፡ የክሱም ይዘት በወረዳዉ 02 ቀበሌ ዉስጥ በክሱ በተጠቀሱት አዋሳኞች የሚታወቅ በ1983ዓ/ም የተመራሁበትንና በደብተር ያስመዘገብኩትን 4 ገመድ የእርሻ መሬት አመልካች ይዞብኝ ለስር 2ኛ ተከሳሽ በመሸጡና 2ኛ ተከሳሽ ቤት ሊገነባ ስለሆነ የያዙብኝን መሬት እንዲለቁልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ መሬቱ የከሳሽ ሳይሆን ከሚች አሊ ፈለቀ ጋር በ1983ዓ/ም አብረዉ ተመርተዉ አቶ አሊ ፈለቀ በ2003ዓ/ም ሲሞት እኔ ከሚች ጋር በቤተሰብ አባልነት አብሬ ያደኩ በመሆኔ ወራሽነቴን አረጋግጩ ለሁለት ከከሳሽ ጋር ሁለት ሁለት ገመድ ተካፍለናል፡፡በደረሰኝ መሬት ላይ ቤት ልሰራ እንጨትና ድንጋይ አራግፌያለሁ እንጂ የከሳሽን አልነካሁም በማለት ተከራክረዋል፡፡የስር 2ኛ ተከሳሽም መሬቱን አልገዛሁም፤የአሁን አመልካች ቤት ሊሰራ ነዉ በማለታቸዉ ድንጋይና እንጨት አራግፌያለሁ በማለት ለክሱ መልስ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በክርክሩ ጣልቃ በመግባት ክስ የተመሰረተበት መሬት የሚች አባታችን አሊ ፈለቀ ሲሆን የአሁን አመልካች 2 ገመድ መሬት መብት ሳይኖራቸዉ በመያዝ ለሌላ ሰዉ በሽያጭ አስተላልፈዉ ቤት ሊያሰሩበት ስለሆነ ወርሰን የያዝነዉን መሬት እንዲያስረክበን ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡በዚህ የጣልቃ ገቦች አቤቱታ ላይ የስር ከሳሽ በሰጡት መልስ መሬቱ የጣልቃ ገቦች መሆኑን በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን የአሁን አመልካች ደግሞ የሚቹ የቤተሰብ አባል በመሆን ወራሽነቱን አረጋግጩ የያዝኩት ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 28616 ላይ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶና መርምሮ በቀን 12/05/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ለክርክሩ መነሻ ከሆነዉ 4 ገመድ መሬት ዉስጥ 2 ገመድ መሬት የሚች አሊ ፈለቀ እንደሆነና አመልካች የሚች የአቶ አሊ ፈለቀ የቤተሰብ አባል በመሆን መሬቱን ሊይዙ እንደቻሉ በማስረጃ ስለተረጋገጠና ይሕም በአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 17/5 መሰረት የሕግ ድጋፍ ያለዉ በመሆኑ አመልካች መሬቱን በሕግ አግባብ ስለያዙ ሊለቁ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡ የአሁን ጣልቃ ገቦች ከሌሎች የሥር ጣልቃ ገቦች ጋር በመሆን ይግባኝ ለደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 45606 ላይ በቀን 18/05/2012ዓ/ም በሰጠዉ ብይን ይግባኙን ሰርዞባቸዋል፡፡

በመቀጠል ተጠሪዎች የሰበር አቤቱታቸዉን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዉ ችሎቱ በመ/ቁጥር 03-28591 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 07/04/2013ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ክርክሩ አዲሱ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 ተፈጻሚ በሆነበት ጊዜ የተጀመረ እና በቀድሞዉ አዋጅ መሰረትም ተወርሶ ሕጋዊ መብት የተቋቋመበት ስላልሆነ በአሁን አዋጅ መሰረት ቅድሚያ ሊወርስ የሚገባዉ ማነዉ?የሚለዉ ዉሳኔ ማግኘት ያለበት ጭብጥ ነዉ፡፡በአዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/5 መሰረት የሚች መሬት በቅድሚያ ለመዉረስ መብት ያለዉ የሚች ልጆች ሲሆኑ ልጆች ሞተዉ ከሆነ ደግሞ የልጅ ልጅ ምትክ ሆነዉ እንዲወርሱ ሊደረግ የሚቻል ስለመሆኑ በንዑስ አንቀጽ 6 ተደንግጓል፡፡ የአሁን ተጠሪዎችም የቀድሞ አዋጅ ፀንቶ ባለበት ጊዜ ወራሽነታቸዉን ያሳወጁ ቢሆንም ቀድመዉ ወርሰዉ ያልያዙ በመሆኑ በአሁን አዋጅ የሚስተናገድ ከመሆኑ አንጻር ከአሁን አመልካች ቀድመዉ የሚች አሊ ፈለቀን መሬት የመዉረስ መብት ያላቸዉ የአሁን ተጠሪዎች ስለሆኑ አመልካች የሚችን ሁለት ገመድ መሬት ለተጠሪዎች ሊያስረክብ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 27/04/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡- ለክሱ መነሻ ከሆነዉ መሬት የስር ከሳሽ ድርሻቸዉን መዉሰዳቸዉ ከመረጋገጡም በተጨመሪ ክሳቸዉን በማስረጃ ባለማስረዳታቸዉ ክሱ ዉድቅ መደረግ ነበረበት፡፡ለተጠሪዎች(ለጣልቃ ገቦች) ሕጉ የወራሽነት መብት የሚጠብቅ ቢሆንም ተጠሪዎች የራሳቸዉ የሆነ መሬትና መተዳደሪያ ደንብ ያላቸዉ ሲሆኑ በአንጻሩ አመልካች ከሁለት ዓመቶ ጀምሮ እዚያዉ አድጌ አያቴ አቶ አሊ በሞት እስከተለዩበት 2003ዓ/ም ኖሬ ያደኩኝ ነኝ፡፡ለመሬቱ በተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ላይ በቤተሰብ አባልነት ተመዝግቤያለሁ፡፡አያቴ ከሞቱበቱ በኋላ ከ2003ዓ/ም ጀምሮ በስሜ ግብር እየገበርኩ እገኛለሁ፡፡የክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/5 የራሱ የሆነ መሬት የሌለዉ የቤተሰብ አባል መሬቱን በቅድሚያ እንዲወርስ መብት የሚሰጥ ነዉ፡፡ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የቤተሰብ አባል መሆኔ ተረጋግጦ እያለ የያዝኩትን መሬት እንዲለቅ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች መሬቱን የያዙት የቤተሰብ አባል በመሆን በሕጋዊ መንገድ ነዉ ተብሎ የተወሰነዉን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመዉረስ መብት የላቸዉም በማለት የሻረበትን አግባብነት ከአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/5 አንጻር ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 26/09/2013 ዓ/ም የተፃፈ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡የመልሳቸዉም ይዘት በአጭሩ፡-ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት በ1983 ዓ/ም የተደለደለዉ ለሟች አቶ አሊ ፈለቀ እና ለስር ከሳሽ ወ/ሮ ተዋበች አስናቀዉ ነዉ፡፡ሆኖም አቶ አሊ ፈለቀ ከሞቱ በኋላ ከ2003ዓ/ም ጀምሮ 1ኛ ተ/ጠሪ እናቴን ወ/ሮ ዘነበች አሊን በመተካት እንዲሁም ሁለተኛ ተጠሪ የወላጅ አባቴ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ መሆኔን ከሌሎች ወራሾች ጋር በማረጋገጥ መሬቱን ከስር ከሳሽ ጋር በመሆን አከራካሪዉን መሬት ስንጠቀም ቆይተናለ፡፡በ2011ዓ/ም ወ/ሮ ተዋበች አስናቀዉ ሰባት ሰዎች በሚል የመሬት ማረጋገጫ ደብተር በስማችን አዉጥተን እየተጠቀምን እንገኛለን፡፡ክርክሩ የተጀመረዉ የክልሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 252/2009 ጸድቆ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ በመሆኑ፣አመልካች በመሬቱ ላይ ቀድመዉ የመሬት ባለይዞታነት ደብተር በማዉጣት ያቋቋሙት መብት ባለመኖሩ፣አዋጅ ቁጥር 252/2009 አንቀጽ 17/5 ላይ ባስቀመጠዉ የወራሽነት ቅደም ተከተል መሰረት የቀድሞዉ አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 16/5 እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣዉን ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 11/7 ስለወራሽነት ቅደምተከተል አካሄድ ለዉጦ ቅድሚያ መዉረስ የሚገባዉ የቤተሰብ አባል ሳይሆን የሚች ልጆች ናቸዉ በማለት ደንግጓል፡፡ ይህንን መሰረት በማድረግ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅድሚያ የመዉረስ መብት ያላቸዉ የሚች ልጆች ናቸዉ በማለት የአመልካችን ክርክር ባለመቀበል የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻሩና አመልካች መሬቱን እንዲለቁ በመወሰኑ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ በማሻሻል የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት ለአመልካች አይገባቸዉን በማለት ሲወስኑ ለጉዳዩን

ተገቢውን ሕግ መሰረት በማድረግ ነው ወይስ አይደለም የሚል ጭብጥ በመያዝ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም የስር ከሳሽ ወ/ሮ ተዋበች አስናቀው በክሱ የተጠቀሰውና ለክርክሩ መነሻ የሆነው 4 ገመድ መሬት በአጠቃለይ የእሳቸው እንደሆነ በመግለጽ አመልካችና የስር 2ኛ ተከሳሽ እንዲለቁላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡ የአሁን ተጠሪዎች እና ሌሎች አራት ሰዎች በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በጣልቃ ገብነት መከራከራቸውን ክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ ከቀረበው ክርክርና ማስረጃዎች ለክሱ መነሻ ከሆነው ስፋት 4 ገመድ ከሆነ መሬት 2 ገመድ የስር ከሳሽ ይዞታ እንደሆነ ቀሪው ግማሽ መሬት ደግሞ የሚች አቶ አሊ ፈለቀ ይዞታ እንደሆነ በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠና በግራ ቀኙም የታመነ ነው፡፡እንዲሁም አመልካች የሚች ቤተሰብ አባል እንደሆኑና የስር ጣልቃ ገቦችን ጨምሮ የአሁን ተጠሪዎች(የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሚች አቶ አሊ ፈለቀ ሚስት ወራሽ እንደሆኑ ለዚህ ችሎት ባቀረቡት መልስ ላይ ገልጸዋል) የሚች አቶ አሊ ፈለቀ ወራሾች እንደሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረውና የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻው ጭብጥ አከራካሪው የሚች አቶ አሊ ፈለቀ መሬት የሚቹ የቤተሰብ አባል ለሆኑት አመልካች ሊተላለፍ የሚገባ ሳይሆን ለአሁን ተጠሪዎች ሊተላለፍ የሚገባ ነው ተብሎ መወሰኑ እና ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 51/1999 ሳይሆን የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 252/2009 ነው ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነው፡፡

እንደሚታወቀው ሕግ በዜጎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመቆጣጠር ሲባል በሕግ አውጪው አካል የሚወጣ መሣሪያ ነው፡፡ በዚህ አግባብ የሚወጣውም ሕጉ በሥራ ላይ ባለበት ወቅት በዜጎች መካከል ያለውን ወይም ወደ ፊት የሚፈጠረውን ግንኙነት ለመቆጣጠር ወይም ለመዳኘት በመሆኑ ሕጉ ከመውጣቱ በፊት ወይም ከተሻረ በኋላ በተፈጠረ/በሚፈጠር ግንኙነት ላይ ሕግን ተፈፃሚ ማድረግ አይቻልም፡፡ ይህም ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም ከሚለው አጠቃላይ መርህ (the principle of non-retroactivity of laws) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለውም መርህ መሠረተ ሃሳቡም ሕጉ በስራ ላይ ከዋለ በኋላ ለተፈጠረ መብትና ግዴታ ወይም ፍሬ ነገር ላይ ተፈጻሚ መሆን ስላለበት እና ዜጎች በሚያውቁት ሕግ መተዳደር አለባቸው የሚለውን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡እንዲሁም አንድ ሕግ የሚጸናበትን ጊዜ አስመልክቶ በሕግ አውጪው ከተደነገገው ቀን በፊት ለተፈጠሩት ክስተቶች ወይም መብትና ግዴታዎች ተፈፃሚነት አይኖረውም የሚል ሃሳብ ያለው ነው፡፡ የዚህ መርህ ተግባራዊነት የሕግ የበላይነት ከሚረጋገጥባቸው መገለጫዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም አንድ መሠረታዊ ሕግ (substantive law) ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲሰራ ሕግ አውጪው በሕጉ ላይ በልዩ ሁኔታ ካላመላከተ በስተቀር ፍርድ ቤት ወይም ሌላ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው አካል ለያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለውን መሠረታዊ ሕግ ሲወስን መሠረት ሊያደርግ የሚገባው ወይም

መሠረት እንዲያደርግ የሚጠበቅበት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ በተፈጠረበት ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆን የነበረዉን ሕግ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ መሰረት አንድ ሕጋዊ ዉጤት ያለዉ ተግባር (Juridical act) ወይም መብትና ግዴታ በተፈጠረበት ጊዜ የነበረዉ ሕግ በሌላ ሕግ የተተካ ሆኖ ሲገኝ እና ክርክሩ ለፍርድ ቤት ወይም ለዳኝነት ሰጪ አካል የቀረበዉ አዲሱ ሕግ በሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ሆኖ ከተገኘ ፍርድ ቤቱ ክርክሩን መምራት እና ዉሳኔ መስጠት ያለበት በመብትና ግዴታው በተፈጠረበት ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆን በነበረው ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡ ክርክሩ አዲሱ ሕግ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ለፍርድ ቤት መቅረቡ ጉዳዩ በአዲሱ ሕግ መሠረት እንዲመራ ምክንያት ሊሆን አይገባም፡፡ ይህን ማድረግ ሕግ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም የሚለዉን የሕግ መርህ የሚጥስ ከመሆኑም በላይ የሕግ የባላይነት እንዳይረጋገጥ ወይም እንዲሸረሸር ምክንያት ይሆናል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ መሬት ባለመብት አቶ አሊ ፈለቀ የሞቱት በ2003ዓ/ም መሆኑ በግራ ቀኙ የታመነ ነዉ፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የገጠር መሬትን ወራሽነት መብትን የሚመለከት ሲሆን የወራሽነት መብት የሚተላለፍላቸዉን ሰዎች ማንነትና ቅደምተከተል አስመልክቶ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ከተመለከተዉ ዉጭ ከዉርስ ጋር በተያያዘ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ላይ የተመለከቱ ደንቦች እና መርሆዎች ከገጠር መሬት ወራሽነት ጋር በተያያዘም እንደየአግባብነታቸዉ ተፈፃሚነት አላቸዉ፡፡ ዉርስ የሚከፈትበትን ሁኔታ አስመልክቶ በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 826/1 ስር እንደተደነገገዉ ዉርስ የሚከፈተዉ አዉራሹ በሞተበት ጊዜ እና ቦታ ነዉ፡፡ስለሆነም አንድ ሰዉ የሟች ወራሽ መሆን ያለመሆኑ የሚረጋገጠዉ ሟች በሞተበት ጊዜ በሥራ ላይ ያለዉን ሕግ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡ የወራሽነት ማረጋገጫ ከስሙም መገንዘብ እንደሚቻለዉ በሕግ የተገኘን መብት ለማረጋገጥ የሚሰጥ እንጂ በእራሱ መብት የሚሰጥ ስላልሆነ ዉርሱ ተከፈተ የሚባለዉ የወራሽነት ማረጋገጫ የተወሰደበት ጊዜ እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡በዚህ መሰረት የአከራካሪዉ መሬት ባለመብት የሞቱት በ2003 ዓ/ም በመሆኑ በዚህ ጊዜ ተፈጻሚ ሲሆን የነበረዉ ከቀን 21/09/1998ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ መሆን የጀመረዉ የተሻሻለዉ የአማራ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ከቀን 21/12/1998ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ የሆነዉ ደንብ ቁጥር 51/1999 ናቸዉ እንጂ ከሐምሌ 2009ዓ/ም ጀምሮ ተፈጻሚ መሆን የጀመረዉ የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 252/2009 አይደለም፡፡ በዚህ አዋጅ ቁጥር 252/2009 በመሸጋገሪያ ድንጋጌ በአንቀጽ 57 ላይ በሌሎች ሕጎች የተቋቋሙ መብቶች እና ግዴታዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተጋጩ ድረስ ተፈፃሚነታቸዉ እንደሚቀጥል እንዲሁም አዋጁ ከመዉጣቱ በፊት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት አግባብ እልባት ያገኛሉ በሚል መደንገጉ ከዉርስ ጋር በተያያዘ ለሚነሳ ክርክር ይህ አዋጅ ወደ ኋላ ተመልሶ ተፈጻሚ እንዲሆን ተደንግጓል የሚያስብል አይደለም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን በየደረጃዉ ያዩት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ አዋጅ ቁጥር 252/2009 ነዉ በማለት ይህንን አዋጅ መሰረት አድርገዉ መወሰናቸዉ ሕግ ወደኋላ ተመልሶ አይሰራም በሚል የሚታወቀዉን ተቀባይነት ያለዉን የሕግ መርህ የሚጥስ በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

በዚህ መሰረት በአዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 7(1/ለ) ስር እንደተደነገገዉ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣዉ ደንብ ላይ በሚወሰነዉ መሰረት በክልሉ ዉስጥ ነዋሪ የሆነና በግብርና ሥራ የሚተዳደር ወይም በዚሁ ሥራ ለመተዳደር የሚፈልግ ማንኛዉም ሰዉ የመሬት ይዞታ መብት በዉርስ የማግኘት መብት አለዉ፡፡በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 16/5 ላይ አንድ የመሬት ባለይዞታና የመጠቀም መብቱን በተመለከተ ሳይናዘዝ የሞተ ሰዉ መብቱ በግብርና ሥራ ለሚተዳደር ወይም በዚሁ ሥራ መተዳደር ለሚፈልግ የሚቹ ልጅ ወይም ቤተሰብ አባል ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ በሚደነገገዉ ቅደም ተከተል መሰረት እንደሚተላለፍ ተደንግጓል፡፡ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በወጣዉ ደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 11/7 ስር ማንኛዉም የገጠር መሬት ባለይዞታ ሳይናዘዝ የሞተ እንደሆነ ወይም ኑዛዜዉ በሕግ ፊት የማይጸና የሆነ እንደሆነ የመሬት ይዞታዉ ለሚቹ የቅርብ ዘመዶች በዉርስ የሚተላለፍበት ቅደም ተከተል ተደንግጓል፡፡በዚህ ቅደም ተከተል መሰረት በአንቀጽ 11(7/ሀ) ላይ እንደተደነገገዉ በቀዳሚነት የመዉረስ መብት የተሰጣቸዉ ለአካለ መጠን ያልደረሱ የሚቹ ልጆች፣ልጅ ከሌለዉ የቤተሰብ አባላቱ እንደሆኑ ተደንግጓል፡፡ከእነዚህ ሕግጋት አንጻር የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን መርምረዉ አከራካሪዉ መሬት ተጠሪ ሊለቁ የሚገባ መሆን አልመሆኑን በተመለከተ ዉሳኔ አለመስጠታቸዉ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ጉድለት ነዉ፡፡በተጨማሪም ክሱን የመሰረቱት የስር ከሳሽ አመልካች መሬቱን እንዲለቁላቸዉ ያቀረቡት ዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ ከተደረገና የአሁኑን ተጠሪዎች ጨምሮ የስር ጣልቃ ገቦች በክርክሩ ተሳታፊ የሆኑት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በመሆኑ ከሥነ ሥርዓት ሕጉ አንጻር የክርክሩ ዉጤት ምን ሊሆን ይገባል የሚለዉም ተገናዝቦ ታይቶ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ የሥነ ሥርዓት ጥያቄ ነዉ፡፡በመሆኑም በእነዚህ ጭብጦች ላይ የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ስላልሰጡበት ከላይ ከተመለከተዉ አንጻር ተገቢዉን ሕግ ተግባራዊ ካለማድረግ እና ከክርክር አመራር አንጻር የተፈጸመዉ የሕግ ስህተት ታርሞ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የወግድ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 28616 ላይ በቀን 12/05/2012 ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ ፣የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 45606 ላይ በቀን 18/05/2012ዓ/ም የሰጠዉ ብይን እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-28591 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 07/04/2013ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የወግድ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የሚች አቶ አሊ ፈለቀ መሬት በቤተሰብ አባልነት አመልካች ይዘዉ ሊቀጥሉ የሚገባ ነዉ ወይስ ለወራሶች ሊተላለፍ ይገባል የሚለዉን ከአዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ከደንብ ቁጥር 51/1999 አንቀጽ 11/7 መስፈርቶችና ቅደም ተከተል አንጻር በመመርመርና እነዚህ ሕግጋት ካስቀመጡት መስፈርቶች ጋር በተያያዘ በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚገባ ፍሬ ነገር ካለም በማስረጃ በማጣራት ከላይ በፍርዱ ሀተታ ላይ የተጠቀሰዉን የሥነ ሥርዓት

ጥያቄ ከግምት በማስገባት ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 343/1 መሰረት መልሰንለታል፡፡

3. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭ የየራሳቸውን እንዲችሉ ተወስኗል፡፡

ት እ ዛ ዝ

1. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር የወረዳ ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ግራ ቀኙ ሲጠይቁም ግልባጩ ይሰጣቸው፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ እግድ ካለ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

??/? /??? 200492
?? 27/3/2014 ?/?

ተፈሪ ገብሩ /ዶ/ር/

ዳኞች ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች - አቶ እንዳለማው ተመስገን

የቀረበ የለም

ተጠሪ - አቶ ሀብታሙ መላኩ

ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር መዝገብ ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የቀረበው አመልካች ታህሳስ 26 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 89392 ታህሳስ 14 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 01-75094 ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የቁጭ ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 01-02393 ግንቦት 22 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ቅሬታውን በማቅረቡ ነው፡፡ ቅሬታውም አቤት የተባለበትን ውሣኔ፣ አመልካች የሚቃወምባቸውን ምክንያቶች የሚዘረዝርና በሰበር ሰሚው ችሎት በኩል ሊታይልኝ ይገባል የሚለውን ዳኝነት የሚጠይቅ ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ቀደም ብሎ ከአቶ በልስቲ ተመስገን ጋር ተከራክሬ ተጠሪ ወደ ክርክሩ መግባት ሲገባው ትቶ በፍርድ ባለቀ ጉዳይ በአዲስ ክስ ማቅረብ አይችልም፡፡ ይርጋን በተመለከተ መሬቱ ከመቼ ጀምሮ እጄ እንደገባ ታስቦ መወሰን ሲገባ የከሳሽ እድሜ ታይቶ መወሰኑ ተገቢ አይደለም፡፡ መሬቱ የኔ ስለመሆኑ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የምስክር ወረቀት አቅርቤ እያለ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

በስር ፍ/ቤት የነበረው ክርክር የጀመረው ከአብክመ. የቁጭ ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ባቀረበው ክስ ተከሳሽ የአሁን አመልካች የወላጅ አባቴን 45*50 የሆነ የመሬት ይዞታ ከ2007 ዓ/ም ጀምሮ የያዘብኝ በመሆኑ ይልቀቅልኝ ሲል ጠይቋል፡፡ ተከሳሽም በዚህ መሬት ላይ አቶ በልስቲ ተመስገን በመ/ቁጥር 00544 ከሶኝ የተወሰነልኝ ስለሆነ እና ከሳሽ በዛን ሰዓት ጣልቃ ገብቶ ያልተከራከረ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 5 መሰረት ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ፡፡ መሬቱ የከሳሽ አባት አይደለም፡፡ ይህን ይዞታ ከ1989 ዓ/ም ጀምሮ ይገፉ ስለምገኝ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው፡፡ ይዞታው በኔ ተመዝግቦ የሚገኝና የኔ መሬት በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በሚል መልስ ሰጥቷል፡፡ የቁጭ ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤትም በመ/ቁጥር 01-02393 ግንቦት 22 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ከሳሽ ጉዳዩ ካሁን በፊት ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነው ላለው ቀደም ብሎ በነበረው ክርክር የአሁኑ ከሳሽ ተከራካሪ ባለመሁኑ የከሳሽ ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 5 ውድቅ የሚሆን ባለመሆኑ የተከሳሽ ተቃውሞ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ይርጋን በተመለከተ የምስክር ቃልና አግባብነት ያለውን የህግ ድንጋጌዎችን ከግንዛቤ ውስጥ አስገብተን ተከሳሽ ያነሳው የ10 ዓመት ይርጋ ውድቅ ነው፡፡ በፍሬ ነገሩ ላይ የከሳሽ ምስክሮች ይህ ክስ የቀረበበት መሬት ለከሳሽ አባት የተደለደለ መሆኑን መስክረዋል፡፡ የተከሳሽ ምስክሮች መሬቱ ከ1989 ዓ/ም ጀምሮ በተከሳሽ እጅ ያለ መሆኑን መስክረዋል፡፡ ቀበሌው ይዞታው በ1996/97 ዓ/ም በአቶ መላኩ ተመስገን የተቆጠረ መሆኑን አጣርተው ገልፀዋል፡፡ የቡሬ ወረዳ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ጽ/ቤትም በ1989 ዓ/ም ለከሳሽ ወላጅ አባት የተደለደለ መሆኑን አጣርቶ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ይህ መሬት ለከሳሽ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ሊሰራለት ሲገባ ባልታወቀ ሁኔታ ለተከሳሽ የተሰራለት መሆኑ ታውቋል፡፡ ይዞታው የከሳሽ አባት መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ተከሳሽ ለከሳሽ መሬቱን ይልቀቅለት ሲል ወስኗል፡፡ ተከሳሽ ለምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቦ በመ/ቁጥር 01-75094 ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትእዛዝ የወረዳ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ስህተት የተፈተመበት ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት አያስቀርብም ሲል ይግባኙን ውድቅ አድርጎታል፡፡ ተከሳሽ የአሁን አመልካች ለአብክመ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ አከራክሮ በመ/ቁጥር 89392 ተህሳስ 14 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ የከፍተኛ እና የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካችም ይህን ውሳኔ በመቃወም ቀርቧል፡፡ መዝገቡም ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ያከራካሪው መሬት ባለቤትነት ደብተር ለአሁን አመልካች ተሰጥቶ ያለው ባልተሰረዘበት ሁኔታ ታልፎ መሬቱ የተጠሪ ነው የተባለበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ቀርቧል፡፡ መልስና የመልስ መልስም ተሰጥቶበታል፡፡ ተጠሪ ጥር 18 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳልተፈጸመበት በማንሳት ይጽናልኝ ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም የካቲት 10 ቀን 2013 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል፣ እኛም የቀረበውን አቤቱታ፣ መልስ እና የመልስ መልሱን እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔዎችን እና ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኙን ያከራከረው የመሬት ይዞታ በ1989 ዓ/ም ለአሁን ተጠሪ አባት የተደለደለ መሆኑንን፣ በ1996/97 ዓ/ም ለአሁን ተጠሪ አባት የተመዘገበ መሆኑን የወረዳ የመሬት አስተዳደርና አጣቃቀም ጽ/ቤት አጣርቶ ሪፖርት አድርጓል፡፡ የወረዳ የመሬት አስተዳደርና አጣቃቀም ጽ/ቤት ለአሁን አመልካች የመሬት ባለይዞታነት ማረጋገጫ የምስክር

ወረቀት የተሰራለት ባልታወቀ ሁኔታ መሆኑንና የመሬት ባለይዞታነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለአሁን አመልካች ሊሰራለት የማይገባ መሆኑንም ገልጿል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች በቀረበው ማስረጃ መሰረት አጣርተው ያከራከረው የመሬት ይዞታ የአሁን ተጠሪ መሆኑን ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የአሁን አመልካች ባከራከረው የመሬት ይዞታ ላይ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰራለት በህጉ አግባብ እንዳልሆነና ሊሰራለት የማይገባ መሆኑን፣ ይዞታውም ለአሁን አመልካች እንዳልሆነና የአሁን ተጠሪ ወላጅ አባት ይዞታ መሆኑ ተጣርቶ መወሰኑ ቅር የሚያሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 44634 ላይ በሰጠው ውሳኔ በፍ/ብሔር ክርክር አንድ መብት ወይም ግዴታ አለ ብሎ የሚከራከር ወገን መብቱ ወይም ግዴታው ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት ይገኛል፡፡ የአሁን አመልካች ያከራከረው የመሬት ይዞታ የሱ ስለመሆኑ ባላስረዳበት ሁኔታ ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያላው ሆኖ ያልተገኘ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ውሳኔ

1. የአማራ ብ/ክ/መ. ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 89392 ታህሳስ 14 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ፣ የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 01-75094 ግንቦት 29 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትእዛዝ እና የቁጭ ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 01-02393 ግንቦት 22 ቀን 2011 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔበፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ታህሳስ 28 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የቁጭ ንዑስ ወረዳ ፍ/ቤት የመ/ቁጥር 01-01393 ላይ የሰጠው የአፈጻጸም እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. በዚህ መዝገብ ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

4. የዚህ ውሳኔ ትክክለኛ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤት ይድረሳቸው ብለናል፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

ማ/አ የማይነበብ የአምሰት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

-የሰ.መ.ቁ.200482

ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡..... ወ/ሮ ሐቢባ ሸምሱ ስሩር - ቀርበዋል

ተጠሪ፡..... አቶ ቴዎድሮስ ገብሩ ብዛ- ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የፍቺ ክርክር የተጀመረዉ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች እና የአሁን ተጠሪ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.251802 ጥር 26 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበችዉ ክስ ከተጠሪ ጋር ግንቦት 12 ቀን 2001 ዓ.ም በግብጽ ሀገር ጋብቻ ፈጽመን አብረን ሲንኖር ህጻን ሊና ቴዎድሮስ የተባለችዉን ልጅ የወለድን ቢሆንም ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ግንኙነታችን ተቋርጦ በጋብቻ መቀጠል ስላልቻልን ጋብቻችን እንዲፈርስልን በማለት ዳኝነት ጠይቃለች፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ መልስ ከአመልካች ጋር ጋብቻ አልፈጸምንም፣ በጋብቻ ሰነዱ ላይም አልፈረምኩም፣ አመልካች ጋብቻ እንደሌላቸዉ ስለመሆኑ ማስረጃ ተሰጥቷል፤ በግብጽ አገር ጋብቻ የሚፈጸመዉ በፍ/ቤት ነዉ፤ ከአመልካች ጋር በነበረን የግብረ ስጋ ግንኙነት የተጠቀሰችዉን ልጅ ከመዉለዳችን ዉጭ በጋብቻም ሆነ ጋብቻ ሳይፈጽም እንደባልና

ሚስት አለመኖራቸዉን ገልጸዉ ጋብቻ በሌለበት የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በመስማት፣ ከሚመለከተዉ አካል በማጣራትና የቀረበዉን የሰነድ ማስረጃ በመመርመር ባሳለፈዉ ዉሳኔ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በግብጽ አገር ጋብቻ ስለመፈጸማቸዉ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ባለመረጋገጡ አመልካች የጋብቻ ፍቺ እንዲወሰን ያቀረበችዉ የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም፤ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የተፈጸመ ጋብቻ የለም፣ የሚሰጥ ፍቺ የለም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ጉዳይ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.254606 በ20/4/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ግራ ቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤትን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ታህሳስ 26 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ አመልካች እና ተጠሪ መንግስትን ተቃዉመን ከአገር ተሰደን ለብዙ ጊዜ እንደባልና ሚስት አብረን ሲንኖር ዕድሜዋ 10 ዓመት የሆናትን ልጅ ሊና ቴዎድሮስ የተወለደች ሲሆን በግብጽ አገር የጋብቻ ዉል ያደረግን ሲሆን እኛ በግብጽ አገር በስደት የሚንኖርና ሕጋዊ ነዋሪዎች ባልሆንበት በአገሪቱ በሕጋዊ መንገድ እንደሚኖር ዜጋ የጋብቻ ዉሉ በፍ/ቤት አልተመዘገበም በማለት የጋብቻ ዉል የለም በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ አመልካች ይህን ክርክር ለማስረዳት የሰዉ ምስክሮችን ቆጥረን እያለ የሥር ፍ/ቤቶች ምስክሮቹን ሊቀበሉን አልቻሉም፣ ተጠሪ የጋራ ሀብት ነዉ በማለት በአመልካች ስም ለኮንዶሚኒየም የተቆጠበዉን ገንዘብ ማሳገዱ ጋብቻ መኖሩን እያመነ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ ሳለ የሥር ፍ/ቤቶች ጋብቻ የለም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በዝርዝር አመልክታለች፡፡

ይህ ችሎት የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት ሚያዚያ 21 ቀን 2013 ዓ.ም በተጻፈ መልስ፡ አመልካች እና ተጠሪ በግብጽ አገር በስደተኞች ካምፕ ጋብቻ ስለመኖሩ የጋብቻ ሰነድ መፈረሙ ተረጋግጧል ይበሉ እንጂ ሰነዱ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ በኢፌዴሪ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ የገባ ስላልሆነ ሕጋዊ ሆኖ የቀረበ ሰነድ አይደለም ተቀባይነት የለዉም፤ የሥር ፍ/ቤት ከግራ ቀኙ ክርክር አንጻር የሰዉ ምስክሮችን መስማት እንደማያስፈልግ ስላመነበት ማለፉ ትክክል ነዉ፤ አመልካች ከተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት አብረን ኖረናል ያሉት በሥር ፍ/ቤት ያልተነሰ ክርክር ስለሆነ ተቀባይነት የለዉም፤ ለኮንዶሚኒየም የተቆጠበዉን ገንዘብ ያሳገድኩት የጋራ ሀብት ነዉ በሚል ሳይሆን በዚህ ክርክር ምክንያት ለሚደርስብኝ ወጪና ኪሳራ የሚወሰንልኝ ከሆነ ይህን ገንዘብ ለመዉሰድ እንዲችል ነዉ፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በአግባቡና ሕጋዊ ስለሆነ የቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ እንዲሆንልኝ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታዋን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ምላሽ የሚሻዉ ፣ይህ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት ነዉ ወይስ አይደለም?

ጉዳዩ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ህግን የሚመለከት ከሆነ ክርክሩን ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ያለዉ የትኛዉ ፍ/ቤት ነዉ? የሚሉት ነጥቦች መሆናቸዉን ተገንዝበናል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች ካቀረበችዉ ክርክር እና የሥር ፍ/ቤቶች በዉሳኔያቸዉ እንዳመለከቱት አመልካች ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ፈጽመናል የሚትለዉ በግብጽ አገር በስደተኞች ካምፕ መሆኑን ጠቅሳ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን ጋብቻቸዉን በምስክሮች ፊት አስፈጽሟል ያለችበትን የጋብቻ የምስክር ወረቀት የሰጠ መሆኑን እና ተጠሪም ይህን ሰነድ መፈረሙን በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የፎረንሲክ ምርመራ ክፍል መረጋገጡን ነዉ፡፡ ተጠሪ ግን ከአመልካች ጋር በግብጽ አገር ጋብቻ አለመፈጻቸዉን፣ በግብጽ አገር ተጋቢዎች ጋብቻ መፈጸም ያለባቸዉ በፍ/ቤት መሆኑን፣ የተባለዉ የጋብቻ ሰነድ አግባብነት ባለዉ ሕግ መሰረት በኢትዮጵያ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጦ ወደ አገር ያልገባ መሆኑንና ተቀባይነት ሊኖራዉ እንደማይገባ ገልጸ መከራከሩን መዝገቡ ያሳያል፡፡ በግራ ቀኙ መካከል ከሚነሳዉ የፍሬ ነገር እና የህግ ክርክር አንጻር ጉዳዩ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን [Private International Law] የሚመለከት ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

እንደሚታወቀዉ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ የዉጭ አካል ተካፋይ የሆነበትን የህግ ክርክር የሚመለከቱ መርሆዎችና ደንቦችን የሚያካተት ነዉ፡፡ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ ወይም የሕግ ግጭት [Conflict of laws] የሚመለከተዉ በተያዘዉ የህግ ክርክር የትኛዉ ሕግ ተፈጻሚነት እንዳላዉ እና የትኛዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን እንዳለዉ የሚወስኑ የህግ መርሆችን ነዉ፡፡ የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5 (1፣ ሀ) እና 11 (1፣ ሀ) መሰረት የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን በሚመለከቱ የፍትሕ ብሔር ጉዳዮችን ለማየት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን ይደነግጋል፡፡

በዚህ አግባብ አሁን የተያዘዉ ጉዳይ ሲታይ አመልካች ባቀረበችዉ ክርክር ከተጠሪ ጋር ጋብቻ ፈጽመናል ያለችዉ በግብጽ አገር በሚገኘዉ በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ካምፕ በከፍተኛ ኮሚሽንና በምስክሮች ፊት መሆኑን ገልጻ ተከራክራለች፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች ከተጠሪ ጋር አድርገናል የሚትለዉ ጋብቻ እንዲፈርስላት ክስ አቅርባ ዳኝነት የጠየቀችዉ በኢትዮጵያ ፍ/ቤት መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት ከግራ ቀኙ ክርክር አንጻር በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በግብጽ አገር በሚገኘዉ በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ካምፕ አመልካች ተፈጽሟል የሚትለዉ ጋብቻ በተመለከተ ሕጋዊ ጋብቻ ተፈጽሟል ለማለት የትኛዉ ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል? የሚለዉ ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገዉ ጉዳይ ሆኖ እናገኘለን፡፡ እንዲሁም በግራ ቀኙ መካከል በግብጽ አገር በሚገኘዉ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ካምፕ ተፈጽሟል የተባለዉ ጋብቻ፣ በሕግ አግባብ የተፈጸመ ጋብቻ ነዉ የሚባል ከሆነና ጋብቻቸዉ በፍቺ ዉሳኔ እንዲፈርስ የሚወሰን እንደሆነ የፍቺ ዉጤት በምን አግባብ ይታያል? የሚለዉ ነጥብ ሊነሳ እንደሚችል ሌላዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የግራ ቀኙን የጋብቻ ይፍረስልን ክርክር በተመለከተ ተፈጻሚነት ያለዉ ሕግ የትኛዉ ነዉ? የሚለዉን ነጥብ መወሰንን ይጠይቃል ማለት ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የግራ ቀኙ ክርክር የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ እናገኘለን፡፡ ይህ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት ከሆነ ደግሞ በኢትዮጵያ ዉስጥ የትኛዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን አለዉ? የሚለዉ አግባብነት ካለዉ ሕግ አንጻር ታይቶ ምላሽ ሊሰጥበት የሚገባዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 5 (1፣ ሀ) እና 11

(1፣ ሀ) መሰረት የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከቱ የፍትሕ ብሔር ጉዳዮችን የማየት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን ይደነጋገል፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤት አንድን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን አለዉ ወይስ የለዉም? የሚለዉን አስመልክቶ ተከራካሪ ወገኖች ከዚህ አንጻር የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ባያነሱም ፍ/ቤት በራሱ ተነሳሽነት በማንሳት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ ሊሰጥበት እንዲሚገባዉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.9 (1)፣ 231 (1፣ ለ)፣ 244 (3) እና 245 (2) ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ይህ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግ ጥያቄን የሚያስነሳ መሆኑን እና ጉዳዩን ለማየት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት መሆኑን በመገንዘብ የአሁን አመልካች ያቀረበችዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን ማቅረብ እንደሚችችል በማመልከት መወሰን ሲገባቸዉ ይህን ባለማድረግ ያሳለፉት ዉሳኔ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ሕጎች አንጻር ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ ለማየት የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረዉ ጉዳዩን አይቶ ያሳለፈዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ዉሳኔ ማረም ሲገባዉ በማጽናት የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ.251802 ጥር 26 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.254606 በ20/4/2013 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ይህ ጉዳይ የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት ስለሆነ ጉዳዩን ለማየት የመጀመሪያ ደረጃ የሥረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እንጂ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አይደለም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኞቸዉ ይህን ጉዳይ ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ከማቅረብ ይህ ዉሳኔ የሚከለክላቸዉ አይሆንም ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
6. ይህ ዉሳኔ ታህሳስ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ተነቧል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ማ/አ **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

የሰ.መ.ቁ.200480

ህዳር 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡....1. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

2. ቀነዓ ቂጣታ

3. ፈይሳ ወርቁ

4. ደጀኔ አያንሳ

5. ብርቅነሽ እሱባለዉ

አመልካች፡.....አቶ በድሩ አባገላን - ቀርበዋል

ተጠሪ፡..... የሚች አቶ አባድጋ አባጎጃም ወራሾች ወ/ሪት አልፋ አባድጋ አባጎጃም እና

አቶ ሀምዛ አባድጋ አባጎጃም- ወ/ት አልፍያ አግድጋ- ቀርበዋል

ይህ መዝገብ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍርድ

ይህ የእርሻ መሬት ክርክር የተጀመረዉ በየም ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ ነበር። ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.14976 በ1/9/2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት በማመልከታቸዉ ነዉ።

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ባቀረበዉ ክስ በሚች አባቴ አቶ አባገላን አባጊቤ እጅ ለ56 ዓመታት የቆየን ባህር ዛፍ ይዞታ ከዚህ ቀደም በመ.ቁ.09921 ላይ ባህር ዛፍ የሚች አባቴ ነዉ ተብሎ የተወሰነዉ የዉርስ ይዞታዬን በጉልበት ስለያዘብኝ የአሁን ተጠሪ ይዞታዉን እንዲለቅልኝ፣ የወደመዉን ንብረት ግምትና በክሱ ምክንያት የወጠዉን ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል።

የአሁን ተጠሪ በዚህ ክስ ላይ ባቀረበዉ መልስ አመልካች ይህ መሬት በመ.ቁ.09921 ላይ ተወስኖልኝ በንብረት ክፍፍል አግኝቻለሁኝ በማለት ያቀረበዉ ክርክር ሀሰት ነዉ፣ ይህን ይዞታ

ከደርግ መንግስት ጀምሮ ስንገብርበትና ለሶስት ዙር ያስለካን ስለሆነ ክሱ ዉድቅ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የወረዳዉ ፍ/ቤት የአመልካችን የሰዉ ምስክሮች በመስማት፣ ከሚመለከተዉ አካል በማጣራት ባሳለፈዉ ዉሳኔ ለክርክር መነሻ የሆነዉ የእርሻ መሬት የአሁን ተጠሪ አባት የአባጎጃም አባቂጤ መሆኑ እና በተጠሪ ወንድም በሚች አቶ አባጊዲ አባጎጃም ስም ግብር ሲገበር የቆየ መሆኑን በማስረጃ የተረጋገጠ ስለሆነ፣ በመ.ቁ.09921 ላይ የተሰጠዉ ዉሳኔ የአሁን አመልካች አባት ከተጠሪ አባት ጋር በይዞታዉ ላይ ባህር ዛፍ በጋራ ተክለዉ ሲጠቀሙበት ስለነበር አመልካች መሐመድ አባጊዲ ላይ ክስ አቅርቦ የተወሰነዉ ባህር ዛፍ እንጂ ይዞታዉ አይደለም፣ አሁን ባህር ዛፉ ሸጠዉ ገንዘቡነሰ የተካፈሉ ሆኖ ቦታዉ መንገድ ዳር ስለሆነ ጉቶዉ ደርቆ ተጠሪ እህል ዘርቶ የሚጠቀመዉ በመሆኑ፣ በመሆኑም የአሁን ተጠሪ ይዞታዉን ለአመልካች የሚለቅበት እና ካሳ የሚከፍልበት አግባብ የለም በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁን አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም በየደረጃዉ ላሉት የክልሉ ፍ/ቤቶች ቅሬታዉን ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቶቹ ቅሬታዉን በትዕዛዝ በመሰረዝ የሥር የወረዳዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ26/4/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ፡ የአመልካች አባት በ1954 ዓ.ም ባህር ዛፍ ተክሎ እስከ 2000 ዓ.ም ሲጠቀምበት የቆየዉና በመ.ቁ.09921 ላይ በተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረት በክፍፍል የባህር ዛፍ ይዞታ ለአመልካች ደርሶ እያለ እና ተጠሪ ይዞታዉን በጉልበት መያዙ ተረጋግጦ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ፣ በጉልበት የተቀመሁት ባህር ዛፍ እንዲመለስልኝ የተጨፈጨፈዉ ባህር ዛፍ ግምት እንዲጠይቅ እንዲወሰንልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ጉዳይ የሰጡት ዉሳኔ አስቀድሞ አመልካች በመ.ቁ.09921 ላይ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተከራክሮ ያስፈረደዉን ፍርድ በአግባቡ ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ሲባል የሰበር አቤቱታ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ባዘዘዉ መሰረት የተጠሪ ወራሾች ባቀረቡት መልስ የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ጉዳይ በማስረጃ በማጣራት የሰጡት ዉሳኔ ተገቢ ስለሆነ እንዲጸናልን ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክስ የጠየቀዉ ዳኝነት የመሬት ይዞታን የሚመለከት እና ተጠሪ ይህን መሬት በጉልበት ስለያዘብኝ እንዲለቅልኝ የሚል ነዉ፡፡ የአሁን ተጠሪ በዚህ ረገድ ባቀረቡት ክርክር ለክርክር መነሻ የሆነዉ ይዞታ የአመልካች አባት ይዞታ ሳይሆን የሚች አቶ አባጎጃም አባቂጤ መሆኑን ገለጸዉ ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መሰረት በማድረግ ፍሬ ነገር የማጣራት እና ማስረጃን የመስማት የመመርመርና የመመዘን በሕግ የተሰጠዉን ስልጣን መሰረት በማድረግ የሰዉ ምስክሮችን በመስማት ከሚመለከተዉ አካል ተጣርቶ እንዲቀርብ

በማድረግ ባሳለፈዉ ዉሳኔ ለክርክር መነሻ የሆነዉ የእርሻ መሬት የሥር ተከሳሽ አባት የአቶ አባጎጃም አባቂጤ መሆኑን እና በሥር ተከሳሽ ወንድም ስም ተገቢ የመንግስት ግብር ሲከፈል እንደነበር መረጋገጡን የሥር ፍ/ቤት የዉሳኔ ግልባጭ ያሳያል፡፡

በዚህ ይዞታ ላይ የሥር ተከሳሽ አባት አቶ አባጎጃም አባቂጤ እና የአሁን አመልካች አባት አባገላን አባጊቤ ባህር ዛፍ ተክለዉ ሲጠቀሙበት እንደነበር እና የአሁን አመልካች የዉርስ ይዞታን በተመለከተ በሌሎች ወራሾች ላይ ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ መሐመድ አባጊዲ ላይ አሁን ለክርክር መነሻ በሆነዉ ይዞታዉ ላይ ያለዉን ባህር ዛፍ በተመለከተ ክስ ማቅረቡን የመ.ቁ.09921 ላይ የተደረገዉ ክርክር ያመለክታል፡፡ የየም ልዩ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ.09921 ግራ ቀኙን በማከራከር በ15/6/2008 ዓ.ም ባሳለፈዉ ዉሳኔ አከራካሪዉን ባህር ዛፍ 7ኛ ተከሳሽ መሐመድ አባጊዲ ከአመልካች አባት ጋር የእኩል ነዉ በማለት መወሰኑን የዉሳኔዉ ግልባጭ ያሳያል፡፡ ከዚህ ዉሳኔ ይዘት መረዳት የሚቻለዉ ለአሁን አመልካች የተወሰነዉ ባህር ዛፍ እንጂ ባህር ዛፉ ያረፈበት ይዞታ እንዳልሆነ ነዉ፡፡

አሁን በተያዘዉ ክርክር ደግሞ የአመልካች አባት ባህር ዛፉን አብረዉ ከተከሉት ሰዉ ጋር ባህር ዛፍ ሸጠዉ ገንዘቡን የተካፈሉ መሆኑንና በአሁኑ ወቅት በይዞታዉ ላይ ጉቶዉ እንኳን ተነስቶ የሌለ መሆኑንና በመሬቱ ላይ እህል የተዘራ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ ይህ ማለት ለክርክር መነሻ በሆነዉ ይዞታ ላይ ቀድሞ የነበረዉ ባህር ዛፍ አሁን የሌለ እና ይዞታዉ ለእርሻ ሥራ እያዋለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ለአመልካች በመ.ቁ.09921 ላይ ተወስኖ የነበረው ባህር ዛፍ እንጂ የመሬት ይዞታ አይደለም፤ ባህር ዛፉም ቢሆን አሁን በይዞታዉ ላይ እንደሌላ የሥር ፍ/ቤቶች በማስረጃ አጣርተዉ ያረጋገጡት ጉዳይ ነዉ፡፡ አመልካች በኦሮሚያ ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 6 (1) መሰረት በዚህ ይዞታ ላይ የመሬት የባለይዞታነት መብት ያለዉ መሆኑን በሥር ፍ/ቤት የረጋገጠዉ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ ይህ ችሎት በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80 (3፣ ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 (1) መሰረት ከተሰጠዉ ስልጣን አንጻር የአሁን አመልካች ያቀረበዉ ቅሬታ የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት መፈጸማቸዉን የሚያመለክት ስላልሆነ ተቀባይነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ለክርክር ምክንያት የሆነዉን የገጠር መሬት ተጠሪ በጉልበት ስለያዘብኝ እንዲለቅልኝ በማለት ያቀረበዉን ክስ ዉድቅ በማድረግ ያሳለፉት ዉሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1. የደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.14976 በ1/9/2012 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
3. ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምሰት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መ/ቁ/200247

ሐምሌ 27 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ አቶ ታሪኩ ዮናስ

ተጠሪ ፡ ዳንኮቴ ኢትዮጵያ ሲምንቶ ፋብሪካ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ የስራ ክርክር የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን አደዓ በርጋ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን የአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን የተከራከሩበት ነዉ፡፡አመልካች 02/06/2012 ዓ.ም ባቀረበው ክስ ተጠሪ በሰው ኃይል አስተዳደር የሥራ ዘርፍ በደብዳቤ ቁጥር DI-HR-009-14 ሕዳር 24 ቀን 2007 ዓ.ም በወር ደመወዝ ብር 7,100 የቀጠረኝ ሲሆን የሥራ ብቃት ምዘናዬ ከፍተኛ ስለሆነ በተለያየ ጊዜ እድገት ሰጥቶኝ በመጨረሻ በወር ደመወዝ ብር 29,980.14 እየሰራዉ እያለ ታህሳስ 22 ቀን 2012 ዓ.ም ያለአንዳች ጥፋት ከስራዬ ስላሰናበተኝ በአዋጅ ቁ/1156/2011 መሰረት ወደ ስራዬ እንዲመልሰኝ ወይም ካልመለሰኝ የተለያዩ ክፍያዎች በድምሩ ብር 435,711.34 እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በቀን 12/06/2012 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ አመልካች ከፍተኛ የኦፊሰር ስራ ዘርፍ እና የድርጅታችን የሰው ኃይል መመሪያ ኃላፊ በመሆን ሲሰራ ቆይቷል፣ሃላፊነቱ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ሰው ደግሞ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 3(2ሐ) መሰረት በአሰሪና

ሰራተኛ አዋጅ መክሰስ ስለማይችል ክሱ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ እንዲሆን ጠይቋል፡፡

ፍ/ቤቱም የመጀመሪያ መቃወሚያ ላይ የግራ ቀኝ ክርክር በመስማት አመልካች የተቀጠሩበት የስራ ዘርፍ የድርጅቱን የዓመት ዕቅድና በጀት ማውጣት፣ መከታተል፣ የሚቆጣጠርና የሚያቀናብር እንደሆነ የጽሁፍ ማስረጃ የሚስገነዝብ ነው፣ የስራ ቅጥሩም የሚያሳየው በሥራ አስኪያጅነት የስራ ዘርፍ ላይ ተቀጥሮ እንዳለ ስለሚገልፅ ሥራ አስኪያጅ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 3(2)(ሐ) መሰረት በአሰሪና ሰራተኛ ክርክር የሚታይ አይደለም በማለት በብይን ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ አመልካች የአስተዳደር መመሪያ ኃላፊ ሥራ አስኪያጅ ሆኖ እያለ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ጠቅሶ መብቱን መጠየቁ አግባብነት የለውም በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

አመልካች ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል እንዲታረምልኝ በማለት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ አመልካች መጀመሪያ ሥራ አስኪያጅ መሆኑን አምኖ በክሱ ላይ ስለገለፀ ተጠሪው በታመነው ጉዳይ ላይ ማስረጃ ለማቅረብ አይገደድም፣አመልካች በፊት ከነበረበት የስራ ዘርፍ ወደ ሌላ ስራ ዘርፍ ተቀይሮ ከስራ መሰናበቱ ያቀረበው ማስረጃ የለም፣አመልካች በተመደበበት የሥራ ዘርፍ ላይ ደመወዝ ሲጨመርለት እንደቆየ ክሱ ያሳያል፣በተጨማሪም አመልካች ለተለያዩ መ/ቤቶች የፃፈዉ ደብዳቤ ስራ አስኪያጅ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፣ሥራ አስኪያጅ መሆን የግድ ሰራተኛ መቅጠርና በጥፋት ከስራ ማሰናበት ብቻ አይደለም፣ስለዚህ የስር ፍ/ቤት አመልካች ሥራ አስኪያጅ እንጂ ሠራተኛ አይደለም በማለት የደረሰበት አቋም የህግ ስህተት የለዉም በማለት አጽንቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ይዘት ባጭሩ መጀመሪያ በተሰጠኝ የስራ ቅጥር ደብዳቤ ስልጣን አልሰጠኝም እንጂ ቢሆንም እንኳ ተጠሪ ከስራ ሲያሰናብተኝ ከአስተዳደር የሥራ ዘርፍ ወደ ማህበራዊ ጉዳይ የስራ ዘርፍ(corporate social responsibility officer) ሚባል ቀይሮኛል፣ በዚህ ስራ ዘርፍ ደግሞ የሚቆጣጠረው፣ የሚቀጥረው፣የማያስተዳድረው ወይም የምወስደው የስነ ምግባር እርምጃ የለም፣በመጀመሪያ የስራ ዘርፍም የዓመት ስራ ዕቅድ እንዳወጣ፣ የዓመት በጀት እንዲመድብም ሆነ ሰራተኛ

ለመቅጠሪም ሆነ ለማባረር ስልጣን አልተሰጠኝም፣በሥራ አስኪያጅነት የፈረምኩት የፅሁፍ ማስረጃም አልቀረበም፣የስራ ደረጃዬም 9ኛ እርከን ሲሆን፣ ታህሳስ 1 ቀን 2018 እ.ኤ.አ ሥራ ላይ በዋለው የድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ደግሞ ሥራ አስኪያጅ የሚባለው የሥራ ደረጃው ከእርከን 12 በላይ ከ13 አስከ 17ኛ እንደሆነ በስር ፍ/ቤት እየተከራከርኩ በማስረጃ ሳያጣራ በግምት አመልካች ሥራ አስኪያጅ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ አመልካች ሰራተኛ ነዉ ተብሎ ውሳኔ እንዲሰጥ በማለት አመልክቷል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች የሥራ መሪ ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሳኔ ስለ ስራ መሪ በህጉ የተመለከቱትን ዝርዝር ድንጋጌዎችን ያገናዘበ መሆኑን አለመሆኑን ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ ያቀረበው መልስ ባጭሩ አመልካች በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በከፍተኛ የሰው ሀብት ኦፊሰር ስራ መደብ ላይ ተቀጥሮ ሲሰራ የቆየ መሆኑን ለስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ ላይ ገልፀዋል፣ በዚህ ስራ መደብ ላይ ተቀጥሮ የሚሰራ ሰው ደግሞ የአመራር ስራ በመሆኑ የዓመት ስራ ዕቅድ ማውጣት፣ አስፈላጊውን በጀት መመደብ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ መደገፍና ማቀናጀት እንደሆነ መጋቢት 2011ዓ.ም በተፈረመው መመሪያ ተገልፀዋል፣ አመልካች በተጨባጭ ይህንን ሲሰራ ቆይቷል፣ይህም በተለያየ ጊዜ አመልካች ሲጽፍ ከነበረው ደብደዳቤ መረዳት ይቻላል፣አመልካች በማስረጃ አልተደገፈም የሚለው ሀሰት ነው፣በስር ፍ/ቤት ባቀረብነው መልስ ላይ ማስረጃ በዝርዝር አያይዘን በማቅረብ አመልካች የስራ መሪ መሆኑን አስረድተናል፣ስለዚህ አመልካች የሥራ መሪ ነው መባሉ የህግ ስህተት የለውም፡፡አመልካች ከስራ ሲሰናበት የስራ መደቤ ተቀይሯል የሚለው በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣የሥራ መደቡ ቢቀየርም እንኳ የስራ መደቡ ተመሳሳይ የአመራር መደብ ነው፣ አመልካች በመተዳደሪያ ደንብ ታህሳስ 01/2018 መሰረት ሥራ አስኪያጅ ከእርከን 12 በላይ ነው የሚለው፣አመልካች ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ስለተቀጠረ ደንቡ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሰራም፣ ደንቡ ተፈፃሚ ይሆናል ቢባል እንኳ ይህንን ክርክር በስር ፍ/ቤት አንስቶ አልተከራከረም፣ስለዚህ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 329 መሰረት ክርክሩ ውድቅ ተደርጎ የስር ውሳኔ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች በመልስ መልሱ ላይ አሁን የተነሱት ክርክሮች በስር ፍርድ ቤት የተነሱ ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ብይን ያሳያል በሚል አቤቱታዉን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የሥራ ዉል ግንኙነት እንደነበር አላከራከረም፡፡አከራካሪዉ ጉዳይ አመልካች ከስራ ሲሰናበት ሲሰራ የነበረዉ የሥራ መሪ የሥራ መደብ ላይ ነዉ ወይሥ አይደለም የሚለዉ ነዉ፡፡

በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 10/2/ እንደተመለከተዉ የሥራ መሪ ማለት በህግ ወይም እንደድርጅቱ የሥራ ጠባይ በአሰሪዉ በተሰጠዉ የዉክልና ስልጣን መሰረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማዉጣትና የማስፈጸም ስልጣን ያለዉ ወይም ሰራተኛን የመቅጠር፤የማዘዋወር፤የማገድ፤የማሰናበት ወይም የመመደብ ተግባሮችን የመወሰን ስልጣን ያለዉ ግለሰብ ሲሆን፤እነዚህ የሥራ አመራር ጉዳዮችን አስመልክቶ የአሰሪዉን ጥቅም ለመጠበቅ አሰሪዉ ሊወስደዉ ስለሚገባዉ እርምጃ በማንም ሳይመራ የራሱን የዉሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የህግ አግልግሎት ሃላፊን ይጨምራል፡፡ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ አንድን ሰራተኛ የሥራ መሪ የሚያሰኘዉ ተግባር ሁሉንም በዝርዝር የተገለጹ ተግባራትን የማከናዉን አለማከናወን ጉዳይ ሳይሆን እንደድርጅቱ የሥራ ጠባይ የሥራ አመራር ስራ ተብለዉ የተለዩ ተግባራትን እንዲፈጽም ሃላፊነት የተሰጠዉ መሆን አለመሆኑን የመለየት ጉዳይ ነዉ፡፡ስለዚህም አንድ ሰራተኛ የድርጅቱ የሥራ መሪ ነዉ ወይሥ አይደለም የሚለዉን ለመወሰን ከድርጅቱ የሥራ ባሕርይ አንጻር የተሰጠዉ ሃላፊነትና ተግባር መታወቅ አለበት፡፡

በተያዘዉም ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች የስራ መሪ ነዉ ከሚል ድምዳሜ ላይ የደረሱት በድርጅቱ የሥራ ጠባይ የተሰጠዉ ሃላፊነት በከፍተኛ የሰው ሀብት ኦፊሰር ስራ መደብ የዓመት ስራ ዕቅድ ማውጣት፣ አስፈላጊውን በጀት መመደብ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ መደገፍና ማቀናጀት በተጨባጭ ሲሰራ ቆይቷል በማለት ነዉ፡፡

አመልካች የሥራ መሪ አይደለሁም ብሎ የሚከራካረዉ ሁለት ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ክርክሩ ያሣያል፡፡አንደኛዉ ምክንያት የተቀጠረበት የሥራ ዘርፍ የሥራ መሪ የሚያሠኝ ነዉ ቢባል እንኳን በተጨባጭ ሰራተኛ መቅጠር፣ ማሰናበት እና የዲስፕሊን እርምጃ መዉሰድ ስልጣን አልነበረኝም ስለዚህም የሥራ መሪ አይደለሁም የሚል ሲሆን ሁለተኛዉ ምክንያት ቀደም ሲል የነበረበት የሥራ መደብ የሥራ መሪ ነዉ የሚባል ቢሆን እንኳን ከስራ ሲሰናበት የስራ መደቡ ተለዉጧል በማለት ነዉ፡፡እነዚህ የፍሬ ነገር ክርክሮች በስር ፍርድ ቤት የተነሱ ጉዳዮች ስለመሆኑ መዝገቡ ያሣያል፡፡የመከራከሪያ ነጥቦቹን አግባብነት በቅደም

ተከተል እንመለከታለን፡፡ የመጀመሪያዉ ነጥብ አመልካች ሲሰራ የነበረበት የሥራ መደብ የሥራ መሪ የሚያሰኘዉ ነዉ ወይሥ አይደለም የሚለዉን በሚመለከት ማስረጃ በመመዘን የክርክሩን ፍሬነገር የማጣራት ሃላፊነት የተሰጣቸዉ የሥር ፍርድ ቤቶች እንዳረጋገጡት አመልካች ከፍተኛ አፍሰር የሥራ ዘርፍ /HCM and Administration/ ሆኖ ሲሰራ የዓመት ስራ እቅድና አስፈላጊ በጀት ማዉጣት፣መቆጣጠር፣መከታተልና መደገፍ ሲሰራ እንደነበር የተረጋገጠ ፍሬነገር ጉዳይ ነዉ፡፡የድርጅቱን የበጀት ጉዳዮች ማቅድና ማስፈጸም ስራ በማናቸዉም ሰራተኛ የሚከናወን መደበኛ ስራ ሳይሆን የሥራ አመራር ስራ ስለመሆኑ አዋጁ ስለስራ መሪ ከሰጠዉ ትርጉም መገንዘብ ይቻላል፡፡ይህን የሚያሣየዉ አመልካች በድርጅቱ የስራ አመራር ተግባር ሲያከናዉን የነበረ መሆኑን ነዉ፡፡በእርግጥ የድርጅቱ የሰዉ ሃይል መምሪያ ሃላፊ ሆኖ ሲሰራ እንደነበር እንጂ የሰዉ ሃይል በመቅጠር፣በማስተዳደርና የዲስፕሊን እርምጃ በመዉሰድ ረገድ ያከናወነዉ ተግባር ስለመኖሩ በማስረጃ አልተረጋገጠም፡፡ይሁንና አመልካች ሌሎች የድርጅቱን የሥራ አመራር ተግባራት ሲሰራ እንደነበር ከተረጋገጠ ሰራተኛ ቅጥር እና አስተዳደራዊ ተግባራት አለመስራቱ ብቻዉን የሥራ መሪ ከመባል የሚያሥቀር አለመሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነዉ፡፡ምክንያቱም ከላይ እንደተገለጸዉ የህጉ ይዘት ሲታይ ሰራተኛን የመቆጣጠር ጉዳይ በተጨማሪነት ወይም ራሱን ችሎ የሚቆም የሥራ አመራር ተግባርና ሃላፊነት መለያ ሆኖ ሊወሰድ እንደሚችል አመልካች በመሆኑ ነዉ፡፡የአዋጁን አንቀጽ 3/1/ሐ ይመለከታል፡፡በመሆኑም የመጀመሪያዉ የክርክር ምክንያት በስር ፍርድ ቤቶች ዉድቅ መደረጉ ስህተት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የቀረበዉ መከራከሪያ አመልካች ከስራ ሲሰናበት የሥራ መደቡ ማህበራዊ ጉዳይ የስራ ዘርፍ(corporate social responsibility officer) የሚለዉ ላይ እንደነበር እና ይህ የሥራ ዘርፍ የስራ አመራር የሥራ ዘርፍ አለመሆኑን ገልጾ ስለመከራከሩ መዝገቡ ያሣያል፡፡በዚህ ረገድ በተጠሪ በኩል የቀረበዉ ክርክር የሃላፊነት ደረጃዉ ተመሳሳይ ነዉ የሚል ነዉ፡፡ይሁንና የሥር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ አከራካሪ ጉዳይ በጭብጥነት ይዘዉ በማስረጃ አጣርተዉ እና ከድርጅቱ የሥራ ደንብ ጋር አገናዝበዉ ያረጋገጡት ፍሬነገር ባለመኖሩ የሥራ መደቡ መለወጥ የሥራ ሃላፊነቱ ላይ ያስከተለዉን ለዉጥ ምንድነዉ የሚለዉንና ህጋዊ ዉጤቱን በዚህ ሰበር ችሎት ለመወሰን የሚቻል ሆኖ አላገኘንም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበዉን ፍሬነገር ክርክር የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ አጣርቶ እንዲወሰን ማድረግ ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

ዉሳኔ

1ኛ/የአደኣ በርጋ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ/41550 ላይ በ10/07/2012ዓ.ም የሰተዉ ብይን እና ይህንኑ በማጽናት የም/ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንደቅደም ተከተላቸዉ በመ/ቁ/31966 እና በመ/ቁ/333425 ላይ የሰጡት ዉሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ተሽሯል፡፡

2ኛ/አመልካች ከስራ ሲሰናበት የሥራ ዘርፍ ለዉጥ ተደርጓል ወይሥ አልተደረገም?ለዉጥ ተደርጓል ከተባለ የተመደበበት የሥራ ዘርፍ የሥራ መሪ ነዉ ወይሥ አይደለም የሚለዉን በማስረጃ በማጣራት ተገቢዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት በማለት መዝገቡን በፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 343/1/ መሰረት ለአድኣ በርጋ ወረዳ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡ይጻፍ፡፡

3ኛ/ በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ



በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ. 200178
ቀን ፡- ሐምሌ 28 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ወ/ሮ ህብስት ምሕረቱ፡- ጠበቃ ባንታምላክ ብናልፍ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ገቢዎች ቢሮ፡- ዐ/ህግ ማዘንጊያ ደምሴ ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ሠራተኛ የነበሩ ሲሆን በወንጀል ተጠርጥረውና ተከሰው የነበረ ሲሆን በኋላም ከወንጀል ክሱ በፍርድ ቤት በነጻ በመሰናበታቸው ወደሥራ ለመመለስ አመልክተዋል፡፡ መሥሪያ ቤቱ በሰው ኃይል አስተዳደር ደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 41 መሠረት በወንጀል ተጠርጥሮ ሥልጣን ባለው አካል በእስር ላይ የነበረና እስከ ሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ከወንጀል ነጻ መሆኑ ተረጋግጦ ወደሥራ ካልተመለሰ አገልግሎቱ ይቋረጣል በሚል በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑና አመልካች በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን ያላቀረቡ በመሆኑ ተቀብለን መድበን ለማሰራት አንችልም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጓል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት የአማራ ክልል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የአስተዳደር ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ የአማራ ክልል የተሻሻለው የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 253/2010 አንቀጽ 85(3) መሠረት ከወንጀል ክስ ነጻ የተባለ ሠራተኛ ወደሥራ የሚመለስበትን የጊዜ ገደብ አያስቀምጥም፡፡ ደንብ ቁጥር 79/2003 አዋጁን ሊጻረር አይችልም፡፡ አመልካች ወደሥራ ሊመለሱ ይገባል

በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የአማራ ክልል የገቢዎች አዋጅ ቁጥር 168/2002 ተከትሎ በወጣው ደንብ ቁጥር 79/2003 መሠረት ተጠሪ ሠራተኞቹን ያስተዳድራል፡፡ በደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 44(1) መሠረት የመንግስት ሠራተኞች አዋጅና ተያያዥ ሕጎች በደንቡ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ብቻ ተፈጻሚ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ በወንጀል የታሰረ ሠራተኛን አስመልክቶ ስለሚመለስበት ሁኔታ በደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 41 ላይ ስለተሸፈነ በዚህ ጉዳይ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ተፈጻሚነት የለውም፡፡ መመሪያ ቁጥር 1/2011 ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በሥራ ቦታ አለመገኘትን አስመልክቶ ገቢዎች ቢሮ ያወጣው መመሪያ በወንጀል ተጠርጥሮ ታስሮ ነጻ የተባለን ሠራተኛ የሚመለከት አይደለም፡፡ አመልካች በሦስት ወር ውስጥ ከወንጀል ክሱ ነጻ መባላቸውን አረጋግጠው ወደሥራ ለመመለስ ያላመለከቱ በመሆኑ በደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 41 መሠረት ወደሥራ ሊመለሱ አይገባም በማለት የአስተዳደር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ሽሯል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎት የአመልካችን የሠበር አቤቱታ ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም በወንጀል ነጻ የተባለ ሰው እንኳን ቀድሞ የነበረውን ሕጋዊ መብት ቀርቶ አላግባብ ለታሰርኩበት ካሣ ከመጠየቅ ሕጉ አይከለክልም፡፡ ደንብ ቁጥር 79/2003 በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 253/2010 ተሽሯል፡፡ አዋጅ ቁጥር 253/2020 አንቀጽ 85(3) ታስሮ ከስድስት ወር ጊዜ በላይ የቆየ ሠራተኛ እንኳን በፍርድ ቤት ነጻ ከተባለ ወደሥራ መመለስ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ደንብ ቁጥር 79/2003 ተፈጻሚ ነው ቢባል እንኳን በመመሪያ ቁጥር 1/2011 እስር ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ከወንጀል ክሱ በነጻ እንደተባልኩ ወደሥራ ለመመለስ ስለጠየቅሁ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎኝ ወደሥራ እንድመለስ ሊወሰን ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ አመልካች ከሥራ ቦታ ያልተገኙት በእስር ምክንያት ከአቅማቸው በላይ በሆነ ምክንያት ከመሆኑ አኳያ ወደሥራ ሊመለሱ አይገባም መባሉ ከአዋጅ ቁጥር 253/2010 ድንጋጌዎችን ያገናዘበ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ የሠጠው መልስ የሰበር አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜው አልፏል፡፡ ተጠሪ ሠራተኞችን የሚያስተዳድረው ከሲቪል ሰርቪስ ሕጉ ውጭ በተለየ ደንብ ቁጥር 79/2003 ነው፡፡ አመልካች ስድስት ወር በላይ ታስረዋል፡፡ በደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 41 መሠረት የታሰረ ሠራተኛ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ነጻ መሆኑን አረጋግጦ ካልተመለሰ አገልግሎቱ እንደሚቋረጥ ተደንግጓል፡፡ መመሪያ ቁጥር 1/2011 አንቀጽ 7 ላይ በደንቡ መሠረት አገልግሎቱ የተቋረጠ ወይም የተፈረደበት ሠራተኛ ወደስራ ለመመለስ የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው የሚገልጽ በመሆኑ አመልካች ወደሥራ ሊመለሱ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል ብሏል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቀረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም አመልካች ወደሥራ ሊመለሱ አይገባም መባሉ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን? የሚለውን በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ሠራተኛ የነበሩ ሲሆን በወንጀል ተጠርጥረውና ተከሰው የነበረ ሲሆን በኋላም ከወንጀል ክሱ በፍርድ ቤት በነጻ በመሰናበታቸው ወደሥራ ለመመለስ አመልክተዋል፡፡ አመልካች ለክርክር መሠረት ያደረጉት የአማራ ክልል የተሻሻለው የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 253/2010 አንቀጽ 85(2) በተመለከተው መሠረት የታሰረ ሠራተኛ የሥራ መደቡ እስከ ስድስት ወር ጊዜ ድረስ ክፍት ሆኖ እንደሚጠብቀውና በንዑስ ቁጥር ሦስት ላይ ደግሞ ከወንጀሉ ነጻ ተብሎ ከስድስት ወር በኋላ ከመጣ ባለው ክፍት የሥራ መደብ እንደሚመደብ የሚገልጸውን በመያዝ ነው፡፡ በሌላ በኩል የተጠሪ የክርክር መሠረት የአማራ ክልል ገቢዎች ቢሮ ሠራተኞችን የሚያስተዳድረው በአዋጅ ቁጥር 253/2010 ሳይሆን በተለየ ሕግ በመሆኑና ሠራተኞች የሚተዳደሩበት ደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 41 ላይ ከሦስት ወር በላይ የታሰረ ሠራተኛ አገልግሎቱ ይቋረጣል ስለሚል አመልካች ከሦስት ወር በበለጠ ጊዜ ታስረው የቆዩ በመሆኑ ወደሥራ ሊመለሱ አይገባም የሚል ነው፡፡ ይሕም ጉዳዩ የሚገዛበት ሕግ ላይ የክርክር ልዩነት ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡

በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 171/2002 ሆነ ይህን አዋጅ የሻረው አዋጅ ቁጥር 253/2010 የተፈጻሚነት ወሰኑ በአንቀጽ 4 እንደተመለከተው በመንግስት መሥሪያ ቤትና በመንግስት ሠራተኞች ላይ ነው፡፡ በመርሕ ደረጃ ማንኛውም የክልሉ የመንግስተ ሠራተኛ የሚተዳደረው በዚሁ ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ሕግ አውጪው ሲፈቅድና በተለየ ሕግ ሲደነግግ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞቻቸውን በተለየ ሕግ ሊያስተዳድሩ ይችላሉ፡፡ የአማራ ክልል የገቢዎች ባለስልጣን ተግባራትን እንደገና ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 168/2002 አንቀጽ 14 እና 8(1) መሠረት መሥሪያ ቤቱ ሠራተኞቹን በአዋጁና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሠረት እንደሚያስተዳድር ተመልክቷል፡፡ ይህን ተከትሎም ደንብ ቁጥር 79/2003 የተደነገገ ሲሆን ሠራተኞቹን የሚተዳደሩበትን ዝርዝር ድንጋጌዎች ይዟል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ መሥሪያ ቤት ሠራተኞችን የሚያስተዳድረው በተለየ ሕግ ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በደንቡ አንቀጽ 44(1) ላይ የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ተፈጻሚነቱ በደንቡ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡

በደንብ ቁጥር 79/2003 አንቀጽ 41 ላይ አንድ የባለስልጣኑ ሠራተኛ በወንጀል ተጠርጥሮ ሥልጣን ባለው አካል በእስር ላይ ከዋለና እስከ ሦስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ከወንጀሉ ነጻ መሆኑ ተረጋግጦ ወደሥራው ካልተመለሰ አገልግሎቱ ይቋረጣል ሲል ይደነግጋል፡፡ ድንጋጌው በአንድ በኩል ወንጀል ያልፈጸመ ሠራተኛ የሥራ መደቡ ምን ያህል ጊዜ ክፍት ሆኖ እንደሚጠብቀው የተመለከተ ሲሆን በሌላ በኩል መሥሪያ ቤቱ ከምን ያህል ጊዜ በላይ የሥራ መደቡን ክፍት አድርጎ ሠራተኛ ሳይቀጥረበት ሥራውን ማስቀጠል ይችላል የሚለው ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ይሕም የሠራተኛው መብትና ጥቅም እና በሕዝብ/መንግስት ጥቅም መካከል ሁለቱን ጥቅሞች ለማስታረቅ ታስቦ መቀረጹን ያሳያል፡፡ አመልካች በሕጉ እንደተመለከተው በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ከወንጀሉ ነጻ ተብለው ወደመሥሪያ ቤቱ ያላመለከቱ በመሆኑ የሥራ አገልግሎታቸው ተቋርጧል፡፡ አመልካች መመሪያ ቁጥር 1/2011 ጠቅሰው ጉዳዩ ለአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ መመሪያው ሊያስፈጽም የወጣው ደንብ ቁጥር 79/2003 ሲሆን በደንቡ ስለታሰረ ሠራተኛ ግልጽ ድንጋጌ ያለ በመሆኑ ለጉዳዩ መመሪያው ተፈጻሚነት የለውም ተብሎ ክርክሩ በሥር ፍርድ ቤት

ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው። በአጠቃላይ ተጠሪ ሠራተኞቹን በሚስተዳድረበት ሕግ መሠረት አመልካችን ወደሥራ የሚመልስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል።

ውሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 97087 ግንቦት 27 ቀን 2012 ዓ/ም እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 52577 ታህሳስ 14 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል።

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ።
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ.200144

ቀን፡- 02/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ እማሆይ አዛል አይናለም

ተጠሪ፡ አቶ ምህረት በላይ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የስጦታ ውል እንዲፈርስ የቀረበ ክስ የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን ቡሬ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን የአሁኑ ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ እንዲሁም የቡሬ ወረዳ መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ጽ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የአመልካች ክስ ይዘት ባጭሩ ለተጠሪ ያደረግሁለት የሥጦታ ውል በመንፈስ ልልነት እና በዕድሜ የገፋሁ አቅመ ደካማ በመሆኔ ምክንያት ከፈቃዴ ውጭ ህጉን ሳይከተል ያደረግሁት በመሆኑ እና በስር 2ኛ ተከሳሽ ከአሁኑ ተጠሪ ጋር በመመሳጠር የስጦታ ውሉን ያፀደቀ በመሆኑ የስጦታ ውሉ ይፍረስልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ አመልካች በፈቃዷ ስጦታውን ያደረገችለት መሆኑን እና ክሱ የቀረበው የአመልካች ልጆች ከቅን ልቦና ውጭ በሆነ ሁኔታ መሬቱን ለመውሰድ በማሰብ ነዉ፤የስጦታ ውሉ የሚፈርስበት የህግ ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡የስር 2ኛ ተከሳሽም አመልካች

የራሷን ይዞታ በሙሉ ፈቃዷና ፍላጎቷ በወቅቱ በነበሩ ሽማግሎችና የመሬት ባለሙያዎች ባለበት ግልጽ የስጦታ ውል በህጉ መሰረት የተደረገ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት መልስ መስጠቱን መዝግቡ ያሣያል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ክርክርና ማስረጃ መርምሮ አመልካች በቀን 24/06/2005 ዓ.ም በቀበሌ ጽ/ቤት የመሬት ስጦታ ውል ላይ መፈረሟን አልካደችም፣የስጦታ ውሉ በሙሉ ፍላጎት ማመልከቻ አቅርባ እንዲታሰብበት ተደርጎ በቀበሌውም ማስታወቂያ ተለጥፎ ዉሉ የተፈፀመ መሆኑን በተጠሪ ምስክሮች በተገቢው ሁኔታ ተረጋግጧል፣ የአመልካች ምስክሮች ግን ስለስጦታ ውሉ የሚያውቁት የሌለ በመሆኑ ክሱን ማስረዳት አልቻሉም፣ስለዚህ አመልካች ስጦታ ያደረገችዉ በሙሉ ፍላጎቷና ፍቃዷ መሆኑን እንዲሁም የስር 2ኛ ተከሳሽም ስጦታውን ተቀብሎ ያፀደቀው በህጉ አግባብ በመሆኑ የስጦታ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምዕ/ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርባ ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኝ ክርክር መርምሮ የተጠሪ ምስክሮች የቀበሌ መሬት አስተዳደር ኮሚቴ የሆኑት አመልካች ለተጠሪ መሬት ለመስጠት ፍላጎት ኖሯት ያቀረበችው ማመልከቻ እንደሌለ እና መሬቱ ባለበት ቦታ ያጣሩት ነገር እንደሌለ ገልፀው በተለይ 1ኛ ምስክር ተጠሪ ስጦታ ልትሰጠኝ ነው ብሎ ወረቀት ይዞ መጥቶ አመልካች አብራ ካልመጣች በሚል እንደመለሰው እና በዛው ሳይመጣ እንደቀረ የሰጠዉ ቃል እንዲሁም ተጠሪ የሚጠበቅበትን ቢያንስ 3(ሶስት) ዓመት አመልካችን ስለመጦሩ ማረጋገጫ ሳይቀርብ እና የወረዳው መሬት አስተዳደር ተጠሪ ያቀረቡት ማመልከቻ ላይ ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ የለጠፈው ማስታወቂያ ማግኘት እንዳልቻሉ የገለፁ በመሆኑ የተደረገው የስጦታ ውል ህግና መመሪያውን ተከትሎ የተፈፀመ ነው ለማለት የሚያስችል ባለመሆኑ ስጦታው ሊሻር ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሯል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኝ ክርክር መርምሮ የአመልካች ምስክሮች ስጦታ ሲደረግ እንደማያውቁ መናገራቸዉን፣ስጦታ ሲደረግ የነበሩት የተጠሪ ምስክሮች ቃል የሚያስተባብል ባለመሆኑ በህጉ የተቀመጠውን መስፈርት በማሟላት ስጦታ ተደርጓል የተባለው አነጋገር የተሻለ ተቀባይነት ያለው ነው፣ ተጠሪ የህጉን መስፈርት አሟልቶ ስጦታ ተጠቃሚ ከሆነ በኋላ ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች አግባብ ባለው አካል አለመገኘታቸው ስጦታውን ሊያፈርስበት የሚገባ አይደለም፣ የመጦር ግዴታ የከፍተኛ ፍ/ቤት በራሱ አንስቶ የሰጠው

ዳኝነት ሲታይ አግባብ ሆኖ አልተገኘም በማለት የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በመሻር የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ይህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ይታረምልኝ በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ላይ ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኝ ክርክር መርምሮ የስጦታ ውሉ በመስፈርት ረገድ ጉድለት ያለበት አይደለም፤አመልካች ስጦታውን ለማድረግ ያመለከቱችበት ማመልከቻ እና ቃለጉባኤ ማግኘት ባይቻልም አመልካች በወረዳው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርባ ስጦታውን ያደረገች መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ እና ውሉ በማጭበርበር ወይም ከአመልካች ፈቃድ ውጭ በሆነ ሁኔታ ስለመፈፀሙ በማስረጃ እስካልተረጋገጠ ድረስ የስጦታ ውሉ የሚፈርስበት ሁኔታ የለም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች አቤቱታ ይዘት ባጭሩ ሲታይ፤ የስጦታ ውሉ የመሬት አስተዳደር ደንብ ቁ.51/99 እና የአፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 12/7/ ላይ የተመለከተውን ሂደት ሳይከተል፣የፍ/ህ/ቁ 881 መሰረት ስጦታው የግልጽ ኑዛዜ ስርዓትን ያልተከተለ በመሆኑ በፍ/ህ/ቁ 2443 መሰረት ተቀባይነት የሌለው እና በስጦታ ቅጽ ላይ ተጎትቼ እንዲፈርም ተደርጎ የአንድ ዓመት ቆይታ ጠብቆ ሳይመዘገብ ለስጦታ ተቀባይ ማረጋገጫ ደብተር መስጠቱ እየታወቀ ውሉ የጸና ነው ሲል ውሳኔ መስጠቱ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የስጦታ ውሉ እንዲፈርስ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የአሁኑ አመልካች መሬት በስጦታ ለተጠሪ ለመስጠት ለሚመለከተው አካል ማመልከቻ ባልሰጡበት እንዲሁም ተጠሪ የመጦር ግዴታ መወጣቱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የስጦታ ውሉ ሕጋዊ ነው ሊፈርስ አይገባም ተብሎ በስር ፍ/ቤት የተወሰነበትን አግባብ ከፍ/ሕ/ቁ 881 እና 2443 እንዲሁም ከክልሉ ገጠር መሬት አዋጅ ጋር በማገናዘብ መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ ያቀረበው መልስ ባጭሩ አመልካች በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ተጠሪ በማባበልና በማስፈራራት ያለፈቃዴና ፍላጎቴ ወደ ቢሮ ወስዶኝ እጄን ጎትቶ ያስፈረመኝና ስጦታውም የጸደቀ ስለሆነ ውሉ ይፍርስልኝ የሚል እንጂ ተጠሪ ግዴታውን አልተወጣም ወይም አበል ከለከኝ አልተባለም፣ስለዚህ ግዴታውን አልተወጣም የሚል በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ስለሆነ አጣሪ ችሎቱ የመጦር ግዴታውን መወጣት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የሚለው ጭብጥ

ተቀባይነት የለውም፤አመልካች በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት የእርሷ ቤተሰብ አባል በመሆን ከ3 አመት በላይ በነፃ ሳገለግልና ስጦር እንደቆየሁ በግልጽ በማመን የስጦታ ውሉ እንዲደረግ በማመልከቻ ጠይቃ የተደረገ መሆኑ በአዋዋይ ሽማግሌዎች በመረጋገጡ፤ የስጦታ ውል በህግ የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልቶ የተደረገ መሆኑ ተረጋግጦና ተመዝግቦ ውሉ ፀድቆ የባለይዞታነት መብት በተጠሪ ስም የተላለፈ ስለመሆኑ አዋዋይ ሽማግሌ በሆኑት ምስክሮችና በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘበንዉ አመልካች ለተጠሪ ያደረጉት የገጠር መሬት ስጦታ ዉል በመሬት አስተዳደር አካል ተመዝግቦና በመሬቱ ላይ የይዞታ መረጋገጫ ደብተር ለተጠሪ መሰጠቱ የተረጋገጠ ፍሬነገር ጉዳይ ሲሆን ይህ ዉል እንድፈርስ አመልካች ዳኝነት የጠየቁት የሥጦታ ዉሉ በመንፈሰ ልልነትና አቅመ ደካማነት የተደረገ ነዉ በሚል ምክንያት ስለመሆኑ መዝገቡ ያሣያል፡፡

የስጦታ ዉል ማለት ሰጪዉ ለሌላ ሰዉ ችሮታ በማድረግ ሃሳብ ከንብረቶቹ አንዱን የሚለቅበት ወይም ግዴታ የሚገባበት ዉል ስለመሆኑና ስጦታ ማድረግ የሰጪዉ የግል ተግባር ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2427 እና 2434 ይደነግጋል፡ከዚህ እንደምንገነዘበዉ ስጦታ ዉል የጸና ዉል እንዲሆን እንደማናቸዉም የዉል ጉዳዮች በዉል ህግ የተደነገገዉን መሰረታዊ መስፈርት አሟልቶ መገኘት ያለበት መሆኑን ነዉ፡፡የስጦታ ዉሉ በህግ የተመለከተዉን መሰረታዊ መስፈርት እና ስለስጦታ ዉል የተደነገጉትን ደንቦች አላሟላም በሚል መብትና ጥቅሙ የተነካበት ወገን ዉሉ እንዲፈርስ ሊጠይቅ እንደሚችል ከዉል ህጎች ጠቅላላ ድንጋጌ እና ስለስጦታ ዉሎች ከተደነገገዉ ልዩ ከፍል መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሰረቱ አንድ ዉል እንዲፈርስ የሚደረገዉ ዉሉ የተቋቋመበት ሁኔታ ከመሰረቱ ግድፈት ሲኖርበት ነዉ፡፡ይኸዉም የተዋዋይ ወገን ለመዋዋል ችሎታ ወይም ፈቃድ ጉድለት ሲኖር ወይም የዉለታዉ ጉዳይ ህግን ወይም ግብረ ገብነት/ሞራል/ የሚጻረር ሲሆን ወይም በህግ የተደነገገዉን ፎርም ሳያሟላ ሲቀር ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1808 ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ከእነዚህ ምክንያቶች በአንዱ ወይም በሌላ ሁኔታ ዉሉ ጉድለት አለበት በሚል ዉሉ እንዲፈርስ መጠየቅ የሚችለዉ ወገን ማንነት እንደየምክንያቱ የሚለያይ መሆኑም በዚሁ ድንጋጌ ላይ ተመልክቷል፡፡

ይህ እንደ አጠቃላይ ሆኖ የስጦታዉ ዉል ሊፈርስ የሚችልባቸዉ ልዩ ሁኔታዎች በህጉ አንቀጽ 2437 እስከ 2440 ላይ ተዘርዝረዋል፡፡በዚህም መሠረት የስጦታ ዉል ሊፈርስ የሚችለዉ ስጦታዉ በተደረገበት ወቅት ስጦታ አድራጊዉ የአእምሮ ችግር እንዳለበት ታዉቆ በፍርድ ክልከላ የተደረገበት (judicial interdiction) ወይም ስጦታዉ የተደረገዉ ስጦታ ሰጪዉ የፍርድ ክልከላ እንዲደረግበት ለፍርድ ቤት ጥያቄ ከቀረበ በኋላ ወይም ስጦታዉ ሲደረግ የስጦታ ሰጪዉ አእምሮ ጤነኛ አለመሆኑን የወሌ ይዘት የሚያሳይ ሲሆን፣ ስጦታዉን ለማድረግ መነሻ የሆነዉ ምክንያት ከህግ ወይም ከሞራል ተቃራኒ ከሆነ፣ ስጦታዉ ሲደረግ ስጦታ ሰጪዉ በመንፈስ ጫና (undue influence) ስር መሆኑ ከተረጋገጠ ስለመሆኑ ከድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ስለሆነም የስጦታ ዉል እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ የሚያቀርብ ሰዉ ከእነዚህ ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንድ ሁኔታ መኖሩን የመግለጽ እና ይህንኑ የማረጋገጥ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ስጦታዉ እንዲፈርስ የጠቀሱት ምክንያት ስጦታ ያደረጉት በመንፈስ ልልነትና አቅመ ደካማነት በተጠሪ ጫና ተደርጎባቸዉ መሆኑን በመግለጽ ሲሆን የሥር ፍርድ ቤቶች የግራቀኙን ማስረጃ መርምረዉ እና አመዛዝነዉ በዚህ ረገድ የአመልካች ምስክሮች ያስረዱት አሳማኝ ምክንያት አለመኖሩን አረጋግጠዋል፡፡በመሰረቱ የስጦታ ዉሉ የተደረገዉ በመንፈስ መጫን ነዉ የሚለዉን ፍሬነገር ጉዳይ የማስረዳት ሸክም የአመልካች ስለመሆኑ ህጉ ያስገነዝባል፡፡የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 2439፣2001/1/ እና የፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 259 ድንጋጌዎችን ይመለከታል፡፡ይሁንና አመልካች በክሱ የጠቀሱት ሁኔታ ስለመኖሩ ወይም በስጦታ አድራጊዉ አእምሮ ላይ ተፅዕኖ ስለመኖሩ የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ስለዚህም እንደክሳቸዉ አቀራረብ ዉሉ በጫና የተደረገ መሆኑን ማስረዳት ባልቻሉበት ሁኔታ በዚህ ምክንያት ዉሉ እንዲፈርስ ያቀረቡት ቅሬታ ተገቢነት የለዉም፡፡ሌላዉ አመልካች መከራከሪያ የሥጦታ ዉሉ ፎርም የሚመለከት ነዉ፡፡ አከራካሪዉ የሥጦታ ዉል የተደረገዉ በ24/06/2005ዓ.ም መሆኑን መዝገቡ ያሣያል፡፡ የገጠር መሬት ባለይዞታ የይዞታ መብቱን በስጦታ ሌላ ሰዉ ሊያስተላለፍ የሚችል ስለመሆኑና መሟላት ያለባቸዉ ሁኔታዎች አስመልክቶ በወቅቱ ስራ ላይ የነበረዉ አማራ ክልል የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 15 እና 17 በዝርዝር ደንግጓል፡፡ የዉሉን ፎርም አስመልክቶ የስጦታ ዉሉ በጽሁፍ መደረግ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡የአዋጁን አንቀጽ17/5/ይመለከታል፡፡እንዲሁም ስምምነቱ መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ባለዉ የባለስልጣኑ ቅርንጫፍ መ/ቤት ቀርቦ መመዝገብ እንዳለበትም ያመለክታል፡፡በተያዘዉም ጉዳይ ማስረጃ የመመርመርና ፍሬነገር ማረጋገጥ ሃላፊነት የተሰጣቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች እንዳረጋገጡት

የመሬት ስጦታ ዉሉ የተደረገዉ በአካባቢ ሽማግሌዎችና በቀበሌዉ ጽ/ቤት ፊት በጽሁፍ የተደረገ ስለመሆኑና በአዋጅ እና የአዋጁን ማስፈጸሚያ ደንብ ተከትሎ ተገቢዉን ሂደት ተከትሎና ፎርማሊቲ ተሟልቶ ምዝገባና የይዞታ ማረጋገጫ በተጠሪ ስም የተከናወነ መሆኑን ያረጋገጡት ጉዳይ ስለመሆኑ ዉሳኔዉ ያሣያል፡፡ስለሆነም የገጠር መሬት ስጦታ ዉል አፈጻጸም በሚመለከት በልዩ ህጉ የተደነገገዉ ፎርምና ምዝገባ ስርዓት ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 881 እና 2443 የተደገገዉን አላሟላም የምባልበት ምክንያት የለም፡፡በዚህም ረገድ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉ ሌላዉ ጭብጥ ተጠሪ አመልካችን ስለመጦሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የሥጦታ ዉሉ ሊፈርስ አይገባም መባሉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን በሚመለከት ነዉ፡፡በመሰረቱ ይህ የክርክር ነጥብ በስር ፍርድ ቤት ዳኝነት ያልተጠየቀበት አዲስ ክርክር ነዉ በሚል በሰበር ላይ የቅሬታ ነጥብ ሆኖ መቅረቡ ተገቢነት እንደሌለዉ በመግለጽ ተጠሪ ተከራክሯል፡፡ከመዝገቡ እንደሚታዉ ተጠሪ አመልካችን የመጦር ግዴታ አልተወጣም በሚል ምክንያት የሥጦታ ዉሉ እንዲፈርስ አመልካች በግልጽ ዳኝነት ስለመጠየቃቸዉ መዝገቡ አያሣይም፡፡በዚህ ረገድ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ዉሳኔ እንደሚያሣየዉ የመጦር ግዴታ አስመልክቶ ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት በራሱ ጊዜ ያነሳዉ እንጂ የአመልካች የክስ ምክንያት አለመሆኑን አረጋግጧል፡፡ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዉሳኔ የሻረበት አንዱ ምክንያትም የመጦር ግዴታን በሚመለከት በስር ፍርድ ቤት ያልቀረበ የክርክር ነጥብ በመሆኑ ነዉ፡፡በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 329/1/ እንደተደነገገዉ በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ ክርክርና አዲስ ነገር በይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀባይነት የለዉም የሚለዉ የክርክር አመራር መርህ ይህንኑ የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ይህ መርህ ለሰበር ችሎትም ተፈጻሚነት እንዳለዉ እሙን ነዉ፡፡ስለሆነም ተጠሪ አመልካችን ለመጦር ከስጦታ ዉሉ ወይም ከህግ የመነጨ ግዴታ ስለመኖሩ ገልጸዉ ዳኝነት ባልጠየቁበት ብሎም ግዴታዉን ማንደል አለማንደሉ የክርክር ምክንያት ሆኖ በስር ፍርድ ቤት ተጣርቶ ዉሳኔ ባልተሰጠበት ሁኔታ ይህ ሰበር ችሎት የክርክር ጭብጥ አድርጎ የምወስንበት ስነስርዓታዊ መሰረት የለዉም፡፡ይሁንና የመጦር ግዴታን አስመልክቶ በማንኛዉም ጊዜ ዳኝነት ከመጠየቅ የሚገድብ አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ሲጠቃለል የሥጦታ ዉሉ በጽሁፍ የተደረገ እና በሚመለከተዉ አካል የተመዘገበ መሆኑን በማረጋገጥ ዉሉ የሚፈርስበት ሌላ ህጋዊ ምክንያት መኖሩን አመልካች በተገቢዉ ማስረጃ ባለማስረዳታቸዉ ክርክራቸዉን ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ

በግራቀኙ የቀረበዉን ክርክርና በማስረጃ የተረጋገጠዉን ፍሬነገር መሰረት በማድረግ መሆኑን መገንዘብ ችለናል፡፡በመሆኑም በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/4/ እና 10 ድንጋጌዎች መሰረት ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የማረም ስልጣን አንጻር ሲታይ ዉሳኔዉ ህጉንና እና ስለገጠር መሬት ስጦታ ዉል አፈጻጸም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ የተደነገገዉን ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩን ዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/48692 ላይ በ28/05/2011ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና ይህንኑ በማጽናት ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/03-84881 ላይ በ27/11/2012ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ ህግ ቁጥር 348/1/መሰረት ጸንቷል፡፡ 2ኛ/በዚህ ፍርድ ቤት ለተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የመ.ቁ.199901
መስከረም 27/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1ኛ. ወ/ሮ ዘውዴ እረዳ

2ኛ. ወ/ሮ ጥሩወይ በላይ እረዳ

3ኛ. አቶ ጌታሁን ተረፈ እረዳ

4ኛ. ወ/ሮ እመቤት አማረ እረዳ

ተጠሪ፡ ወ/ሮ የሹምነሽ ስዩም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ንብረት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁን አመልካቾች በሰቆጣ ወረዳ ፍ/ቤት በአሁን ተጠሪ ላይ ጥቅምት 14/2011 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ ከአያታቸው ቄስ ረዳ ተክለሃይማኖት በውርስ የተላለፈላቸውን ቦታ እና አዋሳኙ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰውን በ245.8 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ አንድ ህድሞ ክብ ቤት የአሁን ተጠሪ ከነበረባቸው የቤት ችግር በመነሳት እንዲኖሩበት ፈቅደዉላቸው በኋላም በቤቱ ላይ በ2007 ዓ.ም በወራሾች ስም ካርታ አስወጥተው ለመከፋፈል ተጠሪ እንዲለቁላቸው ሲጠይቋቸው ያለምንም መብትና ጥቅም አለቅም ብለው ይዘው የሚገኙ መሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ተገደው እንዲለቁላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት ተጠሪ ጥቅምት 23/2011 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አመራሯ የስረ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ መቃወሚያውም ሁለት ነው፡፡ የመጀመሪያው ቄስ ረዳ ተ/ሓይማት ከሞቱ በኋላ 1ኛ አመልካች፣ ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አመልካቾች ወላጆች እና ወላጅ እናቴ ወ/ሮ ውዴ ረዳን ጨምሮ በሰባት ወራሾች መካከል የውርስ ሀብት ክፍፍል ተደርጓል፤ በክፍፍሉም ወላጅ እናቴ ቀድሞኑም ከአባቸው ቄስ ረዳ ጋር ክስ በቀረበበት ቤት ውስጥ ይኖሩ የነበረ ሲሆን አባታቸውን ጦረው፣ ሲታመሙም አስታመው፤ ከሞቱ በኋላ ደግሞ አስፈላጊውን ሃይማኖታዊ ስርዓት ሁሉ የፈፀሙላቸው መሆኑ ከግንዛቤ ገብቶ አሁን ክስ የቀረበበት ቤት ለእናቴ በክፍፍል እንዲደርስ እና ቀሪውን ንብረት ሌሎች ወራሾች እንዲካፈሉት በአስማሚ ሽማግሌዎች ፊት ስምምነት ፈፅመዋል፤ በስምምነቱ መሰረት ወላጅ እናቴ ክስ የቀረበበትን ቤት ለ25 ዓመታት ኖረውበት እርሳቸው ከሞቱ በኋላም በውርስ ተላልፎልኝ ለ7 ዓመታት ሲጠቀምበት የነበረ ነው፤ በመሆኑም ክሱ በወራሾች መካከል በስምምነት ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የውርስ ሀብት ክፍፍል ከተደረገ ከሶስት ዓመት በኋላ ክስ/መቃወሚያ ሊቀርብበት የማይችል በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ በአማራጭ የስረ ነገር ክርክር ደግሞ ክስ የቀረበበት ንብረት ከእናቴ በውርስ የተላለፈልኝ ሆኖ እያለ አመልካቾች በመመሳጠር ሆነ ብለው የተጠሪን የውርስ ሃብት አካተው ካርታ ያወጡበት በመሆኑ ልለቅ አይገባም የሚል ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ክሱ የቀረበው በስምምነት ባለቀ ጉዳይ ላይ ነው? ወይስ አይደለም? በሚል ጭብጥ ላይ የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ሰምቷል፡፡ በዚሁ መሰረት በተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክሮች የውርስ ክፍፍል ስምምነቱን መርተዋል የተባሉት ሽማግሌዎች መሆናቸውን፤ በሰጡት ቃልም የግራ ቀኙ አያት በሞቱ ጊዜ የግራ ቀኙን ወላጆች ጨምሮ በሰባት ወራሾች መካከል በስምምነት የውርስ ሀብት ክፍፍል ያደረጉ መሆኑን፤ በስምምነቱ መሰረትም አሁን ክስ የቀረበበትን ቤት ለአሁን ተጠሪ ወላጅ እናት እንዲደርስ እና የተቀረውን የውርስ ሀብት ሌሎች ወራሾች ለመካፈል ተስማምተው በዚሁ መሰረት ጉዳዩን በስምምነት የጨረሱ ስለመሆኑ ሲመሰክሩ በአመልካቾች በኩል የቀረቡት ምስክሮች ደግሞ ክፍፍል መደረጉን አናውቅም በማለት የተናገሩ ስለመሆኑ መዝግቦ በሰጠው ብይን “የክፍፍል ስምምነቱ በቃል የተደረገ ቢሆንም በግራ ቀኙ ወላጆች መካከል የውርስ ሀብት ክፍፍል ስምምነት የተደረገ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፤ የውርስ ሀብት ክፍፍልን አስመልክቶ በህግ ተለይቶ የቀመጠ ፎርማሊቲ የለም፤ ክሱም በስምምነት በተጠናቀቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው” በማለት ውድቅ አድርጓል፡፡

ይህንኑ ብይን በይግባኝ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ ስምምነቱ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተደረገ ሲሆን የፍ/ብ/ህ/ቁ/1567፣ 1568 እና 1723 በሚደነግገው መሰረት በፅሁፍ የቀረበ ስምምነት ባለመኖሩ ተቀባይነት የለውም በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮ በይርጋ መቃወሚያው ላይ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ እንዲወስን፤ ክሱ በይርጋ የማይታገድ ከሆነ በክሱ ስረ ነገር ክርክር ላይ አከራክሮ የመሰለውን እንዲወስን በነጥብ መልሷል፡፡ የአሁን ተጠሪ በተራቸው ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ለውርስ ሀብት ክፍፍል ስምምነት በህግ ተለይቶ የተቀመጠ ልዩ ፎርማሊት የለም፤ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተጠቀሱት የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1567፣ 1568 እና 1723 የውል ጉዳይን እንጂ የውርስ ጉዳይን የሚመለከቱ ባለመሆናቸው ለጉዳዩ አግባብነት የላቸውም በማለት የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት ብይን አፅንቷል፡፡ ይኸው ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ህዳር 30/2013 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍሬ ቃሉም አመልካቾች የሚቹ ወራሽ ስለመሆናችን የወራሽነት ማረጋገጫ በማውጣት እነ ቄስ ተረፈ እረዳ በሚል በ2007 ዓ.ም በስማቸው በማዞር ካርታ አሰርተው እስከ 2012 ዓ.ም ግብር እየገበሩ በጋራ የያዙት እና ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት ስለመሆኑ የሰነድና የሰው ማስረጃ አቅርበው አሰምተው እያለ በአግባቡ ሳይታይ የወረዳው ፍ/ቤት በብይን መዝጋቱ ትክክል ነው በሚል መወሰናቸው አግባብ አይደለም፤ ተጠሪ ቤት ስለሌላቸው ቤቱን እየጠበቁ እንዲኖሩበት የተደረገ እንጅ ከቤቱ ላይ መብት የላቸውም፤ ተደረገ የተባለው ስምምነትም በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተደረገ ሲሆን ስምምነቱን የሚገልፅ የቀረበ የሰነድ ማስረጃ የለም፤ ይህ

በሌለበት ወንድም እና የአባታቸውን ወገን አቅርበው ስምምነት ነበር በመባሉ ብቻ ጉዳዩ በስምምነት ያለቀ ነው ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ያስቀርባል በመባሉ ምክንያት ተጠሪ የፅሁፍ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል። በዚሁ አግባብ ተጠሪ መጋቢት 22/2013 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። ፍሬ ቃሉም አንድን ፍሬ ነገር ለማስረዳት ተለይቶ የተመለከተ ማስረጃ እንዲቀርብ ህጉ ካላስገደደ በቀር ፍሬ ነገሩን በማንኛውም የማስረጃ አይነት ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/47551 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፤ የውርስ ሀብት ክፍፍል ስርዓትን አስመልክቶ በወራሾች መካከል በሚደረግ ስምምነት ብቻ ሊፈፀም የሚል ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1079 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ስር ከመገለፁ ውጭ ክፍፍሉ ሊፈፀም ስለሚገባበት የተለየ ፎርማሊቲ አልተመለከተም፤ የአያታችን የውርስ ሀብት ክፍፍል አስመልክቶ ወላጆቻችን በራሳቸው በመረጧቸው ሽማግሌዎች ስምምነት ተደርጎበት ክስ የቀረበበት ንብረት ለወላጅ እናቴ ስለመድረሱ የወረዳው ፍርድ ቤት በማስረጃ አረጋግጦ ወስኗል፤ ስለ ውርስ ሀብት ክፍፍል በህግ ተለይቶ የተመለከተ ፎርማሊቲ በሌለበት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸውን እና ስለ የማይንቀሳቀስ ሀብት ርስት ምዝገባ የተመለከቱትን የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1567 እና 1568 ድንጋጌዎችን ጠቅሶ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን መሻሩ አግባብ ባለመሆኑ የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ተረድተው በማረማቸው የፌፀሙት መሰረታዊ የህግ ስህተት የለም፤ አመልካቾች ክስ ያቀረቡት የውርስ ሀብት ክፍፍሉ ከተደረገ ሶስት ዓመት በኋላ በመሆኑ በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1106 መሰረት ከመነሻው በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው። አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በመስጠት ሞግተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ክስ በስምምነት ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው በሚል በመወሰኑ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመኖሩ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል።

እንግዲህ ከክርክሩ አመጣጥ መረዳት እንደሚቻለው የስር ፍርድ ቤቶች የተለያዩት የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ በወራሾች መካከል የውርስ ሀብት ክፍፍል ስምምነት ሊፈፀም የሚገባበትን ፎርማሊትን አስመልክቶ ነው። በመሰረቱ የውርስ ንብረት ክፍፍል አሰራር በወራሾች መካከል በሚደረግ ስምምነት፣ በወራሾቹ መካከል ስምምነት ከሌለ ደግሞ ከእነርሱ መካከል አንዱ ተግቶ ያሰናዳውን የክፍያ ሐሳብ ለዳኞች አቅርቦ በማፀደቅ ሊከናወን እንደሚችል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1079 ይደነግጋል። በእርግጥ ህጉ የውርስ ሀብት ክፍፍል በዚህ መልኩ ሊከናወን እንደሚችል ከመደንገጉ ውጭ በወራሾች መካከል የሚደረገው የክፍፍል ስምምነት ሊፈፀም ስለሚኖርበት ፎርማሊቲ በግልፅ አላስቀመጠም። እናም ስለክፍፍሉ የተለየ ፎርም አለመቀመጡ የስምምነቱ ፎርም አፈፃፀም ለወራሾች የተተወ ነፃነት ነው ሊባል ይችል ይሆናል። ሆኖም በዚህ መልኩ የሚደረገው ስምምነት በተስማሚዎቹ መካከል መብትና ግዴታን የሚፈጥር ውል እንደመሆኑ መጠን የስምምነቱ ፎርማሊቲ ስምምነት ከሚደረግበት ንብረት ዓይነት እና ባህሪ አኳያ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው።

በዚሁ አግባብ በፍትሐብሔር ህጉ አምስተኛ መፅሐፍ ውስጥ ስለልዩ ውሎች የተደነገገው ልዩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከውልም ሆነ ከውል ውጭ የሚመነጩ ማናቸውም ስምምነት በፍትሐብሔር ህጉ አራተኛ መፀሀፍ ውስጥ ስለውሎች በጠቅላላው በተደነገገው መርህ መሰረት የሚመራ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1677 ድንጋጌ ይዘት ያሳያል። ስለውሎች በጠቅላላው ከሚደነግገው የህጉ ክፍል ውስጥ ከተመለከቱት መሰረታዊ መርሆዎች ውስጥ አንዱ በቁጥር 1719 ስር የውል ፎርማሊቲን አስመልክቶ የተቀመጠው መርህ ነው። በዚህ ድንጋጌ መሰረት በህግ በልዩ ሁኔታ የውል ፎርም ካልተመለከተ በቀር ተዋዋይ ወገኖች ስምምነታቸውን በተስማሙበት አኳኋን ሊፈፅሙ እንደሚችሉ ተመልክቷል። የተዋዋይ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ወገኖች የስምምነታቸውን ፎርማሊት የመወሰን ነፃነት ከሚገደብበት ልዩ ሁኔታ ወይም በስተቀር ውስጥ አንዱ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚደረግ ስምምነትን አስመልክቶ ስለመሆኑ በቁጥር 1723 ስር ተመልክቷል፡፡ በዚሁ አግባብ የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስምልክቶ የሚደረግ የክፍፍል ወይም የማዛወር ስምምነቶች ሁሉ በጽሑፍና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት መደረግ እንደሚገባው የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1723(2) ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረትን አስምልክቶ የሚደረግ ስምምነት በዚህ አይነቱ ጥብቅ የአፈፃፀም ስርዓት መሰረት እንዲመራ የተፈለገበት የራሱ ህጋዊ እና አስተዳደራዊ ምክንያት እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ ከህግ አኳያ ንብረቱ በተፈጥሮው ዘለቄታዊ ባህሪ ያለው በመሆኑ ምክንያት በእንደዚህ ዓይነት ንብረት ላይ የሚፈጠር ማናቸውም መብት የሶስተኛ ወገኖችን መብት እንዳይጎዳ ተገቢን ቁጥጥር እና ጥንቃቄ ለማድረግ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ከአስተዳደር አንፃር ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም የማይንቀሳቀስ ንብረት በህግ አግባብ በተቋቋመ መንግስታዊ አስተዳደር ክፍል ዘንድ መመዝገብ ያለበት እና በንብረቱ ላይ የሚደረግ ማናቸውም የመብት መለዋወጥ መረጃዎች ሁሉ በሰነድ መደራጀት ያለበት ስለመሆኑ ስለ የማይነቀሳቀስ ንብረት መዝገብ በሚደነግገው የፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀፅ 10 ከቁጥር 1553 ጀምሮ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በእርግጥ የፍትሐብሔር ህጉ አንቀፅ 10 ስራ ላይ የሚውልበት ቀን በነጋሪት ጋዜጣ እስኪታወጅ ድረስ ተፈፃሚ እንደማይሆን በፍ/ብ/ህ/ቁር 3363(1) ስር ተመልክቷል፡፡ ይህ እስከሚሆን ድረስም በምትኩ በፍ/ብ/ህ/ቁጥር 3364 - 3367 ድረስ የተመለከቱት ልማዳዊ ደንቦች ተግባራዊ የሚደረጉ ስመሆኑ በቁጥር 3363(2) ስር ተመልክቷል፡፡ በጊዜ ሂደትም መሬትን እና ሌሎች የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ምዝገባ እና አስተዳደር የሚመለከቱ የአስተዳደር መዋቅሮች በህግ እንዲቋቋሙ ተደርጎ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ ስምምነቶች ላይ አስተዳደራዊ ቁጥጥር እየተደረገበት ያለ ለመሆኑ በችሎት ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ አግባብ ያላቸው የአስተዳደር አካላት በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተደረገን ስምምነት ተቀብለው ለመመዝገብ እና በስምምነቱ መሰረት በንብረቱ ላይ ተጓዳኝ መብት ለመፍጠር ስምምነቱ በህጉ በተመለከተው ልዩ ፎርም ተፈፅሞ ሊቀርብላቸው ይገባል ማለት ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ለክርክር ምክንያት የሆነው የማይንቀሳቀስ ንብረት ከ1ኛ አመልካች አባት እንዲሁም ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያለት እና ከተጠሪ አያት በተዋረድ የመጣ የውርስ ሀብት ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይልቁም የሚከራከሩት ንብረቱን አስመልክቶ በወራሾች መካከል የተደረገ የክፍፍል ስምምነት ስለመኖሩ ላይ ነው፡፡ የተጠሪ መከራከሪያ ክስ የቀረበበት ቤት የአያታችን የውርስ ሀብት ቢሆንም የውርስ ሃብቱን አስመልክቶ በወራሾች መካከል በቃል ስምምነት ክፍፍል ተደርጎ ቤቱ ለእናቴ ደርሷቸው ከእናቴ የተላለፈልኝ ነው የሚል ነው፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው ስምምነት ስለመኖሩ ክደዋል፡፡ እንዲያውም በንብረቱ ላይ በወራሾች ስም በጋራ የባለሀብትነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አውጥተው ግብርም በስማቸው እየገበሩ የሚገኙ መሆኑን ገልፀው ይከራከራሉ፡፡ እንግዲህ ተጠሪ የሚጠቅሱት ስምምነት የተደረገው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በመሆኑ ከላይ በተሰጠው የፍርድ ትችት መሰረት ስምምነቱ ቢያንስ በፅሁፍ የተዘጋጀ እና በሚመለከታቸው ወራሾች የተፈረመበት ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ መልኩ የቀረበ ስምምነት በሌለበት እና ስምምነት ስለመኖሩም ከሌሎች ባለመብቶች ጭምር መከራከሪያ ቀርቦ ባለበት በህግ ረገድ እውቅና የሚሰጠው እና ህጋዊ ውጤት የሚኖረው ስምምነት አለ ለማለት አይቻልም፡፡ ክስ የቀረበበትን ንብረት አስምልክቶ ቀድሞ የተደረገ እና ህጋዊ ውጤት የሚኖረው ስምምነት ከሌለ ደግሞ በዚሁ ምክንያት የአመልካቾች ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የሚዘጋበት አግባብ የለም፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩ ይህ በሆነበት የወረዳው ፍርድ ቤት የአመልካቾችን ክስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መዝጋቱ እና የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ መቀበላቸው ስምምነት ተደርጎበታል የተባለውን የውርስ ሀብት ባህሪ እና ከዚያው አኳያ የተቀመጠውን ተጓዳኝ አስገዳጅ የህግ ፎርማሊትን መሰረት ያላደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/03-27166 ላይ ጥቅምት 18/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳዳር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/01037 ላይ ጥር 29/2011 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ.መ.ቁ.199542
መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1. አቶ ዳዊት ወ/ዮሐንስ ፋሪስ
2. ወ/ሪት ሰርካለም ወ/ዮሐንስ ፋሪስ
3. አቶ ዳንኤል ቸርነት
} ጠበቃ መስፋን መኮንን ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ገዛኸኝ ቢራ ዱቤ - ጠበቃ አድማሱ አለማየሁ -ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ታሕሳስ 08 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 242906 መጋቢት 08 ቀን 2012 ዓ.ም የሰር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 260 ውስጥ የሚገኙትን ስድስት ክፍል ቤቶች ለአመልካቾች ሊያስረክብ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 194433 ጥቅምት 11 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩ የቤት ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው። በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪ 1ኛ ተከሳሽ፤ በዚህ የሰበር ክርክር የሌሉ ወ/ሮ ፊንታዬ ወ/ዮሐንስ ደግሞ 2ኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል። የአሁን አመልካቾች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 260 ካርታ ቁጥሩ ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/341/18371/02 የሆነ ቤት እና ይዞታ ወ/ሮ አልማዝ ኤርኮ እና አሥር አለቃ ወ/ዮሐንስ ፋሪስ በውርስ የተላለፈላቸው መሆኑን እና ቀሪው ይዞታ በካርታ እንዲካተትላቸው በሂደት ላይ የሚገኙ መሆኑን፤ ሟች እናታቸው ወ/ሮ አልማዝ ኤርኮ በሕይወት በነበሩበት ወቅት ተጠሪ እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ስድስት ክፍል ቤት ሰርተው እንዲኖሩበት የተፈቀደላቸው መሆኑን፤ የውርስ ሐብት በተጣራበት የመ.ቁ. 33448 በሆነው መዝገብ በቀን 03/11/06 ዓ.ም በጸደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ የተከሳሾች መብት ስድስት ክፍል ቤት መሆኑን እና በይዞታው ላይ መብት የሌላቸው መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑን በመግለጽ የቤቱን ግምት በመክፈል ተጠሪ እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ቤቱን እና ይዞታውን ለቀው እንዲወጡ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው።

የአሁን ተጠሪ በሰጠው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ላይ ደግሞ አመልካቾች የወሰዱት ካርታ መክኗል፤ ሟች ወ/ሮ አልማዝ ኤርኮ በሕይወት እያሉ ቦታውን ሰጥተዋቸው ቤት ሲሰሩ አመልካቾች አልተቃወሙም፤ 1ኛ ተጠሪ እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ቤቱን ከሰሩበት ቦታ ውጪ ባለው ይዞታ ላይ ካርታ ለማሰራት አመልክተው በሂደት ላይ እያሉ በአመልካቾች እንቢተኝነት ተቋርጧል፤ የአሁን ተጠሪ እና የስር 2ኛ ተከሳሽ መብት በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ የተረጋገጠ በመሆኑ ክሱ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

የስር 2ኛ ተከሳሽ በሰጡት መልስ ከተጠሪ ጋር ባል እና ሚስት መሆናቸውን እና የአመልካቾች ወላጅ እናት በህይወት እያሉ ሶስት ክፍል ቤት ሰርተው ከሞቱ በኋላ ደግሞ ሌላ ተጨማሪ 3 ክፍል ቤት መስራታቸውን አመልካቾች የሚያውቁ መሆኑን፤ የአመልካቾች እናት ተጠሪ እና 2ኛ ተከሳሽ ወደፊት ቤት ሲሰሩ እንደሚለቁ እንደነገረቻቸው እና ከ1968 ዓ.ም ጀምሮ በ 820 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ግብር እየተገበረበት የቆየ መሆኑን እና አመልካቾች መብት ካላቸው ቢወሰንላቸው የማይቃወሙ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውን በብይን ውድቅ ያደረገ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ ደግሞ የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና ከሚመለከታቸው የአስተዳድ አካላት በአመልካቾች እና በተጠሪ ስም የሚገኙ ማሕደሮች እንዲቀርቡለት እና ስለጉዳዩ ተጣርቶ ምላሽ እንዲላክለት ካደረገ በኋላ በአመልካቾች አውራሽ ፍቃድ በይዞታው ላይ ተጠሪ እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ስድስት ክፍል ቤት መስራታቸው እና የአመልካቾች አውራሽ በ820 ካ.ሜ ላይ ግብር ሲከፍሉ መቆየታቸው ተረጋግጧል፤ ተጠሪ ይዞታው በስጦታ የተላለፈለት ስለመሆኑ አላስረዳም፤ በይዞታው ላይ የሰፋ መብት ያላቸውም የአመልካቾች አውራሽ እንጂ ተጠሪ አይደለም፤ ተጠሪ እና የስር 2ኛ በአመልካቾች አውራሾች ይዞታ ላይ ስድስት ክፍል ቤት ሲሰሩ አመልካቾች ያልተቃወሙ በመሆኑ በመሐንዲስ በተረጋጠው መሠረት የቤቱን ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ብር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

142,201 / አንድ መቶ አርባ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ አንድ / ከፍለዋቸው ተጠሪ እና የስር 2ኛ ተከሳሽ በአመልካቾች አውራሽ ይዞታ ላይ የሰሩትን ስድስት ክፍል ቤቶች ለቀው እንዲስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የአመልካቾች አውራሾች በፈቀዱላቸው ባዶ ቦታ ላይ የአመልካቾች አውራሽ ከመሞታቸው በፊት ሶስት ክፍል ቤት መስራታቸውን እንዲሁም ወ/ሮ አልማዝ ኤርኮ ከሞቱ በኋላም አመልካቾች ሳይቃወሙ ተጨማሪ ሶስት ክፍል ቤቶችን መስራታቸው ተረጋግጧል፤ በእነ ፋንታዬ ወልደዩሐንስ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የቦታ ስፋቱ 366 ካ.ሜ እንደሆነ ለተጠሪ እና ለስር 2ኛ ተከሳሽ የተፈቀደላቸው ይዞታ በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኝ የይዞታ ይካተትልኝ ጥያቄ ተነስቶ በጽ/ቤቱ በኩል ስራው እንዳልተከናወነ ተረጋግጧል፤ ተሰሩ የተባሉት ቤቶች የሚገኙት የውርስ ሐብት ክርክር በተነሳበት ቤት ውስጥ መሆኑን በፍርድ ቤት የጸደቀው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ያመለክታል፤ ለባልና ሚስቱ የተፈቀደላቸው ቤት እንዲሰሩ ብቻ ሳይሆን ባዶ ቦታ ጭምር መሆኑን እና የውርስ ሀብት አካል አለመሆኑ ተረጋግጦ ባለበት የስር ፍርድ ቤት የተፈቀደላቸው ይዞው ላይ ቤት እንዲሰሩ እንጂ ይዞታውን ጭምር አይደለም ሲል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ስድስት ክፍል ቤቶች ለቀው በመውጣት ሊያስረክቡ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ ይህንኑ ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጸንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪ እና የስር 2ኛ ተከሳሽ በወቅቱ የነበረባቸውን የመጠለያ ችግር እስኪፈቱ ድረስ 3 ክፍል ቤት ሰርተው በይዞታው ላይ እንዲጠቀሙ ለጊዜው የመጠቀም መብት የተሰጣቸው መሆኑን የስር 2ኛ ተከሳሽ አምነዋል፤ የአመልካቾች እናት ከሞቱ በኋላ አመልካቾች ልጆች በመሆናችን በእህታችን በ2ኛ ተከሳሽ ሞግዚትነት እና አስተዳዳር ስር በመሆናችን 3 ክፍል ቤቱን እንዲሰሩ ፍቃድ አልሰጠንም፤ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር 2ኛ ተከሳሽ በስር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ባላቀረቡበት በተጠሪ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ ብቻ መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የለውም፤ በመሆኑም የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ የክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት እንደሚለቁ ከሚች እናታቸው ጋር የተስማሙ ስለመሆናቸው በመግለጽ መልስ በሰጡበት እና በተሰጠው ውሳኔ ላይም ይግባኝ ባላቀረቡበት ሁኔታ ተጠሪ ስድስት ክፍል ቤቶች ለቀው ሊያስረክቡ አይገባም በማለት የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 33448 በቀን 02/11/2006 ዓ.ም የቀረበው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ጸድቋል፤ አከራካሪ የሆኑት ስድስት ክፍል ቤቶች በተጠሪ እና በስር

2ኛ ተከሳሽ ያለምንም ተቃውሞ ስለመስራታቸው አመልካቾች አልካዱም፤ አከራካሪው ይዞታ ተጠሪ ቤት ሰርቶ እንዲጠቀምበት የተሰጠው መሆኑ ተረጋግጧል፤ የስር 2ኛ ተከሳሽ ቤቱ በጊዜያዊነት ስለመሰጠቱ የሚያቀርቡት ክርክር በማስረጃ አልተረጋገጠም፤ አመልካቾች በተጠሪ እና በስር 2ኛ ተከሳሽ እህታቸው ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በጋራ በተሰራው 6 ክፍል ቤት ላይ በመሆኑ ተጠሪ በዚህ ረገድ ይግባኝ መጠየቁ ተገቢ ነው፤ አመልካቾች 3 ክፍል ቤት ያለፈቃዳችን ተሰራ በማለት የሚያቀርቡት ክርክር በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካቾች በአሁን ተጠሪ እና ባለቤታቸው በሆኑት የስር 2ኛ ተከሳሽ ላይ አቅርበውት በነበረው ክስ ሟች እናታቸው ወ/ሮ አልማዝ ኤርኮ በሕይወት በነበሩበት ወቅት ተጠሪ እና የስር 2ኛ አከራካሪ በሆነው ይዞታ ላይ ቤት ሰርተው እንዲጠቀሙበት የፈቀዱላቸው ስለመሆኑ ገልጸዋል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ተጠሪ እና ባለቤታቸው የሆኑት የስር 2ኛ ተከሳሽ የአመልካቾች አውራሾች በፈቀዱላቸው ባዶ ቦታ ላይ የአመልካቾች አውራሽ ከመሞታቸው በፊት ሶስት ክፍል ቤት መስራታቸውን የአመልካቾች እናት ከሞቱ በኋላም አመልካቾች ሳይቃወሙ ተጨማሪ ሶስት ክፍል ቤቶችን ክርክር በተነሳበት ይዞታ ውስጥ የሰሩ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/1 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የለውም፡፡

አከራከሪ የሆኑት ስድስት ክፍል ቤቶች በአመልካቾች አውራሽ ፈቃድ ተጠሪ እና ባለቤታቸው የሆኑት የስር 2ኛ ተከሳሽ የሰሯቸው መሆኑ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ እና ለዚህ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያልተሰጠው በመሆኑ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠውን ፍሬነገር መሠረት በማድረግ ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆኑትን ስድስት ክፍል ቤቶች ለቀው በመውጣት ሊያስረክቡ አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1179/1 ድንጋጌን እና ይህንኑ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 30101፤ 36636፤ 105125 እና በሌሎችም መዛግብት ላይ የሰጠውን አስገዳጅ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሕግ ትርጉም መሠረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 242906 መጋቢት 08 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 194433 ጥቅምት 11 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

የሰ/መ/ቁ. 199518
ቀን ፡- ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. ወ/ሮ ከጀ ሆዕለሞ
2. አቶ አብራ ክበሞ } አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ ብርሃኑ ሸንቆ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰ/መ/ቁ. 199518
ቀን ፡- ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- 1. ወ/ሮ ከጀ ሆዕለሞ
2. አቶ አብሬ ክበሞ } አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- አቶ ብርሃኑ ሸንቆ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ተከሳሾች ሲሆኑ ተጠሪ ደግሞ የአፈጻጸም ከሳሽ ነበሩ፡፡ ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው አመልካቾች ሁለት ጥማድ የይዞታ መሬት ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ነው፡፡ ተጠሪ የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡትም በዚህ መሠረት እንዲፈጽምላቸው ሲሆን አመልካቾች በበኩላቸው ለተጠሪ የተወሰነው በይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ከተመዘገበው በላይ የእኛን የይዞታ መሬትና መኖሪያ ቤት ቤትን ጭምር ለተጠሪ አሳልፎ የወሰነ በመሆኑ በተጠሪ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በተመለከተው አግባብ ፍርዱ እንዲፈጸም ጠይቀዋል፡፡ የአፈጻጸም ክርክሩን ሲመራ የነበረው የሻሸጎ ወረዳ ፍርድ ቤት ቤት አመልካቾች እንዲለቁ የተወሰነው መውጪያ መግቢያ ላይ የሠሩትን ቤት ጨምሮ ስለመሆኑ በውሳኔው የተመለከተ በመሆኑና አመልካቾችም ቤቱን ለማንሳት ጊዜ እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ ቆይተው ቤቱ ያለበት መሬት የእኛ ነው ማለታቸው ተገቢነት የሌለው ነው በማለት ቤቱ ተነስቶ እንዲፈጽም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በይግባኝ እና በሠበር የተመለከቱት በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የአፈጻጸም ችሎት ውሳኔን አጽንተዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ከተወሰነው ሁለት ጥማድ መሬት ውጭ መወጪያ መግቢያ በሚል አራት ጥማድ መሬታችን አስረክቡ መባላችን ሆነ ቤት አፍረሱ መባሉ ከፍርዱ ውጭ የተሰጠ ትዕዛዝ ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ቤት ያፍርሱ መባሉ በውሳኔውና በአፈጻጸም ክሱ መሠረት የተጠየቀ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ይዘቱ አመልካቾች በያዙት ሁለት ጥማድ መሬት ቤት ሰርተው የሚገኙ መሆኑ ተረጋግጦ በውሳኔው መሠረት እንዲፈጸም የተወሰነ ነው፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ሊፀና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የአፈጻጸም ክርክሩ ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነውን ፍርድ እና የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ የተመራ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው አመልካቾች ሁለት ጥማድ የይዞታ መሬት ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ነው። ተጠሪ የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡትም በዚህ መሠረት እንዲፈጽምላቸው ነው። አሁን አከራካሪ ሆኖ የዚህን ችሎት ምላሽ የጠየቀው አመልካቾች ቤት እንዲያፈርሱ ተብሎ በአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠጠቱ በፍርዱ መሠረት እየተፈጸመ ያለ መሆን አለመሆኑ ነው። በዋናነት ሥነ-ሥርዓት ሕግ የተቀረጸው ሠዎች ግጭቶችን ሠላማዊ በሆኑ ሁኔታ እንዲፈቱ ለማስቻል (peaceful resolution of disputes)፣ መብታቸውን የሚያስከብሩበት ዘዴ እንዲኖርና ፍርድ ቤቶች ክርክርን ፍትሐዊ እና ወጭ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት እንዲችሉ ነው። የአፈጻጸም ችሎት ጉዳዩን መምራት ያለበት የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎችና ለአፈጻጸም መሠረት የሆነውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ሲሆን ውጤቱም ሠዎች በፍርድ ያገኙትን መብት ማስፈጸም ነው። በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 212 መሠረት የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ያለበት ፍርድ በይግባኝ ካልተለወጠ የጸና እና ሊፈጸም የሚችል ፍርድ እንደሆነ ተመላክቷል። በህግ የተቋቋመ የዳኝነት አካል ከነግድፈቱም ቢሆን የሰጠው ውሳኔ መከበር እና መፈጸም አለበት። ፍርድ የማይፈጸም ከሆነ የሕግ የበላይነት መገለጫ የሆነውን ዋናውን የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት አለመወጣት ይሆናል። ዜጎች በፍትሕ ሥርዓቱ የሚጠቀሙት መብታቸውን ለማስከበር ነው። የመብት ማስከበር መሠረቱ ደግሞ ፍርድን ከማናቸውም መሠናክል ነጻ በማድረግ ማስፈጸም ነው። ፍርድ ቤቶች በዚህ አግባብ ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ዜጎች በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 ያገኙት ፍትሕ የማግኘት መብትን ማረጋገጥ እና ማስፈጸም አይቻልም። ውጤቱ ደግሞ መብት ካለመከበሩም በተጨማሪ ፍርድ ቤቶች ላይ እምነት (public trust) እንዳይኖር ያደርጋል። ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ሰብዓዊ መብቶችን ከማስከበር እና የሕግ የበላይነት እንዲኖር ያላቸውን የማይተካ ሚና የመወጣት ግዴታ ያለባቸው በመሆኑና አንዱ መገለጫ የወሰኑትን ውሳኔ ማስፈጸም በመሆኑ ተከራካሪዎች በፍርድ ያረጋገጡትን መብት ሳይፈጸምላቸው ፍርዱ ያለውጤት ቀሪ እንዳይሆን የመከላከል የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ነው።

በሌላ በኩል የአፈጻጸም ችሎት በመርህ ደረጃ የቀረበን ውሳኔ የማስፈጸም ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ለአፈጻጸም የቀረበው ውሳኔ በህግ ዳኝነት ለመሥጠት ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ፣ የዳኝነት አካሉ በሕግ አግባብ የተቋቋመ እና የውሳኔው መሠረት የሆነው ነገር ሕልውና ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጥና በአጠቃላይ ለአፈጻጸም የቀረበው ውሳኔ የጸና እና የሚያስገድድ መሆኑን መመርመር አለበት። ዋነኛው የፍርድ መገለጫ የተከራካሪዎችን የፍሬ ነገር ሆነ የሕግ ክርክር ልዩነትን በጭብጥነት በመያዝ ለጉዳዩ የመጨረሻ እልባት መስጠት ነው። የአፈጻጸም ችሎት ተግባርም በፍርድ እልባት ያገኘውን መብት ማስፈጸም ነው። ስለዚህ ለአፈጻጸም የሚቀርበው ውሳኔ በዚህ ደረጃ ክርክሩን የቋጨና የአፈጻጸም ችሎቱን ወደሙግት ሂደት የማያስገባ መሆን ይገባዋል። ምክንያቱም አፈጻጸም ችሎት የተከራካሪዎችን መብት በራሱ እየወሰነ ሊያስፈጽም ስለማይችል ነው።

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረቡት ክስ ካለኝ 0.306 ሄክታር መሬት በቤተዘመድ ፊት የሠጠሁትን ሁለት ጥማድ የአደራ መሬት ሊያስረክቡኝ ይገባል ሲሆን የሻሸጎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02179 ታህሳስ 06 ቀን 2010 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ አመልካቾች በአደራ የያዙትን ሁለት ጥማድ

መሬት ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ወስኗል፤ ለአፈጻጸም መሠረት የሆነው ውሳኔም ይኸው ነው፡፡ አመልካቾች በውሳኔው መሠረት ሁለት ጥማድ መሬቱን የማስረከብ ግዴታ አለባቸው፤ ይህንን ካልፈጸሙ አፈጻጸም ችሎቱ በውሳኔው በተመለከተው መሠረት ይዞታውን እንዲያስረክቡ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ሁለት ጥማድ መሬቱ ላይ የተወሰነው ውሳኔ ቢፈጸም ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የሠበር አቤቱታው መሠረት ከፍርድ ውጭ ቤትና አራት ጥማድ መሬት ላይ እየተፈጸመ ነው የሚል ነው፡፡ አፈጻጸም ችሎቱም የቆርቆሮ ክዳን ቤት አንሰተው ፍርዱን እንዲፈጽሙ ማዘዙን ከአፈጻጸም ትዕዛዙ ግልባጭ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ ዋናውን ክስ ያቀረቡ ጊዜ ቤት እንዲፈርስላቸው ዳኝነት የጠየቁ ስለመሆኑ የፍርዱ ይዘት አያሳይም፡፡ ፍርድ ቤቱም በውሳኔ መልክ ያስቀመጠው ሁለት ጥማድ መሬት እንዲለቀቅ ነው፡፡ በሌላ በኩል ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው ፍርድ ገጽ 09 ሁለተኛ አንቀጽ ላይ አመልካቾች ቤት ሰርተው የተጠሪን መውጪያ የከለከሉ ስለመሆኑ መረጋገጡን አስፍሯል፡፡ በፍርድ የሠፈረው ነጥብ ዳኝነት ያልተጠየቀበትና በፍርዱ ውሳኔ ክፍል ላይ ያልተመለከተ በመሆኑ የሚፈጸመው የውሳኔ ክፍል አካል ነው ሊባል አይችልም፡፡ ቤት እንዲፈርስ ለመወሰን በይዞታው ላይ ቤት መሠራቱ ተገልጾ ቤቱ ላይ ግልጽ ዳኝነት ሊጠየቅበት ይገባል፡፡ ቤቱን የሠራው ወገንም ራሱን የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት ቤቱ በማን ይዞታ ላይ ተሰራ? በፈቃድ የተሰራ ነው ወይስ አይደለም? ሕጋዊ ውጤቱስ ምንድን ነው? የሚሉና ተያያዥ ጭብጦች ተይዘው ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ነው፡፡ አመልካቾች ቤት እንዲያፈርሱ በዚህ ረገድ ዳኝነት ያልተጠየቀበትና ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ ቤት እንዲፈርስ የተሠጠ ውሳኔ ስለሌለ ቤቱን እንዲያነሱ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ ከፍርዱ ውጭ የሆነና የአመልካቾች መብት የሚጎዳ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች አራት ጥማድ መሬት እንድንለቅ በአፈጻጸም እየተገደድን ነው በሚል ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ክርክሩ ቤቱ ያለበት ይዞታን የሚጨምር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ቤቱ ያለበት ይዞታ በአመልካቾች እጅ ሲቀር ለተጠሪ የሚያስረክቡት ይዞታ መጠን ምን ያህል ይሆናል የሚለው ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው ፍርድ ላይ የተመለከተው አዋሳኝ እንዲሁም በውሳኔው የተገለጸው ሁለት ጥማድ መሬት ከሚለው ጋር ተጣርቶ ሊፈጸም የሚችል በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14137 ግንቦት 14 ቀን 2012 ዓ/ም፤ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20779 መስከረም 29 ቀን 2012 ዓ/ም እና የሻሾጎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02179 ነሀሴ 15 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካቾች ቤት እንዲያነሱ/እንዲያፈርሱ በአፈጻጸም ሊገደዱ አይገባም በማለት ወስነናል፡፡

3. የሻሾጎ ወረዳ ፍርድ ቤት ለአፈጻጸም መነሻ በሆነው ውሳኔ ላይ የተመለከተውን ሁለት ጥማድ ይዞታ አመልካቾች ቤት ከሰሩበት ውጭ ያለውን በማጣራት እንዲያስፈጽም ጉዳዩን መልሠናል፡፡

4. ተጠሪ በይዞታቸው ላይ ቤት ከተሰራ መብታቸውን ክስ አቅርበው ከማስከበር ይህ ውሳኔ አያግድም፡፡

5. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የሻሾጎ ወረዳ ፍርድ ቤት በዚህ ውሳኔ መሠረት ያስፈጽም፡፡ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠ እገድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ተጠሪ የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡትም በዚህ መሠረት እንዲፈጽምላቸው ሲሆን አመልካቾች በበኩላቸው ለተጠሪ የተወሰነው በይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ከተመዘገበው በላይ የእኛን የይዞታ መሬትና መኖሪያ ቤት ቤትን ጭምር ለተጠሪ አሳልፎ የወሰነ በመሆኑ በተጠሪ ይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በተመለከተው አግባብ ፍርዱ እንዲፈጸም ጠይቀዋል፡፡ የአፈጻጸም ክርክሩን ሲመራ የነበረው የሻሾጎ ወረዳ ፍርድ ቤት ቤት አመልካቾች እንዲለቁ የተወሰነው መውጪያ መግቢያ ላይ የሠሩትን ቤት ጨምሮ ስለመሆኑ በውሳኔው የተመለከተ በመሆኑና አመልካቾችም ቤቱን ለማንሳት ጊዜ እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ ቆይተው ቤቱ ያለበት መሬት የእኛ ነው ማለታቸው ተገቢነት የሌለው ነው በማለት ቤቱ ተነስቶ እንዲፈጽም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በይግባኝ እና በሠበር የተመለከቱት በየደረጃው የሚገኙ ፍርድ ቤቶች የአፈጻጸም ችሎት ውሳኔን አጽንተዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ከተወሰነው ሁለት ጥማድ መሬት ውጭ መወጪያ መግቢያ በሚል አራት ጥማድ መሬታችን አስረክቡ መባላችን ሆነ ቤት አፍረሱ መባሉ ከፍርዱ ውጭ የተሰጠ ትዕዛዝ ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ቤት ያፍርሱ መባሉ በውሳኔውና በአፈጻጸም ክሱ መሠረት የተጠየቀ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ ያቀረቡት መልስ ይዘቱ አመልካቾች በያዙት ሁለት ጥማድ መሬት ቤት ሰርተው የሚገኙ መሆኑ ተረጋግጦ በውሳኔው መሠረት እንዲፈጸም የተወሰነ ነው፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ሊፀና ይገባል ብለዋል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የአፈጻጸም ክርክሩ ለአፈጻጸሙ መነሻ የሆነውን ፍርድ እና የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ የተመራ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው አመልካቾች ሁለት ጥማድ የይዞታ መሬት ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ነው። ተጠሪ የአፈጻጸም ክስ ያቀረቡትም በዚህ መሠረት እንዲፈጽምላቸው ነው። አሁን አከራካሪ ሆኖ የዚህን ችሎት ምላሽ የጠየቀው አመልካቾች ቤት እንዲያፈርሱ ተብሎ በአፈጻጸም ትዕዛዝ መሠጠቱ በፍርዱ መሠረት እየተፈጸመ ያለ መሆን አለመሆኑ ነው። በዋናነት ሥነ-ሥርዓት ሕግ የተቀረጸው ሠዎች ግጭቶችን ሠላማዊ በሆኑ ሁኔታ እንዲፈቱ ለማስቻል (peaceful resolution of disputes)፣ መብታቸውን የሚያስከብሩበት ዘዴ እንዲኖርና ፍርድ ቤቶች ክርክርን ፍትሐዊ እና ወጭ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት እንዲችሉ ነው። የአፈጻጸም ችሎት ጉዳዩን መምራት ያለበት የፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና ተከታዮቹን ድንጋጌዎችና ለአፈጻጸም መሠረት የሆነውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ሲሆን ውጤቱም ሠዎች በፍርድ ያገኙትን መብት ማስፈጸም ነው። በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 212 መሠረት የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ያለበት ፍርድ በይግባኝ ካልተለወጠ የጸና እና ሊፈጸም የሚችል ፍርድ እንደሆነ ተመላክቷል። በህግ የተቋቋመ የዳኝነት አካል ከነግድፈቱም ቢሆን የሰጠው ውሳኔ መከበር እና መፈጸም አለበት። ፍርድ የማይፈጸም ከሆነ የሕግ የበላይነት መገለጫ የሆነውን ዋናውን የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት አለመወጣት ይሆናል። ዜጎች በፍትሕ ሥርዓቱ የሚጠቀሙት መብታቸውን ለማስከበር ነው። የመብት ማስከበር መሠረቱ ደግሞ ፍርድን ከማናቸውም መሠናክል ነጻ በማድረግ ማስፈጸም ነው። ፍርድ ቤቶች በዚህ አግባብ ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ ዜጎች በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 37 ያገኙት ፍትሕ የማግኘት መብትን ማረጋገጥ እና ማስፈጸም አይቻልም። ውጤቱ ደግሞ መብት ካለመከበሩም በተጨማሪ ፍርድ ቤቶች ላይ እምነት (public trust) እንዳይኖር ያደርጋል። ስለሆነም ፍርድ ቤቶች ሰብዓዊ መብቶችን ከማስከበር እና የሕግ የበላይነት እንዲኖር ያላቸውን የማይተካ ሚና የመወጣት ግዴታ ያለባቸው በመሆኑና አንዱ መገለጫ የወሰኑትን ውሳኔ ማስፈጸም በመሆኑ ተከራካሪዎች በፍርድ ያረጋገጡትን መብት ሳይፈጸምላቸው ፍርዱ ያለውጤት ቀሪ እንዳይሆን የመከላከል የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት ነው።

በሌላ በኩል የአፈጻጸም ችሎት በመርህ ደረጃ የቀረበን ውሳኔ የማስፈጸም ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ለአፈጻጸም የቀረበው ውሳኔ በህግ ዳኝነት ለመሥጠት ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ፣ የዳኝነት አካሉ በሕግ አግባብ የተቋቋመ እና የውሳኔው መሠረት የሆነው ነገር ሕልውና ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጥና በአጠቃላይ ለአፈጻጸም የቀረበው ውሳኔ የጸና እና የሚያስገድድ መሆኑን መመርመር አለበት። ዋነኛው የፍርድ መገለጫ የተከራካሪዎችን የፍሬ ነገር ሆነ የሕግ ክርክር ልዩነትን በጭብጥነት በመያዝ ለጉዳዩ የመጨረሻ እልባት መስጠት ነው። የአፈጻጸም ችሎት ተግባርም በፍርድ እልባት ያገኘውን መብት ማስፈጸም ነው። ስለዚህ ለአፈጻጸም የሚቀርበው ውሳኔ በዚህ ደረጃ ክርክሩን የቋጨና የአፈጻጸም ችሎቱን ወደሙግት ሂደት የማያስገባ መሆን ይገባዋል። ምክንያቱም አፈጻጸም ችሎት የተከራካሪዎችን መብት በራሱ እየወሰነ ሊያስፈጽም ስለማይችል ነው።

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በአመልካቾች ላይ ያቀረቡት ክስ ካለኝ 0.306 ሄክታር መሬት በቤተዘመድ ፊት የሠጠሁትን ሁለት ጥማድ የአደራ መሬት ሊያስረክቡኝ ይገባል ሲሆን የሻሸጎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02179 ታህሳስ 06 ቀን 2010 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔ አመልካቾች በአደራ የያዙትን ሁለት ጥማድ

መሬት ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ወስኗል፤ ለአፈጻጸም መሠረት የሆነው ውሳኔም ይኸው ነው፡፡ አመልካቾች በውሳኔው መሠረት ሁለት ጥማድ መሬቱን የማስረከብ ግዴታ አለባቸው፤ ይህንን ካልፈጸሙ አፈጻጸም ችሎቱ በውሳኔው በተመለከተው መሠረት ይዞታውን እንዲያስረክቡ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታቸው ሁለት ጥማድ መሬቱ ላይ የተወሰነው ውሳኔ ቢፈጸም ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የሠበር አቤቱታው መሠረት ከፍርድ ውጭ ቤትና አራት ጥማድ መሬት ላይ እየተፈጸመ ነው የሚል ነው፡፡ አፈጻጸም ችሎቱም የቆርቆሮ ክዳን ቤት አንሰተው ፍርዱን እንዲፈጽሙ ማዘዙን ከአፈጻጸም ትዕዛዙ ግልባጭ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ ዋናውን ክስ ያቀረቡ ጊዜ ቤት እንዲፈርስላቸው ዳኝነት የጠየቁ ስለመሆኑ የፍርዱ ይዘት አያሳይም፡፡ ፍርድ ቤቱም በውሳኔ መልክ ያስቀመጠው ሁለት ጥማድ መሬት እንዲለቀቅ ነው፡፡ በሌላ በኩል ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው ፍርድ ገጽ 09 ሁለተኛ አንቀጽ ላይ አመልካቾች ቤት ሰርተው የተጠሪን መውጪያ የከለከሉ ስለመሆኑ መረጋገጡን አስፍሯል፡፡ በፍርድ የሠፈረው ነጥብ ዳኝነት ያልተጠየቀበትና በፍርዱ ውሳኔ ክፍል ላይ ያልተመለከተ በመሆኑ የሚፈጸመው የውሳኔ ክፍል አካል ነው ሊባል አይችልም፡፡ ቤት እንዲፈርስ ለመወሰን በይዞታው ላይ ቤት መሠራቱ ተገልጾ ቤቱ ላይ ግልጽ ዳኝነት ሊጠየቅበት ይገባል፡፡ ቤቱን የሠራው ወገንም ራሱን የመከላከል መብቱ ተጠብቆለት ቤቱ በማን ይዞታ ላይ ተሰራ? በፈቃድ የተሰራ ነው ወይስ አይደለም? ሕጋዊ ውጤቱስ ምንድን ነው? የሚሉና ተያያዥ ጭብጦች ተይዘው ውሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ነው፡፡ አመልካቾች ቤት እንዲያፈርሱ በዚህ ረገድ ዳኝነት ያልተጠየቀበትና ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ ቤት እንዲፈርስ የተሠጠ ውሳኔ ስለሌለ ቤቱን እንዲያነሱ በሚል የተሰጠው ትዕዛዝ ከፍርዱ ውጭ የሆነና የአመልካቾች መብት የሚጎዳ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾች አራት ጥማድ መሬት እንድንለቅ በአፈጻጸም እየተገደድን ነው በሚል ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ክርክሩ ቤቱ ያለበት ይዞታን የሚጨምር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ቤቱ ያለበት ይዞታ በአመልካቾች እጅ ሲቀር ለተጠሪ የሚያስረክቡት ይዞታ መጠን ምን ያህል ይሆናል የሚለው ለአፈጻጸም መነሻ የሆነው ፍርድ ላይ የተመለከተው አዋሳኝ እንዲሁም በውሳኔው የተገለጸው ሁለት ጥማድ መሬት ከሚለው ጋር ተጣርቶ ሊፈጸም የሚችል በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 14137 ግንቦት 14 ቀን 2012 ዓ/ም፤ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 20779 መስከረም 29 ቀን 2012 ዓ/ም እና የሻሾጎ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02179 ነሀሴ 15 ቀን 2011 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካቾች ቤት እንዲያነሱ/እንዲያፈርሱ በአፈጻጸም ሊገደዱ አይገባም በማለት ወስነናል፡፡

3. የሻሾጎ ወረዳ ፍርድ ቤት ለአፈጻጸም መነሻ በሆነው ውሳኔ ላይ የተመለከተውን ሁለት ጥማድ ይዞታ አመልካቾች ቤት ከሰሩበት ውጭ ያለውን በማጣራት እንዲያስፈጽም ጉዳዩን መልሠናል፡፡

4. ተጠሪ በይዞታቸው ላይ ቤት ከተሰራ መብታቸውን ክስ አቅርበው ከማስከበር ይህ ውሳኔ አያግድም፡፡

5. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡ የሻሾጎ ወረዳ ፍርድ ቤት በዚህ ውሳኔ መሠረት ያስፈጽም፡፡ይጻፍ
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠ እገድ ካለ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-199400 ቀን፡

03/02/2014ዓ.ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ አበበ አድገህ-ጠበቃ ዘመኑ ተሰጋ ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡- 1. ወ/ሮ ዘሪቱ ደርሰህ
2. አቶ ፍሬዉ ተገኝ
3. አቶ በቃሉ ተገኝ
4. አቶ መስፍን ተገኝ
5. አቶ መልሰዉ ተገኝ
6. አቶ መኮንን ተገኝ
7. አቶ አያሌዉ ተገኝ
8. አቶ ሽታ ተገኝ
9. ወ/ሮ እቴነሽ ተገኝ

ጠበቃ፡- አሊ መሀመድ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል መኖሩ በተካደ ጊዜ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚገባውን ውል አይነት የሚመለከት ነዉ፡፡አመልካች በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ በመሰረቱት ክስ ከ1ኛ ተጠሪ እና ከተራ ቁጥር 2-5 ድረስ የተጠቀሱ ተጠሪዎች አባት ከሚች አቶ ተገኘ ፀሐይ ጋር በቀን 13/10/1987 ዓ/ም በተጻፈ የቤት ሽያጭ በደንበጫ ከተማ ዉስጥ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰዉን ስፋቱ 5 ሜትር በ10 ሜትር ወይም 50 ካሬ ሜትር ላይ የተሰራ በሚች አቶ ተገኘ ፀሐይ ስም ተመዝግቦ የሚገኘዉን 32 ዚንጎ የቆርቆሮ ቤት በብር 10,000.00 ሸጠዉልኛል፡፡ገንዘቡን በእለቱ ተረክበዉ የሽያጭ ዉሉን በደንበጫ ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት አስገብተነዉ በፋይሉ ዉስጥ ይገኛል፡፡ቤቱን በግዥ ያገኘሁ ስለመሆኑ በተለያዩ ጊዜ የታመነ እና የተረጋገጠ ቢሆንም አሁን ላይ በቤቱ ለመጠቀም ስፈልግ የተለያዩ ተግባራትን እንዳላከናዉንና የቤቱ ስመ ሀብት በስሜ ዞሮ እንዳይመዘገብ ተጠሪዎች ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ስለሆነም ተጠሪዎች በሚመለከተዉ አካል ፊት ቀርበዉ የቤቱን ስመ ሀብት በስሜ እንዲያዛዉሩልኝ እንዲወሰንልኝ፡፡ዉሉ የሚፈርስበት ምክንያት አለ ከተባለም ቤቱ በአሁኑ ጊዜ የሚያወጣዉን የዕለት ዋጋ ብር 200,000.00 እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማስቀደም ለክሱ በሰጡት መልስ የቤት ሽያጭ ዉል የለም፡፡ዉሉ አለ እንኳን ቢባል ስመ ንብረት የማዛወር ጉዳይ አስተዳደራዊ ጉዳይ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣኝ የለዉም፡፡አመልካች ዉል ይፈጸምልኝ ዳኝነት የጠየቁት ዉሉ ከተደረገ ከ23 ዓመት በኋላ በመሆኑ ክሱ በ10 ዓመት ይርጋ የታገደ ነዉ፡፡ዉል ነዉ ተብሎ የቀረበዉ ሰነድ 1ኛ ተጠሪም ሆኑ ከተራ ቁጥር 1-5 የተጠቀሰን ተጠሪዎች ወላጅ አባት ያልፈረሙበት ነዉ፡፡ማንበብና መጻፍ የማይችሉ ሆነዉ እያለ በእጅ ጽሁፍ ተፈርሞ በሀሰት የተዘጋጀ በመሆኑ እንደረቂቅ የሚቆጠር ነዉ፡፡የሚጸና የቤት ሽያጭ ዉል የለም፡፡የቤት ሽያጭ ዋጋ አልተከፈለም፡፡አመልካች ቤቱን አልተረከቡም፡፡ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 መሰረት በዉል አዋዋይ ተቋም ያልጸደቀና ያልተመዘገበ በመሆኑ ፈራሽ ነዉ፡፡ብር 10,000.00 ገዝቻለሁ እያሉ ብር 200,000.00 ይከፈለኝ ማለታቸዉ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡ከ6ኛ እስከ 9ኛ ከተጠቀሰን ተጠሪዎች የሚጠይቁት ዳኝነት ግልጽ አይደለም በማለት ክሱ ዉድቅ እንዲደረግላቸዉ በመጠየቅ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 01-73063 ላይ አስቀድሞ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ዉሳኔ በመስጠት ዉድቀ ካደረገ በኋላ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ በቀን 05/03/2012ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ በቀን 13/10/1987ዓ/ም የተጻፈ የቤት ሽያጭ ዉል በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ እና በተጠሪዎች አዉራሽ በሚች አቶ ተገኘ ፀሐይ መካከል ተደርጎ የሽያጩን ገንዘብ መቀበላቸዉ በምስክሮች ቃልና በሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል፡፡ሆኖም ተጠሪዎች ዉሉ የለም በማለት ክደዉ ስለተከራከሩ የቤት ሽያጭ ዉሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 አኳያ ዉል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ያልተመዘገበ ወይም በፍርድ ቤት ፊት ያልተፈጸመ በመሆኑ አመልካች ዉል እንዲጸናላቸዉ ወይም ስመ ንብረት እንዲዞርላቸዉ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለዉም፡፡ነገር ግን አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች አስረክበዉ በሽያጭ ዉሉ ምክንያት አመልካች ለ1ኛ ተጠሪ እና ለሚች አቶ ተገኘ ፀሐይ የከፈሉትን ብር 10,000.00(አስር ሺህ ብር) ተጠሪዎች በአንድነት ሊመልሱላቸዉ ይገባል በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 50815 ላይ በቀን 27/05/2012ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞባቸዋል፡፡እንዲሁም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ ችሎቱ በመ/ቁጥር 03-97032 ላይ በቀን 05/10/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ሰርዞባቸዋል፡፡

አመልካች በቀን 06/04/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታቸዉ ይዘት በአጭሩ፡-ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቤት ሽያጭ ዉሉ 1ኛ ተጠሪና ሟች ከ2-9 የተጠቀሱ ተጠሪዎች አባት ቤቱን ከሸጡልኝ በኋላ በቤቱ ማህደር ዉስጥ ተያይዞ የባለስልጣኑ ማህተም አርፎበት ጸድቆ የሚገኝ ስለሆነ ዉሉ የዉል ምዝገባ ሂደቱን በሚመለከተዉ ባለስልጣን አካል ፊት ተደረጎና ተመዝግቦ ያለፈና የቀረዉ የሥም ማዞር ሂደት ብቻ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ስመ ንብረት ማዞር ደግሞ ከቤት ሽያጭ ዉል ምዝገባ በኋላ ያለ ቀሪ የሥራ ክንዉን ሂደት እንጂ ምዝገባ አይደለም፡፡የቤት ሽያጭ ዉል ተመዝግቧል ወይም ሥርዓቱን ጠብቆ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ተከናዉኗል ሊባል የሚችለዉ በስ/መ/ቁጥር 16109 እና 36740 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉምና በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723፣1680፣1681 እና 2878 መሰረት ተዋዋዮች የሽያጭ ዉሉን ይዘዉ ቀርበዉ የሽያጭ ስምምነታቸዉ ሲገልጹና ዉሉ ከማህደሩ ጋር ሲያያዝና የባለስልጣኑ ማህተም ሲያርፈበት በመሆኑ አከራካሪዉ ዉልም በዚህ አግባብ የተፈጸመ ሆኖ እያለ በዉል አዋዋይ ፊት ተርጎ የተመዘገበ ዉል ስላልሆነ ረቂቅ ነዉ በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሠጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡ከዚህ ቀደም በነበረዉ የሑክት ይወገድልኝ ክርክር የተጠሪዎች አባት ቤቱን የሸጡልኝ መሆኑን አምነዋል፡፡ስለሆነም የቤት ሽያጭ ዉሉ በሚመለከተዉ ማዘጋጃ ቤት ፊት ቀርቦ የተመዘገበና ፀድቆ ማህተም የተደረገበት ስለሆነ ተጠሪዎች እንደዉሉ እንዲፈጽሙ አለመወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ተብሎ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታቸዉን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ቤት ሽያጭ ዉል ስለመኖሩ በአመልካች የቀረቡ ምስክሮች አስረድተዉ ባለበትና ዉሉም በሚመለከተዉ ማዘጋጃ ቤት ቀርቦ ማህተም ተደርጎበት ከቤቱ ማህደር ጋር የተያያዘ መሆኑን ተከትሎ አመልካች ቤቱን ተረክበዉ እየተጠቀሙ መሆናቸዉ በተገለጸበት ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት አልተመዘገበም በሚል ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት እንዲመለሱ የተወሰነበት አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት እንዲመረመር ትዕዛዝ በመስጠቱ ተጠሪዎች በቀን 08/07/2013 ዓ/ም የተጻፈ በአጭሩ የሚከተለዉን መልስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች ለክርክሩ መነሻ የሆነዉን ዉል ከመካድ ባለፈ በሰነዱ ላይ ያለዉ ፊርማ የሟች እንዳልሆነ በመግለጽ በግልጽ ክደን ተከራክረናል፡፡በዉሉ ላይ ያለዉ ፊርማ በፎረንሲክ ቢመረመርም ፊርማዉ የሟች መሆን አለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡እንዲሁም ዉሉ በዉል አዋዋይ ፊት ያልተደረገና ያልተመዘገበ ነዉ፡፡እነዚህን ምክንያቶች ተቀብሎ የስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723 ስር የተደነገገዉን መሰረት አድርጎ የሰጠዉ ዉሳኔ የስ/መ/ቁጥር 21448 የተሰጠዉን አስገዳጅ ትርጉም መሰረት ያደረገ ነዉ፡፡ዉሉ በቤቱ

ማህደር ውስጥ የተያያዘውና ማህተም ያረፈበት ያለሚች ፈቃድና እውቅና ውጭ በሕገ ወጥ መንገድ በአመልካች ጠያቂነት ነዉ እንጂ በአመልካችና በሚች መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ አመልካች ክስ የቀረበበትን ቤት በፀናና ሕጋዊ ዉጤት ባለዉ የሽያጭ ዉል የገዛዉ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለባቸዉ አመልካች ሆነዉ እያለ ሕጋዊ ተቀባይነትና ተዓማኒነት ያለዉን ማስረጃ በማቅረብ ያላስረዱ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም በቀን 27/07/2013 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ በክልሉ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ ፍሬ ነገርን የማረጋገጥ ሥልጣን የተሰጠዉ የስር ፍርድ ቤት እንዳረጋገጠዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቤት ሽያጭ ዉል በማዘጋጃ ቤት ዉስጥ በሚገኝ ማህደር ዉስጥ የሚገኝ መሆኑ ቢረጋገጥም ዉሉ የማይንቀሳቀስ ንብረት የሆነዉን ቤት በሽያጭ ማስተላለፍን የሚመለከት እንደመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 ስር በተደነገገዉ አግባብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት ያልተደረገ (ያልተረጋገጠ) እና ያልተመዘገበ(non-authenticated) እንደሆነ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡
እንደሚታወቀዉ በአገራችን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሕዝቡ ዘንድ ካለዉ ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የተነሳ የፍትሐ ብሔር ሕጋችንና የፍትሐ ብሔር ፍትህ አስተዳደሩ በአጠቃላይ ለዜጎች የማይንቀሳቀስ የንብረት መብት ልዩ ጥበቃ ያደርጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ከዘረጋዉ የጥበቃ ሥርዓት ዉስጥ አንዱ በፍትሐ ብሔር ሕጉ የተለያዩ አናቅጽ የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማስተላለፍ የሚደረጉ ዉሎች መከተል ያለባቸዉ ፎርማሊቲዎች እና ስለ ምዝገባ የተደነገገዉ ነዉ፡፡ (አንቀጽ 1553-1646 እንዲሁም 1723፣ 2878 እና 3052 ይመለከቷል)፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የየራሳቸዉ የሆኑ ዓላማዎች ያላቸዉ ቢሆንም፤ አጠቃላይ ዓላማቸዉ ግን ለማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ልዩ ጥበቃ በመስጠት እነዚህን ንብረቶች በተመለከተ ባለይዞታዉ መብቱን ሲያገኝ ወይም ንብረቱ በሆነ ምክንያት ወደ ሌላ ሦስተኛ ወገን በሚያስተላልፍበት ወቅት የመመዝገብ ስልጣን በተሰጠዉ መንግስታዊ አካል ካልተመዘገበ ሕግ ፊት የሚጸና መብት እንዳይኖረዉ በማድረግ ዜጎች በዚህ ግዙፍነት ባለዉ ንብረት ላይ ያላቸዉን መብት ከፍላጎታቸዉ ዉጪ በሆነ መንገድ እንዳያጡ ጥበቃ ለመስጠት፤ ብሎም ንብረቱ ወይም ንብረቱን የሚመለከቱ መብቶች በዉል ሊተላለፉ የሚችሉ መሆን ያለመሆኑንም በማጣራት የዉሉን ሕጋዊነት ለማረጋገጥ ጭምር ስለመሆኑ ከየድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ ከሚከናወኑት ሕጋዉያን ተግባራት ጋር በተያያዘ ምዝገባ ወይም ዉሉ በሚመለከተዉ አካል ዘንድ እንዲረጋገጥ የግድ ከሚልባቸዉ ዉስጥም አንዱ በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 1723(1) ስር የተመለከተዉ ድንጋጌ ሲሆን፣ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስተላለፍ

የሚደረጉ ውሎች በጽሑፍና ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠዉ አካል ፊት መሆን አለበት፡፡ ሕግ አዉጪዉ ይህ እንዲሆን የፈለገበት ምክንያትም ዉሉ በተዋዋዮች መካከል ስለመደረጉ ለማረጋገጥ (certainty in transactions) ስለመሆኑ በዙሪያዉ ከተፃፉት አንዳንድ ጽሑፎች መገንዘብ የሚቻል ሲሆን፤ ይህ ሰበር ችሎትም በሰ/መ/ቁጥር 36887 ላይ በሰጠዉ የህግ ትርጉም በዚህ ድንጋጌ መሠረት የሚከናወን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ምዝገባ ዓላማ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ዉል መኖሩን ለማስረዳት ስለመሆኑ ወስኗል፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 ስር የተደነገገዉ ፎርማሊቲ በተዋዋዮች መካከል በፀና አካኋን የተደረገ ዉል መኖሩን ለማረጋገጥና በዋናነት የተዋዋዮቹን መብት ለመጠበቅ የተደነገገ ሲሆን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2878 እና በሌሎች ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተመለከተዉ ምዝገባ (Registration) ደግሞ ተዋዋዮች የማይነቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ለማስተላለፍ ወይም ባንድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የአላባ ጥቅም መብት ወይም የመያዣ ወይም የሌላ አገልግሎት መብት ለመቋቋም ወይም በድንጋጌዎቹ ላይ የተመለከቱትን ሌሎች መብቶችን ለመመስረት ዉል በመዋዋላቸዉ የሦስተኛ ወገኖች መብትና ጥቅም እንዳይነካ ለሦስተኛ ወገኖች ጥበቃ ለማድረግ ነዉ፡፡ይህ አይነት ምዝገባ (Registration) የሚከናወነዉም ንብረቱ ተመዝግቦ በሚገኝበት አስተዳደር አካል ዘንድ በሚገኘዉ የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ ነዉ፡፡በመሆኑም ተዋዋዮች የቤት ሽያጭ ዉል የለም በሚል ዉሉን ተካክደዉ በሚከራከሩበት ጊዜ በእርግጥም በፀና አካኋን የተደረገ ዉል ማድረግ አለማድረጋቸዉን ? ዉሉ የተደረገዉ መቼ ነዉ? የሽያጭ ዉል ከሆነ በምን ያህል ዋጋ ነዉ የተደረገዉ? ለዉሉ ምክንያት የሆነዉ ምን ዓይነት ንብረት ነዉ? የትስ የሚገኝ ነዉ? የሚሉና ንብረቱን ለማስተላለፍ መብት ባለዉ ሰዉ መፈረም አለመፈረሙን የሚመለከትና መሰል የይዘት ክርክሮች የተነሱ እንደሆነ ይህን ለማጣራት ሊቀርብ የሚገባዉ ማስረጃ ዓይነትም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 ስር በተደነገገዉ አግባብ በጽሑፍ ሆኖ ዉል ለማዋዋል ሥልጣን ባለዉ አካል ፊት የተደረገ ዉል ሊሆን ይገባል፡፡ ይህን አስመልክቶም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 78398 በሰ/መ/ቁጥር 188881 እና በሌሎችም ላይ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

በተያዘዉም ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ የቤት ሽያጭ ዉል በመካከላችን አልተደረገም በማለት 1ኛ ተጠሪ በራሳቸዉ ሌሎች ተጠሪዎች ደግሞ አባታቸዉን ወርሰዉ ባገኙት የወራሽነት መብት ክደዉ መከራከራቸዉ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡አመልካች ደግሞ የቤት ሽያጭ ዉል አለ ብለዉ ክስ በማቅረብ እንደዉሉ እንዲፈጸምላቸዉ ዳኝነት መጠየቃቸዉ ግልጽ ነዉ፡፡አንድን ፍሬ ነገር ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ሸክምን ከሚመለከተዉ መሠረታዊዉ መርህ (Basic Principle of Burden of Proof) መረዳት እንደሚቻለዉ አንድ አከራካሪ ፍሬ ነገር አለ ወይም የለም ብሎ የሚከራከር ሰዉ ፍሬ ነገሩ መኖሩን ወይም አለመኖሩን በማስረጃ የማስረዳት ሸክም(ግዴታ) አለበት፡፡ (የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 258-260 እና የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2001 ይመለከቷል)፡፡በዚህ መሰረት አመልካች ይህንን ፍሬ ነገር ለማስረዳት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 መሰረት በዉል አዋዋይ ፊት ተደርጎ የተመዘገበ (authenticated) ዉል ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ሆኖም አመልካች በዚህ አግባብ የተደረገ ዉል ለስር ፍርድ ቤት አላቀረቡም፡፡ዉሉ በማዘጋጃ ቤት በሚገኝ ማህደር ዉስጥ ስለሚገኝ

እንደተመዘገበ ይቆጠራል ብለዉ ያቀረቡት ክርክርም ቢሆን ይሕ ተግባር ተፈጽሞ ቢሆን እንኳን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 ስር የተደነገገዉን የፎርም ስርዓት የሚተካ ካለመሆኑም በላይ ይህ ተፈጸመ ያሉት ስርዓት የተዋዋዮቹን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ የተዘረጋ ስርዓት ባለመሆኑ ይህ መከራከሪያቸዉ በክልሉ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት በማጣቱ የተፈጸመ ስህተት አላገኘንም፡፡

ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1723/1 መሰረት በዉል አዋዋይ ፊት ተደርጎ የተመዘገበ የቤት ሽያጭ ዉል በማስረጃነት አቅርበዉ ባለማስረዳታቸዉ ተጠሪዎች የቤት ሽያጭ ዉል አልተደረገም በማለት ክደዉ የተከራከሩትን ክርክር ተቀብሎ አመልካች በዉሉ መሰረት እንዲፈጸምላቸዉ ያቀረቡትን ዳኝነት ጥያቄ ዉድቅ በማድረግ የሰጠዉ ዉሳኔ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝና በሰበር ይሄዉ ዉሳኔ መጽናቱ ሕግን መሰረት ያደረገ ነዉ ከሚባል በስተቀር የተፈጸመ ስህተት ባለመኖሩ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. ምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-73063 ላይ በቀን 05/03/2012ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 50815 ላይ በቀን 27/05/2012ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-97032 ላይ በቀን 05/10/2012 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ.መ.ቁ. 199004
መስከረም 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ዘውዱ ሸፈራው

ተጠሪ፡- አቶ ፍሬው በቀለ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 57013 በሕዳር 11 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 329068 ጥር 28 ቀን 2012 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 332581 በመጋቢት 07 ቀን 2012 የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው።

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውልን መነሻ ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ሸዋ ዞን ሉሜ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው። በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል። የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- በ460 ካ.ሜ ላይ ያረፈ መኖሪያ ቤት በ12/03/2011 ዓ.ም በተዛፊ ውል ከተጠሪ ላይ በብር 250.000 ገዝቶ ሙሉ በሙሉ ገንዘቡን የከፈለ መሆኑን፤ በስሙም ቦርታ ቁጥር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

4378/2011 ማስረጃ የተሰጠው መሆኑን፤ ተጠሪ በውሉ መሰረት ቤቱን እስከ 12/03/2011 ዓ.ም. ለመልቀቅ የተስማማ ቢሆንም ቤቱን የለቀቀው በ03/09/2011 ዓ.ም መሆኑን፤ ተጠሪ በቤቱ ላይ የነበረውን ባለ 3 ፌዝ መብራት ቆጣሪ የወሰደ መሆኑን በመግለጽ ቆጣሪው የቤቱ አካል ስለሆነ እንዲመልስለልኝ እና የቤቱን ኪራይ ብር 30,000 እንዲከፍል ይወሰንልኝ በሚል ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው።

የአሁን ተጠሪ በሰጠው መልስ በግራ ቀኞችን መካከል የኪራይ ውል የለም፤ ባለ 3 ፌዝ መብራት ቆጣሪ የተባለው ከቤቱ ጋር ለአመልካች አልሸጥኩም፤ ቆጣሪው ለንግድ ቤት በኢትየጵያ ልማት ባንክ እና መብራት ሀይል በጻፉልኝ ድጋፍ ለዳቦ ቤት ተብሎ የተሰጠው ነው፤ የዳቦ ማሽኑ ያለቆጣሪው ስለማይሰራ እና የቤቱ አካል አለመሆኑን በመግለጽ የአመልካች ክስ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ባለ 3 ፌዝ የተባለው ቆጣሪ ተጠሪ የሸጠው ዳቦ ቤት ላይ የነበረ እና ተጠሪ ሲጠቀምበት የቆየ ነው፤ተጠሪ ዳቦ ቤቱን በሚሸጥበት ጊዜ ከ3 ፌዝ ቆጣሪ ጋር አብሮ መሸጡ ተረጋግጧል፤ በግራ ቀኙ መካከል የኪራይ ውል መኖሩ ተረጋግጧል፤ በመሆኑም ተጠሪ ከዳቦ ቤቱ ላይ ነቅሎ የወሰደውን ባለ 3 ፌዝ ቆጣሪ እንዲመልስ እና ከ12/04/2011 ዓ.ም እስከ 03/09/2011 ዓ.ም ያለውን የ5 ወር የቤት ኪራይ በወር 6,000 ታስቦ በአጠቃላይ ብር 30,000 ለአመልካች ይክፈል በማለት ወስኗል።

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርበዋል። ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤትም አመልካች ከተጠሪ በግዥ ያገኘው መኖሪያ ቤት የራሱ የሆነ ቆጣሪ ያለው መሆኑን በግራቀኙ አልተካደም፤ በፍታብሔር ህግ 1132(1) መሰረት የመኖሪያ ቤት የተፈቀደው ቆጣሪ መብራት ከቤቱ ጋር ለአመልካች ተላልፏል፤ ክርክር ያስነሳው ቆጣሪ ግን የንግድ ቤቱ መሆኑ ግራ ቀኙ ባልተካካዱበት የስር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ የሸያጭ ውል ላይ የሌለውን ተጠሪ ዳቦ ቤቱን ሲሸጥ ቆጣሪውንም ጭምር እንደሸጠ የሚቆጠር ነው እንዲሁም የሸያጭ ውሉ በ12/04/2011 ዓ.ም ከተደረገበት ጀምሮ አመልካች በዚህ ቤት ውስጥ ለመቆየት መብት የለውም፤ የቤት ኪራይ ውል ስለመኖሩ በሰው ምስክሮች ተረጋግጧል፤ አመልካች ከቤቱ ውስጥ በ12/04/2011 ዓ.ም ለመውጣት የተስማሙ እና 03/09/2011 ዓ.ም ድረስ የቆየ ሲሆን ይህም አራት ወር ከ21 ቀናት ሲሆን የአንድ ወር በ6,000 ሺህ ብር ሲታሰብ 28,200 ስለሚሆን አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት በማሻሻል ወስኗል። ይህንኑ ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ጸንቷል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- ክርክር ያስነሳው ቆጣሪ የንግድ ቤት መሆኑ ግራ ቀኙ ያልተካካዱ እና በማስረጃ ጭምር የተረጋገጠ ነው፤ ተጠሪ ቤቱን በሚሸጥልኝ ጊዜ ዳቦ ቤትም ሆነ የዳቦ ስራ አልነበረውም የዳቦ ማሽኑ የገዛው ቤቱን ሸጦልኝ ስም ካዛወረልኝ በኋላ በባንክ ብድር ነው፤ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት ክርክር ያስነሳው ቤት ላይ ያለው ባለ 3 ፌዝ ቆጣሪ የቤቱ አካል አይደለም በማለት የወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- ክርክር ያስነሳው ባለ 3 ፌዝ ቆጣሪ የዳቦ ማሽን አካል እንጂ የተሸጠው ቤት አካል አይደለም፤ በቀን 12/03/2011 ዓ.ም የተደረገው ውል የቤት ሽያጭ እንጂ የዳቦ ማሽን ድርጅት ሽያጭ ውል አይደለም፤ የዳቦ ማሽኑ ቀድሞ የነበረ ነው፤በመሆኑም የስር ክፍተኛ፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው።

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የቻልነው የሚያከራክረው በሽያጭ ከተላለፈው ቤት ላይ ያለው ባለ 3 ፌዝ ቆጣሪ ከቤቱ ጋር አልተሸጠም በመሆኑም ተጠሪ ከቤቱ ላይ ነቅሎ መውሰዱ ተገቢ አይደለም የኪራይ ገንዘብም ያልተከፈለ ይከፈለኝ ሲል የአሁን አመልካች ክስ ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ ራሱን የቻለ ቆጣሪ ያለውና ባለ 3 ፌዝ ቆጣሪው ግን የተሸጠው ቤት አካል ሆኖ ባለመሆኑ ልመልስ አይገባም በሚል ተከራክረዋል።አከራካሪውን ቤት አመልካች ህዳር 12 ቀን 2011 ዓም በተደረገ የሽያጭ ውል ሲገዙ ውሉ የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ውል ተብሎ መዘጋጀቱ ግራ ቀኙ ያልተካካዱበት ነጥብ ሲሆን ማስረጃን የመስማት፤የመመርምርና የመመዘን ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ማረጋገጣቸውን በውሳኔያቸው ላይ አመልክተዋል።

አመልካች ቤቱን ሲገዙ አከራካሪውን ባለ ሶስት ፌዝ የመብራት ቆጣሪ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለዚህም ተገቢውን ክፍያ በመጨመር የገዙ መሆኑን፤የቤቱ አንድ ክፍልም(ሰርቪሱ) የመብራት ቆጣሪውን የሚጠቀም የንግድ ቤት መሆኑን ገልፀው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ ቤቱን ሲሸጡ አከራካሪው ባለ ሶስት ፌዝ የመብራት ቆጣሪ በቤቱ ላይ ያልነበረ መሆኑን ፤የቤቱ አንድ ክፍል ባለ ሶስት ፌዝ መብራት የሚጠቀም የንግድ እንቅስቃሴ የማይደረግበት መሆኑን በመግለፅ ተጠሪ በግልፅ ያቀረቡት ክርክር የለም።ከዚህ ይልቅ ተጠሪ ያቀረቧቸው ምስክሮች ተጠሪ የሸጡት የመኖሪያ ቤትና የዳቦ ቤት መሆኑን ከሽያጩ በኋላ ተጠሪ በመኖሪያ ቤቱ ለ3 ወር በዳቦ ቤቱ ደግሞ ቤት እስኪያገኝ ድረስ እንዲጠቀሙበት የተስማሙ መሆኑን ማስረዳታቸው የሽያጭ ውሉ ሲከናወን በውሉ ላይ ከተመለከተው ባለፈ የተነጠለ የንግድ ስራ የሚከናወንበት የንግድ ድርጅት መኖሩን ሁለቱ ቤቶችም ተነጣጥለው ርክክብ ሊፈፀምባቸው እንደሚችል የተጠሪ ምስክሮች ማስረዳታቸውን ያሳያል።

ተዋዋይ ወገኖች ውላቸውን ከመዋዋላቸው አስቀድመው ወይም ከተዋዋሉ በኋላ የነበሩትን ሁኔታዎች፤የፈፀሙትን ተግባር በማመዛዘን ሀሳባቸው ምን እንደነበረ ለማወቅ መሞከር ለውሉ ጉዳይ አግባብ ያለው ትርጉም ለመስጠት ተገቢ መሆኑን በፍ/ብ/ህ/ቁ.1734(1) የተመለከተ ሲሆን ይህንኑ ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 38544 አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቶበታል።ተጠሪ የሸያጭ ውሉ ላይ የመኖሪያ ቤት የሸያጭ ውል በሚል መመልከቱን መሰረት በማድረግ ቤቱ ሌላ የመብራት ቆጣሪ ያለው መሆኑን በመጥቀስ አከራካሪው ባለ ሶስት ፌዝ የመብራት ቆጣሪ የሸያጩ አካል አለመሆኑን በመጥቀስ ቢከራከሩም ስለ ውሉ ቀርበው ያስረዱት የተጠሪ ምስክሮች ራሳቸው ከውሉ በኋላ የተጠሪን አቆያየት አስመልክቶ ግራ ቀኙ ሲስማሙ የነበረውን ሁኔታ ሲያስረዱ ሽያጩ በርግጥም በመኖሪያ ቤት ላይ ብቻ አለመደረጉን በግልፅ እያመለከቱ “ተጠሪ የሸጡት የመኖሪያ ቤትና የዳቦ ቤት መሆኑን ” ማስረዳታቸው በወቅቱ የንግድ ድርጅትን ባካተተ መልኩ የሸያጭ ውል መደረጉን ያሳያል።

ከመነሻውም በአከራካሪው የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ወቅት የዳቦ ቤት የንግድ ስራው ከነበረ ፤ይህ የንግድ ስራ የሚከናወነው በዚሁ የቤቱ አካል ከሆነ ደግሞ ይህ ለንግድ ስራው መሰረት የሆነው አከራካሪው ባለ ሶስት ፌዝ የመብራት ቆጣሪ የሸያጩ አካል አለመሆኑን በውል የተገለለበትን ማስረጃ በማቅረብ ተጠሪ አላስረዱም።ወይም በንግድ ህጉ አንቀፅ 127(2)(ሠ) አግባብ አከራካሪው ባለ ሶስት ፌዝ የመብራት ቆጣሪ ነጋዴውን የሚከተል እንጂ የንግድ መደብሩ ሽያጭ አካል ሆኖ የማይጠቃለል መሆኑን ተገቢውን ማሳያ በማቅረብ አላስረዱም።ከዚህ ይልቅ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1732 አግባብ በጉዳዮች ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ስርአት በመከተል ውሉን ስንተረጉመው አከራካሪው ባለ ሶስት ፌዝ የመብራት ቆጣሪ ነጋዴውን የሚከተል የንግድ መደብር ሽያጭ ቢከናወንም ነጋዴውን ተከትሎ የሚሄድ የንግድ መደብሩ አካል ባልሆነበት ከዚህ ይልቅ ከነጋዴው ተነጥሎ የንግድ መደብሩ አካል ሊሆን የሚችል ሆኖ እያለ የስር የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አከራካሪውን ባለ ሶስት ፌዝ የመብራት ቆጣሪ ተጠሪ ለአመልካች ሊመልስ አይገባም በማለት የስር የሎሜ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር መወሰኑና በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች ይህንን ውሳኔ ማፅናታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

<u>ውሳኔ</u>

1. የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.57013 በ11/03/2012 ዓም የሠጠው ውሳኔና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 329068 ጥር 28 ቀን 2012 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

332581 በመጋቢት 07 ቀን 2012 የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሸረዋል።

2. *የሎሜ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.86641 ሰኔ 24 ቀን 2011 ዓም የሰጠው ውሳኔ ከውጤት አንፃር ፀንቷል።*
3. *በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።*

<u>መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ይመለስ</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-198891

ቀን፡-02/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ አክሉሉ ካሕሳይ - ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አኪር ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር - በሌለበት የሚታይ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ጥር 25 ቀን 2005 ዓ/ም በተደረገ የመኪና ኪራይ ውል ስምምነት መሠረት የሠሌዳ ቁጥር 3-83597 አ.አ. የሆነ ተሽከርካሪ ለ10 ወራት ከ15 ቀናት ለሰራው ብር 346,500.00 ተጠሪ መክፈል ሲገባው ብር 100,000.00 ብቻ ከፍሎ ቀሪ ገንዘብ ስላልከፈለ ብር 246,500.00 ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፈላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረበው መልስ የሠዓት መቆጣጠሪያ ሳያቀርቡ ብር 136,147.00 ከፍለናል፡፡ በውሉ መሠረት ታይምሽት ሳይቀርቡ ክፍያ መጠየቃቸው አግባብነት የለውም፡፡ የቀረበው ማስረጃም በአመልካች መኪና ሥራ መስራታችን አያሳይም፤ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ብሏል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግራቀኙን ማስረጃ በመስማት በውሉ መሠረት የተሰራውን ስራ በሠዓት መቆጣጠሪያ ማስረዳት አለበት፡፡ በአመልካች የቀረበው የሠዓት መቆጣጠሪያ ለክሱ መነሻ በሆነው መኪና የተሰራ ስራ ስለመኖሩ አያስረዳም፡፡ የቀረቡት ምስክሮችም መኪናው መከራየቱን እንጂ ስለክፍያው የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ከብር 100,000.00 በላይ መክፈሉን አስረድቷል፡፡ ቀሪ ክፍያ ያለበት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፤ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባለመቀበል ሠርዟል፡፡

ይህ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ይዘትም በግራቀኛችን የተደረገው ውል እና የቀረበው የሠዓት መቆጣጠሪያ ክፍያው ብር 346,500.00 መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ መክፈሉን ማስረዳት ያለበት ተጠሪ ነው፤ ብር 346,500.00 መክፈሉን አላስረዳም፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የሠዓት መቆጣጠሪያ ቀርቦ እያለ በሥር ፍርድ ፍርድ ቤት አልቀረበም ተብሎ ክሱ ውደቅ መደረጉ ተገቢነቱን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪ ተጠርቶ ባለመቅረቡ ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር፣ የሠበር አጣሪ ችሎት የያዘው ጭብጥ፣ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ያቀረቡት ክስ ከተጠሪ ጋር ጥር 25 ቀን 2005 ዓ/ም በተደረገ የመኪና ኪራይ ውል ስምምነት መሠረት የሠሌዳ ቁጥር 3-83597 አ.አ. የሆነ ተሽከርካሪ ለ10 ወራት ከ15 ቀናት ለሰራው ተጠሪ መክፈል ሲገባው ያልከፈለው ቀሪ ገንዘብ ብር 246,500.00 ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፈላቸው ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ የሚከራከረው በውሉ መሠረት የሠዓት መቆጣጠሪያ ሳያቀርቡ ክፍያ መጠየቃቸው አግባብነት የለውም፡፡ የቀረበው ማስረጃም በአመልካች መኪና ሥራ መስራታችን አያሳይም፤ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ነው፡፡ ግራቀኙ ባላቸው የመኪና ኪራይ ውሉ ስምምነት መነሻ ያደረገ ክርክር የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡትን ክስ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት ወስነዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሥር ፍርድ ቤት ሆነ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ በሕግ ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው ናቸው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ ነገር ግን ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣን የተሠጠው ፍርድ ቤት ማስረጃ ሲቀበል የተከራካሪዎችን እኩል የመደመጥ መብት ካላከበረ፣ የማስረዳት ሸክም (burden of production) የማን ነው የሚለውን ካልለየ፣ የማስረጃ ተቀባይነትና ተገቢነት ላይ መከተል የሚገባውን ሥርዓት ካልተከተለ፣ በምዘና ጊዜ የሁሉንም ተከራካሪዎች ማስረጃ አብሮ ካልመዘነ፣ የተለየ የማስረዳት ደረጃ (standard of proof) የሚጠይቁ ጉዳዮችን በሚጠይቀው ደረጃ ልክ መረጋገጡን ካላሳየ እና በመሠረታዊ ሕግ ሆነ በሥነ-ሥርዓት ሕግ ያሉትን የማስረጃ ሕጎችና መርሆች ካላከበረ ጉዳዩ

የማስረጃ ምዘና ሳይሆን የሕግ አተረጓጎምና አተገባበር ስህተትና ፍርድ ቤት ያለበትን ኃላፊነት አለመወጣት ስለሚሆን የሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚመለከተው ጉዳይ ይሆናል፡፡

በያዘነው ጉዳይ የግራቀኙ የመኪና ኪራይ ውል አንቀጽ 9 እና 10 መሠረት የሠዓት መቆጣጠሪያ ማስረጃ በአከራይ እና ተከራይ ተወካይ ተሞልቶ በፕሮጀክቱ ኃላፊ ተረጋግጦና ፀድቆ ለክፍያ መቅረብ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ አመልካችም በሥር ፍርድ ቤት የሰዓት መቆጣጠሪያ ሠነድ እና የሠው ማስረጃዎች አቅርበዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ማስረጃውን የመዘነ ሲሆን የሠዓት መቆጣጠሪያ ሠነድ መቅረቡን ገልጾ ነገር ግን ሠነዱ አመልካች ክስ ያቀረቡበት የሠሌዳ ቁጥር 3-83597 አ.አ. የሆነ ተሽከርካሪ የሚመለከት አይደለም፣ የሠው ምስክሮችም ስለክፍያው መጠን አያውቁም በሚል ውድቅ ያደረገው ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ይህም ውሳኔ ላይ የተፈጸመ የማስረጃ አቀባበል ሆነ ምዘና መርሕ ስህተት አለመኖሩን ያሳያል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው መክፈሉን ማስረዳት ያለበት ተጠሪ ነው ያሉ ቢሆንም አመልካች በውሉ የተመለከተው መኪና ምን ያህል ሰዓት እንደሰራ ባላስረዱበት ሁኔታ የማስረዳት ግዴታው ወደተጠሪ የሚዞርበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 256601 ጥቅምት 12 ቀን 2013 ዓ/ም እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 83281 የካቲት 16 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-198805

ቀን፡-29/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ ወርቁ ኃይለመስቀል

ተጠሪ ፡- አቶ ከበደ ደስታ

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች የስር ተከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ከሚች አባታቸው አቶ ደስታ አድማሱ በውርስ የሚተላለፍ የሚንቀሳቀስ እና በዚህ ችሎት ደረጃ አከራከሪ ሆነ የቀረበውን የገጠር እርሻ መሬት አመልካች ለቀው እንዲያስረክቧቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ስለመሬቱ ያቀረቡት መልስ ይዞታው የሚች ደስታ አድማሱና የባለቤቱና የአመልካች አያት የሆኑት የወ/ሮ እህተጊዮርጊስ ኃይለጊዮርጊስ ሲሆን አያቱ ወራሽ ስለሆን የሚች ደስታ አድማሱን ድርሻ በኑዛዜና በሥጦታ አስተላፈውልኛል፡፡ በድጋሜ ከልጆቹ ጋር መሬቱን አውርሰውኛል፡፡ የሚች ደስታ ድርሻ ሊተላፍልህ አይችልም ቢባል እንኳን የአያቱ የቤተሰብ አባል ስለሆንኩ ግማሽ ድርሻውን ተጠሪ ሊጠይቁኝ አይገባም ብለዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ መሬቱ የሚች ደስታ

አድማሱና የእህተጊዮርጊስ ኃይለጊዮርጊስ ይዞታ ነበር፤ ለአመልካች የተሰጠ ኑዛዜ ሆነ ሥጦታ የነበረ ቢሆንም በወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ደረጃ አልጸደቀም፡፡ ስለሆነም ግማሹ የሟች ደስታ ድርሻ ለተጠሪ በውርስ የሚገባቸው ሲሆን የሟች እህተጊዮርጊስን ድርሻ በውርስ ለአመልካች የሚተላለፍ ነው፡፡ ከመሬት ውጭ ያሉ ንብረቶች ለአመልካች ኑዛዜ ስላላቸው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ በየደረጃው የሚገኙ ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የይግባኝና የሠበር አቤቱታ ባለመቀበል ሠርዘዋል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ግንቦት 09 ቀን 2009 ዓ/ም ሥጦታ ውል የተደረገ ስለመሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ውሉ በወረዳ ጽ/ቤት ደረጃ በራሱ ቸልተኝነት ባለመጽደቁ ውጤት የለውም መባሉ ተገቢ አይደለም፡፡ ነሀሴ 08 ቀን 2010 ዓ/ም ለአመልካች እና ለሁለቱ ልጆቹ አቶ ደስታ አድማሱ ኑዛዜ አድርገውልን ስም ባለመዛወሩ ብቻ ውድቅ መደረጉ ሕጋዊ አይደለም፡፡ የሟች ደስታ አድማሱን ደርሻ መሬት ላስረክብ አይገባም የሚል ነው፡፡ የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን ተመልክቶ ስጦታ ውሉ ባይመዘገብ እንኳን አመልካች የኑዛዜ ወራሽ ከመሆናቸው አኳያ በግማሽ ድርሻ መሬቱ ላይ መብት የላቸውም መባሉ ተገቢነቱን ለመመርመር ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ ያዘዘ ሲሆን ተጠሪ ያቀረቡት መልስ የተደረገ ኑዛዜ ሆነ ስጦታ ውል የለም፤ ሟች ከሞተ በኋላ ተጠሪን ከውርስ ለመንቀል የተዘጋጁ ሠነዶች ናቸው፡፡ እውነት ቢሆን ኖሮ ኑዛዜ እንዲሁም የሥጦታ ውልም ተደርጎልኛል ሊል አይችልም፡፡ በሕግ አግባብ የተደረገና የተመዘገበ ውል ባለመኖሩ ውሳኔው ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የግራቀኙ ክርክር፣ የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘውን ጭብጥ በሥር ፍርድ ቤት ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮችና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ከሟች አባታቸው አቶ ደስታ አድማሱ በውርስ የሚተላለፍ የገጠር እርሻ መሬት አመልካች ለቀው እንዲያስረክቧቸው ላቀረቡት ዳኝነት አመልካች ሟች ደስታ አድማሱ ድርሻቸውን በ08/12/2010 ዓ/ም በተደረገ ኑዛዜና በ09/09/2009 ዓ/ም በተደረገ ሥጦታ አስተላፈውልኛል፡፡ ተጠሪ ግማሽ ድርሻውን ሊጠይቁኝ አይገባም በማለት ነው፡፡ ግንቦት 09 ቀን 2009 ዓ/ም ተደረገ የተባለው የሥጦታው ውል ሕጋዊነት ውሉ በተደረገበት ጊዜ በሥራ ላይ ባለው ሕግ መሠረት ሊመረመር የሚገባ ሲሆን በአማራ ክልል የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 133/1998 አንቀጽ 17(6) መሠረት የገጠር መሬት ላይ የሚደረግ የሥጦታ ውል መሬቱ በሚገኝበት የወረዳ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት ሊመዘገብ እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ኑዛዜው ደግሞ የክልሉ ገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ነሀሴ 08 ቀን 2010 ዓ/ም የተደረገ በመሆኑ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 17(4) መሠረት በተመሳሳይ መሬቱ በሚገኝበት የወረዳ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት ቀርቦ መመዝገብ አለበት ተብሎ ተመልክቷል፡፡ የሥር ወረዳ ፍርድ ቤት በሕግ አግባብ የተመዘገበ ሥጦታ ወይም ኑዛዜ የሌለ መሆኑ በማረጋገጥ ድምዳሜ ላይ ድርሷል፡፡ የፌደራል

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3) ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሠበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሠጠውም፡፡ አመልካች በ2009 ዓ/ም መሬቱ በሥጦታ ተሰጥቶኛል ካሉ በኋላ እንደገና በ2010 ዓ/ም በኑዛዜ አግኝቼዋለሁ የሚለው ክርክርም እርስ በእርሱ የሚቃረን አሳማኝ ያልሆነ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤትን ድምዳሜ ተቀብለናል፡፡ ስለሆነም መሬቱ የሟች ደስታ አድማሱና የእህተጊዮርጊስ ኃይለጊዮርጊስ ይዞታ ተጠሪ የአባታቸውን ግማሽ ድርሻ እና አመልካች የሟች እህተ ጊዮርጊስን ወራሽ ስለሆነ ግማሽ ድርሻ ሊካፈሉ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ውሳኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-11784 ጥቅምት 23 ቀን 2013 ዓ/ም፣ የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 013366 ግንቦት 18 ቀን 2012 ዓ/ም እና የሞጃና ወደራ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0114235 ታህሳስ 16 ቀን 2012 ዓ/ም የሠጡት ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- አፈጻጸሙ ላይ የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሄ/መ

የሰ.መ.ቁ 198703
ሐምሌ 29 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ፡- አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አበባየሁ ተዘራ፡- ከጠበቃ ነቢያት ግርማ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 16 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 183756 ሐምሌ 10 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመሻር ተጠሪን ከተከሰሰችባቸው ሁለት ክሶች በነፃ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪ ላይ በሥር ፍ/ቤት አቅርቦአቸው የነበሩት ክሶች ሁለት ሲሆኑ ይዘታቸውም፡-

1ኛ ክስ፡- ተጠሪ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 543(3) እና ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 26 ድንጋጌዎች በመተላለፍ የሌላውን ሰው ሕይወት፣ ጤንነት እና ደሕንነት የመጠበቅ የሙያ ግዴታ እያለባት ባለመወጣት በቀን 23/07/2010 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 1፡30 ሠዓት ሲሆን የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2-57534 አ.አ የሆነ ተሽከርካሪ እያሽከረከረች ከስድስት ኪሎ ወደ መገናኛ አቅጣጫ ስትጓዝ የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ልዩ ቦታው ኮከበ ፅባሕ ትምህርት ቤት ፊት ለፊት ስትደርስ ለእግረኛ ቅድሚያ በመከልከል በእግረኛ ማቋረጫ መንገድ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ላይ ስታቋጥ የነበረችውን ሚች አስምረት ንጉሴን በመኪናው የፊት ለፊት አካል ገጭታ በጭንቅላቷ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ ራሷን ስታ ወድያውኑ ሕይወቷ እንዲያልፍ በማድረግ በፈጸመችው በቸልተኝነት ሰውን መግደል ወንጀል ተከሳለች የሚል ነው።

2ኛ ክስ፡- ተጠሪ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 575/2(ሀ) ድንጋጌን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ፣ ቦታ እና አፈጻጸም ሁኔታ በእግረኛ መንገድ ላይ ስታቋርጥ የነበረችውን ሚች አስምረት ንጉሴን በመኪናው ፊት ለፊት አካል ገጭታ ከጣለቻት በኋላ ምንም ዓይነት እርዳታ ሳታደርግላት ስታመልጥ በአካባቢው ሰዎች የተያዘች በመሆኑ በፈጸመችው በአደጋ ላይ የሚገኝን ሰው አለመርዳት ወንጀል ተከሳለች የሚል ነው።

ተጠሪ ክሱ ተነቦላት እንድትረዳው ከተደረገ በኋላ መቃወሚያ ያቀረበች ሲሆን መቃወሚያው በብይን ውድቅ ተደርጓል፤ የእምነት ክሕደት ቃሏን ስትጠየቅም ድርጊቱን አልፈጸምኩም በማለት ክዳ በመከራከሯ ፍርድ ቤቱ የዓቃቤ ሕግን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተጠሪ በተከሰሰችበት በሁለቱም ክሶች እንድትከላከል ሲል ብይን ሰጥቷል። ተጠሪም በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 142/3 መሠረት ቃሏን የሰጠች ሲሆን መከላከያ ምስክሮቿንም አቅርባ አሰምታለች። ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ሚችን በእግረኛ መንገድ ላይ እያቋረጠች እያለች ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረግ እና ሚችን ቅድሚያ በመከልከል በመግጨት እና ከገጨችም በኋላ ምንም ዓይነት እርዳታ ሳታደርግ ጥላ ለማምለጥ የሞከረች ስለመሆኑ የዐቃቤህግ ምስክሮች በመግለጽ ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር ተጠሪ አላስተባበለችም በማለት በተከሰሰችባቸው ሁለቱም ክሶች ጥፋተኛ ብሎ በሦሥት ዓመት ከሦሥት ወር ጽኑ እሥራት እና በብር 2,500 የገንዘብ መቀጮ እንድትቀጣ ሲል ወስኗል።

ተጠሪም ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታዋን አቅርባለች። ይግባኙ የቀረበለትም ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የምስክርነት ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነው፤ በመኪና ግጭት አደጋ የሟች ሕይወት ማለፉ ቢረጋገጥም አደጋው የደረሰው በተጠሪ መኪና መሆኑን የተሰጠው የምስክርነት ቃል አጠራጣሪ ነው፤ ተጠሪ ባቀረበቻቸው ምስክሮች በይግባኝ ባይ መኪና ላይ የደረሰ ጉዳት ያልነበረ እና ግጭቱ በደረሰበት ቦታ ላይ ግን የመኪና ፍሬቻ እና መስታወት ስብርባሪ የነበረ መሆኑን፤ ተጠሪ በወቅቱ የደሰች እርጉዝ እና ሶስት ሕጻናት ልጆችዋን የጫነች መሆኑን መስክረዋል፤ ተጠሪ የነበረችበት ሁኔታ መኪናውን በፍጥነት ታሽከረክራለች ለማለት የሚያሳምን አይደለም፤ ተገኘ የተባለው የመኪና አካል ስብርባሪ የእኔ መኪና አይደለም በትእዛዝ ቀርቦ ይታይልኝ በማለት ብትጠይቀም ጥያቄዋ ውድቅ ተደርጓል፤ በራሺያ ኤምባሲ በደህንነት ካሜራ ተቀርጾአል የተባለውን አደጋው የደረሰበት አካባቢ እንቅስቃሴ ማስረጃ ፖሊስ እንዲያቀርብ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ቢሰጥም ማስረጃውን ፖሊስ እና ዐቃቤ ሕግ በጋራ ማየታቸውን ነገር ግን ዐቃቤሕግ በክሱ የማስረጃ ዝርዝር ውስጥ ያላካተተው እና ማስረጃው በፍላሽ ላይ የነበረ በመሆኑ በቫይረስ ችግር የተበላሸ መሆኑን በመግለጽ ማስረጃው ሳይቀርብ መቅረቱ ሲታይ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ለክሱ የሚረዳው ሆኖ ባለማግኘቱ በተቃራኒው ለተጠሪ ሊጠቅም የሚችል ከመሆኑ አንፃር የተወው ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፤ ስለሆነም ዓቃቤ ሕግ

በወቅቱ በደረሰ የመኪና አደጋ ሚች ተገጭው ሕይወታቸው ማለፉን እንጂ ግጭቱ የደረሰው በተጠሪ መኪና መሆኑን ባላስረዳበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪን ክሱን አላስተባበለችም በማለት የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ አግባብ አይደለም በማለት ሽሮ ተጠሪን ከተከሰሰችባቸው ሁለቱም ክሶች በነፃ በማሰናበት ወስኗል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- በራሺያ ኤምባሲ ደህንነት ካሜራ የተቀረጸው በፍላሽ የነበረ በመሆኑ በቫይረስ የተጠቃ እና ማስረጃውን ዐቃቤ ሕግ እና ፖሊስ በጋራ ያዩት መሆኑና ማስረጃውም የአደጋው አደራረስ የማያሳይ ስለመሆኑ ፖሊስ በቀን 06/10/2011 ዓ.ም ለፍርድ ቤቱ በፃፈው ደብዳቤ ተረጋግጧል፤ ዐቃቤ ህግ ይህን ማስረጃ በክሱ የማስረጃ ዝርዝር ውስጥ በማስረጃነት አለመጥቀሱ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የዓቃቤሕግ የማስረጃ የመምረጥ እና ለክሱ የሚጠቅመውን የመለየት መብት ግምት ውስጥ ያላስገባ እና የማስረጃ ምዘና ስነ ስርዓት ሕግን ያልተከተ ነው፤ ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን እንደ አቃቤ ህግ ክስ አቀራረብ ባቀረባቸው ማስረጃዎች የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ተጠሪ አላስተባበለችም፤ በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪን ከሁለቱም ክሶች በነፃ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪን ከተከሰሰችባቸው ሁለት ክሶች በነጻ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ አግባብነት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 89676 ከሰጠው ውሳኔ አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

ተጠሪ መጋቢት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠችው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ክርክር በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ አይገባም፤ አመልካች እንደ ክሱ አቀራረብ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ አላስረዳም፤ ተጠሪ ባቀረብኩት ማስረጃ ክሱን አስተባብያለሁ፤ በኤግዚቢትነት የተያዘው የመኪና ስብርባሪ ተጠሪ እንዲቀርብ ያቀረብኩትን ጥያቄ ውድቅ ተደርጎብኛል፤ በራሺያ ኤምባሲ የደህንነት ካሜራ የተቀረጸው የአካባቢው እንቅስቃሴ ማስረጃ የአደጋውን ሁኔታ የሚያሳይ እንደመሆኑ መጠን እንደ ማንኛውም ማስረጃ በጥንቃቄ ሊያዝ ሲገባው ዐቃቤ ህግ ክሱን ውድቅ ስለሚያደርገበት ብቻ በክሱ በቫይረስ ጠፍቷል በሚል ምክንያት እንዲቀርብ አላደረገም፤ ስለሆነም የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪነ በነጻ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው።

አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

አመልካች ለዚህ ችሎት ባቀረበው ክርክር ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸሟ በበቂ ሁኔታ በተረጋገጠበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪን ከተከሰሰችበት ክስ በነጻ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሚከራከር ቢሆንም በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጡትን ፍሬነገሮች የመመርመር፤ ማስረጃን የመመዘን እና ያልተጣራ ፍሬነገር ካላ ራሱ የማጣራት ወይም እንዲጣራ የማድረግ ስልጣን ያለው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የምስክርነት ቃል እርስ በእርሱ የሚጋጭ እና በመኪና ግጭት አደጋ የሟች ሕይወት ማለፉ ቢረጋገጥም አደጋው የደረሰው በተጠሪ መኪና መሆኑን የተሰጠው የምስክርነት ቃል አጠራጣሪ መሆኑን፤ ተጠሪ ባቀረበቻቸው ምስክሮች በይግባኝ ባይ መኪና ላይ የደረሰ ጉዳት ያልነበረ እና ግጭቱ በደረሰበት ቦታ ላይ ግን የመኪና ፍሬቻ እና መስታወት ስብርባሪ የነበረ መሆኑን፤ ተጠሪ በወቅቱ የነበረችበት ሁኔታ መኪናውን በፍጥነት ታሽከረክራለች ለማለት የማያሳምን መሆኑን፤ ተጠሪ ተገኘ የተባለው የመኪና አካል ስብርባሪ የእኔ መኪና አይደለም በትእዛዝ ቀርቦ ይታይልኝ በማለት ብትጠይቀም ጥያቄዋ ውድቅ የተደረገ መሆኑን፤ በደህንነት ካሜራ ተቀርጾአል የተባለውን የአካባቢውን እንቅስቃሴ ማስረጃ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ቢሰጥም ዐቃቤሕግ በክሱ የማስረጃ ዝርዝር ውስጥ ያላካተተው እና በቫይረስ ችግር ተበላሽቷል በሚል ምክንያት ያልቀረበ መሆኑን፤ ዓቃቤ ሕግ በወቅቱ በደረሰ የመኪና አደጋ ሟች ተገጭው ሕይወታቸው ማለፉን እንጂ ግጭቱ የደረሰው በተጠሪ መኪና መሆኑን ያላስረዳ መሆኑን አረጋግጧል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/1 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የለውም፡፡

በያዝነው ጉዳይ የዓቃቤሕግ ማስረጃዎች እርስ በእርሳቸው የሚጣረሱ እና ዓቃቤ ሕግ በወቅቱ በደረሰ የመኪና አደጋ ሟች ተገጭው ሕይወታቸው ማለፉን እንጂ ግጭቱ የደረሰው በተጠሪ መኪና መሆኑን ያላስረዳ መሆኑ፤ ተጠሪም ባቀረበችው መከላከያ ማስረጃ በዓቃቤሕግ ማስረጃ ላይ ጥርጣሬን የፈጠረች ስለመሆኑ በስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተረጋገጠ እና ይህ ችሎትም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪን ከቀረበባት ክስ በነጻ በማሰናበት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አልተገኘበትም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 183756 ሐምሌ 10 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2//ሀ/ መሠረት ጸንቷል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

የሠ/መ/ቁጥር 198669
ህዳር 29 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡-ብርሃኑ አመነዉ

ተሾመ ሽፈራዉ

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግሥቱ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች ፡- አቶ ወንድማገኝ ታደሰ- ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አጋር የጥበቃ አገለግሎት ኃ/የተ/የግ/ማኅበር - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስራ ክርክር የሚመለከት ነዉ፡፡ አመልካች በሐረር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ ተጠሪ ለጥበቃ ስራ ከቀን 01/02/2010 ዓ/ም ጀምሮ በወር ብር 1,293.00 ደመወዝ እየከፈለ ሊያሰራቸዉ ቀጥሯቸዉ እስከ ቀን 13/02/2011 ዓ/ም ድረስ እየሰሩ ቆይተዉ በስራ መመዝገቢያ ላይ ፈርሜ የተረከብኩት ጥበቃ ቀጠና ውጪ ሌላ ቀጠና ላይ ሄደህ የጥበቃ ሥራ እንዲሰሩ ሲያዛቸዉ በሥራ መመዝገቢያ ላይ ፈርሜ የተረከብኩት ጥበቃ ቀጠና ላይ ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ እሆናለሁ በማለታቸዉ ብቻ በቀን 13/02/2011 ዓ/ም ከሥራ እንዳሰናበታቸዉ ገልጸዉ ሥንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት የተለያዩ ክፍያዎችን በድምሩ ብር 22,487.08 ተጠሪ እንዲከፍላቸዉ እንዲወሰንላቸዉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስ ተጠሪ የአመልካችን መብት ሳይነካ በተመሳሳይ ቦታ ላይ ተዛውረዉ እንዲሰሩ አዘዛቸዉ እንጂ ተጠሪ አመልካችን አላሰናበታቸዉም፡፡ተጠሪ በተዛወሩበት ቦታ እንዲሰሩ በጽሁፍ ቢታዘዙም ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ ተጠሪ የዓመት እረፍት ተጠቅመዋል፡፡ስለሆነም እንዲከፈላቸዉ

የጠየቁት ክፍያዎች አይገባቸዉም፡፡የሽምዝና የጫማ በሚል እንዲከፈላቸዉ የጠየቁት 6000.00 ብር ያለአግባብ የጠየቁትና የተጋነነ ስለሆነ ዉድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 50384 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና ማስረጃዎችን መርምሮ በቀን 03/07/2012 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ የተመደብኩበትን ቦታ ትቼ ወደሌላ ምድብ ብሄድ ፊርሜ በተመደብኩበት ቦታ ችግር ቢፈጠር ተጠያቂ ስለምሆን በሌላ ምድብ አልሰራም በማለቱ አመልካች የተጠሪን የሥራ ዉል ማቋረጡ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 ስር የተደነገገዉን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ የአመልካች የሥራ ዉል ከሕግ-ወጭ ተቋርጧል ሲል ወስኗል፡፡ይህንን ተከትሎም የአገልግሎት ክፍያ የ2 ዓመት ብር 1,724.00፣ የካሳ ክፍያ ብር 1,293.00 ፣ የሥራ ውሉ በተጠሪ አነሳሽነት ከሕግ-ዉጭ ስለተቋረጠ በአንቀጽ 41/1 መሰረት የአንድ ወር ደመወዝ ካሳ ብር 1,293.00 ፣ በአንቀጽ 43 መሰረት ከሕግ-ውጪ የስራ ዉሉ በመቋረጡ የአመልካች የቀን ደመወዝ በ180 ተባዝቶ ካሳ ብር 7,758.00 ፣ የ28 ቀን የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ብር 1,206.60፣ ክፍያ ለዘገየበት ብር 3,879.00 ፣ የጥበቃ ደንብ ልብስና ጫማ በአመት 2 ጊዜ የ2010 እና 2011 ዓ/ም በግራ ቀኙ ያልተካደ ቢሆንም የዋጋ ዝርዝር በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ በአማካይ ብር 3,000 እንዲሁም ወጪ ኪሳራ በቁርጥ 500 ብር አጠቃላይ ብር 19,360.00 ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሀረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ፍርድ ቤቱ በመ/ቁጥር 20027 ላይ በቀን 30/10/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞባቸዋል፡፡ በመቀጠል ተጠሪ አቤቱታውን ለሀረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ችሎቱ በመ/ቁጥር 00101 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ በቀን 26/02/2013 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ለሥራ ውሉ መቋረጥ መነሻ የሆነው ጉዳይ አመልካች በቀን 13//02/2011 ዓ/ም በተመደቡበት የሥራ ቦታ በሥራ ሰዓት ባለመገኘተቻዉ በቦታቸው ሌላ ሠራተኛ ተመድቦ አመልካች አርፍደዉ በመምጣቱ ተጠሪ አመልካችን በሌላ ቦታ ጥበቃ ቀጠና በዚያው በተቀጠረው ቅጥር ግቢ ምንም አይነት የደመወዝ ቅነሳ ሳያደርግ በያዘው ደመወዝ መብትና ጥቅም ጋር ያዛወረውን አመልካች ባለመቀበላቸዉ እንደሆነ ከክርክሩ መረዳት ችለናል፡፡ተጠሪ የአመልካችን ለሥራው አመቺ በሆነ ቦታ አዘውሮ ማሰራቱ አስተዳደራዊ ስልጣኑ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በአመልካች በኩል ቅን ልቦና አለመኖሩን ለመረዳት ችለናል፡፡በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የጉዳዩን አመጣጥና የተጠሪን የአስተዳደር ስልጣን ግምት ውስጥ ሳያስገባ እና አመልካችን ከስራ አላሰናበትኩም አሁን ተመልሶ መስራት ይችላል የሚል ክርክር አቅርቦ እያለ ተጠሪ በሕገ-ወጥ መንገድ የሥራ ውል አቋርጧል በማለት የሠጠዉ ዉሳኔ አበዋጅ ቁጥር 1156/2011 ከአንቀጽ 23 እስከ 45 የተደነገገዉን ያላገናዘበ በመሆኑ አግባብ አይደለም በማለት ሽሮ ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 03/03/2013 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡትም በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ ይዘት በአጭሩ፡- የሥር

መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካች የሥራ ዉል የተቋረጠዉ በተጠሪ ጥፋት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ተጠሪ ምንም ዓይነት የዝውውር ደብዳቤ ሳይሰጠኝ እና ሳይደርሰኝ በሌላ ቀጠና ሄጄ እንድሰራ ሲያዘኝ አስቀድሞ ፊርማ የተረከብኩት ንብረት ቢጠፋ ተጠያቂ ስለሚሆን የፊረምኩት ፊርማ እንዲሰረዝልኝ በማለቴ ፈቃደኛ አልሆነም በማለት ያለማስረጃ ያቀረበዉን ክርክር የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መቀበሉና የሥር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ መሻሩ ስህተት ስለሆነ ተሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የሰበር ችሎት አምስት ዳኞች የሚሰየሙበት ከመሆኑ አኳያ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሶስት ዳኞች ተሰይመዉ የወሰኑበትን አግባብ ሰበር አምስት ዳኞች የሚሰየሙበት ችሎት ከመሆኑ አኳያ የሀረር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሶስት ዳኞች ብቻ ጉዳዩን አይቶ የወሰነበት አግባብ እንዲመረመር ትእዛዝ በመስጠቱ ተጠሪ በቀን 26/11/2013 ዓ/ም የተፃፈ መልሱን አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡- የሚከተለው ነው፡፡

ተጠሪ አመልካችን ከሥራ ያሰናበተው አመልካች እንደሚሉት ሳይሆን አመልካች ሥራ ከገቡ በኋላ የተመደቡበትን ሥራ ቦታ ላይ እየሰራ እያለ ሌላ ክፍተት ያለበት ቦታ ላይ ሂደዉ እንዲሰሩ ሲመደቡ አልሄደም ከዚህ ከተመደብኩበት ቦታ ውጪ አልሰራም በማለታቸዉ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካችን ሌላ ቦታ ላይ የመደበዉ አመልካችን ተጠያቂ ለማድረግ ሳይሆን የሥራ ክፍተትን ለመሸፈን ነው፡፡በተጨማሪም በኃላፊው ታዞ በሌላ ስራ ላይ የተመደበ ሰራተኛ ተጠያቂ የሚሆነው ለተመደበበት ቦታ እንጂ በኃላፊው ታዞ ለተነሳበት ቦታ አለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ስለዚህ የሀረሪ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመለከተዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጭብጥ በተጨማሪ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር በሰጠዉ ዉሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

በመጀመሪያም የሐረሪ ሕዝብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሦስት ዳኞች በተሰየሙበት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር ለማለየት የቻለበትን የሕግ መሰረት መርምረናል፡፡ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ የክልል ጉዳይ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ለ) ላይ እና በሐረሪ ሕዝብ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 70(2/ሐ) ላይ እንደተመለከተዉ ዝርዝሩ በሕግ በሚወሰነዉ መሰረት የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳይ ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንዳለዉ ተደንግጓል፡፡ይህንን ተከትሎ በወጣዉ ሕግ በሐረሪ ሕዝብ ክልል ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋሚያ አዋጅ ለማሻሻል በወጡ አዋጆችና እንደገና ለማሻሻል በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 68/1999 አንቀጽ 7(ሀ እና ለ) (ይህ አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 107/2004 እንደገና

ቢሻሻልም ይህ አንቀጽ አልተለወጠም) ስር ከተደነገገዉ መረዳት የሚቻለዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚኖሩት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ሦስት ዳኞች (አንድ ሰብሳቢ ዳኛና በሁለት ተጨማሪ ዳኞች) ተሰይመዉ እንደሚዳኙ ደንግጓል፡፡በሌላ በኩል በቀድሞዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988(በአዋጅ ቁጥር 454/1997 እንደተሻሻለዉ) አንቀጽ 10/4 እና ይህንን አዋጅ ከነማሻሻያዉ በሻረዉ የፌደሬል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/2 ላይ በተደነገገዉ መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚያስችለዉ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት እንደሆነ የተደነገገ ቢሆንም ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነዉ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ እንጂ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ አይደለም፡፡ይህም ታሳቢ ያደረገዉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የየክልላቸዉን ሕገ መንግስትና የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት በማስገባት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ የሚሰየሙትን ዳኞች ብዛት የመወሰን ሥልጣን እንዳላቸዉ ነዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከዚህ ቀደም በሰ/መ/ቁጥር 185278 ላይ በቀን 25/01/2013 ዓ/ም በተሰጠ ዉሳኔ ላይ እና በሌሎች መዝገቦች ላይ የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሦስት ዳኞች በተሰየሙበት ሰበር ችሎት ዉሳኔ በመስጠቱ የተፈጸመ ስህተት እንደሌለ ተገልጾ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የሐረሪ ሕዝብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከላይ በተጠቀሱት ሁለቱም ሕገ መንግስታት በተፈቀደዉ መሰረት ባወጣዉ ሕግ ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሦስት ዳኞች እንደሚያስችል በተደነገገዉ መሰረት ይህንን ጉዳይ ሦስት ዳኞች ተሰይመዉ በሰበር አይተዉ በመወሰናቸዉ ከአሰያየም አንጻር በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ ስህተት የለም ብለናል፡፡

ዋናዉን ጉዳይ በተመለከተ የተያዘዉን ጭብጥ እንደመረመርነዉ የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎችን መርምሮና መዝኖ የሥራ ዉል ማቋረጫ ምክንያት ነዉ ተብሎ በሕግ የተደነገገ በቂ ምክንያት ሳይኖር ተጠሪ አመልካችን የሥራ ዉል ማቋረጡን ማረጋገጡን ገልጾ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ ሲል ወስኗል፡፡ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ላይ እነደተመለከተዉ ተጠሪ እንደ አሠሪ ሠራተኛዉን ሥራ ወዳለበት አዛዉሮ የማሰራት መብት ያለዉ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ሆኖም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ለክሱ በሰጠዉ መልስ ያቀረበዉ ክርክር አመልካችን አላሰናበትኩም የሚል እንጂ ስንብቱ ሕጋዊ ነዉ የሚል አይደለም፡፡አመልካች ደግሞ ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ማስረጃ ተጠሪ እንዴት በሕገ-ወጥ መንገድ እንዳሰናበታቸዉ አስረድተዉ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ በሕግ ከተመለከተዉ አግባብ ዉጭ ተጠሪ አመልካችን እንዳሰናበታቸዉ የቀረቡለትን ማስረጃዎች መርምሮና መዝኖ አረጋግጦ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡በሐረሪ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 70(2/ሐ) ላይ እንደተደነገገዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ፍርድ ቤቶች በተወሰነ የክልል ጉዳይ የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ የሚገኝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ከማረም ባለፈ ማስረጃ መዝኖ የአንድን ፍሬ ነገር መኖር አለመኖር አረጋግጦ የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ በመድረስ ዉሳኔ እንዲሰጥ ሥልጣን አልተሰጠዉም፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ አመልካችን ከሕግ ዉጭ አላሰናበተም የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ የሥር ፍርድ ቤቶች የሠጡትን ዉሳኔ የሻረዉ ማስረጃ በመመዘን ጭምር በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ ብለናል፡፡

የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሥንብቱ ሕገ-ወጥ ነዉ ካለ በኋላ የወሰናቸዉ ክፍያዎችን እንደመረመርነዉ አመልካች ክሱን ያቀረቡት ተጠሪ ከሕግ-ዉጭ ከሥራ አሰናብቶኛል በሚል ሆኖ እያለና በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 32/1 ስር በተመለከቱ ምክንያቶች የሥራ ዉሉ እንደተቋረጠ ባልተረጋገጠበት የሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች በአዋጁ አንቀጽ 41/1 መሰረት የአንድ ወር ደመወዝ በካሳ መልክ እንዲከፍል የሠጠዉ ዉሳኔ የሕግ መሰረት ስለሌለዉ ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡እንዲሁም የጥበቃ ደንብ ልብስና ጫማ በአመት 2 ጊዜ የ2010 እና 2011 ዓ/ም አልተሰጠኝም በሚል አምላክች ብር 6000.00 እንዲከፈላቸዉ ጠይቀዉ የሥር ፍርድ ቤት በርትዕ 3000.00 እንዲከፈላቸዉ የወሰነዉም ቢሆን የደንብ ልብስ የሚሰጠዉ በሥራ ላይ ተገኝቶ ለሚሰራ ሠራተኛ በመሆኑ የሥራ ዉሉ ሲቋረጥ አብሮ የሚቋረጥ እንጂ ሕገ-ወጥ ስንብት በተፈጸመ ጊዜ አሠሪዉ ወደ ግንዘብ ለዉጦ እንዲከፈል የሚገደድበት ጥቅማጥቅም ባለመሆኑ ከዚህም አንጻር የተሠጠዉ ዉሳኔ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ ስህተት በመሆኑ የሚከተለዉን ወስነናል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የሐረሪ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 00101 ላይ በቀን 26/02/2013ዓ/ም የሠጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የሐረሪ ክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 50384 ላይ በቀን 03/07/2012ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የሐረሪ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20027 ላይ በቀን 30/10/2012ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1 መሰረት ተሻሻለዋል፡፡

3. የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች በአዋጁ አንቀጽ 41/1 መሰረት የአንድ ወር ደመወዝ በካሳ መልክ እንዲከፍል እና የደንብ ልብስና የጫማ በሚል በርትዕ ብር 3000.00 እንዲከፍል የወሰነዉ ብቻ ተሽሮ ሌላዉ የዉሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡

4. ግራ ቀኝ በዚህ ችሎት ደረጃ ያወጡትን ወጭ የየራሳቸዉን እንዲችሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

1. የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ ለግራ ቀኙም ግልባጩ ይሰጣቸዉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የዕግድ ትእዛዝ ካለ ተነስቷል፤ይጻፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማ/አ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 198400
ሐምሌ 27 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- መሀመድ አባ ቡልጉ

ተጠሪ፡- የጌምቤ ከተማ ማዘጋጃ ቤት

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሕዳር 14 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 51111 ጥር 5 ቀን 2012 ዓ.ም የስር ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር አመልካች ይዞታው የእኔ ነው የሚል ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 721/2004 እና ደንብ ቁጥር 182/2008 መሠረት ለሚመለከተው አካል አቤቱታ አቅርቦ እንዲከፈለው ማድረግ ሲገባው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት በየደረጃው ያሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን ጎማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካች ከሳሽ፤ የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ፤ በዚህ የሰበር ክርክር የሌለው የጌምቤ ከተማ መምሕራን ማህበር እነ አቶ ደሳለኝ አበበ / 14 ሰዎች ደግሞ ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በአጭሩ፡- አመልካች በሕጋዊ መንገድ የያዝኩት አንድ ፈጫሳ የቡና ችግኝ እና አንድ ፈጫሳ ባህር ዛፍ በ 2004 ዓ.ም ተክለው ጸድቆ የነበረ መሆኑን፤ ተጠሪ ምንም ካሳ ሳይሰጣቸው ከአመልካች ወስዶ ለሰዎች ሲሰጥ የቀረውን አንድ ፈጫሳ በጌምቤ ከተማ ከሶ በር አካባቢ ተብሎ በሚጠራው አዋሳኙ በክሱ ላይ በተገለጸው ይዞታ ውስጥ በቀን 23/09/2011 ዓ.ም በመግባት አጠቃላይ ግምቱ ብር 3830 የሚያወጣ አራት ደጃፍ 3*4 የሆነ 10 ቅጠል ቆርቆሮ ቤት፤ መሪ እንጨት እና ማገር እንዲሁም ከንች ያፈረሰባቸው መሆኑን በመግለጽ አፍርሶ የወሰደውን የንብረት ግምት ብር 3830 / ሶስት ሺሕ ስምንት መቶ ሠላሳ ብር / እንዲከፍላቸው እና በይዞታቸው ላይ የፈጠረው ሁከት እንዲወገድ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ በሰጠው መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው መሬት በከተማው አስተዳደርም ሆነ በአመልካች ቁጥጥር ስር አለመሆኑን፤ መሬቱ ሳይት ፕላን ወጥቶበት በሕጋዊ መንገድ ለሌሎች ሰዎች የተሰጠ እና አመልካች መብት ሳይኖራቸው ክስ ያቀረቡ መሆኑን በመግለጽ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 33/2 መሠረት ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ጣልቃ-ገብ ባቀረበው የጣልቃገብነት ክርክር በክሱ ላይ የተገለጸው መሬት በቀን 26/07/2011 ዓ.ም ተጠሪ ተሰጥቶአቸው ለቤት መስሪያ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን አጠራቅመው ባሉበት ሁኔታ አመልካች ሁከት በመፍጠራቸው ቤቱን ለመስራት እንዳልቻሉ በመግለጽ በይዞታው ላይ ቤት እንዲሰሩበት እና የንብረቱን ግምት የማግኘት መብታቸው እንዲጠበቅ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

የስር ጣልቃገብ ላቀረበው መከራከሪያ አመልካች በሰጡት መልስ ይዞታው ለጣልቃ ገብ መሰጠቱን አላውቅም፤ ጣልቃገብ የሰጠውን አካል ከመጠየቅ በቀር ከአመልካች ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፤ ይዞታው የአመልካች እንጂ የቀበሌ አስተዳደር አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ጣልቃገቡ ላቀረበው መከራከሪያ በሰጠው መልስ፡- ይዞታው በሕጋዊ መንገድ ለጣልቃ ገብ የተሰጠ ነው፤ አመልካች ይዞታውን ኮሎኔል ለማ ዋሚ ከሚባሉ ግለሰብ በምን አግባብ እንዳገኙ ያልገለጹ ሲሆን ግብር የገበሩበትንም ሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ አላቀረቡም፤ ቦታው ለሕዝብ ሲሰጥም አልተቃወሙም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ስለጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ካደረገ በኋላ አመልካችን ጨምሮ ክስ በቀረበበት ይዞታ ላይ በአካባቢው ላለ ለማንኛውም ባለይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ያልተሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል፤ አንድ ይዞታ ለልማት ሲፈልግ አስፈላጊው ካሳ ለባለይዞታው ሊከፈለው እና ምትክ መሬት ሊሰጠው ይገባል፤ ተጠሪ ከሕግ ውጪ የአመልካችን የግል ይዞታ የወሰደ እና ሁከት በመፍጠር ብር 3830 / ሶስት ሺሕ ስምንት መቶ ሰላሳ / የሚገመት ንብረት ያወደመበት በመሆኑ ይህንኑ ገንዘብ ከፍሎ የፈጠረውን ሁከት በማቆም ይዞታውን ለቆ እንዲወጣ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል። ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም አመልካች ይዞታውን የገዛበትን ውል እና ይዞታውን ሽጠለት የተባለው ግለሰብ መብት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፤ አመልካች ይዞታው የእኔ ነው የሚል ከሆነም በአዋጅ ቁጥር 721/2004 እና ደንብ ቁጥር 182/2008 መሠረት ለሚመለከተው አካል አቤቱታ አቅርቦ እንዲከፈለው ማድረግ ሲገባው የሁከት ይወገድልኝ ክስ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮታል። ይህም ውሳኔ በየደረጃው ባሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ጸንቷል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካች አከራካሪውን ይዞታ በሕገወጥ መንገድ የያዝኩት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፤ የስር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ከተጠየቀው ዳኝነት ውጪ በመውጣት እና በአግባቡ በማስረጃ ሳያረጋግጥ አዋጅ ቁጥር 721/2004 እና ደንብ ቁጥር 182/2008 መሰረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ አመልካች ባቀረቡት ምስክሮች እና በሚመለከተው የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የሐገር ሽማግሌዎችን ያካተተ ኮሚቴ ተዋቅሮ ተጠሪ የአመልካችን ይዞታ ከሕግ ውጪ ለጣልቃ ገብ የሰጠ ስለመሆኑ ተገልጾ ባለበት ሁኔታ ተጠሪ የፈጠረው ሁከት የለም በሚል የመወሰኑን አግባብነት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል። ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች ኮሎኔል ለማ ዋሚ ከሚባል ግለሰብ በሽያጭ ያገኘበትን የሽያጭ ውልም ሆነ ይዞታውን በሌላ አግባብ ያገኘ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፤ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ ለሕዝብ ሲሰጥ አመልካች ለየትኛውም የአስተዳደር አካላት ቅሬታ አላቀረበም፤ ማሕበሩ ቤት ለመስራት ሲል አመልካች በሕገ ወጥ መንገድ ቤት መስራቱ አግባብ አይደለም፤ አመልካች ከሽማግሌዎች እና ከሰው ማስረጃ በቀር የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እና የግብር ደረሰኝ አላቀረበም፤ መሬትን መሸጥ መለወጥ አይቻልም፤ አመልካች ያቀረበውን የአላባ ጥያቄ ለዚሁ ጉዳይ ለተቋቋመው የአስተዳደር ክፍል ማቅረብ ይችላል፤ የግንባታ ፍቃድ ሳይኖረው የገነባውን ቤት ተጠሪ ለማፍሰም ሆነ ለማገድ የሚያስችል ሙሉ ስልጣን ስላለው የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል የሚል ነው።

አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

በመሠረቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 40(4) ማናቸውም ኢትዮጲያዊ አርሶአደር የመሬት ባለይዞታ የመሆን እና ከይዞታው ያለመፈናቀል መብት ያለው መሆኑን ይደነግጋል። የዚሁ ሕግ

አንቀጽ 40(1)እና(7) ድንጋጌዎችም ማንኛውም ኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆን የተከበረለት/ላት መሆኑን፤ በጉልበቱ፣ ወይም በገንዘቡ በመሬቱ ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት እንዳለው፤ይህ መብትም የመሸጥ፤የመለወጥ፤ የማውረስ፤የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፤ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን የሚያካትት እና ዝርዝር አፈጻጸሙም በሕግ የሚወሰን መሆኑን ይደነግጋሉ፡፡ የዚሁ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ ስምንት ደግሞ የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም አስፋላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

ሕገ-መንግሥቱን ተከትለው የወጡት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን እና የንብረት ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 455/ 1997 እና የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 ድንጋጌዎችም የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መንግስት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ እንደሚችል በተመሳሳይ ሁኔታ ይደነግጋሉ፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አከራካሪ በሆነው ይዞታ ላይ አመልካች መብት ያለው ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፤ ቦታውም ለሕዝብ ተሰጥቷል በማለት የሚከራከር ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በሚመለከተው የመሬት አስተዳደር እና በአካባቢው ሽማግሌዎች ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት አመልካችን ጨምሮ በአካባቢው ላሉ ባለይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ያልተሰጣቸው ቢሆንም አመልካች ይዞታውን በሰነድ አልባ ለረጅም ጊዜ ይዘውት የነበረ መሆኑን እና ተጠሪ ከሕግ ውጪ የአመልካችን ይዞታ በመውሰድ ሁከት የፈጠረባቸው እና ንብረታቸውን ያወደመባቸው ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በዚህ አግባብ ይዞታውን ይዘው ሲጠቀሙበት የነበረ ስለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና የአፈጻጸም መመሪያዎች መሠረት ከመሬት አለመነቀልን እና ካሳን አስመልክቶ ሰነድ አልባ ይዞታዎች በልዩ ሁኔታ ሊስተናገዱ የሚችሉበት ስርዓት ስለመኖር አለመኖሩ በቅድሚያ ተጣርቶ እንዲቀርብ ካልተደረገ በቀር በጉዳዩ ላይ ፍትሐዊ ውሳኔ መስጠት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ይህ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የየራሳቸውን ምክንያት በመስጠት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጎማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 44184 ሕዳር 12 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 51111 ጥር 5 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 222416 ጥር 22 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 332900 መጋቢት 03 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የጎማ ወረዳ ፍርድ ቤት አግባብነት ባላቸው ሕጎች እና የአፈጻጸም መመሪያዎች መሠረት ከመሬት አለመነቀልን እና ካሳን አስመልክቶ ሰነድ አልባ ይዞታዎች በልዩ ሁኔታ ሊስተናገዱ የሚችሉበት ስርዓት ስለመኖር አለመኖሩ ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማድረግ እና ጉዳዩን ለማጣራት የሚያስችለውን ተገቢ ነው ያለውን ትዕዛዝ በመስጠት ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞየኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የሰ/መ/ቁጥር 198071
ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሀምሌ 27 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ተስፋዬ ኪዳኔ፡- ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አቶ ወርቁ ዋበሎ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርምራ ሲሆን በዚህ አግባብም ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል

ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የከተማ ቦታን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች አከራካሪውን ይዞታ በመልቀቅ ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች መፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አመልካች ስላመለከቱ ነው፡፡አመልካች በሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት ተከሳሽ የነበሩ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡

ተጠሪ የካቲት 19 ቀን 2011 ዓ.ም ጽፈው በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስም አዋሳኙ በክሱ ውስጥ የተጠቀሰውን በቢቾ ቀበሌ የሚገኘውን ይዞታ ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ በስጦታ አግኝቼ ቆርቆሮ ቤት ሰርቼ የምጠቀምበትን በ2008 ዓም በተደረገው ህገ ወጥ ይዞታን ስርአት የማስያዝ አሰራር ይገር ካለሁበት 6 ሜትር መንገድ በመውሰዱ ወደ አመልካች ይዞታ ውስጥ ሲያስገባኝ አመልካችም ከኋላ ለኔ ለቅቆ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ወደፊት እንዲሸጋሸግ ሲደረግ ለኔ በተሰጠኝ ይዞታ ላይ ቤት ገንብቶ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላልሆነ በራሱ ወጪ አፍርሶ እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጡ በታዘዙት መሰረት አመልካች በሰጡት መልስም ለተጠሪ ተለክቶ ድንጋይ ተተክሎ 200 ካሜ የሰጠ አካል ስለሌለ ፣አመልካች ከአቶ አለማየሁ ቃልቤ 260 ካሜ በውል አግኝቼ ቤት ሰርቼና ንብረት አፍርቼ ባለሁበት በ2008 ዓም ሽንሻኖ ሲደረግ በአካባቢው ካለው ችግር አንፃር ባለንበት እንድንቆይ ከማድረግ ባለፈ ድንጋይ ተተክሎ ተለክቶ የተሰጠ ይዞታ ባለመኖሩ የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ በአካል ቦታው ተገኝቶ ምልከታ አድርጎ ተገቢውን ማጣራት አድርጎ በሰጠው ውሳኔም የአመልካች ምስክሮች በስፍራው ምንም አይነት ሽንሸና አለመደረጉን ሁሉም እንደያዘ እንዲቆይ የመንገድ መለያ ድንጋይ ብቻ ተተክሎ መታለፉን ማስረዳታቸውን፣በምልከታም ይኸው መረጋገጡን፣ማዘጋጃ ቤቱ በሰጠው ምላሽም ግራ ቀኙ በህገ ወጥነት ይዞታውን የያዙ ሆኖ ሰነድ እየተጠባበቁ ያሉ እንጂ አንዱ በአንዱ ይዞታ ውስጥ የሚገባበት አካሄድ የለም በማለት መግለፁን በመጥቀስ አመልች ይዞታውን ለተጠሪ የሚለቅበት የህግ አግባብ የለም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በሰጠው ውሳኔም የተጠሪ ምስክሮች እንደ ክስ አቀራረባቸው ሲያስረዱ የአመልካች ምስክሮች ደግሞ በሽንሻኖ ወቅት ሁለቱ በመጣላታቸው ምክንያት መሀንዲሶቹ ድንጋይ ሳይተክሉ ወጥተዋል በሚል ያስረዱ መሆኑን፣ተጠሪ በሊዝ አዋጁ መሰረት ይዞታውን ህጋዊ ለማድረግ በ2008 ዓም ቅጣት ለመንግስት ገቢ ያደረጉ ለመሆኑ የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ፣የክፍለ ከተማው ማዘጋጃ ቤት ለተጠሪ ይዞታ ማህደር ሲኖር ለአመልካች ይዞታ ማህደር የሌለው መሆኑን መግለፁን ፣የግራ ቀኙ ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል በስፍራው ሽንሻኖ መኖሩን የሚያሳይ መሆኑን በመጥቀስ አጠቃላይ ማስረጃዎቹ እንደ ተጠሪ ክርክር የሚያስረዱ መሆኑን በመጥቀስ አመልካች ምንም እንኳ በእጁ ምንም አይነት ህጋዊ ሰነድ ባይኖረውም ተጠሪ ይልቀቅልኝ ለሚለው ማካካሻ ከፊት ለፊት መንገድ የሆነውን ያገኘ ስለሆነ 6 ሜትር ለተጠሪ ለቆ ያስረክብ በማለት ወስኗል፡፡ይህ ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና በሰበር ሰሚ ችሎቱ ፀንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ህዳር 08 ቀን 2013 ዓም በተፃፈ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ባለይዞታ መሆኔን፣በይዞታውም ላይ ንብረት መኖሩን፣ይዞታውም ያልተሸነሸነ መሆኑን ከሰውና ከሰነድ ማስረጃ እንዲሁም ከማዘጋጃ ቤቱ ምላሽ አረጋግጦ እያለ፣ተጠሪ ንብረቱ በእጃቸው መኖሩን ሳያረጋግጡ ይመለስልኝ በማለት ሊጠይቁ የሚችሉበት የህግ አግባብ ሳይኖር ፣በአስተዳደር አካል ያልተሰጠውን መብት ፍርድ ቤቶቹ ለተጠሪ መስጠታቸው አግባብነት የለውም፣በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረት ቢፈፀም የቤቴን ሙሉ ሳሎን በመሰንጠቅ ቤቴን ሙሉ

ለሙሉ የሚያፈርስ ሆኖ ከመኖሪያ ቤቱ የሚያፈናቅለኝ በሆነበት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከማዘጋጃ ቤቱ ማብራሪያ ውጪ ቦታው ተሸንሽኗል በማለት ተጠሪ ድንጋይ ቢተከል እዚህ ጋር ይሆናል በማለት ያሳየውን በመቀበል የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤

አመልካች ይዞታዬን ለማጣት የምገደደው የከተማ መሬት በሊዝ ስለመፍቀድ በወጣው ደንብ ቁጥር 123/2007 ለማስፈፀም ተሸሽሎ በወጣው መመሪያ ቁጥር 08/07 መሰረት ስታንዳርዱ 200 ካሜ ተደርጎ መብቴ ተጠብቆ ፤መሬትም የሚሰጠኝ ከሆነ ድርሻዬ ተሰጥቶኝ የሸንሸና ድንጋይ ተተክሎ ሊሆን ሲገባ ይህ ባልተደረገበት ፤ምልከታውንም በተመለከተ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለምልከታ ግራ ቀኙችን እንድንገኝ ትዕዛዝ ሳይሰጥ ከፍርድ ቤት አንድም ተወካይ ሳይኖር የተፈፀመ በመሆኑ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተሽሮ የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር የመ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ግራ ቀኙ ያላቸው ይዞታ ሰነድ አልባ ስለመሆኑ ከተገቢው የአስተዳደር አካል በመጣው ምላሽ ተገልፆ እያለ አመልካች አልፎ የያዘውን የተጠሪን ይዞታ እንዲለቅ የተወሰነበትን አግባብ ለማጣራት ለዚህ ሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ የካቲት 11 ቀን 2013 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት መልስ የጎፈር ሜዳ ክ/ከተማ ማዘጋጃ ቤት ቀድሞ የያዝኩትን 6 ሜትር ከፊት ለፊት እንድለቅና ወደ ኋላ እንድሄድ ድንጋይ ሲተከል በዚህ በተወሰደብኝ ምትክ የአመልካች በምስራቅ በኩል 6 ሜትር የተሰጠኝ ሲሆን አመልካችም በዚሁ በሚለቀው ቦታ ምትክ በስተምዕራብ በኩል 6 ሜትር ተሰጥቶት የያዘ በመሆኑ ለመልቀቅም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ፤ይዞታዬ የሆነውን 200 ካሜ ህጋዊ ለማድረግ ተገቢውን ክፍያ የፈፀምኩኝ በመሆኑ፤አመልካች ለኔ የተሰጠኝንና ለራሱ በምትክ የተሰጠውን ይዞታ ይዞ ከመደበኛው የቦታው አሰጣጥ 200 ካሜ በላይ በድምሩ 353.08 ካሜ ይዞ የሚገኝ በመሆኑ ፤አመልካች ለይዞታው ህጋዊ የሆነ ምንም አይነት ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲፀናላቸው ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ከሰበር ቅሬታው አኳያ እና ከስር ፍ/ቤት መዝገብ ይዘት አንፃር አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡በመሰረቱ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ክሳቸውን ያቀረቡት ማዘጋጃ ቤቱ በ2008 ዓም ባደረገው ህገ ወጥ ይዞታን ስርአት የማስያዝ አሰራር ይዘው ካለበት 6 ሜትር መንገድ በመውሰዱ ወደ አመልካች ይዞታ ውስጥ ሲያስገባቸው አመልካችም ከኋላ ለቅቆላቸው ወደፊት እንዲሸጋሸግ የተደረገ መሆኑን ነገር ግን በሸግሸግ የደረሳቸውን ይዞታ አመልካች ለመልቀቅ ፈቃደኛ አለመሆኑን ገልፀው በፍርድ ሀይል ለቅቆ እንዲያስረክባቸው በመጠየቅ ነው፡፡የተጠሪ የይገባኛል ጥያቄ መነሻው በማዘጋጃ

ቤቱ እውቅናና ፍቃድ መሰረት የሚደረግን ሰነድ አልባ ይዞታን በህግ አግባብ ስርአት በማስያዝ ሂደት የተፈጠረን ሽግሽግ መሰረት ያደረገ በመሆኑ በዋነኝነት በማዘጋጃ ቤቱ እውቅናና ክትትል የተፈፀመ ሽግሽግ መኖር አለመኖሩ ላይ ግራ ቀኙ የተካካዱ በመሆኑ የሂደቱ ባለቤት የሆነው ማዘጋጃ ቤቱ ለክሱ መነሻ የሆነውን ሽግሽግ ማድረጉን ተጠሪ ሊያስረዱ ይገባል፡፡

የተጠሪ ምስክሮች የተጠሪን ቦታ 6 ሜትር ያህል መንገድ ስለወሰደው ማዘጋጃ ቤቱ ድንጋይ ተክሎ ወደ አመልካች ይዞታ 6 ሜትር ገብተው ሰነድ አልባ ይዞታውን ህጋዊ ስርዓት የማስያዙ ሂደት የተጠናቀቀ መሆኑን ያስረዱ ቢሆንም ማስረጃን የመስማት ፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ያለው የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባደረገው ማጣራት ማዘጋጃ ቤቱ ተጠሪ የያዙት ይዞታ ቀድሞውኑ በቂ በመሆኑ አንዱ ወደ አንዱ ይዞታ ውስጥ ገብቶ ሽግሽግ የተደረገበት ሁኔታ አለመኖሩን በ17/10/2011 ዓም በሰጠው ምላሽ እንዳረጋገጠ በውሳኔው ላይ አመልክቷል፡፡ይህም በግልፅ በማዘጋጃ ቤቱ እውቅና የተሰጠው ለተጠሪ መብት የሚፈጥር ሽግሽግ አለመኖሩን ያሳያል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሲሽሩ ለተጠሪ መብት መፈጠር መነሻ የሆነውን ለስር ፍርድ ቤት ከተሰጠው የተለየ የማዘጋጃ ቤቱ ምላሽ መኖሩን በውሳኔያቸው ላይ አላመለከቱም፡፡

የተጠሪ ክስ መነሻው ማዘጋጃ ቤቱ በፈፀመው ሽግሽግ ምክንያት የተፈጠረን መብት መሰረት ያደረገ ሆኖ እያለ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ማዘጋጃ ቤቱ ያደረግኩት ሽግሽግ የለም እያለ ምስክሮቹ ሽንሻኖ እና ሽግሽግ መኖሩን በሚያሳይ መልኩ አስረድተዋል የሚል መነሻ በመያዝ ክርክሩ በይዞታው ላይ በህግ የተረጋገጠ የቀደመ መብት አለኝ የሚል ባልሆነበት ተጠሪ በሊዝ አዋጁ መሰረት ይዞታውን ህጋዊ ለማድረግ በ2008 ዓም ቅጣት ለመንግስት ገቢ ያደረጉ ለመሆኑ የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን ፣የክፍለ ከተማው ማዘጋጃ ቤት ለተጠሪ ይዞታ ማህደር ሲኖር ለአመልካች ይዞታ ማህደር የሌለው መሆኑን መግለፁን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩና በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች በዋነኝነትም ሰበር ሰሚ ችሎቱ የግራ ቀኙን የይዞታ ስፋት ልክ በማወዳደር አመልካች ለችሎቱ የገለፀውና በአካል ሲለካ የተገኘው ልዩነት አለው በማለት ለግራ ቀኙ ክርክር መሰረታዊ ነጥብ የሆነውን በማዘጋጃ ቤቱ እውቅና የተደረገ ሽንሻኖና ሽግሽግ መኖሩን የጉዳዩ ባለቤት ከሆነው ማዘጋጃ ቤት በማጣራት ከስር ፍርድ ቤት የተለየ ምላሽ ሳያገኙ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻራቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ውሳኔ

1.የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.20670 ነሀሴ 23 ቀን 2011 ዓም የሰጠው ውሳኔ እና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.14065 ጥር 27 ቀን 2012 ዓም እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.14731 ነሀሴ 18 ቀን 2012 ዓም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2.የሆሳዕና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.28508 ሀምሌ 05 ቀን 2011 ዓም የሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

3.ጥር 17 ቀን 2013 ዓም በዋለው ችሎት በአፈፃፀም መዝገብ ቁጥር 29719 በተያዘው አፈፃፀም ላይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

4.ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>ክርክሩ ተግቢውን እልባት ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ክራሲያዊ ሪፐብሊክ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 197432
ሐምሌ 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ

ተጠሪ፡- መልካሙ ዳታ ደሴ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥቅምት 20 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 192545 ሐምሌ 27 በቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ወንጀልን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- ተጠሪ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 670 ድናጋጌን በመተላለፍ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሡ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በቀን 08/03/2012 ዓ.ም ከሌሊቱ በግምት 11፡00 ሠዓት ሲሆን በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ክልል ልዩ ቦታው ሸገር ሕንጻ አካባቢ በሚገኘው የግል ተበዳይ አቶ ብሌን ጎይትኦም ብርክስትን ክለብ ውስጥ አበባየሁ ከተባለው ካልተያዘ ግብረ አበሩ ጋር በመሆን የበሩን ቁልፍ ፈልቅቀው በመግባት ክለብ ውስጥ የነበረውን 2ኛ የዓቃቤሕግ ምስክር ቃለአብ ቱፋን በተኛበት መጥተው ተጠሪ ቢላዋ በመያዝ ከተንቀሳቀስክ እወጋሃለሁ በማለት ካስፈራራው በኋላ አፉን በፎጣ ሲያፍነው ያልተያዘው ግብረአበሩ ደግሞ በሲባጎ ገመድ አንገቱን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አንቆ ከአልጋው ብረት ጋር በማሰር ራሱን እንዲስት ካደረጉ በኋላ አጠቃላይ ግምቱ ብር 202,000.00 / ሁለት መቶ ሁለት ሺሕ / የሆነ የሙዚቃ ማጫወቻ ሚክሰር፤ የሙዚቃ ማጫወቻ፤ ላፕቶፕ እና ሞባይል በመውሰድ ከተሰወሩ በኋላ በክትትል ተይዞ በምሪት የተገለጹት ንብረቶች ተመላሽ በማድረግ በፈጸመው የውንብድና ወንጀል ተከሷል የሚል ነው።

ተጠሪ ክሱ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በኋላ ክሱን ሳይቃወም የእምነት ክሕደት ቃሉን ሲጠየቅ ዕቃዎቹን የወሰድኩት ድርጅቱ የሠራሁበትን የአምስት ወር ደመወዝ እና የሁለት ዓመት የአገልግሎት ክፍያ ስለከለከለኝ ነው በማለት መብቱን ጠብቆ ቃሉን መስጠቱ ፍርድ ቤቱ በክሕደት መዝግቦ የዓቃቤ ሕግን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን መፈጸሙ የተመሰከረበት በመሆኑ ክሱን እንዲከላከል ሲል ብይን ሰጥቷል። ተጠሪም መከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን በመግለጹ ፍርድ ቤቱ ተጠሪን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 መሠረት ጥፋተኛ ብሎ በአራት ዓመት ከአምስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል።

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል። ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በዓቃቤሕግ ምስክሮች በኩል ሳይቀር የተነገረው ተጠሪ በግል ተበዳይ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ ይሰራ እንደነበር እና በወቅቱም ከስራ ተሰናብቶ ባለበት ወቅት ያልተከፈለው ደመወዝ ክፍያ የነበረው መሆኑን ነው፤ ተጠሪ ወሰደ የተባለውን ንብረት ሙሉ ለሙሉ ለግል ተበዳይ የመለሰ ስለመሆኑም አልተካደም፤ ይህም የሚያሳየው የግል ተበዳይን ንብረት ሕገወጥ በሆነ መንገድ የወሰደው ውንብድና ለመፈጸም ሳይሆን ያልተከፈለውን ክፍያ ለማስፈጸም ስለመሆኑ ግልጽ በመሆኑ ተጠሪ የነበረው የወንጀል ሐሳብ ውንብድና ሳይሆን መብቱን በሕገወጥ መንገድ ማስከበር ወንጀል ነው በማለት ጥፋተኛ የተባለበትን የሕግ አንቀጽ ቀይሮ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 431/ለ / ይህ አንቀጽ በስሕተት የተጠቀሰ እና አንቀጽ 436/ለ ለማለት ተፈልጎ እንደሆነ ግንዛቤ ተወስዶበታል / መሠረት ጥፋተኛ ብሎ በስድስት ወር ቀላል እሥራት እንዲቀጣ ሲል ወስኗል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል ሲሆን ይዘቱም፡- የወንጀል ድርጊቱ በተፈጸመበት ጊዜ ተጠሪ ከስራ ተሰናብቶ እንደነበር እና ያልተከፈለው ደመወዝ እንደነበረው የተሰጠ የምስክርነት ቃል የለም፤ ተጠሪ ንብረቱን ለግል ተበዳይ መመለሱ የውንብድና ወንጀል ለመፈጸም ሀሳብ እንደሌለው ያሳያል መባሉም ተገቢ አይደለም፤ የተወሰደውን ሐብት የመመለስ ጉዳይ በአድራጊው ፈቃደኝነት የተፈጸመ ቢሆንም የተፈጸመውን ወንጀል አያስቀረውም፤ ተጠሪ ንብረቱን የመለሰው በራሱ ፈቃደኝነት ሳይሆን በፖሊስ ቁጥጥር ስር ከዋለ በኋላ ነው፤ ስለሆነም እነዚህ ሁኔታዎች ከግንዛቤ ሳይገቡ በስር ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 ሥር የተመለከተውን ወንጀል በመተላለፍ የውንብድና ወንጀል የፈጸመ ስለመሆኑ በተገለጸበት ሁኔታ በሕገ ወጥ መንገድ መብቱን ለማስከበር የተደረገ ድርጊት ነው በሚል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 436/ለ ጥፋተኛ የመባሉን አግባብነት

ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ስላልቀረበ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይሕ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድን ሰዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 የተመለከተዉን የዉንብድና ተግባር ፈጽሟል ብሎ ጥፋተኛ ለማድረግ ድርጊቱ ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት አስቦ፤ የሌላ ሰዉ ንብረት የሆነዉን ተንቀሳቃሽ ዕቃ ለመዉሰድ እንዲያመቸዉ ወይም በሚወስድበት ጊዜም ሆነ ከወሰደ በኃላ የገጠመዉን ተቃዉሞ ዉጤታማነት ለማስቀረት ሲል በሌላ ሰዉ ላይ የኃይል ድርጊት ወይም ከባድ የሆነ የማንገላታት ተግባር ወይም ዛቻ የፈጸመ ወይም በማናቸዉም ሌላ መንገድ ይህንን ሰዉ ለመከላከል እንዳይችል ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት የተሰሙትን የዓቃቤሕግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል መርምሮ እና መዝኖ ተጠሪ ድርጊቱን የፈጸመው በተከሰሰበት ድንጋጌ ላይ የተገለጹትን የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች መሠረት ሳይሆን ያልተከፈለውን ደመወዝ ለማስከፈል ስለመሆኑ አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የአመልካች አድራጎት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 670 ድንጋጌን የሚያቋቁም አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ የሀይል ተግባር በመጠቀም የራሱ ያልሆነውን ንብረት የወሰደ ስለመሆኑ የተረጋጠ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው አድራጎቱ ሊሸፍነው በሚገባው የሕግ አንቀጽ ሥር ነዉ፡፡ የተጠሪን አድራጎት የሚሸፍነዉ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 436/ለ ማንም ሰው መብት ሳይኖረው ወይም ሕግን ተቃራኒ በሆነ መንገድ ሊከፈለው የሚገባውን ክፍያ ለማግኘት ሲል የባለዕዳው ንብረት የሆነውን ማናቸውንም ተንቀሳቃሽ ዕቃ የወሰደበት እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ይቀጣል በማለት ይደነግጋል፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አልተከፈለኝም የሚለውን ክፍያ እንዲከፈለው ለማድረግ ሲል ድርጊቱን የፈጸመ በመሆኑ ጥፋተኛ ሊባል የሚገባው አድራጎቱ በሚሸፍነው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 436/ለ ድንጋጌ ነው፡፡ ስለሆነም የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንኑ መሠረት በማድረግ ተጠሪን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 436/ለ መሠረት ጥፋተኛ በማለት ቅጣቱን አሻሽሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አልተፈጸመበትም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ውሳኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 192545 ሐምሌ 27 በቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ለ/2 መሠረት ጸንቷል፡፡

- መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሰ/ኃ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

ሰ/መ/ቁ፡-197405

ቀን፡- 29/02/2014ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡- 1ኛ. የቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 አስተዳደር ጽቤት } አልቀረቡም

2ኛ. የቂ/ክ/ከተማ ቤቶች አስተዳደር ጽቤት }

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያና ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት- ነ/ፈጂ ወይንሸት እንድሪስ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 247606 ግንቦት 17 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፀው በሰበር ችሎት ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ባቀረቡት ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡አመልካቾች በስር በፌደራል መጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት ተከሳሾች የነበሩ ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ ነበር፡፡

ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካቾች ላይ ባቀረበው ክስ ተጠሪ በኢትዮጵያ ጅቡቲ መንግስት መካከል በተደረገው ዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት በተቋቋመ የሁለቱ መንግስታት ንብረት የሆነ የዓለም አቀፍ ድርጅት ሲሆን በሁለቱ መንግስታት የመሬት ይዞታ ተለክቶ ተሰጥቶታል፡፡በአዋጅ ቁ. 47/67 አንቀጽ 43 እና 5 (3) መሰረት የዓለም አቀፍ ድርጅት ቦታ የማይወረስ ሲሆን የተጠሪ ቤትና ይዞታ ያልተወረሰ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤም በወቅቱ ከነበረው የከተማ ልማትና ቤት ሚኒስቴር ተሰጥቶታል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ተጠሪ ለአጣዳፊ ስራ ለሚፈልጉ ሰራተኞች ቤት ስለሚሰጥ በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 159 ለአቶ ነጋሽ ተፈራ ሰጥቶ ነበር፡፡የእኚህ ግለሰብ የስራ ግንኙነት በሞት ምክንያት የተቋረጠ ሲሆን በህይወት እያለ ቤቱን ከሕግና ከድርጅቱ አሰራር ውጪ ኃ/ማሪያም አስራት ለተባለ ሰው አስተላልፈው አቶ ኃ/ማሪያም አስራት ደግሞ ቤቱን የቀበሌ በማስመሰል በወቅቱ ከአመልካቾች ጋር ውል ተዋውሏል፡፡ግለሰቡ አሁን በህይወት የሌለ ሲሆን ወራሾች ኮንዶሚንየም ደርሷቸው ወረዳው ቤቱን ተረክቦ አሽነት በነበረ ጊዜ ጥቅምት 27/2010 ዓ.ም ቤቱን እንዲያስረክቡ ማስጠንቀቅያ ቢሰጣቸውም ለማስረከብ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡በመሆኑም አመልካቾች በአዋጁ ያልተወረሰ ቤት የያዙ ስለሆነ ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንልን በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካቾች መቃወሚያ አቅርበው ፍርድ ቤቱም መቃወሚያዎቹን መርምሮ ውድቅ በማድረግ ብይን የሰጠ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጡት መልስም የቤት ቁጥር 159 በአዋጅ ቁ.47/67 መሰረት ተወርሶ መንግስት የሚያስተዳድረው የመንግስት ቤት ነው፡፡ የተወረሰውም ከአቶ ነጋሽ ተፈራ ላይ ሲሆን ቤቱ ለአቶ ኃ/ማሪያም አስራት ተከራይቶ ቆይቶ አሁንም ለሌለ ሰው ተከራይቶ ያለ ነው፡፡ስለዚህ የተጠሪ ክስ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌደራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ መርምሮ በሰጠው ውሳኔም ተጠሪ አለም አቀፍ ድርጅት ሆኖ በሁለቱ መንግስታት ተለይቶ የተሰጠውን ይዞታ የሚያመለክት የአየር ካርታና በዚህ በተለየው ቦታ ውስጥ የሚገኙትን ቤቶች ዝርዝር ያቀረበ መሆኑን፣ተጠሪ ለንብረቱ ካርታ ማቅረብ የማይጠበቅበት መሆኑን በሰበር መዝገብ ቁጥር 21684 ከተሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ መገንዘብ የሚቻል መሆኑን፣አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ከአቶ አስራት ኃ/ማሪያም ጋር የኪራይ ውል በማድረግ የአስተዳደር አካሉ ኪራይ ሲሰበስብበት የነበረ ቢሆንም አመልካቾች ለተጠሪ ተለይቶ የተሰጠው ይዞታ የለም ይህ ቤትም በዚህ በተለየ ይዞታ ውስጥ አይገኝም በተጠሪም አልተሰራም በማለት ያቀረቡት ክርክር ባለመኖሩና ባለንብረትነትን የሚያፀድቀው የስራና ቤት ሚኒስቴር ለተጠሪ በተሰጠው ክልል ውስጥ ያለ ይዞታና ንብረት ሊወረስ እንደማይችል፣የተወሰደ ይዞታና ንብረት ካለም እንዲመለስለት የተፃፈውን ደብዳቤ በማቅረብ ያስረዳ ስለሆነ አመልካቾች ክርክር የቀረበበትንና በቂ/ክ/ከተማ ወረዳ 10 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 159 ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፀንቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ከዓለም አቀፍ ሕግ አንፃር ያቀረቡት ክርክር የፌደራል ቤቶችን ለማቋቋም በወጣው ሕግ አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቅጽ 11(2) መሰረት ዓለም አቀፍ ሕግን የሚመለከት በመሆኑ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ ሳለ የስር የመጀመሪ ደረጀ ፍርድ ቤት ከፍርድ ቤቱ የስረ ነገር ስልጣን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖረው የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ አከራካሪው የቤት ቁጥር 159 የሆነው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ በመሆኑ አስተዳደሩ ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ጉዳዮች በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 መሰረት የከተማ የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ ጠቅሰን ለፍርድ ቤቱ ያቀረብነውን አቤቱታ አልፎ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ ተጠሪ ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ ያቀረበው ቃለ ጉባኤ ፣የአየር ካርታ ፣ዓለም አቀፍ ስምምነት ክርክር ባስነሳው ቤት መብት ያለው ስለመሆኑ ያቀረበው የቤት ባለቤትነት ማስረጃ ወይም የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በሌለበት ባለመብት መሆኑን የሚያሳይ ባልሆነበት የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበውን ክስ ተቀብሎ የሰጠው ውሳኔ የማስረጃ መርህ ያልተከተለና መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊሻር ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡

ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 በመንግስት የተወረሰ ስለመሆኑ በተገለፀበትና ተጠሪ የቤቱ ባለቤት ሆነው ለአቶ ነጋሽ ተፈራ ያስተላለፉት ስለመሆናቸው ተረጋግጧል በሚል አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ የተወሰነበትን አግባብ ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት መልስ እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሰጠው መልስም አንድ ክርክር በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 11(2)(ሀ) መሰረት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችለው ድርጅቱ አለም አቀፍ ስለሆነ ሳይሆን ጉዳዩ የአለም አቀፍ ህግን የሚመለከት ሆኖ ሲገኝ በመሆኑ፣የከተማ አስተዳደሩን ፍርድ ቤት ስልጣን አስመልክቶም ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ስልጣን የሚኖረው የከተማው አስተዳር ስለመሆናቸው ክርክር ባልቀረበባቸው የይዞታ፣የኪራይና ተመሳሳይ ክርክሮች ላይ በመሆኑ አመልካቾች ይህንን በተመለከተ ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፣አመልካቾች ክርክር የተነሳበትን ቤት አከራይቼ ይኖሩ ነበር ያላቸው አቶ ኃ/ማሪያም አስራት ሲሞቱ ባለቤታቸው ወ/ሮ እቴነሽ ነጋሽ ቤቱ የተጠሪ መሆኑን አውቀው ቤቱን እንድንረከባቸው ለተጠሪ ድርጅት የፃፉትን ደብዳቤ ለስር ፍርድ ቤት አያይዘን አቅርበናል፣ከዚህም በተጨማሪ የተጠሪ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ሊወረሱ እንደማይችሉ የስራና ከተማ ልማት ቤት ሚኒስቴር የፃፈውን ማስረጃ በማቅረብ ክርክራችንን ያስረዳን ስለሆነ ይህም ክርክር የተነሳበት ቤት በሕግ አግባብ ያልተወረሰ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ አመልካቾች የቤት ቁጥር የማይገልጽ ተዓማኒነት የጎደለውን ቅጽ በማቅረብ ቤቱ ተወርሷል ለማስባል ያቀረቡት ማስረጃ እና መከራከሪያ ፍፁም ከእውነት የራቀ እና በሕግ የተደገፈ ስላልሆነ ፍርድ ቤቱ አመልካቾች ያቀረቡትን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊያፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካቾች የመልስ መልሳቸውን በማቅረብ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የሰበር ክርክሩን ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ፣ከተገቢው ሕግና ከስር ፍርድ ቤት ክርክር አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል፡፡አመልካቾች ከስር ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን አንፃር ሁለት ክርክሮችን ያቀረቡ ሲሆን የመጀመሪያው አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 11(2) ን መሰረት ያደረገ ሆኖ ተጠሪ ከአለም አቀፍ ህግ አንፃር ያቀረበውን ክርክር የማየት ስልጣኑ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤት ተቀብሎ ማስተናገዱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን በመጥቀስ የቀረበ ነው፡፡ተጠሪ በኢትዮጲያና ጅቡቲ መንግስታት መካከል በተደረገ ስምምነት መሰረት የተቋቋመ የሁለቱም መንግስታት ንብረት የሆነ ድርጅት መሆኑ ግራ ቀኙ የተማመኑበት ነጥብ ነው፡፡

የግል አለም አቀፍ ህግን የሚያስነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ ስልጣን የተሰጠው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 11(2)(ሀ) ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጉዳዩ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር እንዲወድቅ የሚያደርገው መሰረታዊ ጉዳይ ተጠሪ በኢትዮጲያና ጅቡቲ መንግስታት መካከል በተደረገ ስምምነት መሰረት የተቋቋመ የሁለቱም መንግስታት ንብረት የሆነ ድርጅት መሆኑ ሳይሆን ለክርክር የቀረበው ጉዳይ የሁለቱን ሀገሮች ህጎችን ገፋ ሲልም የአለም አቀፍ ህግን የተፈፀሚነት ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡(በተመሳሳይ ጉዳዮች በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 100290፣152590 እና በሌሎች ተመሳሳይ መዝገቦች የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ይመለከቷል፡፡)

አሁን በያዝነው ጉዳይ በግራ ቀኙ መሃል የተያዘው ጉዳይ የሁለቱን ሀገሮች ህጎችን አልያም የአለም አቀፍ ህግን የተፈፀሚነት ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኖ በዚህ አግባብም እነዚህ ህጎች ለክርክር የቀረበውን ጉዳይ የሚፈቱበትን አግባብ መለየትን፣ለክርክር የቀረበውን ጉዳይ በመፍታት ረገድ በእነዚህ ሀገር ህጎችና አለም አቀፍ ህግ መሃል አለመጣጣም መኖር አለመኖሩን መለየትን፣አለመጣጣም የሚኖር

ከሆነም አለመጣጣሙ የሚፈታበትን አግባብ መለየትን በመጨረሻም ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ያለውን ህግ መምረጥን የሚጠይቅ የክርክር አመራር ሁኔታ ባልተፈጠረበት ከዚህ ይልቅ በግራ ቀኙ መሃል ያለው የመፋለም ክርክር የሌሎች ህጎችን የተፈፀሚነት ጥያቄ የማያስነሳ በሀገራችን የንብረት ህግና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች አግባብ እልባት የሚያገኝ ሆኖ እያለ ተጠሪ በኢትዮጲያና ጅቡቲ መንግስታት መካከል በተደረገ ስምምነት መሰረት የተቋቋመ የሁለቱም መንግስታት ንብረት የሆነ ድርጅት ስለሆነ ብቻ አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 11(2)(ሀ) መሰረት ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት መከራከራቸው ከላይ በተመለከተው አግባብ ለአዋጁ አንቀፅ 11(2)(ሀ) የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

አከራካሪው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት የተወረሰ ሆኖ አስተዳደሩ የሚያስተዳድረው በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 41 መሰረት በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ስልጣን ያለው አስተዳደሩ ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የተሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጀ ፍርድ ቤት ነው በማለት አመልካቾች ከፍርድ ቤቱ ስልጣን ጋር በተያያዘ ያቀረቡትን መቃወሚያ በተመለከተ በግራ ቀኙ መሃል ያለው ክርክር የቤት ቁጥር 159 የሆነው ቤት ይገባኛል በሚል የቀረበ የመፋለም ክርክር መሆኑ ግራ ቀኙ የተማመኑበት ነጥብ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 41(1)(ረ) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የከተማ አስተዳደሩ ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የሚኖራቸው የቤቱ ባለቤትነት የከተማው አስተዳደር ስለመሆኑ ክርክር ሳይኖርበት ከባለቤትነት በመለስ የሚነሱ ክርክሮችን አስመልክቶ ነው፡፡(በሰበር መዝገብ ቁጥሮች 32376፣33841 እና በተመሳሳይ መዝገቦች ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ይመለከቷል፡፡)ይህ ከሆነ ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ፍርድ ቤቶች ግራ ቀኙ በሚያካሂዱት የመፋለም ክርክር ላይ የዳኝነት ስልጣን አላቸው ሊባል የሚችልበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ አመልካቾች ከፍርድ ቤቱ የዳኝነት ስልጣን ጋር በተያያዘ ያቀረቡትን መቃወሚያ አልተቀበልነውም፡፡

ግራ ቀኙ በፍሬ ጉዳዩ ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ተጠሪ ለንብረቱ ካርታ ማቅረብ የማይጠበቅበት ህዝባዊ ድርጅት ከመሆኑ አንፃር በሁለቱ መንግስታት ተለይቶ የተሰጠውን ይዞታ የሚያመለክት የአየር ካርታና በዚህ በተለየው ቦታ ውስጥ የሚገኙትን ቤቶች ዝርዝር ያቀረበ መሆኑ ማስረጃን የመስማት፣የመመርመርና የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ነጥብ ሲሆን ፣ ለተጠሪ ተለይቶ የተሰጠው ይዞታ የለም ይህ ቤትም በዚህ በተለየ ይዞታ ውስጥ አከራካሪው ቤት አይገኝም ቤቱ በተጠሪም አልተሰራም በማለት አመልካቾች ክርክር ባላቀረቡበት፣ይህም አከራካሪው ቤት በተጠሪ የተሠራና ለተጠሪ ተለይቶ በተሰጠው ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ለመሆኑ በአመልካቾች የታመነ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ፣ ባለንብረትነትን የሚያፀድቀው የስራና ቤት ሚኒስቴር ለተጠሪ በተሰጠው ክልል ውስጥ ያለ ይዞታና ንብረት ሊወረስ እንደማይችል፣የተወሰደ ይዞታና ንብረት ካለም እንዲመለስለት የፃፈው ደብዳቤ መቅረቡም ተጠሪ በአከራካሪው ቤት ላይ ከአመልካቾች የተሻለ መብት ያለው መሆኑን እንዳስረዳ የሚያሳይ በመሆኑ፣ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀፅ 12(2) መሰረት የከተማ ቤት ባለንበረትነትን በወቅቱ በነበረው አወቃቀር የሚያፀድቀው የስራና ቤት ሚኒስቴር የአዋጁን አንቀፅ 43 በመጥቀስ እና በሁለቱ ሀገሮች መሀከል የተደረገውን ስምምነት በመጥቀስ ለተጠሪ የተሰጠው ይዞታ ውስጥ የሚገኝ ይዞታና ንብረት ሊወረስ እንደማይገባ ፣የተወሰደ ንብረትና ይዞታ ካለም ሊመለስ እንደሚገባ መግለፁ በስር ፍርድ ቤቶች መረጋገጡ አመልካቾች አከራካሪው ቤት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሶ የሚያስተዳድሩት መሆኑን በመግለፅና ቅፅ 003 እና ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎችን በማቅረብ በቤቱ ላይ የሚያቀርቡት ክርክር አዋጁንና አዋጁን መሰረት በማድረግ የተፃፈውን የስራና ቤት ሚኒስቴር መግለጫ መሰረት ያላደረገ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ይህም የስር ፍርድ ቤቶች ማስረጃን በመስማት በመመርመርና በመመዘን የደረሱበት መደምደሚያ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ህጎች እና

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መሰረታዊውን የማስረጃ ምዘና መርህ መሰረት ያደረገ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት መሆኑን ስለሚያሳይ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.60123 በቀን 24/02/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካቾች አከራካሪውንን ቤትን ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የሰጠው ፍርድ እና ይህንን ፍርድ በማፅናት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.247606 በቀን 17/09/2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ስለገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሂ/መ